# የኢትዮጵያ 5ሺ ዓመት ታሪክ

# ካልተዘመረለት እያሡ፤ እስከተዘመረለት ኢህአዴግ

ፍስሐ ያዜ ካሣ

2004 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ምዕራፍ 85

የሊቀመናብርቱ ዘመን ከ1966 – 1983 ዓ.ም


| | |
|---|---|
| የ"በለው" ፍርድና የ60ዎቹ ግድያ | 274 |
| የአብዮቱ ፍሬዎች | 277 |
| የደርግ ዘመን ፓርቲዎች ውልደትና ሞት | 287 |
| የኢህአፓ ነጭ ሽብር | 296 |
| የምስራቁ ጦርነት | 302 |
| የሠሜኑ ጦርነት | 307 |
| ከ"ኢሠፓአኮ" ወደ "ኢሠፓ" | 323 |
| የኢኮኖሚ ተሐድሶ | 327 |
| ሕገመንግስትና ምርጫ | 329 |
| መፈንቅለ መንግስቱና ያስከተለው መዘዝ | 335 |
| ግላስኖስት እና ፔሬስትሮይካ | 353 |
| የደርግ መንግስት ፍፃሜና የኢህአዴግ ድል | 358 |
| የመጨረሻዎቹ ቀናት | 369 |
| የሶሻሊስት መሪዎች ውድቀትና የመንግስቱ የስደት ህይወት | 382 |
| ዋቢ መፃህፍት | 390 |


ይህ መጽሐፍ "የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ፣ከኖኅ እስከ ኢህአዴግ" በሚል ርዕስ "መጽሐፍ 1" ተብሎ በ 2003 ዓ.ም የታተመውና ለአንባብያን የተሰራጨው ተከታይ ክፍል ነው:: በመጀመሪያው መጽሐፍ ከኖኅ ጀምሮ እስከ ዳግማዊ ምኒልክ ድረስ የነበረውን የኢትዮጵያን ታሪክ ማንበባችን ይታወሳል::

ያን የ5,800 ዓመታት የረዥም ዘመን ታሪክ በ456 ገጾችና በ81 ምዕራፎች ከቃኘን በኋላ የ100 ዓመት ታሪክ እንደሚቀረንና፤ ከልጅ እያሱ ጀምሮ እስከ ኢህአዴግ ዘመን ድረስ ያለውን ታሪክ በ"መጽሐፍ 2" እንደምንመለስበት ተነጋግረን ነበር::

እናም ቁጥር 2ቱን መጽሐፍ "ካልተዘመረለት እያሡ፣ እስከተዘመረለት ኢህአዴግ" በሚል ርዕስ "ጠብቁት" ብዬ በገባሁት ቃል መሠረት አሁን "እነሆ" ብያለሁ:: ይህም የመጨረሻው ክፍል ነው:: ያቋረጥነው ምዕራፍ 81 ላይ ስለነበርም የምንቀጥለው ምዕራፍ 82 ብለን ይሆናል:: "ከኖኅ እስከ ኢህአዴግ" የሚለውን የመጀመሪያ ክፍል መጽሐፍ በሚመለከት ከጠበቅሁት በላይ በሆነ ሁኔታ ከሠሜን፣ ከደቡብ፤ ከምዕራብና ከምስራቅ፣ እንዲሁም ከመሐል ከተማ ከ1ሺ በላይ የሆኑ የአንባብያንን አስተያየት ተቀብያለሁ::

ከእነዚህ ውስጥ "አንድ ግለሰብ" ብቻ (ከአዲስ አበባ) የተቃውሞ ድምፁን ከማሰማቱ በስተቀር ሌሎች ሁሉ "አበጀህ!" የሚሉ በመሆናቸው፤ ድፍን የኢትዮጵያ ህዝብ የተስማማበት መሆኑን ለማረጋገጥ ብችልም፤ "ፍፁም ስራ ነው" ብዬ ግን አልደመድምም:: ስለዚህ "መጽሐፍ 1"ን ያላነበባችሁ አንባብያን ካላችሁ፤በዚህ አጋጣሚ እንድታነቡት ሳበረታታ፤ከንባብ በኋላ የሚኖራችሁን ማናቸውንም አይነት አስተያየት ለመቀበል በመፈለግና በመዘጋጀት ነው::

የዚያ ተከታይ ክፍል የሆነው ይህ መጽሐፍ 2 ደግሞ የቅርብ ጊዜ ታሪክ ነውና፤ ሁሉንም አንባብያን የሚያስደስት ሆኖ ላይገኝ ይችላል:: ቢሆንም ግን ታሪክ ነውና በታሪክነት እንጂ በወገንተኝነት ለማንበብ መዘጋጀት ከእናንተ አይጠበቅምና ያን እንዳታደርጉ እመክራለሁ::

ስህተትና ግድፈት ከተገኘ ስህተቱን ለማረም፣ ግድፈቱን ለማስተካከል በደንብ የተዘጋጀሁ ልሁን እንጂ፤ "ለምን እኛን? ለምን እሱን? ለምን እኔን?...." የሚሉ ወገንተኝነትን መሠረት አድርገው፣ ተቆርቋሪነትን ተላብሰው የሚሰነዘሩ አስተያየቶችን ለመቀበል አልዘጋጅም:: ምክንያቱም ታሪክ ስለሆነ::

በተረፈ እንደተለመደው እ.ኤ.አ ከሚሉት በቀር ሌሎች የዘመን አቆጣጠሮች ሁሉ በእኛ አቆጣጠር የሰፈሩ መሆናቸውን ገልጬ መግቢያውን መዝጋት አለብኝ::

መልካም ንባብ::

# ምዕራፍ 82

***የልጅ እያሡ ዘመነ-መንግስት***
***ከ1906 - 1909 ዓ.ም***

የልጅ እያሡ እናት ወ/ሮ ሸዋረጋ ከእናታቸው ከወ/ሮ ደስታና ከአባታቸው ከዳግማዊ ምኒልክ ኃይለመለኮት በድብቅ የተወለዱ ነበሩ፡፡ወ/ሮ ደስታ በቤተ-መንግስት ውስጥ በጠጅ ክፍል ሲሰሩ የኖሩ ናቸው፡፡በወ/ሮ ደስታ ውበት የተማረኩት ዳግማዊ ምኒልክ በድብቅ ይገናኙዋቸውና ይፀንሳሉ፡፡ወ/ሮዋ መፀነሳቸውን እንዳወቁ ሸሽተው ወደ ወሎ በማቅናት ኑሯቸውን በዚያው ይመሰርታሉ፡፡ወዲያውም ሸዋረጋን ይወልዱና አሳድገው ይድራሉ፡፡

ሸዋረጋም ከወታደር ባለቤቷ ጋር ወደ ሐረርጌ ሄዳ መኖር ትጀምራለች፡፡የሸዋረጋ ባለቤት ምንም ቢሆን ልታወልቀው የማትደፍረውን የአንገት ክታቧን ተጠራጥሮ አውልቆ ከፍቶ ሲያነበው የዳግማዊ ምኒልክ ልጅ መሆኗን ይረዳል፡፡ሁኔታው ቢያስደነግጠውም ይህን ሚስጥር ገልጦ ለእቴጌ ጣይቱ ቢናገር ሊያሾመው፣ሊያሸልመው እንደሚችል በመገንዘብ ሚስቱን ወስዶ ለእቴጌ ጣይቱ ጉዳዩን ገልጦ ያስረዳል፡፡

እቴጌ ጣይቱም ሸዋረጋን ተቀብለው ቤተመንግስት ውስጥ እንድትቀር አድርገው ሚስጥሩን ለነገራቸው ወታደርም ተገቢውን ወሮታ ከፍለው ያሰናብቱታል፡፡

እቴጌዋ ከቀናት በኋላ ሸዋረጋን አለባብሰው፣ኳኩለው፣ከሌሎች ወይዛዝርት ጋር ቀላቅለው የንጉስ ምኒልክን እጅ እንዲነሱ ሲያደርጉ፣አፄ ምኒልክ ሸዋረጋ ላይ አፍጥጠው "ይች የማናት ልጅ?" ብለው ሲጠይቁ

የወ/ሮ ደስታ ልጅ መሆኗ ይነገራቸዋል፡፡ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የሸዋረጋ ኑሮ በቤተ-መንግስት ውስጥ ሆኖ ቀዬ፡፡ውበቷም የመኳንንቱን ዓይን መሳብ ጀመረ፡፡ብዙም ሳትቆይ የአፄ ምኒልክ አብሮ አደግ ለነበሩት ለራስ ጎበና ዳጬ ልጅ ለወዳጆ ጎበና ተዳረች፡፡ይህ ትዳር ሳይቆይ ቶሎ ፈረሰና በመጨረሻ የወሎውን ባላባት ራስ ሚካኤልን አገባች፡፡

የራስ ሚካኤልን ትውልድ በሚመለከት ቀደምት ወሎየዎች እንደቀድሞው ወጋቸው ቡና ላይ ሲመርቁና ሲተነብዩ ራስ ሚካኤል ከመወለዳቸው በፊት ተከታዩን ትንቢታዊ ስንኝ ቋጥረውላቸው እንደነበር "አባ ጤና እያሱ" በተሰኘው መፅሐፍ ሰፍሮ እናገኛለን፡፡

*"ልጅ ይወለዳል ከገረድ፣*
*ስሙንም አልነው ማመድ፣*



*የአላህን ዲን /እምነት/ የሚንድ፡፡"* እንደተባለው ራስ ሚካኤል ወይም በአፄ ዮሐንስ ጊዜ ክርስትና ከመነሳታቸውና ከመጠመቃቸው በፊት መሐመድ ዓሊ የተወለዱት ከኢማም ዓሊ አባቡላና ከግንደበረት ከተወሰደችው አገልጋይ ከወ/ሮ ጌጤ ነው፡፡ግንደበረት በምዕራብ ሸዋ ውስጥ የሚገኝ በባሪያ ፍንገላ የሚታወቅ ወረዳ ነበር፡፡በዚህ ጋብቻ መሠረት ልጅ እያሱ ከእናቱ ከአፄ ምኒልክ ሴት ልጅ ከወ/ሮ ሸዋረጋ እና ከወሎው ባላባት ከራስ ሚካኤል ዓሊ ጥር 25 ቀን 1888 ዓ.ም በወሎ ጠቅላይ ግዛት ወረሂመኑ ተንታ ውስጥ ተወለደ፡፡የክርስትና ስሙንም ክፍለያዕቆብ አሉት፡፡

ለእያሱም እንደአባቱ ከመወለዱ በፊት እንዲህ ተብሎ ተተንብዮለት ነበር፤ትንቢቱ ጋብቻውንም አካቷል፡፡

"ጌታው ማመድ ዓሊ በአዳራሹ ገብተህ በእልፍኝ ብትወጣ፤
ወቀሣ ቢያገኝህ እኔ በጉድ ልውጣ፤
በዳግመኛው እግርህ ሸዋረጋን እምጣ፡፡
ከእመት ሸዋረጋ የሚገኘው ልጅ፣
እምብዛም አይከፋ እምብዛም አይበጅ፡፡"

ልጅ እያሱ በተወለደ በ6ኛ ወሩ እናቱ ሸዋረጋ ስለሞተች እስከ 7 ዓመቱ ድረስ በአባቱ እጅ ነበር ያደገው፡፡በኋላም በአፄ ምኒልክ ፍላጎት ወደ አንኮበር ሄዶ በሞግዚት እንዲያድግ ተደረገ፡፡ልጅ እያሱ ገና የ12 ዓመት ልጅ እያለም፤እቴጌ ጣይቱ የወንድማቸውን የራስ ወሌ የልጅ ልጅ የሆነችውን ፅጌሮማን መንገሻ ዮሐንስን በ8 ዓመቷ ድረውለት ነበር፡፡

አፄ ምኒልክ በታመሙ ጊዜ ወንድ ልጅ ስላልነበራቸው የልጅ ልጃቸውን እያሱን አስመጥተው አልጋወራሻቸው እሱ መሆኑን አሳወቁ፡፡

አፄ ምኒልክ ግንቦት 10 ቀን 1901 ዓ.ም ልጅ እያሡ አልጋወራሽ መሆኑን ያሳወቁበት ቃል የሚከተለው ነው፡፡

"አፄ ቴዎድሮስ የሞቱ ጊዜ ከሳቸው ጋር የነበረው ሰው ሁሉ ያንዱን አገር አንዱ እደርባለሁ አንዱን ገድዬ እኔ ጌታ እሆናለሁ እያለ ሁሉም ሳይረባ ተላልቆ ቀረ፡፡ከዚህም በኋላ የአፄ ዮሐንስ ሰው የሆነውን የምታውቁት ነው፡፡ባገር በሽታ ሳይገባበት ሌላ የባዕድ ጦር ሳይነሳበት በምቀኝነት እርስ በርሱ እንደተላለቀ አይታችኋል፡፡አሁንም ልጆቼ ወዳጆቼ አንዱ ባንዱ ምቀኝነት ይቅር፣ የአንዱን አገር አንዱ እኔ እደርባለሁ እንዳትሉ፡፡

እኔ እስካሁን በፍቅር እንዳኖርኳችሁ እናንተም ተስማምታችሁ በፍቅር እንድትኖሩ እለምናችኋለሁ፡፡

እናንተ አንድ ልብ ከሆናችሁ በምቀኝነት እርስ በርሳችሁ ተዋግታችሁ ካላለቃችሁ በቀር አገራችንን ኢትዮጵያን ለሌላ ለባዕድ

አትሰጧትም ከፉም ነገር አገራችንን አያገኛትም፡፡ይህንንም ምክር ለእናንተ መስጠቴ እኔማ በእግዚአብሔር ቸርነት ይህንን ያህል ዘመን ገዝቼ የለምን፡፡ነገር ግን ሰው ነኝና እንግዲህ እስንት ያህል ዘመን እቆያለሁ ስል ነው፡፡አሁንም እኔ እንደተመኘሁት እግዚአብሔር የተጨመረበትና ፈቃዱ ሁኖ ልጄን (የልጅ ልጄን ማለታቸው ነው) ቢያቆምላችሁ ከልጄ ጋር ሁናችሁ አገራችሁን ጠብቁ አደራ ብያችኋለሁ፡፡"

በዚያን ጊዜ ልጅ እያሡ ገና 13 ዓመቱ ስለነበረ ራስ ተሰማ ናደውን የራስ ቢትወደድነት ማዕረግ ሰጥተው የልጅ እያሡ ሞግዚት አድርገው ሾሟቸው፡፡ብዙም ሳይቆይ በ1903 ዓ.ም ራስ ቢትወደድ ተሠማ የነበረባቸው የደም ብዛትና የእድሜያቸውም መግፋት ለህልፈት ስለዳረጋቸው ሌላ ሞግዚት አስፈለገ፡፡



ራስ አባተ ቧያለው እንደራሴ ለመሆን ሲሞክሩ ሌሎችም ተመሣሣይ ፍላጎት ነበራቸውና ጥቂት አለመግባባት ተፈጠረ፡፡በዚህ ጊዜ ልጅ እያሡ "እንዲያውም አሁን አድጌያለሁ ያለሞግዚት ማስተዳደር እችላለሁ" አለ፡፡ራስ አባተ ቧያለውም ሆኑ ፊታውራሪ ሃብተጊዮርጊስ ዲነግዴ እንዲሁም ሌሎች ሹማምንት ልጅ እያሡ በዚህ እድሜው ያለሞግዚት አገር እንዲያስተዳድር የተስማሙት "እኔ እንደራሴ ካልሆንኩ



ይቅርበት" በሚል እልህ አዘል አቋም እንጂ፣አቤቶ እያሡ በዚህ እድሜው ያለሞግዚት እንዲያስተዳድር መፍቀድ ለልጅ እያሡም ሆነ ለአገሪቱ እንደማይበጅ ጠንቅቀው ይውቁታል፡፡እያወቁም ልዑሉን ብቻውን ይምራ ብለው ለቀውታል፡፡

ስሩ ወይም መሠረቱ ይሄ ነው፡፡ምክንያቱም ልጅ እያሡ የመጀመሪያው ሞግዚቱ ከሞቱ በኋላ "ሞግዚት አያስፈልገኝም" አላለም፡፡ይህን ለማለት የተገደደው በዙሪያው ያሉት ታላላቅ ሹማምንት ትልቁን የሞግዚትነት /የእንደራሴነት/ ስልጣን ለመያዝ ሲሻኮቱና ወዳላሥፈላጊ ውዝግብ ሲያመሩ በማየቱ ብቻ "በቃ አልፈልግም" አለ እንጂ ሞግዚት እንደሚያስፈልገው ያውቅ ነበር፡፡ማወቅ ብቻም ሳይሆን ሞግዚት መረጣው ተጀምሮ ነበር፡፡

ይህ የልጅ እያሡ የስልጣን ዘመን አጀማመር በደምብ ያልታየና ከልጅ እያሡ ታሪክ ጋር በስፋት ተካቶ የማናገኘው እውነታ ነው፡፡

የልጅ እያሡን አለመብሠልና አለመብሰሉን ተከትሎም የሚፈፅማቸውን መጥፎ ተግባራት እየተነተኑ የሚከሱት፣የሚያብጠለጥሉት፣በመጨረሻም ከስልጣን ያባረሩት እነዚያው ታላላቅ ሹማምንት ጥፋቱን ሁሉ የልጅ እያሡ ጥፋት ያድርጉት እንጂ "አጥፋ" ብለው ራሳቸው መፍቀዳቸውን ዘንግተዋል፡፡

አንድን የ13 ዓመት ልዑል ያለአንዳች አማካሪና ሞግዚት በፈቃዱ ሳይሆን በፈቃዳቸው አገር እንዲመራ ለቀው ሲያበቁ "ልጅ ነው፣ ወመኔ ነው፣ትልቅ አያከብር፣ ያሻውን እያደረገ፣ብዙ ሚስት እያገባ፣ጉግስ እየተጫወተ፣እያውደለደለ ..." እያሉ ሲሉት ለምን? ተብሎ መጠየቅ አለበት፡፡ልዑሉ በአእምሮም በአካልም እስኪጠነክር፣ አገር የመምራት ልምድ እስኪያዳብር... ከጎኑ ሆኖ ያማከረው፣ያስተማረው፣የቀረፀው እስከሌለ ድረስ በራሱ መንገድ ከመጓዝ ውጪ ምንም ምርጫ አልነበረውም፡፡በዚህ ሂደት ቢያጠፋ መወቀሱ አይቀሬ መሆኑን ሳንዘነጋ፣ ነገር ግን እሱን ብቻ ተጠያቂና ተከሳሽ አድርጎ ማቅረቡ ብዙም እንደማይደገፍ በቀላሉ መረዳት ከእኛ ይጠበቃል፡፡

ለዚህም ነው "ይሄንንም እሱ ሆኖ" በሚል መነሻ "ያልተዘመረለት" ብለን የምንቀጥለው፡፡

የልጅ እያሡ የስልጣን ዘመን ተብሎ የሚመደበው ጊዜ ከ1906 እስከ 1909 ዓ.ም ድረስ የነበሩት 3 ዓመታት ይሁኑ እንጂ፤ልጅ እያሡ ራሱን ችሎ ማስተዳደር የጀመረው ከ1903 ዓ.ም ጀምሮ ነው፡፡አፄ ምኒልክ እስከ 1906 ድረስ እስትንፋሳቸው የነበረ ቢሆንም ለዓመታት በፅኑ ህመም ላይ ቆይተው በመጨረሻም እንደበታቸው እስከመዘጋት ደርሶ ነበር፡፡እስከ 1902 ዓ.ም ድረስ የነበረውን ጊዜ ብርሃን ዘኢትዮጵያ እየተባሉ የሚጠሩት የምኒልክ ቀኝ እጅ የነበሩት እቴጌ ጣይቱ ባለቤታቸውን

ተክተው እየሰሩ፣ሹም ሽር እያደረጉ በበላይነት ሊቀጥሉ ቢሉም በሹማምንቱ ምክክር ባለቤታቸውን በማስታመም ብቻ እንዲወሰኑ እና በአስተዳደሩ ስራ ጣልቃ እንዳይገቡ አስወስነው ስላባረሩዋቸው፣ከላይ እንዳየነው የልጅ እያሡ ሞግዚትም ስለሞቱና ተተኪ እንደራሴ ሳይሾም ስለቀረ፣እያሡ ብቻውን አገሪቱን ማስተዳደር የጀመረው የ15 ዓመት ልጅ በሆነበት ጊዜ ከ1903 ዓ.ም ጀምሮ ነው፡፡



ልጅ ኢያሱ ከሞግዚቱ ከራስ ቢትወደድ ተሰማ ጋር

ልጅ እያሡ አፄ ምኒልክ ከመሞታቸው በፊት ወራሽነቱን ካረጋገጡበት ጊዜ ጀምሮ ወደተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ወረድ እያለ ግንኙነት መመስረት፣ራቅ ወዳሉ ግዛቶች ወጣ እያለ አገር መጎብኘትና ያልቀናውን አገር ለማቅናት እንቅስቃሴ መጀመር፣ልዩ ልዩ ባህል ከነበራቸው ብሔረሰቦች ጋር ግንኙነቱን ማጠንከር፣ባለፉት ጊዜያቶች ትኩረት ተነፍገው ነበር የሚላቸውን ህዝቦች ልዩ ትኩረት መስጠት ጀመረ፡፡ አብሮ መዋል ማደር፣ እንዲያም ሲል ለቀናት፣ለሳምንታት መሰንበት ልማዱ አድርጎ ቀጠለበት፡፡በዚህ ባልተለመደ አካሄዱ ሳቢያም በብዙ ሹማምንት ዘንድ ይነቀፍ ጀመር፡፡

ልጅ እያሡ ሌላው የከፋ ተግባሩ ተብሎ የተቆጠረውም ያያትን ቆንጆ ሁሉ ማግባት መጀመሩ ሲሆን፤በዚህም ላይ ሃይማኖት፣ብሔርና የዘር ግንድ ለእያሡ ጋብቻ መመዘኛ አልነበሩምና ነው፡፡በዚህም ሹማምንቱ ከነቀፋ አልፈው ቂጣ ጀመሩ፡፡ቂጣውም ወደ ሰድብ አምርቶ የሸዋ መኳንንት ልጅ እያሡን በገሐድ መዝለፍ ስራቸው ሆነ፡፡እሡም ለዘለፋቸው ተገቢ ነው ያለውን የዘለፋ መልስ መስጠቱን ገፋበት፡፡በዘመናቸው ተከብረው የኖሩትን ታላላቅ ማዕረግና ስም ያላቸውን ሁሉ "የአባቴ ሙክቶች" እያለ መናቅ ማጣጣል ጀመረ፡፡ እነሱም እንደቀድሞው ንጉሣቸውን አጅበው አገር የመዞሩ ልማድ ቀረባቸው፡፡ልጅ እያሡ "እኔ ጎልማሶችን አስከትዬ አገር ለመጎብኘትና ያልቀናውን አገር



ለማቅናት በተነሳሁ ጊዜ ያለፈቃዱ መከተል የለባችሁም፡፡ ወፍራችኋል ፣ሸምግላችኋል፡፡በዘመናችሁ አባቴን ተከትላችሁ አገር አቅንታችኋል፡፡ አሁን ግን ሸሽታችሁ አታመልጡም፡፡ አባራችሁ አትጨብጡምና ተመልሳችሁ በየስራችሁ ጠንክሩ፡፡"ማለቱን መርስዔሐዘን ወልደቂርቆስ ፅፈዋል፡፡

የዘመናዊት ኢትዮጵያ የታሪክ አባት የሚባሉት ፕ/ር ባህሩ ዘውዴ ይህን የልጅ እያሡን አቋም በሚመለከት "በቀና ትርጓሜ እያሡ የሚለው እናንተ በተራችሁ ሠርታችኋል፣ አሁን ደግሞ ዘመናዊት ኢትዮጵያን የመገንባቱ ተራ የእኛ የወጣቶቹ ነው ማለቱ ነው" ተብሎ ሊተረጎም የሚገባው መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡

ልጅ እያሡ የጉርምስና ባህሪ ያጠቃው ልዑል እንደነበረ ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ የሚያከናውናቸው ተግባራቶችም ከፊሎቹ ያለፈውን ስርዓትና ወግ የሚፃረሩ የነበሩ ናቸው፡፡የቀሩት ስራዎቹ ግን በዚያ ዘመን ሹማምንት እይታ ሲታሰብ እንጂ በዘመናዊ አስተሳሰብ እይታ ተራማጅነቱን የሚያጎላ ነው፡፡

ፕ/ር ባህሩ ዘውዴ የእያሡን ዘመነ-መንግስት "በእንቆቅልሽ የተሞላ" ይሉታል፡፡ "አፍን ሞልቶ በክፉም በበጎ ማውሳቱ ያዳግታልና" በማለት፡፡

"በመንግስት ስራ ላይ በዋልፈሰስ ቢመስልም ከእድሜ ለጋነት የመጣ ነው ብሎ ህዝቡ ሊፈርድለት ዝግጁ ነበር፡፡" በማለትም ተራማጅ ሊያሰኙት የሚችሉ ተግባራትን በዘመኑ ማከናወኑን ይጠቅሳሉ፡፡

"የግል ንብረትን የማስከበርና አስራትን በወቅቱ የመሰብሰብ ደንብ በተጨማሪ፣ ከሳሽና ተከሳሽ አብረው እንዲማቅቁ ያደርግ የነበረውን የቁራኛ ስርዓት ለመሻር እርምጃ ወስዷል፡፡እንዲሁም ከፍትህ ይልቅ ለቂም መወጫና ደካማውን ለማጥቂያነት የሚያገለግለውን የሌባ ሻይ ስርዓት መልክ ለማስያዝ ሞክሯል፡፡የመንግስት ሒሳብ ኦዲት በማስደረግ አለአግባብ የመንግስት ገንዘብ ባባከኑት ላይ እርምጃ በመውሰድም እያሡ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ መሪ ሳይሆን አይቀርም፡፡የሚያሳዝነው ግን አንዳንዴ በዚሁ ሳቢያ የጠላውን ሰው በሐሰት እያስወነጀለ ማሰሩ ነው፡፡በመሠረቱ የእያሡ ገፀ-ባህሪም ሆነ ፖሊሲዎች መለዮ ውስጠ ተቃርኖና ቀጣይነት ማጣት ነበር፡፡ባንድ ወገን የተጠቃ እንባ አድራቂ ሆኖ የጅሌ ኦሮሞን ህዝብ በዘረፉት በአፋሮች ላይ ሲዘምት እናየዋለን፡፡በዚያው ዓመት ደግሞ በሰሙ ላይ ጥቁር ነጥብ የጣለውን የጊሚራ ዘመቻ ሲመራና በርካታ ዜጎችን ለባርነትና ሞት ሲዳርግ እናገኘዋለን፡፡ "ጥርንቡሌ" የተባለውን የከተማ ዘበኛ ያቋቋመ አርቆ አሳቢ መሪ ሰዓት እላፊ እየጣሰ ከእነሱው ጋር ሲታኮስ ይገኛል፡፡"

ልጅ እያሡ እራሱ የሰዓት እላፊ አዋጅ በዘመኑ ደንግጎ፣ ነገር ግን አዋጁን ራሱ ጥሶ ከአራዳ ዘበኞች ጋር ሌሊት ሌሊት ሲታኮስ ያድር ነበር፡፡

በ1905 ዓ.ም አጋማሽ ላይ አፄ ምኒልክ በሞትና በህይወት መካከል በነበሩ ጊዜ ልጅ እያሡ ወደ አንኮበር እንዲሄዱ ለማድረግ አስቧል የሚል ወሬ በመሰማቱ የጊቢ ዘበኞች ልጅ እያሡን አናስገባም ብለው በሩን ዘጉ፡፡እያሡ ከውጭ ሆኖ በማስከበብ ስንቅ እንዳያገኙ በማድረጉ ሁከት ተፈጠረ፡፡ ለ5 ሰዓታት በተካሄደ የተኩስ ልውውጥ 17 ሰዎች ከሞቱ በኋላ በጳጳሱ ሽምጋይነት ዘበኞቹ እጅ እንዲሰጡ ተደርጎ ሠላም የወረደው ልጅ እያሡ ወሬው የሐሰት መሆኑን በማስተባበሉ ነበር፡፡

ስለዚህም ከዚህ ግርግር በኋላ ሌላ የጊቢ ዘበኛ ተሾሞ የቀድሞዎቹ ወደ ጎጃምና ወደ አንኮበር ሄደው እንዲታሰሩ ተደረገ፡፡

ልጅ እያሡ የሸዋን መኳንንት እንደቀድሞው ኑሮአቸው አክብሮ ካልያዘ መቸም ቢሆን እንደማይተኙለት ዘግይቶ ነበር የተረዳው፡፡ ሸዋ ያባቴ፣ ወሎ የወላጅ አባቴ፣ትግራይ የባለቤቴ፣ጎጃም የእህቴ፣አፋርም ሐረርም የወዳጆቼ በሚል መነሻ ይመስላል እየተባባሰ የሄደውን የሹማምንቱን ተፅዕኖ ከመጤፍ አልቆጠረውም ነበር፡፡

የአፄ ምኒልክ ሞት ይፋ ከወጣና ቀብራቸው ከተፈፀመ በኋላም በዚያው ዓመት በ1906 ዓ.ም ገና ዘውድ ሳይጭን አባቱን ራስ ሚካኤልን የወሎ፣የትግሬና የጎጃም "ንጉስ" አድርጎ ሲሾም፣ቡተቃራኒው የሸዋን መኳንንት ክብርና ስልጣን ያዳክም ነበር፡፡ከምኒልክ ቀብር በኋላ እንደወጉ ልጅ እያሡ ዘውድ መጫንና "ንጉሠ ነገስት" መባል ነበረበት፡፡ ሆኖም ልጅ እያሡ "ዘውዱ ይቆየኝ" አለ፡፡

ይህን ያለበት ምክንያት "ፈረሴ ቀይ ባህር ውሃ ሳይጠጣ ዘውድ አልጭንም" በሚል አቋም ነው፡፡

ይህ አቋሙም ቀደም ሲል የልጅ እያሱ አዝማሚያ ባላማራቸው ሹማምንት ዘንድ ሌላ ትርጉም ተሰጠውና "ለውልጊቱ እንዲመቸው ንጉሠነገስት መባልን አይፈልግም፣ገና ባልጎም፣ዋልጎም አልጨረሰም"ተብሎ ተወራበት፡፡በኢትዮጵያ ታሪክ "ቅድሚያ ዘውዱን ሌላው ሁሉ ቀስ ብሎ ይደርሳል" ያላለ ብቸኛ መሪ ነው እያሡ፡፡ልጅ ወይም አቤቶ ተብሎ እንደተጠራ የስልጣን ዘመኑ ተቋጨ እንጂ እያሡ ንጉሠነገስት አልተባለም፡፡

ልጅ እያሡ የሹማምንቱን ወሬ ወደ ጎን አድርጎ መቅደም ያለበት ያለውን ጉዳይ ወደማስቀደም አመራ፡፡





ልጅ እያሱ ከአባቱ ከራስ ሚካኤል ጋር

በ1907 ዓ.ም አዲስ ሹም ሽር ሲያደርግም ደጃዝማች ተፈሪ መኮንንን ከሐረርጌ ግዛት ሽሮ ወደ ከፋ እንዲሄዱ ቢያዝም፣ እንዴ ክረምቱ ይለፍ፣ሌላ ጊዜ አልተዘጋጀሁም እያሉ ቆዩ፡፡የጦር ሚ/ሩ ፊታውራሪ ሐብተጊዮርጊስም ደርበው ይዘውት የነበረውን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊቀመንበርነትን እንዲለቁ ተደርጎ በጦር ሚኒስቴርነታቸው ብቻ እንዲወሰኑ ተደረገ፡፡ቀድሞውንም በልጅ እያሡ ላይ ከባድ ጥላቻ የነበረባቸው የፊታውራሪ ሃብተጊዮርጊስ እና የደጃዝማች ተፈሪ ኅብረትም የተፈጠረው በዚህ ጊዜ ነበር፡፡

ልጅ እያሱ በስልጣን ዘመኑ ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው ከፈለጋቸው ጉዳዮች ውስጥ ዋናዎቹ የአገሪቱ ዳር ድንበር የተወሰደው ተመልሶ፣ያለውም በጥብቅ ተከልሎና ተከብሮ እንዲቆይ፣የኢትዮጵያ ህዝቦች ምንም አይነት ብሔር ይኑራቸው በኢትዮጵያዊነታቸው ብቻ እኩልነታቸው እንዲረጋገጥ፣ዜጎች ባህልና ሃይማኖታቸውን በነፃነት እንዲያራምዱና መላው ኢትዮጵያዊ እኩል የአገር ፍቅር ኖሯቸው ብሔራዊ ስሜታቸው እንዲያንሰራራ ማድረግ ነው፡፡ሌላው ቀርቶ በባለርስትና በጭሰኛው መካከል የነበረውን የሰፋ ልዩነት ለማጥበብና የተሻለ ቅርርብ ኖሮ አላስፈላጊ የጉልበት ብዝበዛ እንዲቀነስ አዋጅ እስከማውጣት ደርሷል፡፡ይህን አይነት ያልተለመደ እቅድ ለማሳካት የተጠቀመበት ዘዴ ግን ጠልፎ ሲጥለው እናያለን፡፡

ልጅ እያሡ ከእርሱ በፊት ከነበሩት ነገስታት ለየት ያለ ተግባር ሲፈፅም የሚያስገኘውን አገራዊ ጥቅምና የሚፈጠረውን አንድነት አስቦ ከመደገፍ ይልቅ "ወግ ጣስ" የሚለውን ቁጭት ነበር አግንነው የሚያስተጋቡበት፡፡

ለክርስቲያኑ ቤተክርስቲያን ሲያሰራ ለሙስሊሞችም መስጊድ አሰራ፡፡ይህ ተግባሩ ብዙ ሹማምንትን አሳዘነ፡፡በዘመኑ ስለእሱ የሚወራው ለሙስሊሞች ያሰራው መስጊድ እንጂ ለክርስቲያኖች ያሰራው ቤተክርስቲያን አልነበረም፡፡

ሆኖም የአዲስ አበባውን ቀጨኔ መድሐኒዓለምና የሐረር መድሐኒዓለምን ቤተክርስቲያን አሰርቷል፡፡ (በአሁኑ ጊዜ የቀጨኔ መድሃኒዓለም የቤተክህነቱ የገንዘብ ቤት ሆኖ የሚያገለግለው መቃብር ቤት ከሌላ እናት የሚወለዱ እህቶቹና የሌሎች ቤተሰቦች መቃብር የነበረ ሲሆን፤የእህቱ የወ/ሮ ስሂን ሚካኤል፣የልዕልት እጅጋየሁ አስፋወሰን፣የእመቤት ሆይ ዓለም ፀሐይ እያሡ፣የወ/ሮ እስከዳር ገ/ህይወት ሚካኤልና የሌሎች አፅም ይገኝበታል፡፡) አፄ ኃይለስላሴም በዘመናቸው ሄደውበት የሚያውቁት ብቸኛ ቤተክርስቲያን ይሄው ቀጨኔ መድሐኒዓለም ነበር፡፡

እናም በዚህ ተግባር "ሰልሟል" ብሎ ለመክሰስ የሚያስችለው መንገድ ተያዘ፡፡ይህ በእንዲህ እንዳለም ቀደም ሲል የተጠቀሰው ብዙ ሚስት የማግባቱና እቁባቶቹን የማበርከቱ ጉዳይ ሃይማኖታዊ ቅርፁን እያጎላው ሄደ፡፡ልጅ እያሡ ከሙስሊም ባላባቶች ጋር ጥብቅ ወዳጅነቱን አጠናክሮ ከመቀጠል ጎን ለጎን የአፋሩን ባላባት የደጃዝማች አቡበከርን ልጅ አፍቅሮ አገባት፡፡ወደ አፋር እየሄደም ጥሩ የፍቅር ጊዜ አሳልፏል፡፡

ቀደም ባለው ጊዜ የአፄ ዮሐንስን የልጅ ልጅ አግብቶ እንደነበርም አይተናል፡፡ እንደገና ከጎጃም ባላባት የተወለደችውን ሰብለወንጌልን አገባ፡፡ከዚያም የጅማውን የአባ ጅፋርን ልጅ አገባ፡፡እንደገና የሐረሩን አሚር የአብዱላሂን ልጅ አገባ፡፡ዙሪያውን ለማጠር የፈለገ ይመስል ሰሜን፣ደቡብ፣ምስራቅ፣ምዕራብና መሐል ላይ ጎጆ ቀለሰ፡፡ይህን መሰሉን ጋብቻ ጥቂት ፀሐፍት "ከሁሉም ጎሣ በመውለድ አንድነትን ለማጠንከር ሲል የፈፀመው ነው" ይሉታል፡፡

ምንም ቢባል እያሡ ላይ ገኖ ተወራ እንጂ በይፋዊ ጋብቻ ባይሆንም ቀደምት ነገስታት የጭን ገረድ፣ቅምጥ፣እቁባት፣ውሽማ ... ወዘተ በሚሉ ተመሳሳይ ስሞች በገሃድ ፈፅመውታል፡፡እንደነዘርዓያዕቆብ ያሉ ገናና ነገስታት የግራ ባህልቲት፣የቀኝ ባህልቲት እያሉ በርከት ያሉ ሚስቶች ያገቡ የነበረ ሲሆን፤ነገር ግን ሙስሊሟን ሴት ክርስትና አስነስተው ነበር የሚፈፅሙት፡፡ይህም የሆነው ሳይወዱ በግድ በዚያ ዘመን የነበረውን ጦርነት ለማርገብ ሲሉ ነበር፡፡

ልጅ እያሡ ይህን ሲያደርግ ግን የነበረው ሰላም ዘላቂ ሆኖ እንዲቀጥል በማሰብ ይመስላል፡፡ይህ የልጅነት አስተሳሰቡ ከጥቅሙ ጉዳቱ እንደሚብስ ግን ማመዛዘን አልቻለም፡፡ በዚያ ዘመን ደግሞ ትኩረት በተነፈጉት መኳንንት ዘንድ መስጊድ ከማሰራትና ሙስሊም ከማግባት የከፋ መከነኛ አልነበረም፡፡



ልጅ እያሡ የመኳንንቱን ክስ ቁብ ሳይሰጠው በምስራቃዊው የኢትዮጵያ ድንበር ላይ የሙጥኝ ብሎ ቀረ፡፡

ዘረፋ በመፈፀም ብቻ ኑሮአቸውን መስርተው የነበሩትን ሱማሌዎችን ልጅ እያሡ ልዩ ትኩረት እንክብካቤና አክብሮት በመስጠት ወዳጅ አደረጋቸው፡፡ በአካባቢው የጎሣ መሪ የነበረውን አብደላ ሰዴቅን የኦጋዴን ገዥ አድርጎ ሾመው፡፡ ይህም በአካባቢው ለነበሩ ቅኝ ገዥዎች ትኩረት የሚስብ ሆነ፡፡ ይባስ ብሎ ቅኝ ገዥነታቸውን ካወጁበት ጊዜ ጀምሮ በእንግሊዞችና በጣሊያኖች ላይ ለ15 ዓመታት ያህል ብሔራዊ ጦርነት አውጆ የተካፈሏትን ሱማሌ ነፃ ለማውጣት ሲንቀሳቀስ ለነበረው የሱማሌ መሪ ለሰይድ ሙሐመድ አብደላ ሀሰን ልጅ እያሡ የገንዘብ፣የመሳሪያና የስንቅ ድጋፍ ሲያደርግለት የአውሮፓውያኑ ትልቅ የቤት ስራ እያሡን ከስልጣን ማስወገድ የሚለው ሆነ፡፡

አቤቶ እያሡ ምንም እንኳ እቅዱ ባይሰምርና ባይሳካለትም ሁሉን የኢትዮጵያን ጎሳ በማስተባበር ኤርትራን፣ጅቡቲን፣የበርበራንና የሞቃዲሾ ሶማሌን የማስመለስ ዕቅድ ነበረው፡፡ ከዚህም የተነሳ አቤቶ እያሡ 380 ሺ ጦር ለማሰናዳት ለየደጃዝማቾቹ በየግላቸው የሚያዘጋጁትን የጦር ሠራዊት ብዛት በመንገር የራሱንም ወስኖ "ፈረሴ ከቀይ ባህር ውሃ ሳይጠጣ ዘውድ አልጭንም" እያለ ይፎክር የነበረ ልዑል ነው፡፡

ከዚህ አንፃር ለአካባቢው ነዋሪዎች ድጋፍ ማድረጉ፣በጋብቻ መጣመሩም ሆነ መስጊድ ማሰራቱ፣እንደአፋሮች መፋቂያ መያዙ፣በየተጋበዘበት ቤት እንደእነሱ ለብሶ መታየቱ፣ወዘተ... በአገር ውስጥ ባለሥልጣናት ዘንድ "መናፍቅ" ቢያሰኘውም፤በእያሱ አገዛዝ ክፉኛ ቢበሳጩም፣እንዴት አድርገውና በምን አይነት ዘዴ ከስልጣን እንደሚያስወግዱት፣ጥፋቱን በማስረጃ ደግፈው ለህዝቡ እንዴት ማሳመን እንዳለባቸው የአገር ውስጥ ተቃዋሚዎቹ አልተረዱም ነበር፡፡ስለዚህ ኢትዮጵያውያኑ የልጅ እያሡን አካሄድ አለማማር መሠረት አድርገው ሲቃወሙት፣አውሮፓውያኑ ግን የልጅ እያሡ አካሄድ ሳይሆን አካሄዱ የሚያስከትለውን ውጤት አስበው ተቃወሙት፡፡እናም ኢትዮጵያውያኑ የጠፋባቸውን የማባረሪያ ዘዴ አውሮፓውያኑ በልግስና ሊሰጧቸው የስራ እቅድ ወጣ፡፡

ልጅ እያሡ ምንም የስልጣን ዘመኑ ቢያጥር ምኒልክ የጀመሩትን የአውሮፓ ስልጣኔ ወደአገር ውስጥ ለማስገባትና ኢትዮጵያም ስልጡን አገር እንድትሆን መጣሩን ቢገፋበትም ብዙዎች ሊረዱት አለመቻላቸው ይታወቃል፡፡ ይህ ሲባል ግን የዘመኑ ጥቂት ምሁራን ከጎኑ ሆነው ድጋፋቸውን ይሰጡት እንደነበር አይዘነጋም፡፡

ልዑሉ በዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት ለ3 ዓመታት ያህል ስለተማረም ፈረንሣይኛ ቋንቋን በጥቂቱ ለምዶ ነበርና ከውጭ ትገር ሰዎች ጋር

መግባባት ጀምሮ ነበር፡፡ ጥልቀት ያለው ውይይት ከውጭ ዜጎች ጋር የሚያደርግ ከሆነም በአስተርጓሚው በፊታውራሪ ተክለሃዋርያት ተክለማርያም በኩል ይወያይ ነበር፡፡ ስለዓለም አቀፍ ፖለቲካዊ ጉዳዮችም እንደ አንድ አገር መሪ ግንዛቤው ነበረው፡፡ ስለዚህም በኢትዮጵያ ድንበሮች ባሉ ጎረቤት አገሮች ቅኝ ገዥነታቸውን ተክለው ያሉ አገራት አልችል ብለው እንጂ ኢትዮጵያንም ቅኝ ማድረግ እንደሚሹ ለልጅ እያሡም ሆነ ለማንም ኢትዮጵያዊ ግልፅ ነውና ይህን ስጋት ለመቅረፍ የሚያስችል መንገድ ከተገኘ ማንኛውም አካል ይሄድበታል፡፡. እያሡም የተከተለው ይሄንኑ ነው፡፡

ፈረንሣይ፣ እንግሊዝና ጣሊያን በሱማሌ ግዛት ተካፍለው ለኢትዮጵያም መሣሪያም ሆነ ሌላ ነገር ሊገባ ሲል ወደቡ የነሱ ነውና የመከልከል፣ አንዳንዴም መጥኖ የማሳለፍ ስልጣንን ይተገብሩ ነበር፡፡ በተጨማሪም ኢጣሊያ ኤርትራን ከነወደቧ ወስዳለች፡፡ የልጅ እያሡ የፈረሱ የቀይባህርን ውሃ የመጠጣት ጉዳይና የኦጋዴንና የአካባቢው አልፎም ሱማሌን የመጠቅለል ፍላጎት ግልፅ ግጭት እንደሚከሰት ስለሚታወቅ ልጅ እያሡ እነዚህን ጠላቶቹን ለማባረር ይረዳው ዘንድ የእነሱን ተፃራሪ ቡድን መቀላቀልና ድጋፍ አድርጎ መጠቀምን መምረጡ አያስነቅፈውም፡፡

በዚያን ጊዜ ቱርክ የስዊዝ ካናልን ለመቆጣጠር በመፈለግ በሜዲትራኒያን በኩል ሞክራ ስለከሸፈባት አካሄዷን በመለወጥ የሶማሌን፣ የኢትዮጵያንና የሱዳንን መንግስት ከግብፅ ጋር በማስተባበር እንግሊዝንና ፈረንሣይን ከስዊዝ ካናል ለማባረር ስትል በቀይ ባህር በኩል ጦርነት እንዲከፍቱ ትገፋፋ ነበር፡፡

ልጅ እያሡ በበኩሉ የሶማሌ ግዛቶችን ለመጠቅለል ይፈልግ ነበርና ለአራት ቀን ጅቡቲን ጎብኝቶ በነበረበት ጊዜ ዘንጉን ወደቡ ላይ ተክሎ "እስከዚህ ድረስ ግዛቴ ነው" ብሎ ተመለሰ፡፡ ወዲያውም ለቱርክ አምባሳደር አንድ፣ ለሶማሊ ባለባቶች 12 የኢትዮጵያ ባንዲራዎች ላይ "ላ ኢላ ሐ ኢለላ" የሚል ፅሁፍ አፅፎ ላከላቸው፡፡ ይህን በማድረጉም ክርስቲያንና ሙስሊሙን በእኩልነት የሚያስተዳድር ንጉስ መጣልን በማለት 12ቱ የሱማሌ ጎሳዎች በደስታ ለልጅ እያሡ ገቡለት፡፡

ቱርክም የልጅ እያሡን ወዳጅነት በአዎንታ ተቀበለች፡፡ እያሡ ጅቡቲን በጎበኘበት ጊዜ ተቀብሎ ላነጋገረው ለጅቡቲ ዋና አስተዳዳሪ በግልፅና በድፍረት "በፈረንሣይ እዚህ መኖር ደስተኛ አይደለሁም፡፡ አንተም ወዳገርህ ግባ፡፡ በእኛ አገር ውስጥ እንድትቀመጥ አስፈላጊ አይደለም፡፡" ቢለውም አስተርጓሚው ፊታውራሪ ተክለሃዋርያት ሌላውን ንግግር ሁሉ ተርጉመው ይህንን ግን "ለዲፕሎማሲው ሰግቼ ተርጉሜ ሳልነግረው ቀረሁ" ይሉናል፡፡



በዚህም ላይ የአንደኛው የዓለም ጦርነት እየተካሄደ ነበርና የእያሡ የውጭ ፖሊሲ ለእንግሊዝና ለፈረንሣይ ከፉ ራስ ምታት ሆነ፡፡ ሁለቱ አገሮች ይህን ሁኔታ ሲረዱና አቤቶ እያሡ ከጀርመኑ ንጉስ ከዳግማዊ ዊሊያምና ከቱርክ መሪ ከሱልጣን መሐመድ 6ኛ ጋር መወዳጀቱን እንዳዩ በየቆንሲሎቻቸው በኩል የተቻላቸውን ሴራ በመሸረብ ውድቀቱን ማፋጠን የሚል አቋም ወሰዱ፡፡

ልጁ እያሡ ከጀርመንና ከቱርክ ጋር የማበር አዝማሚያ ያሳየው ስልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ የነበረ ሲሆን፣ ከጀርመናዊቷ ኦስትሪያ መሣሪያ ለመግዛትም ተዋውሏል፡፡ ከዚህም ባለፈ ጀርመንን ለማገዝ ወደቀድሞዋ ታንጋኒካ የአሁኗ ታንዛኒያ ወታደር ልኳል፡፡
እነዚህ ወታደሮች አሩሻ በተባለው ግዛት ስለቀሩ ከአካባቢው ህዝብ ጋር በጋብቻ ተሳስረው በአሁኑ ወቅት የልጅ ልጆቻቸው ወደ 700 ቤተሰብ የሚሆኑት እዚያው ገበሬ ሆነው ቀርተዋል፡፡ ታንዛኒያ ነፃ ከወጣች ጊዜ አንስቶ የእነዚህ ሰዎች ዜግነት ጉዳይ ሲያነጋግር ቆይቷል፡፡

አቤቶ እያሡን ከስልጣን የማውረዱ ሴራ ሲጀመር ሐረር የነበረው የእንግሊዝ ቆንሲል ከሥልጣኑ እንዲለቅ ተደረገና በምትኩ ዓረቦችን ቀሳቅሶ በቱርኮች ላይ እንዲነሱና ቱርኮች ይዞታቸውን እንዲለቁ ያስደረገው የእንግሊዝ ሰላይ የጦር መኮንን የሆነው ሻለቃ ቲ.ኢ. ሎውሬንስ ወደ ሐረር መጣ፡፡ሎውሬንስ ኦፍ ዓረቢያ እየተባለ የሚጠራው ይህ የእንግሊዝ ባለሥልጣን ሐረር ገብቶ እያሡን ከስልጣን ለማውረድ የሚያስችለውን ስራ መጀመር ብቻ ሳይሆን ተተኪውን ገዥም እስከመምረጥ ደረሰ፡፡ለዚህም ሲል የእያሡን የአገር ውስጥ ተቃዋሚ መኳንንቶችን ድክመትና ብርታት፣አጠቃላይ የኢትዮጵያን ሁኔታ፣ ባህል፣ወግ፣አስተሳሰብ ሳይቀር በሚሲዮኖችና ኢትዮጵያ ውስጥ በሚኖሩ የውጭ ዜጎች አስጠንቶ በዙሪያው ካሉ መሰሎቹ ጋር መክሮ የሚከተለውን የስራ እቅድ ወደተግባር ለወጠው፡፡

1ኛ. ለየመኳንንቱ ልጅ እያሡ መስለሙን ማስተጋባት፣

2ኛ. ለዚህ ተግባር ሙሴ ሊዮን የተባለውን አርመናዊ ታዋቂ ፎቶግራፍ አንሺ የልጅ እያሡን መልክ በፎቶግራፍ ጥበብ የሙስሊም ልብስ የለበሰ አስመስሎ 20 ሺ ኮፒ በግብፅ አገር አሳትሞ በማስመጣት በገብረህይወት ባይከዳኝ አማካኝነት እንዲበተን፡፡በዚህ መሠረት ልጅ እያሡን "ሃይማኖት በመለወጥ" በሚል ክስ ወንጅለው ማስረጃው ፎቶ ግራፍ ሆኖ፣ በተጨማሪም ወሬውን በድፍን ኢትዮጵያ እንዲሰራጭ በማድረግ፣ከዚህም ባለፈ በአማርኛና በፈረንሣይኛ ፅሁፎች በድሬዳዋ ማተሚያ ቤት እያሳተሙ በማሰራጨት ሹማምንቱንም፣ካህናቱንም፣ተራውንም ህዝብ አሳመኑት፡፡ የ ቲ ኢ. ሎዎሬንስ እቅድም በትክክል ሰራ፡፡



ቱ. ኤ. ሎምራን

በዚህ ምክንያት ቀጥለን እንደወረደ በምናየው የክስ ዝርዝር መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም ልጅ እያሡ እንዲሻር ተደረገ፡፡

የልጅ እያሡ መሻር ሐረር ላይ እንደተሰማ ከተማው ተረብሾ 500 ያህል ሰው ሞተ፡፡ ልጅ እያሡም መሻሩን እንደሰማና ምክንያቱንም እንዳወቀ መኳንንቶችንና ካህናቱን ሰብስቦ መፅሐፈ ቄዳር ተጠምቆ ሰለመ የተባለውን አስተባበለ፡፡ ሐረር የነበሩትን የካቶሊክ ጳጳስም ጠርቶ ሁኔታውን እንዲረዱትና አለመስለሙን አረጋግጠው ምስክር እንዲሆኑት አደረገ፡፡ ነገር ግን ማንም ሊሰማው አልቻለም ነበር፡፡ "መስለሙን ፈፅሞ አላምንም" ብለው ጥቂት ያንገራገሩት ዋናው ጳጳስ አቡነ ማቴዎስ ብቻ ነበሩ፡፡ ሆኖም ተፅዕኖው ቀላል አልነበረምና የአድማው ተባባሪ ከመሆን አልዳኑም፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ የንግስና ስርዓት በጳጳስ መቀባቱ የግድ እንደነበረ ሁሉ በክስ ሲሻርም የጳጳሱ ይሁንታ የግድ ያስፈልግ ነበርና በመጨረሻ አቡነማቴዎስ ክሱን አፅድቀው ልጅ እያሡ ሊሻር ችሏል፡፡የጳጳሱ ሚና ከክሱ መጽደቅ ይልቅ ግዝቱን በማንሳት ላይ የተመሰረተ ነበር፡፡



አቤቶ ኢያሱ ሚካኤል



ክሱን እንደወረደ ስናየውም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

"በ፲፱፻፱ ዓመተ ምሕረት መስከረም በ፲፯ ቀን፡፡

ልጅ ኢያሱ የጃንሆይን ያጼ ምኒልክን ትእዛዝ ስላፈረሱ ያባታችንን ያቡነ ማቲዎስን የእጨጌ ወልደጊዮርጊስንም የመሐላና የግዝት ቃል ስለጣሱ መኳንንቱም ሠራዊቱም ሕዝቡም ሁሉ ተሰብስቦ ላባታችን ላቡነ ማቲዎስና ለእጨጌ ወልደጊዮርጊስ ያስታወቁበት የጩኸት ቃል ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው፡፡

ጃንሆይ አፄ ምኒልክ ለሃይማኖትዎና ለመንግሥትዎ አጅግ ተጨናቂ ነበሩና ቀድሞ እንዳለፉት ነገሥታት ጊዜ ሠራዊታቸው እርስ በርሱ እንዳይተላለቅባቸው በመንግሥትዎም ንፋስ እንዳይገባበት አስበው ፈጽመው እቤት ሳይውሎ በ፲፱፻፩ ዓመተ ምሕረት ሊቀ ጳጳሱና እጨጌ ቆማችሁ መኳንንቱንና ሕዝቡን ሰብስባችሁ ልጄን ኢያሱን ሰጥቻችኋለሁና ከሉ ፈቃድ የወጣ ሰው ርጉም ይሁን ጥቁር ውሻ ይውለድ፡፡ እሱም እናንተን ያለአግባብ የበደለ እንደሆነ ርጉም ይሁን ጥቁር ውሻ ይውለድ ብለው ሰጡን፡፡ አባታችንም እጨጌም በዚሁ ቃል አውግዛችሁ ሰጣችሁን፡፡ እኛም ደስ ብሎን ተቀበልን፡፡ የግዝትም ቃል እንዳይናወጥብን ተጠንቅቀን ባለንበት አገር ሁሉ በትሕትና ራሳችንን ደፍተን በተቻለን በሙሉ ልባችን መንግሥታችንን እየረዳን እስካሁን ቆየን፡፡ ከግዝቱም ቃል የወጣ ሥራ እንዳልሰራን አባታችንም መላ ኢትዮጵያም ያውቃሉ፡፡

የምናስታውቀውም ቃል ይኸ ነው

፩

መጀመሪያ ጃንሆይ ማረፋቸውን ሰው ሁሉ እያወቀው፤ ባረፉበት ሰሞን በልጅ ኢያሱ ትእዛዝ ሰው ሁሉ ፈረሱን እየጫነ ጉግሥ ሲጫወት ሰነበተ፡፡ የቀረው ቢቀር በዚያው ሰሞን ማዘንና መተከዝ ይገባ ነበር፡፡ መኳንንቱና ሕዝቡም ለጌታው ሳያለቅስ እንባው እንዳረገዘ ቀረ፡፡ ምኒልክን የመሰለ የድኃ አባት እናት የነጋሲው ንጉሣችን መላ ኢትዮጵያን አንድ አድርገው አስማምተው አሕዛብ አቅንተው ባፀኑት መንግሥት በሰሩትም ዐብያተ ክርስቲያናት ጧፍ ዕጣን ሳይባልላቸው ቀረ፡፡ አጽማቸውም የወደቀበትን ቦታ አባታችንም ያውቁታል፡፡ በጃንሆይ ማረፍ ሕዝቡ በግልጽ እንዳያለቅስ ማድረጋቸውና አለማስፈታታቸው መንግሥት እንዳይነቃነቅባቸው ይሆናል፤ ተነገ ዛሬ ፍታት አስፈቱ ምጽዋት አድርጉ ይሉናል እያልን ስንጠብቅ ይህን ያህል ቀን ቆየን፡፡ ያባታቸውንም ማረፍ ከምንም ሳይቆጥሩት የቀሩት ለካ ሃይማኖታቸውን ከለወጡ ብዙ ጊዜያቸው ኖሯል፡፡

፪

ሃይማኖት መለወጣቸውንና ከክርስቲያን መንገድ መውጣታቸውን መግለጽ ከወጡት ዠምሮ የሰሩትን ያልተገባ ሥራ ሁሉን ጽፌን ለመጨረስ አይቻልምና ዋና ዋናውን ብቻ ባጭር ቃል እናመልከት፡፡

ጌታችን ጃንሆይ የሮፓን ሥርዓት እኔው ተሸቀዳድሜ ባገሬ ታላገባሁና በሁሉም ነገር እነርሱን ካልመሰልኋቸው አይሆንም ብለው ከተማ መጠበቁና የሮፓን ሥርዓት ማስለመጃ ይሁን ብለው የሌሊት ዘበኛ ቢያቆሙ፤ ልጅ ኢያሱ አሥር አሥር አሽከር እያስከተሉ ሌሊት እየዞሩ እንደ ሽፍታ ከዘበኞቹ ጋራ እየተታኰሱ ጠንክረው የሚጠብቁትን ዘበኞች እየገደሉ በከንቱ ደማቸውን እያፈሰሱ የቆመውን ደምብ በገዛ እጃቸው ስላልረባ ነገር አፈረሱት፡፡

፫

የእስላም ቃልቾች እየሰበሰቡ የመሐመድንና የግራኝን ታሪክ እያስነበቡ ያያቶቻቸውን ዘር እያስቆጠሩ የይማሞች ዘር ከመሐመድ ዘር የወረደ ነው አሰኝተው እስላምነታቸውን ካደላደሉ በኋላ የእስላም ሴት እየፈለጉ ያባ ጅፋርን ልጅ፣ የእሁቴን ልጅ፣ የአሚር አብዱላሂን ልጅ፣ የነጋድራስ መሐመድን ልጅ፣ ያዳልንም የባላባት ልጅ፣ እነዚህን ሁሉ አግብተው ቁባቱ የቀሩትማ የእስላም ሴቶች ስንቱ ተጽፈው ያልቃሉ፡፡ ስንኳስ ያልተጠመቀችዋንና ክርስቲያኗንም ብትሆን በመጽሐፋችን የታዘዘ አለ፡፡

፬

አባታችንም እጨጌም ይህ ሁሉ ሥራ ሲሰራ እያወቁና እየሰሙ መክረው ለመመለስ ተሸነፉ፡፡ አባታቸው ንጉሥ ሚካኤል ልጃቸውን መክረው ከዚህ ከክፉ መንገዳቸው ይመልሱልናል ብለን ተስፋ ስናደርግ አሸንፈዋቸው ኖሮ አምና በፍልሰታ የእስላም ጾም ገጥሞ ነበርና አባታቸው ከተማ ደሴ ላይ የሰሩት የክህደት ሥራ በጅሌና በጡሙጋ፣ በጨኖ፣ በጀላሌ ሲያደርጉት የከረሙት ሥራ ሁሉ ቢጽፉትም አያልቅ፡፡ ለመስማትም ደስ አያሰኝ፡፡ ይኸን ሁሉ ሥራ ሲሰሩ መኳንንቱም ሠራዊቱም እያየ እየሰማ ህፃን ቢሆኑ ነው እያለ ትዕግሥት ቢያበዛ ልጅ ኢያሱ ዘውዳቸውን ጭነው በክርስትና ፀንተው መንግሥታቸውን ጠብቀው መያዝና ማጥናት ጠልተው እድሜአቸው ለእውቀት ሲደርስ ሃያ ዓመት ሲሞላቸው የቃልቻን ቃል እየሰሙ በኢትዮጵያ የክርስቲያን መንግሥት አልቋል፡፡ ከመሐመድና ከግራኝ ዘር የወረዱት የይማሞች መንግሥት መነሻው ደርሷል እያሉ አምና ሐረርጌ የወረዱ ጊዜ አራቱ አድባራት ቤተ-ክርስቲያን ገብተው አንድ ጊዜ እጅ ሳይነሱ ቀሩ፡፡ ከዚያም ሁሉ አብያተ-ክርስቲያናት ላንዱ እንኳ ገንዘብ ሳይሰጡ የመላው ሐረርጌ



እስላም እየተሰበሰበ የሚሰግድበት መሥጊድ ሄደው አብረው ሰገዱ፡፡ ባምስቱም በር ዙሪያ ላሉት መሥጊዶችና ቃልቾች አትርሱኝ እያሉ ብዙ ገንዘብ ሰጡ፡፡

፭

ጃንሆይ ሐረርጌን የሰበሩ ጊዜ ከክርስቲያን ሰዋጋ ያለቀውን እስላም ቦታውንና ቤቱን ሁሉ ጃንሆይ በፈቃዳቸው ለመንግሥት እርስት ይሁን ብለው ለካህናትና ለከተማው ዘበኛ ከከተማ ለማይለይ ሰራተኛ ሰጥተውት የፈረሰውን መልሶ እየሰራ የዘባውን እያቀና ይህንን ያህል ዘመን ይዞት የኖረውን ቤት ለእስላሙ ልቀቁ ብለው አስለቀቁት፡፡ ካህናቱም ከታቦቱ ተለይቶ ወጣ፡፡ ድኊውም አልቅሶ ለቀቀ፡፡

፮

ያሩሲ ጋላ ሽፍቶ ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስና ቢትወደድ ኃይለጊዮርጊስ ሽፍታውን ለማርጋት ጦር ቢልኩ ይኸውም ከጥፋት ተቆጥሮባቸው ተነቀፉበት፡፡ ይኸም እስላም እንዳይነካ ለማድላት ነው፡፡ እንደዚሁም የመሰለ በደጃዝማች ተፈሪ ግዛት በውጋዴን አርባ አምስቱን ወታደር ሱማሌ አርዶት ሥራት ሳይታይ ይልቁንም ሱማሌዎቹ አዲስ አበባ ቢመጡ ተሸልመው ሄዱ፡፡ የክርስቲያኑም ደም እንደውሻ ደም ሆኖ ቀረ፡፡ ይህም ነገር እስላም በክርስቲያኑ መቀባቱ ነው፡፡

፯

አዲሱ ከተማ ድሬ ደዋ ላይ ቀድሞ ያልነበረውን መስጊድ ተሰርቶ አሁን ከዚህ ከወረዱ የእስላም አሊሞች ልብስ ለብሰው የእስላም ጥምጥም ጠምጥመው ግልድም አገልድመው ፈጽመው የክህደት ሥራ ሠርተው እመሥጊዱም ገብተው አብረው ሠገዱ፡፡ ለመስጊዱም ብዙ ገንዘብ ሰጡ፡፡ የእኛ ታቦት ግን አስቀድሞ ተቆርቁሮ በመቃኞ የኖረውን ካህናቱም መኳንንቱም ቢያስታውቅ እስካሁን ሳይሰራ ቀርቶ የመሥጊዱ ሥራ በልጦ ቀደመው፡፡

፰

ጅጅጋ ላይ ዳርቻ አገር ነው በዚያ ውስጥ የሚቀመጥ ክርስቲያን መቅደስ ካልተተከለለት ሰውነቱ ይማግጣል ብለን የተከልነውን ታቦት ይህ ለመሥጊድ የሚሆን ቦታ ነውና ታቦቱ ከሌላ ቦታ ሄዶ ይደረብ ብለው ካህናቱም ታቦቱን ይዘው ጊሪ ከሚባል ቦታ ተዳብለው ተቀምጠዋል፡፡ ይህስ የእስላም ወገን አጽፒ ነኝ ማለት አደለም፡፡ አሁን መጠቅለያውን የሐረርጌ መድሃኒዓለም ቤተ-ክርስቲያን የተሰራበት ቦታ ቀድሞ መስጊድ ነበርና ታቦቱ ይውጣና እንደጥንቱ መሥጊድ ይሁን ብለው ነበር፡፡ በቅርብ ቀን ነገር የሚነሳባቸው ቢሆን ለጊዜው ትተውታል፡፡ ለኋላው ግን አሳባቸውን ሳይፈጽሙት አይቀሩም፡፡

፱

ከዚህ ሁሉ የሚከፋ ሥራ ሲሰሩ እስካሁን ከስላም ጋራ እየተጋደለ በክርስትና ፀንቶ በዓለም ሁሉ ታውቆ እራሱን ችሎ የኖረውን የኢትዮጵያን የክርስቲያን መንግሥት ስሙን ከምድር አጥፍተው ሃይማኖቱን አስለውጠው የእስላም ዜጋ ሊያደርጉ የመንግሥታችንና ያገራችንን ክብርና ስም መጠሪያ በሰንደቅ አላማችን ላኢላ ሐኢላላ መሐመድ ረሱል አላህ ብለው አስጽፈው ወስደው ለቱርክ መንግሥት ቆንሲል አስረከቡት፡፡ ሰንደቅ ዓላማ ማለት ትርጓሜው በመንግሥት ፋንታ ሆኖ ለዓለም ሁሉ የሚታይና የሚታወቅ ምልክት ማለት ነው፡፡ ለዚሁ ምስክር መንግሥት ሲባል ሰንደቅ ዓላማ የሌለው መንግሥት የለም፡፡ የቱርክ መንግሥትም ቆንሲል ይህነን ሰንደቅ ዓላማ ተቀብሎ ብዙ ደስታ አድርጎ ሻምፓኝ ከፍቶ እያጠጣ የኢትዮጵያ መንግሥት የእስላም ሃይማኖት ከዓለም ሁሉ ሃይማኖት የተመረጠ መሆኑን ተረድቶት ዛሬ አመነ፡፡ ለዚሁም ምስክር ሰንደቅ አላማውን ለእስላሞች ጠቅላይ ለቱርክ መንግሥት አስረከበ፡፡ እንግዴህ ከዛሬ ዠምሮ የቱርክንና የኢትዮጲያ አንድ መሆን የሚጠራጠር ሰው ቢገኝ ወንጀል ይሆንበታል እያለ በጉባኤ መረቀ፡፡ የውጪ መንግሥት እንደራሴዎች ይህነን ሰምተው ሰንደቅ አላማችሁን አስመልሱ እያሉ ቢመክሩ የሚሰማቸው ጠፍቶ ሰንደቅ አላማው አሁንም በቱርክ ቆንሲል እጅ እንዳለ ነው፡፡

፲

በፍፁም መስለማቸውን ለይቶ የሚያስታውቅ እስከ አርባ ትውልዳቸው በጠርቡሽ ላይ አጽፈው ወገናችሁ ነኝና እስላምነቴን እወቁ ብለው ለሐረርና እስላም ሱማሌ ሽልማት ሰጡ፡፡ ድብቅ የሌለው ሕዝብ ያየው ነገር ነው፡፡ ይህስ ክርስቲያኑን መካድ አይደለምን፡፡

፲፩

ሐረርጌ የእስላሙን ቃዲ ጠላና ጠጅ ትጠጣለህ አሉ ስለምን የስላም መጽሐፍ የማያዘውን ትሰራለህ ብለው ከሳሽ ሳይነሳበት ባደባባይ ፍረዱ ብለው ክርስቲያኑንም እስላሙንም አስፈርደው አሰሩት፡፡ እስላሙስ ይፍረድ ክርስቲያኑን በማያውቀው ሕግ ቀላቅለው በፍርሃት ማስፈረዳቸው የምን ማድረግ ይመስላል፡፡

፲፪

አሁን ጅጅጋ ከወረዱ የሱማሌን ውጋዝና ባላገር ሰብስበው ሙሉ የጦር ልብስ ሸልመው የኢትዮጵያን መንግሥት ባለ ግርማ ሰንደቅ ዓላማችንን እዚህ አዲስ አበባ ለቱርክ መንግስት ቆንሲል የተሰጠው አንሶ አስራ ሁለት ሰንደቅ ዓላማ ላኢላ ሐኢላላ መሐመድ ረሱል አላህ የሚል ተጽፎበት ምሳሌ የሚሆን ክር እሰንደቅ ዓላማው ላይ ተንጠልጥሎ ይህነኑ ክር የሚበጥስ ፋስ የያዘ ጠርቡሽ ያደረገ ሰው ሥዕል ተሥሎበት



ለሱማሊዎች ሰጥተዋቸው ባደባባይ ይዘውት መጥተው ፈከሩበት፡፡ ይ
በክርስቲያኑ በኢትዮጵያው ሕዝብ ላይ መነሳት አይደለምን፡፡

፲፫

የኢትዮጵያን መኳንንትና ሕዝብ ወደ ጥፋት መሄዱን እያ
እያወቀ ዝም ብሎ ትዕግሥት ቢያበዛ ፈረንጆች የልጅ ኢያሱን ሥራ ሁሉ ተመልክተው ይህ ነገር ጂሂድ የማስጠናትና የኢትዮጵያን ክርስቲያን አጥፍቶ በመጨረሻው በእኛ ላይ የሚከፋ ነገር ለማምጣት ነውና ይህን ነገር ለመንግሥት እናመልክትና ለራሱ ብላሃት ቢያበጅ ያብጅ በተቀረ እኛ የምንሰራውን ሥራ እናውቃለን ብለው ባንድነት ሆነው በግልጽ አስታወቁ፡፡ ይህነን ነገር አስቀድመው ለመንግሥት ማመልከታቸውን ብናውቅበት ለእኛ እጅግ መልካም ነገር ነው፡፡ ከፋት አሰበው ቢሆን ግን ዝም ብለው ቆይተው ልጅ ኢያሱም አሳባቸውን ከፈፀሙ በኋላ ባገራችን ላይ በክፉ ለመነሳት ይመቻቸው ነበር፡፡ ጃንሆይ የመሠረቱትን ውል ጠብቀን ተጠንቅቀን ከኖርን ግን ኢትዮጵያን የሚነካት ሰው የለም፡፡ ባንድ በልጅ ኢያሱ ውል ማፍረስ ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይጠሉ እንዴት ለምለም አገራችንን እናስወስዳለን ሃይማኖትስ ሲፈርስ ምን እናስተውላለን፡፡ አሁን ደግሞ ጂሂድ እያሉ የጃንሆይን አሽከሮችና የክርስቲያን ደም ያፈሰሱትን እስላሞች ሼኽ ጦለሃን ያሰን እንጃሞን ልጅ ያባ ጅፋርን ልጅ ደግሞ ሌሎች ብዙዎች እንደነዚሁ ያሉትን ይዘው እዋናው እስላም አገር ጅጅጋ ተቀምጠው ውጋዴን ውስጥ ሽፍታ ሆኖ እያስቸገረ ከሚኖረው ጅጅጋም ድረስ መጥቶ ክርስቲያን ሊፈጅ ከነበረው ከከቢራው ጋራ እየተላላኩ ብዙ ጠበንጃና ጥይት መትረየስም ሰደዱለት፡፡ ደግሞ የእንግሊዝንና የኢጣልያንን ዜጎች በየወሩ እየሰበሰቡ ጂሂድ እንበል እያሉ መክረዋል፡፡

ዛሬ ጅጅጋ ወርደው መምከራቸው የእስላም መካከለኛ አገር ነውና ጂሂድ በሚሉበት ጊዜ ኃይላቸው እንዲበረታላቸው ነው፡፡

እሳቸው ግን እስላም ያረደውን እየበሉ አገር ለማስፋትና ሰው ለማባበል ነው እያሉ የሚያታልሉት ይህ ሱማሌና እስላም ከዚህም በፊት በጃንሆይ የገበረ የቀቀለ ዜጋቸው ነው፡፡ ልጅ ኢያሱ ግን ከእስላሙ ጋራ አብረው በመብላታቸው የራሳቸውን እስላምነት ለማጽናት ነው እንጂ በማባበሉስ ፊት ከቀናው አገር በተቀረ ስንዝር መሬት የጨመሩት ነገር የለም፡፡ አሁንም ጃንሆይ ያሸከሮቻቸውን ደም አፍስሰው ያቀኑት አገር የስላም ሰንደቅ ዓላማ ሊሰቀልበት ክርስቲያንም የሰሩት ዐብያተ-ክርስቲያናት የእስላም መስገጃ ሊሆን ነውና ሃይማኖት መፍረሱን መንግሥት መጥፋቱን አስበን እንቻልህ እንታገሥህም ብንለው የማይቻለን ሆነ፡፡ ስለዚህ ከሮፓ በፊት በወንጌል ተሰብኮ በክርስትና ፀንቶ እስካሁን የኖረውን መንግሥት አሁን የእስላሞች ዋና ገዢ የቱርክ መንግሥት

ሊወድቅ በደረሰበት ሰዓት ወደ እስላምነት ሲመለስና የክርስቲያን ደም እንደ ጉርፍ የፈሰሰበት አገር ኢትዮጵያ የእስላም ሰንደቅ ዓላማ ሲሰቀልባት ከማየት አስቀድሞ የሃይማኖት አምላክ ይርዳን ብለን ስለ ሃይማኖትና ስለ መንግሥት ደማችንን ለማፍሰስ ቆርጠናል፡፡ እንግዲህ መንግሥት ያለ ሃይማኖት፣ ሃይማኖት ያለ መንግሥት እንዳይጠና የታወቀ ነውና፣ ለዚሁም መንግሥትና ሃይማኖት ጃንሆይ አልጋ ላይ ከዋሉ ዠምረው እስካሁንም የደከሙበት አባታችን ነዎ ሃይማኖት ይጥና መንግሥታችን ይርጋ ያሉ እንደሆነ የማርቆስ ሃይማኖት አምላክ ለዳዊት እርዳታ ያወረደ መንፈስ ቅዱስ አይለያችሁ ብለው አባታችን መስቀልዎን እፊታችን ይዘው ሃይማኖታችንን ያጥኑልን፡፡

እስላም ጃሂድ ካለ በኋላ ነገሩን ለማብረድ የሰደድ እሳት ለማጥፋት እንዲያስቸግር እንደዚህ ያስቸግራልና በቶሎ ካልነቃንበትና በቶሎ ካላጠፋነው ስር ከሰደደ በኋላ ይልቁን ብዙ የክርስቲያን ደም ይፈስብናል፡፡ ይኸም የተነሳንበት ሁሉ በሹመት በሽረት በማግኘት በማጣት አይደለም፡፡ ለሃይማኖታችንና ለመንግሥታችን ስንል ነው፡፡ ለዚሁም የኢትዮጵያ አምላክ ይመስክርብን፡፡" /ጥላሁን ብርሀነስላሴ ቤት 1996/

ክሱ ያየነውን ሲመስል ዋና ወንጀሉ መስለም የሚለው ነው፡፡ በዚያ ዘመንም ሆነ ያ ዘመን ካለፈ በኋላ ግን ዛሬ ድረስ አለመስለሙን እንጂ መስለሙን የሚያረጋግጥ ምንም ማስረጃ አልተገኘም፡፡

በዚያ ወቅትም ቢሆን በልጅ እያሡ ክስ ያልተስማሙ ታላላቅ ሹማምንት ነበሩ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ደጃዝማች ባልቻ አባነፍሶ እና ሊጋባ በየነ ይጠቀሳሉ፡፡ ሌሎች የእያሡ ደጋፊዎችም ሊታደጉት አልቻሉም እንጂ የሐሰት ክስ መሆኑን በአፅንኦት ገልፀው ነበር፡፡ ነገር ግን የእያሡ ተቃዋሚዎች ነገሩ የተረጋገጠ አስመስለው "ድሮስ ከመሐመድ ዓሊ ልጅ ምን ይጠበቃል?" በሚል እርግጠኝነትን በሚያጠናክር ቃል ያስተጋቡት አሉባልታ በርካቶችን አሳምኖ ነበርና ደጋፊዎቹ ሳይቀሩ ያድማው ተሳታፊ ሆኑ፡፡

የ20ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ በሚለው መፅሐፍ ውስጥ የተካተተውን ገለፃ ስናይ፣"የቅርብ አሽከሮቹ በሙሉ ከእሱ ህይወት በኋላም ሁሉም አለመስለሙን እየገለፁ ይምሉ ይገዘቱ ነበር፡፡ወ/ሮ አስካለማርያም ጆቴን አስልሞና ሙሚና ሰኝቶ አግብቷል የተባለውን ወይዘሮዋ እንዳልሰለሙ ልጃቸው ወ/ሮ ፅጌ ሻረው በኋላ ላይ አስተባብለዋል፡፡" ይላል፡፡በመቀጠልም "የአቤቶ እያሡ ሁኔታ ግራ የሚያጋባ ቢሆንም፣ በይፋ ግን ሃይማኖቱ ክርስቲያን መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በመጨረሻ ላይ እንኳን እጁ የተያዘው ግብፅያ ገዳም ውስጥ ተሸሽጎ ነበር፡፡" ሲሉ ያክሉበታል፡፡





አቤቶ እያሱ ከአብደላ አሊ ሳዲቅ ቤተሰብ ጋር በሃረር

በተመሳሳይ ሁኔታ ፕ/ር ባህሩ ዘውዴ "ክሱ ሀቀኛ መሠረት አልነበረውም፡፡ የአገር ውስጥም ሆነ የውጪ መረጃዎች እንደሚያረጋግጡልን የእያሡ ጥረት ክርስትናን በእስልምና ለመተካት ሳይሆን ያለፈውን አድልኦ የተሞላበት ስርዓት ሽሮ ሙስሊሞች በገዛ አገራቸው እንደባይተዋር መቆጠራቸውን ለማቆም ነበር፡፡ የእያሡ ችግር ፖሊሲውን በግልፅ አለማብራራቱና በአፈፃፀሙ ላይ ከዘዴ ይልቅ ማንአለብኝነት መምረጡ ላይ ነው፡፡" በማለት በሃይማኖት ፖሊሲው እያሡን የሚተካከል ዘመናዊ የኢትዮጵያ መሪ ለማሰብ እንደሚያዳግት ካለፉ ነገስታቶች ጋር እያነፃፀሩ ይተነትኑታል፡፡ሲቀጥሉም "ከዚህ ሁሉ አኳያ ሲታይ የእያሡ የሃይማኖት ፖሊሲ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦችና የሁለቱ ታላላቅ እምነቶች አገር የሆነችውን ኢትዮጵያ ፍትህ በተሞላበት አንድነት ላይ ለመመስረት የተደረገ የመጀመሪያ ሙከራ ተብሎ ሊገመገም ይችላል" ይሉናል፡፡

ተክለፃድቅ መኩሪያ "የኢትዮጵያ ንጉስ ሊያደርገውና ሊፈፅመው ከሚገባው ዋና ዋና ነገሮች ውስጥ ይበልጦቹ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ናቸው" በማለት 5 ነገሮችን ከልጅ እያሡ ታሪክ ጋር በተያያዘ አስፍረዋል፡፡

1.አንድ ሴት በስርዓት ተክሊል አግብቶ መቀመጥ፣
2.ከአብርሃና ከአፅባሃ ጀምሮ በኢትዮጵያ ፀንቶ የኖረውን ?ኦርቶዶክስን ሃይማኖት ጠብቆ መኖር፣

3.ከመሳፍንት እስከተራ ህዝብ ያለውን ማንኛውንም ዜጋ እቅድ ባለው ሕግ ማስተዳደር፣

4ከቁጣና ያለ ሕግ ከመቅጣት ታጋሽ መሆን፣

5.በማንኛውም ረገድ ለንጉስነት የተገባውን ክብሩን በስውርም በግልፅም መጠበቅ ነው፡፡

ልጅ እያሡ ግን በእነዚህ እላይ በተዘረዘሩት ባንደኛው እንኳ የበጎ ስራ ሊይዙ በፍፁም አልፈለጉም ..." በማለት ምክንያታዊ ትችት ለመሰንዘር ይሞክራሉ፡፡
ምናልባት የተራ ቁጥር ሁለቱ ሊያስኬድ ከቻለ እንጂ ሌሎች ደንቦች ያው በልማድና በ"ቢሆን ይመረጣል" እንጂ በአዋጅ የተደነገጉበት ሁኔታ የለም፡፡ቀደም ሲል እንዳየነውም በርካታ ነገስታት በርካታ ሚስቶች ነበሯቸው፡፡ሦስተኛው ገለፃ ደግሞ እያሡ የተጋበት ተግባር መሆኑን ከታሪኩ እንረዳለን፡፡እያሡ ያለሕግ የፈፀመው ቅጣት አለ ለማለትም አያስደፍርም፡፡ክብር መጠበቅን በሚመለከትም እያሡ የንጉስነት ክብሩን የፈለገው ከአገር ዳር ድንበር መከበርና ከዜጎች እኩልነት በኋላ በጥምረት ሊያከብረው ነው ያሰበው፡፡

የፈታውራሪ ተክለሃዋርያት አገላለፅ ደግሞ፤ "... አልጋ ተዛወረ፣ ህዝቡም ለእስላም አንገዛም አለ" የሚል ነው፡፡ ሆኖም ህዝቡ የወሬውን እውነትነት አረጋግጦ አንገዛም አላለም፤ ይልቁንም አውሮፓውያኑ ካገር ውስጥ ሹማምንት ጋር ብቻ መክረው የወሰኑት ውሣኔ እንጂ፡፡ ከሱም ላይ ያየነው፤ "... አገር ለማስፋትና ሰው ለማባበል ነው እያሉ የሚያታልሉት ይህ ሱማሌና እስላም ከዚህ በፊት ለጃንሆይ የገበረ የቀቀለ ዜጋቸው ነው" የሚለውም አገር ማስተዳደር ማለት ሁሉንም ማስገበር መቻል ብቻ የመሰላቸው አስተሳሰብ ነው፡፡ እያስገበሩ ከመግዛት ይልቅ በፍቅር እያስገበሩ መግዛት የሚሻልም የሚመረጥም ዘላቂነት ያለውም መሆኑን ማሰብ የፈለጉ አይመስልም፡፡
በዚህም እያንዳንዱን የልጅ እያሡን አካሄድና ተግባር የሚያዩ የሱ ዘመን ሹማምንት ምን ጥሩ ቢሰራ በበጎ ጎኑ ሊያዩለት ፈፅሞ ዝግጁ ያልነበሩ መሆናቸውን በቀላሉ እንረዳለን፡፡

ምንም ቢባል ግን ልጅ እያሡን "ያልተዘመረለት እያሡ" ብሎ ለመጥራት የሚያስደፍር ቁንጮ ተግባር እንዳከናወነ /ለማከናወን እንደሞከረ/ አይካድም፡፡

ይህም በአሁኑ ጊዜ ስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ የተንቀሳቀሰበት ብሎም "የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የእኩልነት መብት" "የሐይማኖት እኩልነት" ይህን ስራውን ብቻ መዝዞ በማውጣት እንዳልተዘመረለት መግለፅ ይቻላል፡፡ ይህም ሲባል ኤርትራን፣ ጅቡቲን የበርበራንና የሞቃዲሾን ሶማሌ የማስመለስ እቅዱንና ለዚህም ሲል



380,000 ጦር ማደራጀቱንም ሆነ ሌሎች እንቅስቃሴዎችን ሁሉ ወደ ጎን ብናደርግ እንኳ ለማለት ነው፡፡

በጥቅሉ ልጅ እያሡ በስልጣን ዘመኑ ግጭት ውስጥ የገባው በዘመኑ ከነበሩት ሹማምንት ጋር ብቻ አልነበረም፤ ከሴረኞች አውሮፓውያን ጋር ብቻም አልነበረም፤ በዋናነት የተጋጨው ከዘመን ጋር ነበር ማለት ይቻላል፡፡

በሚገርም ሁኔታ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ "የልጅ እያሡን ስም ማጥፋት" የሚለው መርህ በእሱ ዘመን ብቻ ሳይሆን ዘመኑም እሱም ካለፉ በኋላ መቀጠሉን ለመታዘብ አንድ ነገር እንይና ከሽረቱ በኋላ የተከናወኑ ድርጊቶችን ወደማየት እንለፍ፡፡

ጉዳዩ ስለ አንደኛው የዓለም ጦርነት ነው፡፡ ቀደም ሲል እንዳየነው በጦርነቱ ጊዜ የቱርክ መንግስት ለጀርመን የጦር ጓደኛ እንደመሆኑ መጠን ጀርመን ኢትዮጵያን ከቱርክ ጋር አዛምዳ የሁለቱን ኃይል በመደገፍ በሰሜን አፍሪካ ያሉትን የጦርነቱ ተፋላሚዎች የእንግሊዝንና የፈረንሣይን ግዛት ለመቀማት አስባ ስለነበርና፤ ቱርክም የስዊዝ ካናልን በጁዋ ለማድረግ ፈልጋለችና፣ ልጅ እያሡም ለኢትዮጲያ ይበጃታል ያለውን ግዛቶቿን የማስመለስና የማስፋት ዓላማውን ማሳካት ይሻልና፤ ለጀርመንም ለቱርክም ተስማሚ ሆኖ ቀርቧል፡፡ በወቅቱ ለሦስቱ አገራት ከዚህ የተሻለ ምርጫ ነበራቸው ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡ የታሰበው ሳይሆን ቀረና ጀርመን ድል ሆነች፡፡ ስለዚህ በኋለኛው ዘመን "... ልጅ እያሡን በጊዜ ከስልጣን ማውረድ ባይቻል ኖሮ 1ኛው የዓለም ጦርነት ተጠናቆ ጀርመን ድል ስትሆን ኢትዮጵያም የተለየ ገፅታ ይኖራትና በተለያዩ የውል ስምምነቶች አማካኝነት ታሪኳ የሚበረዝበት ሁኔታ ይፈጠር ነበር..." በሚል እያሡና አገዛዙን ለመውቀሻነት አገልግሏል፡፡

ጀርመን እንደምትሸነፍ ልጅ እያሡም ሆነ ራሷ ጀርመን ቀድመው አያውቁም፡፡ ብዙ ነገር መዘርዘር ሳያስፈልግ ባጭሩ ይህ የ"ኖሮ" አስተሳሰብ የልጅ እያሡን መጥፎ ገፅታ አረጋጋጭ ሆኖ መካተት ይገባዋል ወይ? ነው ጥያቄው፡፡ በምንም አቅጣጫ ብናየው መልሱ ግልፅ ነው፡፡ ነገር ግን የእያሡን ደካማነት ለመግለፅ እንደ አንድ ግብአት /ያውም ካለፈ በኋላ/ ጥቅም ላይ የዋለ ገለፃ ሆኖ በብዙ ፅሁፎች ተካቷል፡፡ እዚህ ላይ በአቶ ብርሃነ ስላሴ መፅሐፍ በገፅ 105 የሰፈረውን ሐተታ ላክል፤

"ልጅ እያሡ ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በፊት የወገነው ከጀርመንና ከቱርክ ጋር ስለነበረ እነሱ በተሸነፉ ጊዜ የኢትዮጵያ ዕጣ ፋንታ ምን ይሆን ነበር ብሎ ለገመተ ሰው "እንኳን በጊዜው ልጅ እያሡ ወረደ" ብሎ መደምደም ይችላል፡፡ ባይወርድስ ኖሮ ከማይጨው ጦርነት የባሰ ነገር ኢትዮጵያ ላይ ይደርስባት ኖሯል? ምዕራባውያኖቹ የራሳቸውን ጥቅም እንጂ ወዳጅ የማያውቁ ስለሆኑ ምናልባት ልጅ እያሡ የወሰደው

እርምጃ የተለየ ሁኔታ ሊፈጥር ይችል ነበር ማለትም ሌላ አማራጭ ነው፡፡ ልጅ እያሡ ተሽሮ ሌላ ሰው ስልጣን ስለያዘ ኢትዮጵያ ወደቦቿን እንዳጣች ቀረች እንጂ ያገኘችው የተለየ ጥቅም አልነበረም፡፡"

ልጅ እያሡ በበላይነት በቆየባቸው 6 ዓመታት ለአያቱ መኳንንቶች አንድም ጊዜ ክብር አሳይቷቸው ባለማወቁ ብቻ ሳይሆን የቤተመንግስቱን የወግ እቃዎች የአፄ ምኒልክን ዘውድ ጭምር ወደ ደሴ በመውሰዱ ዋና ከተማውንም ወደዚያው ሊያዞር አስቧል የሚል ግምታቸው በእያሡ ላይ እምነት እንዳይጥሉ ካደረጓቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ ነበር፡፡

እነዚህን የመሳሰሉ አሉባልታዎችም ሆኑ አጠቃላይ የእያሡን አገዛዝ በሚመለከት ስለሚናፈሱ ወሬዎችም ይሁን ስለሚዘጋጅለት የትብብር ወጥመድ ልዑሉ ምንም ያህል ትኩረት አይሰጣቸውም፡፡ የእኔ የሚለው ሰላይም፣ ቃል አቀባይም የለውም፡፡ ወሬ ብለው ሊነግሩት የሚመጡትን ሳይቀር ቢያንስ ሊያዳምጣቸው ዝግጁ አልነበረም፡፡

ሌላው ቀርቶ ራሱ እንኳን የሸዋን መኳንንት በቅርብ ሆኖ ለመከታተል ፍላጎት ኖሮት አያውቅም፡፡ የእሱ የቅርብ ክትትል በኦጋዴንና በአካባቢው ላይ ብቻ ነበር ለማለት ይቻላል፡፡ የጦርነት ዘመቻ ካልሆነ በስተቀር ተደርጎ በማይታወቅ ሁኔታ ከፖለቲካው እምብርት ከአዲስ አበባ ርቆ ለ9 ወራት ያህል ሐረር ተቀምጦ ነበር፡፡

[illegible] ባዮች መኳንንትና ግዛታችን ስጋት ላይ ጣለብን ብለው በተንሰበት አውሮፓውያን ሴራ ባልዋለበት ተከሰ መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም ከስልጣን ሲሻር በምትኩ የአፄ ምኒልክ ልጅ ዘውዲቱ ንግስተ ነገስታት ተብለው ሲነግሱና ደጃዝማች ተፈሪ ራስ በሚል ማዕረግ አልጋወራሽ ተብለው ሲተኩ እንኳን ልጅ እያሡ በኦጋዴን አቅራቢያ በጅጅጋ አካባቢ ነበር የሚገኘው፡፡

ባለበት ቦታ ሆኖ መሻሩን የሰማው ልዑል የአካባቢውን ሹማምንት ሰብስቦ እየማለ እየተገዘተ አለመስለሙን ቢያስተባብልም ተቀባይነት አላገኘም ነበርና ሽረቱ ፀደቀ፡፡

ልጅ እያሡ በዚህ ጊዜ ወደ አባቱ ወደ ንጉስ ሚካኤል መልዕክት ላከ፡፡ ጦርም አዘጋጅቶ ወደ ሸዋ ሊዘምት ተነሳ፡፡ በወቅቱ ጥቂት የእያሡ ደጋፊዎች መሻሩን ቀድመው የሰሙት እሱን በጦር ለማገዝ ወደ ሐረር የሄዱ ነበሩ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ወታደር እንደሀ ሸለለ ይባላል፡፡

"አባ ጤና እያሡ ጥይት ግዛ! ጥይት ግዛ! ወገብክን ይጭነቀው!

እኛ ሰማን ወሬ አንተ የማታውቀው!"

እነዚህን የመሰሉ ጥቂት ደጋፊዎች ይኑሩት እንጂ ከደጋፊዎቹ ውስጥ በርካቶቹ በመጨረሻው ጊዜ ክደውት የአድመኞቹ ተባባሪ ሆነዋል፡፡

የአድማው ተሳታፊዎች ይሰበሰቡ የነበረው በዕጨጌው ቤት ነበር፡፡ ፊታውራሪ ሀብተጊዎርጊስ ዋናው አስተባባሪ ነበሩ፡፡ መሐል ሰፋሪዎች



ከጎናቸው ሲቆሙም ለእያሡ ይከራከሩ የነበሩት ሊጋባ በየነ ወንድማገኘሁ፣ በጅሮንድ ይገዙ በሐብቴ፣ የእያሡን እህት ወ/ሮ ስሂንን ያገቡትና እያሡ ትልቅ ስልጣን የሰጣቸው ቢትወደድ ሃይለጊዎርጊስና የእያሡ አማካሪ የነበሩት የዘመኑ ምሁር ተክለሐዋርያት ተክለማርያም ሳይቀሩ ክደውት ተቀላቅለዋል፡፡

ልጅ እያሡ ጦሩን ሰብስቦ ወደ ሸዋ ለመዝመት ከሐረር ተነስቶ እየተጓዘ ሳለ ሚኤሶ ላይ ከሸዋ ቀድሞ የተላከ 15,000 ጦር ጠብቆ ውጊያ ገጠመውና የእያሡ ጦር ተሸነፈ፡፡ እያሡ የተረፉትን ጥቂት ወታደሮች ይዞ ወደ አፋር በርሃ ለመሸሽ ተገደደ፡፡ በዚህ ጦርነት ከሸዋ ለተላከው ጦር ዋና አዝማች ሆነው የሄዱት የእያሡ የቅርብ አማካሪ የነበሩት ፊታውራሪ ተክለሐዋርያት የነበሩ ሲሆን፤ የተመረጡትም አገሩን በደንብ ያውቃሉ በሚል ነበር፡፡ ይህ ከሆነ በኋላም የልጃቸውን መሻር የሰሙት ንጉስ ሚካኤል "ቢያጠፋ እንኳ እኔ እመክርና አርመው የነበረውን ልጄን እንዴት ሳያማክሩኝ ያባቱን ዙፋን ያስለቅቁታል!" በማለት 80,000 ጦር ሰብስበው "የጠፋ ልጄን አፋልጉኝ" ብለው ወደ ሸዋ ዘመቱ፡፡

የንጉስ ሚካኤልን ጦር ለመግጠምም በሸዋ በኩል 120,000 ጦር ተዘጋጅቶ የመጀመሪያው ጦርነት ጥቅምት 7 ቀን 1909 ዓ.ም በቶራ መስክ ላይ ተካሂዶ የወሎ ጦር አሸነፈ፡፡ በዚህ ጦርነት የሸዋው የጦር መሪ ራስ ልዑልሰገድ አጥናፍሰገድን ጨምሮ በርካቶች አለቁ፡፡ ከዚህ ድል በኋላ ፊታውራሪ ሐብተጊዮርጊስ ለንጉስ ሚካኤል ገፀበረከትና ላዩን እርቅ ውስጡን ጠብቅ የመሰለ ቃላት በመላክ ተረጋግተው ወይም ተዘናግተው እንዲቆዩ አደረጉ፡፡ "በሠላም መወያየቱ ይሻላል" የሚል ጭብጥ ያለው ውሉ ያልለየውን ቃል የሰሙት ንጉስ ሚካኤልም የመጀመሪያውን ድላቸውን እንደጨበጡና እንደተዘናጉ ሠገሌ ሜዳ ላይ ሰፍረው ቆዩ፡፡ ከ10 ቀናት በኋላ ጥቅምት 17 ቀን 1909 ዓ.ም በፊትአውራሪ የጦር እቅድ አውጭነትና መሪነት ለቀናት በስውር ከበባ አድርጎ የቆየው የሸዋ ጦር የከበባ ስልቱን ተጠቅሞ የወሎን ጦር ባላሰበው መንገድ አጠቃው፡፡ ይህ የሠገሌ ጦርነት ከአድዋው ጦርነት በኋላ ብዙ ደም የፈሰሰበት ከባድ ውጊያ መሆኑ ተዘግቧል፡፡ በዚህ ጦርነት የጦር ሠራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ ሆነው የዘመቱት ራስ ተፈሪ መኮንን የነበሩ ሲሆን፤ ከርሳቸው በታች የጦር ሚኒስትሩ ፊታውራሪ ሃብተጊዮርጊስና ራስ ካሣ ኃይሉ መሪ ሆነው ተሳትፈዋል፡፡ እናም የንጉስ ሚካኤል ጦር ያለቀው አልቆ የተረፈው ሲበተን ንጉስ ሚካኤልም ተማረኩ፡፡ በዚህ መልኩ ኩዴታው ተከናወነ፡፡

ልጅ እያሡ ከአባቱ ሽንፈት በኋላ ከነበረበት ከአፋር ተነስቶ በርሃውን አቋርጦ ወደመቅደላ ሄዶ ጦር ሰብስቦ ውጊያ ቢጀምርም ድል ሳይቀናው ቀረ፡፡ በሃብተጊዮርጊስ መሪነት የዘመቱት የሸዋ መኳንንት ወደ መቅደላ ሄደው ሊማርኩት ቢሉም አልቻሉም፡፡ በዚህ ጊዜ ነበር፡

“መቅደላ አፋፉ ላይ ያስካካል ፈረሱ፣
የዘጠኝ ንጉስ ልጅ አስረኛው እሱ፡፡
እንኳን ሴቶችና ወንዶቹ ቢነግሱ፣
አልጋውን አይለቅም አባ ጤና እያሡ” የተባለለት፡፡ ከዚህ ሽንፈት በኋላም እንደገና ተመልሶ ወደ አፋር አቀና፡፡ ጥቂት ጊዜ አሳልፎ በርሃውን መልመድ ሲያቅተው በርሃውን ቆርጦ ወደ ምዕራብ ትግራይ በማቅናት በጋብቻ ወደሚዛመዱት ወደ ራስ ስዩም ግዛት ሄደ፡፡ ምንም እርዳታ እንደማያገኝ ሲረዳ ወደ ምስራቅ ትግራይ ዘልቆ ራስ ጉግሳ አርአያ ዘንድ ቢሄድም ለውጥ የለም፡፡ ይህን ያዩ የሙስሊም ባላባቶች “ወደኛ አገር ወደ ቆላው ግባና እንደብቅሃለን፣ ሚስትም እንድርልሃለን፣ በሰላምም ትኖራለህ፣ ባይመችህም ወደ ኤርትራ ይዘንህ እንጠፋለን” ብለው ሲልኩበት “ከአገሬ አልወጣም፣ ሚስትም አለችኝ፣ መስለምም አልፈልግም” ብሎ እዚያው ትግራይ ውስጥ ግብፅያ ገዳም ገብቶ ተደበቀ፡፡

ራስ ጉግሳም መዘዙን ስለፈሩ በ1913 ዓ.ም ገዳሙን አስከብበው ያዙት፡፡ በዚህ ጊዜ የልጅ እያሡን እህት ያገቡት ራስ ስዩም ራስ ጉግሣን ወግተው እያሡን ሊነጥቁ ይችላሉ ተብሎ ስለተሰጋ ራስ ተፈሪ፣ ፊታውራሪ ሃብተጊዮርጊስና የጎጃሙ ራስ ኃይሉ ተክለሃይማኖት ወደ ትግራይ ለመዝመት ጉዞ ጀምረው ወሎ እንደደረሱ የተፈራው ሳይሆን ቀርቶ ራስ ጉግሳ የእያሡን እጅ ይዘው ደሴ ወስደው ለራስ ተፈሪ አስረከቡ፡፡ በመጨረሻ ወደ ሸዋ ተይዞ መጣና በሰላሌ ከተማ በራስ ካሣ ኃይሉ ስር ግዞት ወረደ /ታሰረ/፡፡ ሰላሌ በነበረበት ጊዜ በራስ ኃይሉ ተክለሐይማኖት አቀነባባሪነት በአውሮፕላን የማስመለጡና ወደ ኤርትራ የመሄዱ ሙከራምክ ከሸፈ፡፡



አቤቶ እያሱ በእስር ላይ።

በ1925 ዓ.ም ከሰላሌው እስር ቤት አምልጦ ወደ ጎጃም ሲሸሽም ተያዘና ወደ ሐረር ተወስዶ በጋራ ሙለታ አውራጃ በግራዋ ከተማ እስር አምባ በግዞት እስከ 1927 ዓ.ም ቆየ፡፡ በዚያ ጊዜ ኢጣሊያ የወልወል ግጭትን በፈጠረች ጊዜ “ከእኛ ጋር ወግነህ ወደ መንግስትህ ብትመለስስ?”



የሚል መልዕክት ቢደርሰውም ከጠላት ጋር አልተባበርም በሚል እንቢ እንዳለ ይነገራል፡፡ ወዲያውም በ1927/28 ዓ.ም ልጅ እያሡ “ልጅ” እንደተባለ ዘውዱንም ሳይጭናት አለፈ፡፡ ተገደለ የሚሉም አሉ፡፡

የልጅ እያሡን አሟሟት በሚመለከት ሦስት አይነት አባባሎች እንዳሉ የሚነግሩን ፀሐፊ ጥላሁን ብርሃነስላሴ “አንደኛው እንደ ልጅ መስፍን እያሱ አገላለፅ” ጃንሆይ በ1928 ዓ.ም ወደማይጨው ሊዘምቱ ሲሉ ያስመጡትና “እኛ ያስመጣንዎ ስለማይጨው ጦርነት እንዲያማክሩን ነው” ሲሉት “አንተ ያስመጣኸኝ ልትገድለኝ ነው፡፡ ቀኑ ይረዝማል እንጂ አንተም ትገደላለህ” ብሎ መለሰና ወደማይጨው ሊሄዱ ሦስት ቀን ሲቀራቸው ተገደለ” ብለዋል፡፡ ሁለተኛው አባባል ማይጨው ሊዘመት ሲል አባ ሃና፣ ራስ አደፍርሰውና ደጃች መኮንን እንዳልካቸው ቀደም ብለው በመኪና ሄደው ልክ ግራዋ ሲደርሱ ልጅ እያሡ ተጠርቶ ሲወጣ እንደሚገድሉት አውቆ አብሮት የታሰረው አባ ሻንቆ መሣሪያ ነጥቆ ሊታኮስ ሲሞክር ተገደለ፡ አስከትሎም ልጅ እያሡ ተገደለና ሁለቱም እዚያው ተቀበሩ የሚል ነው፡፡

ሦስተኛው ገለፃ ደግሞ አቶ ተክለፃድቅ መኩሪያ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ በሚለው መፅሐፍ የገለፁት ሲሆን “መጋቢት 7 ቀን 1927 ዓ.ም ልጅ እያሡ መሞታቸው በቤተ-መንግስት ተነግሮ ሐዘን ተቀምጠው ነበር ብለው አትተዋል፡፡” ፀሐፊው “ይህን ሁኔታ የሚያጠናክር ከአንድ ታሪኩን በደንብ አውቃለሁ ከሚሉ አዛውንት ሴት እንደሰማሁት በማለት ያሰፈሩትን ስናይ “ልጅ እያሡ ከወልወል ግጭት በኋላ በ1927 ዓ.ም መሞቱ ተነግሮ ሸዋፀሐይ እያሡ ቤት ሐዘን ተቀምጠው እቴጌ ልቅሶ መድረሳቸውን አውቃለሁ” ማለታቸውን ነው፡፡ ቀጥለውም “የአሟሟቱን ሁኔታ ግን አላውቅም ብለዋል” በማለት የአዛውንቷ አባባል ተክለፃድቅ መኩሪያ ከጠቀሱት ወቅት ጋር መጋጠሙን ይገልፃሉ፡፡ የልጅ እያሡ አሟሟት ለህዝቡ በይፋ ስላልተገለፀም ሐሜቱን ከእውነቱ መለየት ሳይቻል ቀርቷል፡፡

በከፊል በልጅ አስተሳሰቡ ባጠፋው ጥፋት፣ነገር ግን በከፍተኛ የፕሮፓጋንዳ ውጤት ስልጣኑን ያጣው እያሡ በተለይ በተራው ህዝብ ዘንድ ተወዳጅነት እንደነበረውና አጭሯ የስልጣን ዘመኑም የጥጋብ ጊዜ እንደነበረች የሚጠቁሙ ስንኞች አሉ፡፡ እያሡ በግዞት እያለ በንግስት ዘውዲቱ ጊዜ በአንዳንድ ግዛቶች ችግር ተከስቶ ነበርና

“ወዴት ነው ያለኸው እያሡ አባ ጤና፣
ችጋር ሊገለን ነው እባክህ ቶሎ ና፡፡” ተብሎለታል፡፡ “በእያሡ ዳቦ ነው ትራሱ” የሚለውም አብሮ ይጠቀሳል፡፡

ደጋፊዎቹ ባየነው አይነት ፍቅራቸውን ሲገልፁም በተቃራኒው ተቃዋሚዎቹ የእያሡን መጥፎ ገፅታ የሚተነትኑ ግጥሞችን በፅሁፍም በቃልም ያሰራጩ ነበር፡፡

"የገባር ልጅ እንኳን አባቱ ሲሞት፣
የደረሰው እንደሁ ከአስር አንድ መሬት፣
ተስካሩን ያወጣል እስከ አስር ዓመት፡፡
ሳያበቃው ቀረ ለአንድ ቀን ፍታት፣
ይግረማችሁ ብሎ በሞቱ ማግስት፣
እጃን ሜዳ ወጣ ጉግስ ሊጫወት፡፡
የምኒልክ መንግስት አምራ ተደላድላ፣
ብታንገላታትም ብትላትም ችላ፣
እስካሁን ጠበቀች ነብስ ብታውቅ ብላ፣
አሁን ግን ሃይማኖት ብትለውጥ የሌላ፣
ለዘውዲቱ ሄደች ዘውዲቱ ኮብላ፡፡
ከሆነ አልጋ ወራሽ ተፈሪ ለኋላ፣
ጠቅል እንላለን እንግዲህ ምን አላ!
መቻል እጅግ መልካም የምኒልክ ሎሌ
አልሰማም የማይል አለ ባለሟሌ፣
ቀለብ ደመወዝ ሰጥቶ ያደረገኝ ሎሌ፣
ይህንን የፃፍኩት እኔ ዘውዴ ኃይሌ፡፡"

እነዚህን የመሳሰሉ ግጥሞች ከብዙ ተቃዋሚዎች እየተሰበሰቡ ለእያንዳንዱ ሰው እንዲደርሰው ይደረግ ነበር፡፡ ተባራሪ ጽሁፎች ለህዝቡ የሚደርሱትም በየአደባባዩና በየገበያ ስፍራዎች እየተዘዋወሩ ጽሁፎችን እንዲያደርሱ በታዘዙ ተቀጣሪዎች ነበር፡፡

እያሡን ደግፈው ከተፃፉት በርካታ ግጥሞች ውስጥ አንዱም እንዲህ ይነበባል፡፡

"መቀሌ ቢገባ መቀሌ ገብታችሁ፣
ጉራሌ /አውሣ/ ቢገባ አውሣ ገብታችሁ፣ (አፋር ማለት ነው)
አትመለሱም ወይ አጣነው ብላችሁ፡፡
እንጀራ አትበሉም ወይ እሡን ካልያዛችሁ፡፡
እያሡ ምን ያድርግ አንድ ወጣት ልጅ፣
ግዝት ያፈረሰው ተፈሪ ነው እንጂ፡፡
ይዘው አሰቃዩት እንደ ደሃ ጥጃ፣
ዛሬስ ደስ አላቸው የነገውን እንጃ፡፡
በቅሎው ድንበር አይግጥ፣ እሱ አያስደነግጥ፣
እያሡ ሚካኤል ሊሰዋ ነው በእርግጥ፡፡"



በ2002 ዓ.ም ህዳር ወር ላይ 17ኛው የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ዓለም አቀፍ ጉባኤ ስብሰባን ተከትሎ በደሴ ከተማ "THE LIFE AND TIMES OF LIJ IYASU NEW INSIGHTS" በሚል ርዕስ አንድ ዓለም አቀፍ ጉባኤ ተካሂዶ ነበር፡፡ በሁለቱም ጉባኤዎች የተካፈለ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህርና ተመራማሪ ባቀረበው አንድ ጽሁፍ፤
"ልጅ እያሡን ከስልጣኑ ያስወገደው መፈንቅለ መንግስት በሌላ አገራት ያልተለመደና ያልታወቀ አይነት ባህሪ ያለው ነበር፡፡ይኸውም ግልበጣው ባረጀና ማኅበራዊ ተግባሮችን በፈጠረ ስርዓት ላይ የተቃጣ ሆኖ፣ አዲስ ለውጥን የሚሻና አማራጭ የፖለቲካ አቅጣጫን የሚከተል አልነበረም፡፡ይልቁንም ግልበጣው ለውጥን ሲያቀነቅን በነበረው ልዑል ላይ ያረጀውና … የላዕላዩ ክፍል ያሳረፈው ብኩን በትር ነበር" በማለት ይገልፃዋል፡፡
ይህ ኮንፈረንስ የተካሄደው ደሴ ከተማ "አይጠየፍ" አዳራሽ ውስጥ ነበር፡፡የአዳራሹ ስም "አይጠየፍ" የተባለው ደግሞ ለታችኛው ኅብረተሰብ ልዩ ትኩረት ያደርግ የነበረውን የልጅ እያሡን አመለካከት አባቱ ንጉስ ሚካኤልም ይተገብሩት ነበርና ትልቅ ትንሽ፣ደሃ ሐብታም፣ባለማዕረግ ተራ ሰው፣ሳይሉ፣ሳይመርጡና ሳያበላልጡ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል ሰብስበው ግብር ያበሉበት የነበረ ሰፊ አዳራሻቸው ስለሆነ ነው ዛሬ ድረስ "አይጠየፍ" እየተባለ የሚጠራው፡፡
ልጅ እያሡ አንድነትን ያጠናክራል ብሎ የተጓዘበትና በእጅጉ ያስነቀፈው አንዱ ተግባር ከየጎሳው ሚስት እያገባ መውለዱ መሆኑን አይተናል፡፡በዚህ አካሄድም በርካታ ልጆች አፍርቶ ነበር፡፡እንዲያውም በዘመኑ ብዙ ሴቶች ሲያረግዙ "ያረገዝኩት ከእያሡ ነው" እያሉ ያወሩ ነበር፡፡ስለዚህም የእያሡን ትክክለኛ ልጆች ለመለየት አስቸግሮ ነበር፡፡

በኃይለስላሴ ጊዜም የእያሡ ልጆች ከየቦታው ብቅ እያሉ ልጅነታቸው ሲታወቅ እነሱን በየሰበብ አስባቡ መቆጣጠርና ማሰር አስቸጋሪ ሆኖ ነበር፡፡ ይህን በመፍራትም ብዙ እናቶች ልጆቻቸውን አባታቸው እያሡ እንደሆነ እስከመደበቅ ደርሰው ስለነበር ተደብቀው የቀሩ ልጆች እንደነበሩ ይገመታል፡፡ ሆኖም "ልጅነታቸው የተደረሰበትና የታወቁት የሚከተሉት ናቸው" በማለት ጥላሁን ብርሃነስላሴ በመፅሐፋቸው የልጅ እያሡን ልጆች ዘርዝረዋል፡፡
*ልጅ ግርማ እያሡ፤* በኢጣሊያ ወረራ ጊዜ በስደት ኬንያ ገብቶ የነበረና በእንግሊዞች ቁጥጥር ስር ውሎ ታስሮ የቆየ ሲሆን፣ በመጨረሻ ኢጣሊያ ስትሸነፍ ወደአገሩ ሸሽቶ ሊገባ ሲል እዚያው ኬንያ ተይዞ የተገደለ፡፡
*ሚናስ እያሡ፤* ጎጃሜዋ እናቱ ለአንድ መነኩሴ አደራ ሰጥታው ወደ ወሎ አብረው ሲጓዙና የሞላ ወንዝ ሲሻገሩ እናቱን ወንዙ ሲወስዳት መነኩሴውና ሚናስ ተረፉ፡፡ ሚናስም ወሎ ግሸን ማርያም አጠገብ በምትገኘው ሙፋ

ኪዳነምህረት እየተማረ አደገ፡፡ ጣሊያኖች በገቡ ጊዜ አስረው ቢመረምሩትም መንፈሣዊ ሰው ብቻ መሆኑን ስለተገነዘቡ ፈቱትና ቤት ሰጥተው አስቀመጡት፡፡

ከነፃነት በኋላ ከወሎየዋ እናቱ የሚወለደው ጌድዮን እያሡ የተባለው ወንድሙ ፈረሱን አስጭኖ መሸፈቱ ሲሰማ ሚናስ እያሡም በጥርጣሬ መታየት ጀመረ፡፡ስለዚህም በጃንሆይ ትእዛዝ አልጋ ወራሹ አስፋወሰን ሚናስን ይዞ ወደ ጃንሆይ ላከው፡፡በአልጋ ወራሹ ቤት በቁም እስር በሚመስል አይነት በእንክብካቤ መኖር ጀመረ፡፡ ጃንሆይ ግን ጥርጣሬው አለቃቸው ብሎ ወደወሀኒ ቤት እንዲገባና የፍርድ ሚኒስትሩ ራስ አንዳርጋቸው መሳይ እንዲጠብቁት አዘዙ፡፡ ራስ አንዳርጋቸው ሚናስን ቢያዩት ቢያዩት ሰላማዊና ፀሎተኛ ብቻ መሆኑን ስላረጋገጡ ኃላፊነት ወስደው አስለቀቁት፡፡ እዚያው ፍርድ ሚኒስትር መስሪያቤት ውስጥ እንዲሰራም ተደረገ፣ ስራውን እየሰራ ከቤተሰቦቹ ጋር በሰላም መኖሩን ቀጥሎ ሳለ በ1957 ዓ.ም ምሽት ላይ ከመስሪያቤቱ ፎቅ ላይ ወድቆ ሞተ፡፡ በዚያ ጊዜ ኢትዮጵያና ሱማሌ ፀበኞች ነበሩና የሶማሌ ሬዲዮ "የአቤቶ እያሡን ልጅ ሚናስን የኢትዮጵያ መንግስት ከፎቅ ወርውሮ ገደለው" የሚል ዜና አስደመጠ፡፡ሟቹ 7 ልጆች ወልዶ ነበር፡፡

*ጌድዮን እያሡ፤* ይህ በኃይለኛነቱ የሚታወቀው ልጅ ከወረራው በኋላ ሸፍቶ በወሎ በርሃ ገባ፡፡በኋላም ተይዞ ጋሞጎፋ ታስሮ ነበር፡፡ከጌድዮን እያሡ የተወለዱ እስጢፋኖስ ጌድዮንና በቃሉ ጌድዮን የሚባሉ ልጆች የነበሩ ሲሆን፤ በቃሉ የአየር ኃይል ባልደረባ ሆኖ ነበር፡፡

*ጎሹ እያሡ፤* በግዞት ሲዳሞ በነበረ ጊዜ ሁለት ልጆች የወለደ ሲሆን፤ ተናኘ ጎሹ አዲስ አበባ፣ ሉሊት ጎሹ ሲዳሞ ውስጥ ይኖራሉ፡፡

*እንግዳሸት እያሡ፤* ወላጅ እናቱ ከመንዝ ባላባት የተገኘች ነበረች፡፡እንግዳሸት በወረራው ጊዜ ቡልጋ ውስጥ ይገኝ ነበርና አርበኞች "የንጉስ ልጅ በመሀላችን እያለ እንዴት ያለ ንጉስ እንዋጋለን?" በማለት እምቡር ገበያ ላይ ነጋሪት እየጎሰሙ እንግዳእሸትን "መልዓክፀሐይ ንጉሰ ነገስት" አሰኝተው አውጀው ነበር፡፡በዚህ ጊዜ አርበኛው ሁሉ ከያለበት ተሰባሰበና ሹመት ተካሄደ፡፡በወቅቱ በርካታ ጦር ሠራዊት አስከትሎ የመጣው ባላምባራስ አበበ አረጋይ "ራስ" ተብሎ የጦር አበጋዝ ሆኖ የተሾመው በዚህ ጊዜ ነበር፡፡

መልዓክፀሐይ እያሡ በ1931 ዓ.ም መስከረም 17 ቀን ብዙ አርበኞች ከነወታደሮቻቸው መጥተው በተሰበሰቡበት ቦታ ሆኖ የመስቀልን በዓል ሲያከብር እንደቀድሞው ንጉሣዊ ስርዓት /ጠላት አገሪቱ ላይ ያልነበረ በሚመስል ሁኔታ/ ግብር ያበላ ሲሆን፤ በእለቱም ለ4 ሰዓታት የቆየ የወታደር ሰልፍ ተመልክቶዋል፡፡ በዚሁ ዕለት መልዓክፀሐይ እያሡ ታመመና በቃሬዛ ወደ መምቻ ከተማ ተወስዶ መዳን ስላልቻለ መስከረም



27 ቀን ህይወቱ ያልፍና በከፍተኛ የቀብር ስነ-ስርዓት በቆቦ ማርያም እንደተቀበረ "የአርበኞች ታሪክ" የሚለው መፅሐፍ ላይ ተገልጿል፡፡ በነገሰ በ8ኛ ወሩ የሞተውን ንጉስም በዚያች እለት ከጅቡቲ የመጡ መነኩሴ መርዘው እንደገደሉት ይነገራል፡፡የመነኩሴው ምክንያትና የላከውም ማን እንደሆነ ባይታወቅም፡፡

*ደጃዝማች ዮሐንስ እያሡ፤* ዮሐንስ በወረራው ጊዜ በአርበኝነት ሲዋጋ ቆይቶ ንጉሡ ከስደት ሲመለሱ እንደሌሎች አርበኞች በስሩ ያሉትን ወታደሮች አሰልፎ ንጉሡን የተቀበለ ነው፡፡ ሆኖም የጎንደር አርበኞች "የሸሸ ንጉስ አይነግስም፤ያፈረሰ ቄስ አይቀድስም" በማለት ንጉሡን አናስገባም ብለው ስለነበረና፤በዚያም ጊዜ ደጃዝማች ዮሐንስ እያሡ የመንገስ ፍላጎት አሳይቶ ስለነበር ጃንሆይ ከ5 ዓመቱ የአርበኝነት ዘመን በኋላ በግዞት ወደ ከፋ ልከውታል፡፡በ1966 ዓ.ም የመንግስት ለውጥ ሲደረግ ተፈቶ ጅማ ሄዶ ሲኖር ታሞ ሞተ፡፡

ደጃዝማች ዮሐንስ ሌላው በጃንሆይ ጥርስ እንዲገባ ያደረገው ንጉሡ በስደት ለይ ሳሉ ከአርበኞች ጋር ደብዳቤ ይፃፃፉ ነበርና ሌሎች ሁሉ ከጽሁፋቸው ስር "ባሪያዎ" ወይም "አገልጋይዎ" እያሉ ሲፅፉ እሱ ግን "አከባሪዎ" እያለ ይፅፍ ስለነበር ነው፡፡ ከደጃች ዮሐንስ እያሡ ልጆች ውስጥ ጀርመን አገር የሚኖሩት ፕ/ር ግርማ ዮሐንስ አንዱ ናቸው፡፡

*ቴዎድሮስ እያሡ፤* ስለቴዎድሮስ የሚታወቀው ታሪክ ጋምቤላ ውስጥ ሸፍቶ ሲዋጋ መኖሩና በኋላ ላይ ናዝሬት ውስጥ ታስሮ እንደነበር ነው፡፡

*ምኒልክ እያሡ፤* አፋር ውስጥ የተወለደው ምኒልክ እያሡ ፖለቲካ ውስጥ ባይገባም ከእያሡ በመወለዱ ብቻ አፍንጮ በር እስር ቤት ከ25 ዓመታት በላይ ታስሮ የነበረና በመጨረሻ በነፃ የተለቀቀ ነው፡፡ ያለአንዳች ጥፋት ለረጅም አመታት የተንገላታው ምኒልክ ከተፈታ በኋላ እንኳ አገሩን ለመርዳት በተጠየቀ ጊዜ ፈቃደኛ ሆኖ የተቻለውን የሰራ ነው፡፡ ምኒልክ የኢሣ ተወላጅ የሆነችውን ወ/ሮ መሪማ አብዱራሀማንን አግብቶ ድሬዳዋ ሱማሌ መንደር ሲኖር ቆይቶ ልጅ ሳይወልድ ነው የሞተው፡፡

የጅቡቲ የነፃነት ጉዳይ በተቀማጠለበት ጊዜ የጅቡቲው የበላይ ባላባት አልአሪፍ ከምኒልክ እያሡ ጋር የአንድ አያት ልጆች ስለነበሩ ለማግባባት የተቻለውን ጥሯል፡፡ አልአሪፍ ጃንሆይን "የአክስቴን ባል የገደለ ነው" እያለ ይጠላቸው ስለነበርና ሊያናግራቸውም ፈቃደኛ ስላልነበር ስለ እነዚህ አይነት ጉዳዮች የሚወያየው ምኒልክ ነበር፡፡ ልጅ ምኒልክ በደርግ ጊዜም የጅቡቲ መሪዎችን ለማግባባት ሞክሯል፡፡

*ልጅ መስፍን እያሡ፤* ልጅ መስፍን ዋልድባ ገዳም ተደብቆና ስሙንም መኮንን እንደልካቸው ብሎ ቀይሮ የቆየና በ1983 ዓ.ም የቀድሞ ስሙን መልሶ መስፍን እያሡ በሚል በጋዜጣ አሳውጇል፡፡ ልጅ መስፍን የቤተክህነት ሰው በመሆኑም በፓትሪያሪኩ በአቡነ ተክለሐይማኖት

እርዳታ ተደርጎለት ከብት በማርባት ይተዳደር ነበር፡፡ ኢህአዴግ ሲገባ ደርግ ዘግቶት የነበረውን ወደመንበረ ፀባኦት ቅድስት ስላሴ ቤተ-ክርስቲያን የሚወስደውን መንገድ ያስከፈተና፣ ከማዘጋጃ ቤቱ ፈቃድ ውጪ የአፄ ምኒልክን ሐውልት ብርማ ቀለም ያስቀባ ነው፡፡ ሐውልቱ በነሐስ ስለተሰራ መወልወል እንጂ መቀባት ባይኖርበትም፡፡

በተጨማሪም በእሣት አደጋ መከላከያ መስሪያ ቤት በኩል ያለውንና በብረት ሰንሰለት የተዘጋውን የአራዳ ጊዮርጊስ ቅጥር ጊቢ በር ከባህታዊ ገብረመስቀል ጋር በመጋዝ ቆርጠው አስከፍተዋል፡፡ በዚህም ተከሰው ነበር፡፡

*አባ ዮሐንስ እያሡ /ወልደነጎድጓድ/፤* አባ ዮሐንስ የካቶሊክ መነኩሴ ሆኖ በሐረር ይኖር ነበር፡፡ የአባቱን ስም "ወልደነጎድጓድ" አሰኝቶ ሲኖርም መልኩ ቁርጥ እያሡን ይመስል ስለነበር እንዳይጠረጥሩት ቅን ቡን እያላጨ መልኩን ይለዋውጥ ነበር፡፡

*ሸዋፀሐይ እያሡ፤* ሸዋፀሐይ የልጅ እያሡ የመጀመሪያ ልጅ እንደሆነችና እያሡ ሲሞትም ለቅሶ የተደረሰው እሷ ቤት እንደነበር ተገልጿል፡፡

*እመቤት ዓለምፀሐይ እያሡ፤* እመቤት ዓለምፀሐይ ከራስ ኃይሉ ተክለሐይማኖት ልጅ ከወ/ሮ ሰብለወንጌል የተወለደችና ከመጀመሪያው ጀምሮ በቅርቡ በሞት እስከተለየችበት ጊዜ ድረስ በይፋ የምትታወቅ ልጅ ነበረች፡፡

ሌላው ከልጅ እያሡ ታሪክ ጋር ተያይዞ የሚገለፀው የእሱም ሆነ የአባቱ የዘር ሐረግ በአባት በኩል ሲቆጠር ከነብዩ መሐመድ ጋር መገናኘቱ ነው፡፡ ይህን ጉዳይ በሚመለከት ብርሃኑ ድንቄ "አጭር የኢትዮጵያ ታሪክ" በሚለው መፅሀፋቸው ያሰፈሩትን ስናይ፣



1. ነብዩ መሐመድ
2. ፋጡማ (የአሳብ ዓሊ ሚስት)
3. ሁሴን (እንገቱን የተቀላው)
4. ዘና ሳባዲን
5. ሞሐመድ አልባጂር
6. አብደላህ
7. ሙሳ አልካዲን
8. ዑመር
9. ታጅ አላህ
10. ያህያ
11. ኢስማኤል
12. ኑር አህመድ
13. ከሊል
14. ኢብራሂም
15. ሞሐመድ
16. ታማም
17. ታጅ አዲን
18. ሞሐመድ
19. ያጉት
20. ያኩብ
21. ኢማም ኑር
22. ሳኒ አላህ
23. ኢሳ
24. አይሻ
25. ዛኒ ኤልኬር
26. ኑር ሁሴን
27. ሻምስ አዲን
28. ኑር አዲን
29. ዲሞ አዲን
30. ፓፑ
31. ኢማም ዓሊ /ወደ ኢትዮጵያ መጡ/
32. ኢማም መሐመድ
33. ኢማም አህመድ
34. ኢማም ሙሐመድ
35. ኢማም ሊሃን
36. ኢማም ዓሊ /የንጉስ ሚካኤል አባት/
37. መሐመድ ዓሊ /ንጉስ ሚካኤል/
38. አቤቶ እያሡ

የንጉስ ሚካኤል አባት ኢማም ዓሊ የነብዩ መሐመድ 36ኛ ትውልድ በመሆናቸው ወይም ነበሩ ተብሎ ስለሚታመን ልጅ እያሱ የነብዩ መሐመድ 38ኛ ትውልድ ሆኖ ይቆጠራል፡፡ ልጅ እያሱ ባየነው ዓይነት በውጣ ውረድና በአወዛጋቢ ሁኔታ የተሞላ የስልጣን ዘመኑንና የግል ህይወቱን ፈፅሞ በ39 ዓመቱ አልፏል፡፡

"ያልተዘመረለት እያሱ" ተብሎ የተጀመረውን ይህን ምዕራፍ ከመቋጨታችን በፊትም ለምን እንዳልተዘመረለት የሚጠቁሙ ጥቂት ገለፃዎች ካስፈለጉን፤

1ኛ.በኢትዮጵያ ታሪክ መፃህፍቶች በዘመናዊ መልክ በማተሚያ ቤት መታተም የጀመሩት ልጅ እያሱ በኩዴታ ከስልጣን ከተወገደ በኋላ በነበሩት ተከታታይ ዓመታት ነው፡፡

2ኛ.ንግስት ዘውዲቱም ሆኑ አፄ ኃይለስላሴ ስለልጅ እያሱ መልካም ስራ /ሰርቶ እንኳ ቢሆን/ እንዲነሳ አይፈልጉም፡፡

3ኛ.ልጅ እያሱ ከስልጣን ከተወገደ በኋላ ንጉሣዊ አገዛዙ ለ60 ዓመታት ያህል የዘለቀው ልጅ እያሱን ከስልጣን ባስወገዱት አካላት እጅ ነው፡፡ በርካታ የታሪክ ፀሐፍት የታሪክ መፃህፍቶቻቸውን መፃፍና ማሣተም የጀመሩትም ከተጠቀሰው ጊዜ ጀምሮ ባሉት ጊዜያቶች ስለነበርና፤በዚህም ስለ ልጅ እያሱ የተሻለ ገፅታ ማካተት ወቅቱ ስለማይፈቅድ ለረጅም ዓመታት የእያሱ ክፉ ገፅታ ብቻውን እየመራ እስከቅርብ ጊዜ ሊደርስ ግድ ነበር፡፡ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የተቀበሩ በጎ ገፅታዎች እንደነበሩትም የሚገልፁ እውነታዎች መውጣት ጀመሩ፡፡እነዚህም ከግማሽ ምዕተዓመታት በላይ የተብጠለጠለበትን ፅሑፍ ያህል ያልበረከቱ ናቸው፡፡ ስለዚህ "ያልተዘመረለት" ሲባል ጥሩ ገፅታውን በክፉ ገፅታው ለውጠው ታሪኩን በሐሰት ቀበሩት ማለት ሳይሆን፤ጥፋቱንም ልማቱንም እኩል ማንሳት ሲገባ ጥፋቱ ብቻ ጎልቶ የተተረከለት፤ ነገር ግን ተራማጅነቱ ያልታየለት ልዑል እንደነበር ለመግለፅ የተጠቀምኩበት ቃል ነው - ያልተዘመረለት፡፡



# ምዕራፍ 83

*የንግስተ ነገስታት ዘውዲቱ ዘመ ነ-መንግስት*
*ከ1909 - 1922 ዓ.ም*

በ1909 ዓ.ም ዘውዲቱ ንግስተ ነገስታት፣ ተፈሪ መኮንን ራስ ተብለው አልጋ ወራሽ ሲሆኑ ክንውኑ ያልተለመደ አይነት ነበር፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ የተለመደው ወግና ስርዓት ንጉሠ ነገስት ከተሾመ በኋላ ቆይቶ በተሿሚው ንጉሠ ነገስት ፍላጎትና ምርጫ ነበር አልጋወራሽ የሚሰየመው፡፡ የዘውዲቱና የተፈሪ ግን "በህዝቡ ምርጫ" በሚል የሁለቱም ሹመት በሌሎች ምርጫ በአንድ ቀን የተከናወነ ነበር፡፡

ይህ የሆነበት ምክንያት ልጅ እያሱ ሲሻር በሁለት ጎራዎች ይሁንታ የነበረ በመሆኑና ቀጣይ ተሿሚው ላይም እነዚያ ሁለቱ ጎራዎች መሳተፍ ስለነበረባቸው ነው፡፡ ስለዚህ ራስ ተፈሪ በነበራቸው አውሮፓ ቀመስ ትምህርትና በተራማጅነታቸው የአውሮፓውያኑ ምርጫ ሲሆኑ፤ ዘውዲቱ ደግሞ የኢትዮጵያውያኑ ወግ አጥባቂ የመኳንንት ቡድን ምርጫ ነበሩ፡፡ ይህ በዘመነ መሳፍንት ጊዜ ብቻ የተተገበረና ያልተለመደ የሁለት ባንድ የአሿሿም ዘዴ የዘውዲቱን የአስተዳደር ጊዜ ያልተለመደ አድርጎት ሲቀጥል እናያለን፡፡

ዘውዲቱን ለሥልጣን ያበቃቸው ብቸኛ መመዘኛ የአፄ ምኒልክ ቀጥተኛ ልጅ መሆናቸው ነው፡፡ የሸዋ መኳንንት ምርጫ የሆኑትም የቀድሞውን የምኒልክን ወግና ስርዓት እንደማይጥሱትና እንደ እያሱ የተለየ ጎዳና እንደማይከተሉ እምነት ስለጣሉባቸው ነው፡፡ ራስ ተፈሪም የንጉስ ሳህለሥላሴ ዝርያ ያላቸውና የአፄ ምኒልክ የአክስታቸው የልጅ ልጅ ስለሆኑ፣ በዘር ሐረግ ረገድ ለዘውዱ የልጅን ያህል ባይሆንም የማይተናነስ ቅርበት ነበራቸው፡፡ ነገር ግን የአልጋወራሽነቱን ስልጣን ያገኙት በዘር ቆጠራ ብቻ ሳይሆን እንደተባለው የአውሮፓውያንን ቋንቋ ስለሚናገሩና በዘመናዊ አስተዳደግ ስላደጉ እንዲሁም የቆንሲሎች ወዳጅ ስለነበሩ ነው፡፡ ቀስ በቀስም ከአልጋወራሽነት ወደ ባለሙሉ ስልጣን እንደራሴነት፣ ሲቀጥሉም ባልተለመደ አኳኋን ወደፊት እንደምናየው የአዲስ አበባ ንጉስ ... እያሉ በመጨረሻ ንጉሠነገስት ሆነዋል፡፡

በዚህ አካሄዳቸውም የዘውዲቱን ስልጣን በእርጋታ ከላያቸው ላይ እየገፈፉ፣ እየገፈፉ ስልጣን አልባ ባለሥልጣን ሊያደርጓቸው ችለዋል፡፡ይህም ሲሆን ዘውዲቱ የአስተዳደር ልምድም ሆነ ከቄስ ትምህርት ያለፈ የዘመናዊ ትምህርት እውቀት ስላልነበራቸው በጥቂት ዓለማዊ ስራዎችና በብዙ መንፈሣዊ ስራቸው ተወስነው ስናይ፤ አጠቃላይ ፖለቲካዊ ጉዳዮችንና የአገሪቱን የውጭ ፖሊሲም ሆነ የአስተዳደሩን ስራ ግን አልጋወራሽ ራስ ተፈሪ ከደጋፊዎቻቸው ጋር ሲያከናውኑት

እንመለከታለን፡፡ይህ አካሄዳቸውም ነው የዘውዲቱን ስልጣን ለመገዝገዝ የረዳቸው፡፡

በዚህ መሠረት "የንግስተ ነገስታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግስት" ተብሎ በተመደበው ጊዜ ውስጥ ዘውዲቱ በዘመናቸው ከፈፀሟቸው ስራዎች የበለጠ በዘመናቸው የተፈፀሙ ስራዎች መበርከታቸውን ከወዲሁ ተገንዝበን፣ የዘውዲቱንና ያልጋወራሹን የጋራ የስልጣን ዘመን በጥምረት እናያለን፡፡

ዘውዲቱ ከአባታቸው ከዳግማዊ ምኒልክና ከእናታቸው ከወ/ሮ አብችው በያን ሚያዚያ 22 ቀን 1968 ዓ.ም በእነዋሪ ከተማ ነበር የተወለዱት፡፡ እናታቸው ወ/ሮ አብችው በያን ከወረኢሉ ባላባት የተወለዱ ናቸው፡፡

አፄ ምኒልክ ቀደም ባለው ጊዜ ወ/ሮ ሸዋረጋንና ልጅ አስፋወሰንን ወልደው ስለነበር ዘውዲቱ ሦስተኛ ልጃቸው ነበሩ፡፡ ሁለቱ ልጆች ምኒልክ በህይወት እያሉ ስለሞቱ የቀሩት ልጃቸው ዘውዲቱ ብቻ ነበሩ፡፡

ዘውዲቱ ጥቅምት 13 ቀን 1875 ዓ.ም ገና የ6 ዓመት ተኩል ልጅ ሳሉ ለአፄ ዮሐንስ ልጅ ለራስ አርአያ ዮሐንስ ተድረው ወደ ትግራይ ግዛት ሄዱ፡፡ የባለቤታቸው የራስ አርአያ እድሜም 12 ዓመት ነበር፡፡ ጋብቻውም የንጉሠነገስት ዮሐንስንና የንጉስ ምኒልክን ስምምነት ለማጠንከር ታስቦ የተደረገ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ከ5 ዓመት በኋላ ባለቤታቸው ራስ አርአያ ታሞ ስለሞተ ዘውዲቱ ወደአባታቸው ወደ ሸዋ ተመልሰው መጡ፡፡

በ1884 ዓ.ም ደጃዝማች ውቤ አጥናፍሠገድን አግብተው አራዳ በሚገኘው በደጃች ውቤ ቤት መኖር ጀመሩ፡፡ በወቅቱ የፊታውራሪነት ማዕረግ የነበራቸው ውቤ ከዓመታት በኋላ ከባለቤታቸው ከዘውዲቱ ጋር ይጋጩና በጥፊ ይማታሉ፡፡ ዘውዲቱም በንዴት በጠዋት አምልጠው ወደ ቤተ-መንግስት ሄደው መመታታቸውን ለምኒልክ ሲነግሩ፣ እምየ ምኒልክ ውቤን ያስጠሩና "ምነው በጥፊ መታኸኝ!" ብለው ጠየቋቸው፡፡ ደጃች ውቤ መልስ አጥተው አቀርቅረው ሳለ ምኒልክ በጥፊ ያጮሏቸውና ወደቤታቸው በሰላም ይሸኙዋቸዋል፡፡ ወ/ሮ ዘውዲቱ ወደቤታቸው መመለስ ስላልፈለጉ በዚያው ጊዜ ተፋቱ፡፡

ቀጥሎ በ1893 ዓ.ም የጎንደር ገዥ የነበሩትንና የእቴጌ ጣይቱ የወንድም ልጅ የሆኑትን ራስ ጉግሣ ወሌን አግብተው በኡራኤል ቤተ-ክርስቲያን አጠገብ በሚገኘው የአሁኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና ጥበቃ ቢሮ ያለበት ቦታ ላይ ይኖሩ ጀመር፡፡ (ለዚህም ነው ሰፈሩ የንግስት ሰፈር እየተባለ የሚጠራው)

ምኒልክ ሲታመሙ ዘውዲቱ ከቤታቸው ወደ ቤተ-መንግስት በመሄድ ከእንጀራ እናታቸው ከእቴጌ ጣይቱ ጋር አባታቸውን ሲያስታምሙ ቆዩ፡፡ከምኒልክ ማለፍ በኋላ ጣይቱ ከቤተ-መንግስት እንዲገለሉና በግዞት ወደ እንጦጦ እንዲሄዱ ሲደረግ፣ በተመሳሳይ ዘውዲቱም ርስታቸው ወዳለበት ፋሌ ወደሚባል ቦታ ተላኩ፡፡የምኒልክ ተወላጅ ልጅ እያሡ ከስልጣን በኃይል መውረዱን ህዝቡ እንዳይቃወም በሚል መነሻና ቀደም ሲል በተጠቃቀሱት ምክንያቶች መነሻነትም ዘውዲቱን ማንገስ የውዴታ ግዴታ ነበርና ከነበሩበት ከፋሌ /ሠላሌ/ አስመጥተው አነገሷቸው፡፡

መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም ወ/ሮ ዘውዲቱ ንግስተ ነገስት ተብለው በአባታቸው ዙፋን ሲቀመጡ እድሜያቸው 41 ሞልቶ ነበር፡፡ በዚሁ ጊዜም በሹማምንቱ ምክክር ባለቤታቸውን ራስ ጉግሳ ወሌን የቀድሞውን ግዛታቸውን ጎንደርን እንደገና ሾመው ከቤተ-መንግስቱ እንዲርቁ አደረጓቸው፡፡

የካቲት 4 ቀን 1909 ዓ.ም በአራዳ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን ስርዓተ ንግስ ተደርጎላቸው "ንግስተ ነገስታት ዘውዲቱ ወለተ ለዳግማዊ ምኒልክ ስዩምተ እግዚአብሔር" ተብለው በሊቀ ጳጳሱ በአቡነ ማቴዎስ እጅ ቅብዓ መንግስት ተቀብተው ዘውድ ሲጭኑ፣የሐረር ገዥ የነበሩት የራስ መኮንን ልጅ ተፈሪ ደግሞ አባታቸው ሰጥተዋቸው የነበረው የደጃዝማችነት ማዕረግ ከፍ ብሎ ራስ ተፈሪ ተባሉና ታላቁን የሰለሞን ኒሻን ተሸልመው ለአልጋ ወራሽነት የሚገባው ክብርና ስርዓተ ፀሎት ተደርጎ "ልዑል አልጋ ወራሽ" ተብለው ተሰየሙ፡፡በዚህ እለት ከቤተ-መንግስት አልፎ የማያውቀው የኤሌክትሪክ መብራት ከቤተ-መንግስት እስከ አራዳ ጊዮርጊስ ተዘርግቶ በአውሮፓውያኑ ድጋፍ የአዲስ አበባ ህዝብ ልዩ ነገር እንዲያይ ሆነ፡፡በንግስት ዘውዲቱ የሸዋ መኳንንት ደስ ሲሰኙ፣ በራስ ተፈሪ አልጋወራሽነትም አውሮፓውያን ቆንስሎች ተደሰቱ፡፡የንግስ በዓሉም በደማቅ ሁኔታ አለፈ፡፡



ቀዳማዊ ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ

ይህ በሆነ በሳምንቱ ግርማዊት ንግስተ ነገስታት ዘውዲቱ የከፋ ገዥ ለነበሩትና የአክስታቸው ልጅ ለሆኑት ለራስ ወልደጊዮርጊስ የንጉስነት ዘውድ ሰጥተው የበጌምድርና የሰሜን ንጉስ አድርገው ሾሟቸው፡፡ንግስት ዘውዲቱ ሃይማኖታቸውን ወዳጅ፣በጾም በፀሎት የተጉና የህይወታቸው ሚዛን ወደመንፈሳዊነቱ ያዘነበለ ነበር፡፡

የቀድሞዎቹ የነገስታት ሚስቶች /እቴጌዎች/ እንኳ የዘውዲቱን አይነት ሙሉ የንግስና ስልጣን ዕድል ሳያገኙ በእቴጌነታቸው ብቻ ምን ያህል ለፖለቲካው ልዩ ትኩረት ያደርጉ እንደነበርና ተሳትፏቸው ከነገስታቱ የበለጠ እንደሆነ በቁጥር አንዱ መፅሐፍ ያየነው ነው፡፡
ንግስት ዘውዲቱ ግን ካለፉት ሴት ባለሥልጣናት ፍፁም የተለዩ ነበሩ፡፡ ሌላው ቀርቶ ፊት ለፊት የመጣባቸውን ጠላት እንኳ በአግባቡ የተጋፈጡበት አጋጣሚ የለም፡፡ለዚህም ነው ጥቂት ፀሐፍት "ምስኪኗ ዘውዲቱ" እያሉ የሚጠሯቸው፡፡ማንም ሹም ያለሥልጣኑ ያሻውን ሲፈፅም "ለአገር ከጠቀመ ይሁን ብያለሁ" ማለትን እንጂ "እንዴት ያለሥልጣኑና ያለእኔ ፈቃድ" ማለትን አያውቁበትም፡፡
ፖለቲካዊ ጉዳዩን ሙሉ በሙሉ ለመምራትና የአውሮፓን ስልጣኔ በኢትዮጵያ ለማስፋፋት በሚል ራስ ተፈሪ ያደርጉት ለነበረው ጥረት ሁሉ ዘውዲቱ እንቅፋት ሆነውም፣እኔ እያለሁ እንዴት? ብለውም



አያውቁም፡፡ይህን ማድረጋቸው ተገቢ ቢሆንም፣ገደብ ያለፈው የዋህነታቸው በስተመጨረሻ ሳይጎዳቸው አልቀረም፡፡
"እርስዎ በፀሎትዎ ይርዱኝ፣እኔ እፈፅማለሁ"ይሉ ነበር አልጋወራሹ፡፡ የሚያገኙት መልስ "እሺ" የሚል ነው፡፡

ንግስት ዘውዲቱ እንደነገሡ የነገስታት ደንብ ነውና በወቅቱ የነበረው መገበያያ ገንዘብ በምኒልክ ምስልና ስም የታተመውና የተቀረፀው ስለነበር፣ እሱ ቀርቶ በዘውዲቱ ስምና ምስል ሊቀረፅ ታስቦ በብር፣ በአላድ፣ በሩብ፣ በመሐለቅ ተከፋፍሎ ከተዘጋጀ በኋላ የገንዘብ ሚኒስትሩ አይተው ፈቃዳቸውን እንዲሰጡና እንዲታተም ሲጠይቋቸው "እኔን የኢትዮጵያ ህዝብ መርጦ ያነገሰኝ የዋልኩለት ውለታ ኖሮ ሳይሆን የአባቴን ውለታ አስቦ ስለሆነ እኔም በበኩሌ የአባቴ ስም የሚጠራበትን ማሰብ ስላለብኝ በአባቴ ስም የታተመው ገንዘብ ተሰርዞ በእኔ ስም የታተመ ገንዘብ እንዲተካ አልፈቅድምና በዚያ ይቀጥል፡፡ በእኔ ስም ሊታተም የተሰናዳው የመታሰቢያ ስጦታ ብቻ ይታተምበት፡፡" ስላሉ በምኒልክ ስም የሚታተመው ገንዘብ እንዲቀጥል ሆኗል፡፡

ንግስት ዘውዲቱ ከ1909 - 1922 ዓ.ም ድረስ በነበረው የስልጣን ዘመናቸው ምንም እንኳ በአንኳር አንኳር ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ባያደርጉም በዘመናቸው ሰርተዋቸው ያለፉ ስራዎች ቀላል አልነበሩም፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ዛሬም ድረስ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኘው የንግስተ ነገስታት ዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል አንዱና ግንባር ቀደሙ ነው፡፡ ሐኪም ቤቱን በዘመናቸው ሲያቋቁሙትም ለሴቶች ማዋለጃ እንዲሆን በሚል ነበር፡፡



ንግስተ ነገስት ዘውዲቱ ምኒልክ

አባታቸው የጀመሩትን አገር የማዘመን ጅምርም እንዲቀጥል ይፈልጉ ነበርና፣ ለዚህም ዘመናዊ ትምህርት ወሣኝ መሆኑን በመረዳት የአዲስ አበባውን ቅዱስ ጊዮርጊስ ትምህርት ቤት አሰርተው አገልግሎት እንዲሰጥ አድርገዋል፡፡ በተጨማሪም በ1914 ዓ.ም የተቋቋመው ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤትም የዘመናቸው ውጤት ነው፡፡ ትምህርትን በሚመለከት ያወጁት አዋጅም ለዘርፉ የነበራቸውን ጠንካራ አቋም የሚያረጋግጥ ነው፡፡

"ልጅ ያለው ሰው ሁሉ ልጁን ስጋዊና መንፈሣዊ የሆነ ትምህርት እንዲያስተምር የሚያስገድድ አዋጅ፡፡

"ልጅ ያለው ልጁ ክፉንና በጎን የሚለይበትን፣ ንጉሱንና ፈጣሪውን የሚፈራበትን እውቀትን ለማግኘት የንባብና የጽህፈት ትምህርት ያላስተማረ መቀጫውን ሃምሳ ሃምሳ ብር እየከፈለ የመቀጫው ገንዘብ ወደ ቤተ-ክርስቲያን እየገባ ለነዳይን ምግብና ልብስ ይሆናል፡፡

የንስሃ አባትም የሆንክ ቄስ ሁሉ የንስሃ ልጆችህ ልጆቻቸውን አስተምሩ ብለህ ከመከርክ በኋላ ምክርህን የማይቀበሉ ቢሆኑ ግን አዋጅ አፍራሾች መሆናቸውን ለአገሩ ሹም አስታውቅ፡፡

የገጠር መሬጌታም የሆንክ በቤተ-ክርስቲያኑ ከሌላው ግብርህ ጋር ቀላቅለህ የሰበካውን ሰዎች ልጆች የንባብና የፅህፈት ትምህርት አስተምር፡፡

የደብርም አለቃ የሆንክ ሰው ፈጣሪውን አውቆ የሚጠቅምበትን በደብርህ መንፈሣዊ እውቀት ለምዕመናን በሚገባው ልክ የስብከት ትምህርት በየደብርህ አስተምር፡፡ ሳታስተምር የቀረህ እንደሆነ ግን በሹመትህ ትቀጣለህ፡፡

ደግሞ ልጅ ያለህ ሰው ሁሉ ልጅህ የንባብና የፅህፈት ትምህርት ከተማረ በኋላ ለህይወቱና ለኑሮው የሚያሻውን ገንዘብ ለማግኘት እንዳይቸገር ባገራችን ካለው የእጅ ስራ ልብህ የሚወደውን አንዳንድ የእጅ ስራ እንዲማር አድርግ፡፡ ለትዳሩ የሚሆን የእጅ ስራ ሳታስተምረው የቀረህ እንደሆነ ግን በአካል ጉዳይ ካሣ ግማሽ ወደ ድሆች ተማሪ ቤት የሚገባ መቀጫ ሃምሳ ሃምሳ ብር ትከፍላለህ፡፡ ይኸንንም የተቆጠረውን ትምህርት ይማር የተባለው ልጅ እድሜው ከ7 ዓመት እስከ 21 ዓመት ድረስ ያለውን ነውና ከዚህ በላይ ላለው የትምህርት ዕድሜ በተላለፈው ልጁ አባቱ አላስተማርህም ተብሎ አይቀጣም፡፡›

ጥቅምት 11 ቀን 1921 ዓ.ም"

/ዝክረነገር 1962 ዓ.ም/

ይህ አዋጅ ተግባር ላይ በመዋሉም በተለይ በአዲስ አበባ አካባቢ በርካቶች ልጆቻቸውን ዘመናዊ ትምህርት ቤት እንዲማሩ አድርገዋል፡፡



ንግስት ዘውዲቱ የአባታቸውን የምኒልክን ስራና ተግባር ቀጣዩ ትውልድ ያስበው ዘንድም በቅዱስ ጊዮርጊስ አቅራቢያ የሚገኘውን የምኒልክ ሐውልት አሰርተውላቸዋል፡፡ የዳግማዊ ምኒልክ አደባባይ በሚባለው ቦታ ላይ የቆመውን ሐውልት በጀርመናዊው መሐንዲስ በሙሴ ሂርትል አስጠንተው ሐውልቱ በጀርመን አገር በነሃስ ተሰርቶ እንዲመጣ አዘዙ፡፡ ሐውልቱ መጥቶ የተመደበለት ቦታ ተደልድሎ ከተዘጋጀ በኋላ ገና ሳይተከል ዘውዲቱ ስላረፉ አልጋወራሹ ጥቅምት 22 ቀን 1923 ዓ.ም በታላቅ ክብረበዓል እንዲተከል አድርገዋል፡፡

ወደ መንፈሳዊ ተግባራቸው ስናልፍም፡ለብዙ መቶ ዓመታት ፀንቶ የቆየው "ኢትዮጵያውያን ከሊቃውንቶቻቸው ውስጥ ጳጳስ መሾም አይችሉም" የሚለው ግብጻች በአንቀፅ 42 ያካተቱት ሕግ ቀርቶ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በንግስት ዘውዲቱ የጥረት ውጤት ግንቦት 18 ቀን 1919 ዓ.ም አራት ኢትዮጵያውያን የጵጵስና ሹመት ሊያገኙ ችለዋል፡፡ የእስክንድርያው ፓትሪያሪክ አቡነ ዮሐንስም ኢትዮጵያ ድረስ መጥተው የኢትዮጵያን ተወላጅ ጳጳስ አድርገው አዲስ አበባ ላይ ሾመውና ባርከው ተመልሰዋል፡፡ ይህን ጉዳይ በሚመለከት የንጉስ ላሊበላ ወንድም ቅዱስ ሃርቤይ ሞክሮት እንደነበረና ሳይሳካለት እንደቀረ፣ ይልቁንም በዘመኑ ብዙ ሁከት እንዳስነሳበት በእሱ ታሪክ ውስጥ ያየነው ነው፡፡ በተጨማሪም በአፄ ዮሐንስ 4ኛ ተሞክሮ ሳይሳካ ቀርቶ የነበረና በዘውዲቱ ጊዜ እውን የሆነ የኢትዮጵያውያን ክርስቲያን ነገስታት የዘመናት ህልም ሆኖ የቆየ ጉዳይ ነበር፡፡ ስለዚህ በዘውዲቱ ጊዜ ኢትዮጵያ የራሷ ጳጳስ ኖሯት ቆየችና፣ በ1951 ዓ.ም ደግሞ የራሷ ሊቃነ-ጳጳሳት /መሾም የሚችል/ በማግኘቷ ከእስክንድሪያ ማስመጣቱ ቀረ፡፡

ንግስት ዘውዲቱ በአዲስ አበባና ከአዲስ አበባ ውጪ በሚገኙ ከተሞች በርከት ያሉ አብያተክርስቲያናትን አሳንፀዋል፡፡ያረጁና የፈራረሱትንም አሳድሰዋል፡፡

1. በ1909 ዓ.ም ተመስርቶ ከ10 ዓመት በኋላ የተፈፀመው የበዓታ ገዳምን በማሰራትና ሙሉ መተዳደሪያ በመስጠት በዐሎት ቤታቸው ተቀምጦ የነበረውን የአፄ ምኒልክ አፅም እንዲያርፍበትና እንዲቀደስበት አድርገዋል፡፡
2. የአዲስ አበባ ጴጥሮስ ወጳውሎስን፣
3. የአዲስ አበባ ደብረነገስት ቁስቋምን፣
4. የአዲስ አበባ ቅዱስ ዮሴፍን፣
5. ደብረ አሚን ተክለሐይማኖትን፣
6. ቅዱስ ቂርቆስን፣
7. የአዲስ አበባ ደብረሠላም እስጢፋኖስን በዘመናቸው አሰርተዋል፡፡ የእስጢፋኖስ ቤተ-ክርስቲያንን ካሰሩ በኋላ በታላቅ ሰልፍ ታቦት

እንዲገባ ያደረጉትም ጥቅምት 17 ቀን 1909 ዓ.ም የሠኀሌው ጦርነት ድል በእለተ እስጢፋኖስ ስለተገኘ በሚል ነበር፡፡

8. የአዲስ አበባ ደብረፅጌ ዑራኤል ትክሉ በምኒልክ የነበረ ቢሆንም፤ ስላረጀ አስፈርሰው አሁን ያለውን ህንፃ ያሰሩት ዘውዲቱ ናቸው፡፡
9. የአዲስ አበባ ፅርሐአርያም ቅዱስ ሩፋኤልን አፄ ምኒልክ በጭቃና በሣር ክዳን አሰርተውት የነበረ ሲሆን፤ ዘውዲቱ አስፈርሰው ያሁኑን ህንፃ አሳነፁ፡፡
10. የአቃቂ ቀራንዮ መድሐኒዓለም ትክሉ የንጉስ ሳህለሥላሴ (የአፄ ምኒልክ አያት) የነበረና በምኒልክ ጊዜ የታደሰ የነበረ ቢሆንም፤ አርጅቶ የሚፈርስ ስለሆነ የአሁኑን ህንፃ በአዲስ መልክ አሠርተዋል፡፡
11. የእንጦጦ ማርያም ቤተ-ክርስቲያን በእቴጌ ጣይቱ ስም ሆኖ ቀደም ሲል በምኒልክ ዘመን የተሰራው በጭቃ ስለነበርና ዕድሜ ስለሌለው ንግስት ዘውዲቱ አሁን ያለውን ህንፃ አሠሩት፡፡
12. ልጅ እያሡ ያሰራውን የቀጨኔ መድሐኒዓለም ቤተ-ክርስቲያንንም አሳድሰዋል፡፡
13. ጠራ የደብረ በግዕ አቡነ ሞአን ገዳምንም ቤተ-ክርስቲያን በአዲስ መልክ ያሰሩት ዘውዲቱ ነበሩ፡፡ ይህ ቤተ-ክርስቲያን የንጉስ ሳህለስላሴ ልጅ የሆኑት የአፄ ምኒልክ አባት የንጉስ ኃይለመለኰት መቃብር ያለበት ስለሆነ፣ ዘውዲቱ ከመንገሣቸው በፊት ከነበረው ጊዜ ጀምሮ እስከዘመናቸው ፍፃሜ ድረስ አስፈላጊው ድግስ እየተዘጋጀ ሳይቋረጥ በየዓመቱ በፍትሐት የሸዋው ንጉስ የኃይለመለኮት ስም ሲጠራበት ቆይቶ ነበር፡፡

ሌሎች ከአዲስ አበባ ውጪ በሚገኙ ከተሞች በንግስት ዘውዲቱ የተሰሩ አብያተ-ክርስቲያናትም፤

14. የመናገሻ ማርያም ቤተ-ክርስቲያን፣
15. የፋሌ መድሐኒዓለም ቤተ-ክርስቲያን፣
16. ሜታ የወረብ ማርያም ቤተ-ክርስቲያን፣
17. የአዋሽ ማርያም ቤተ-ክርስቲያን፣
18. የኤጀርሣ ለፎ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን፣
19. የየረር ቅድስት ስላሴ ቤተ-ክርስቲያን፣
20. የአድአ በርጋ አቡነ ተክለሐይማኖት ቤተክርስቲያን ናቸው፡፡

በተጨማሪም በኢየሩሳሌም በሚገኘው ቦታ "የኢትዮጵያ ቤት" ተብሎ የሚጠራውን ከዘጠና በላይ ክፍል ያለውን ትልቅ ፎቅ ቤት አሰርተው፣ ከኪራዩ ገቢ እሩቡ በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ መናንያን መርጃ እንዲውልና ቀሪው ለመንግስት ጉዳይ እንዲሆን አድርገዋል፡፡

ንግስት ዘውዲቱ በዚህ መሰሉ መንፈሣዊ ተግባራት ላይ ትኩረታቸውን አድርገው ሲሰሩ፤ልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ ደግሞ በእነዚህ ዓመታት



በአውሮፓውያኑ ድጋፍና በኢትዮጵያውያን ምሁራን ረዳቶቻቸው እየታገዙ ግዙፍ ግዙፍ ተግባራትን እየከወኑ ኢትዮጵያን የማዘመንና የማሰልጠን ሂደታቸውን ቀጥለዋል፡፡

ራስ ተፈሪ በዘውዲቱ ዘመን የሰሯቸው ስራዎቻቸውም በህዝቡ ዘንድ ልዩ አድናቆት ሲያስገኝላቸው፤በአገር ውስጥ ተራማጅ ሹማምንት ዘንድ ደግሞ ተቀባይነታቸውን አጉልቶላቸዋል፡፡በአውሮፓውያኑ ዓይን ደግሞ ወደርየለሽና በታሪክ ታይተው የማይታወቁ የኢትዮጵያ ተስፋ ተብለው ታዩ፡፡ከሁሉም በላይ ግን የስራቸው ውጤት ያስገኘላቸው ትርፍ የደጋፊዎቻቸው መበርከትን ሲሆን፤ ይህም አንደኛውና ዋናው ግባቸው የነበረ ጉዳይ ነው፡፡ምክንያቱም በየጊዜው ይነሳባቸው የነበረውን አድማ ዝቅ ብለን እንደምናየው በቀላሉ ማክሸፍ የቻሉትም ሆነ የዘውዲቱን ስልጣን እየሸረሸሩ ባዶ ለማስቀረት ቀላል የሆነላቸው የደጋፊዎቻቸውንና የሰላዮቻቸውን ቁጥር በማበርከታቸው ነው፡፡ለዚህ ተግባር ሲሉም በስራ ውጤት ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ገንዘብ መድበው መቸርንም ተጠቅመውበታል፡፡

ጥቂት ምሁራንን ከጎናቸው አሰልፈው የአስተዳደር እንቅስቃሴውን የገፉበት ልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ ከ1909 - 1922 ዓ.ም ካከናወኗቸው ተግባራቶች ውስጥ ኢትዮጵያን የመንግስታቱ ማኅበር አባል ማድረጋቸው ይጠቀሳል፡፡ በ1915 ዓ.ም ኢትዮጵያ የአባልነት ማመልከቻዋን ስታስገባም ጠንከር ያለ ተቃውሞ ገጥሟት ነበር፡፡ "በውስጧ የባሪያ አገዛዝ አለ፣ ግድያና ዝርፊያ አለ፣ የግዛቷ ወሰን በደንብ የተከለለ አይደለም፣ በግዛቷ ላይ የመንግስታቱ ማኅበር የሚያዘውን ሕግ ልታስፈፅም አትችልም..." የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ነበሩ፡፡

ሆኖም የአልጋወራሹን የአስተዳደር ስራ ያዩ አገራት ድጋፋቸውን ሰጡ፡፡ አልጋወራሹም የባሪያ አገዛዝ በሕግ እንደተሻረና አገራቸውም ሠላም መሆኗን አስረድተው በ1916 ዓ.ም በሚያዚያ ወር ኢትዮጵያ የመንግስታቱ ማኅበር አባል አገር ልትሆን ቻለች፡፡ ዋና ደጋፊዎቹም እንግሊዝ፣ ፈረንሣይና ጣሊያን ነበሩ፡፡ በመጀመሪያ የተቃወሙትም እነሱው ነበሩ፡፡

እነዚህ አገሮች ወዳጅ መስለው አባል አድርገው መልሰው ደግሞ "ትወረር" ብለው በኢጣሊያ የዳግም ወረራ ጊዜ እውቅና ሰጥተዋል፡፡ የሆነ ሆኖ ኢትዮጵያ በልዑል አልጋወራሹ ጥረት በ1916 ዓ.ም አባል አገር ሆናለች፡፡ ይህም በወቅቱ ለኢትዮጵያ የማይገኝ እድል ተደርጎ የተወሰደና ልዑል አልጋወራሹም በከፍተኛ ደረጃ የተወደሱበት ትልቅ ተግባራቸው ነበር፡፡

ኢትዮጵያ አባል ከሆነች በኋላ ወዲያው በሚያዚያ ወር አልጋ ወራሹ መኳንንቱን አስከትለው በተመቻቸላቸው የጉብኝት ፕሮግራም

የፈረንሣይን፣ የቤልጂየምን፣ የስዊዲንን፣ የኢጣሊያን፣ የእንግሊዝን፣ የግሪክን ... ዋና ከተሞች ተዘዋውረው እየጎበኙና ከየአገራቱ መሪዎች ጋር እየተወያዩ ደፕሎማሲያዊ ግንኙነቱን አጠናከሩት፡፡ የመንግስታቱን ማኅበር መቀመጫ ጄኔቭንም ጎበኙ፡፡

የመጀመሪያው አውሮፓን የጎበኙ አልጋወራሽ ናቸውና በምሁራኑ ዘንድ ልዩ አድናቆት ተቸራቸው፡፡ጉብኝቱ ለኢትዮጵያውያኑ ልዑካን ቡድንም ብዙ ነገርን ያስገነዘበ ነበር፡፡ከወራት በኋላ ነሐሴ 29 ቀን 1916 ዓ.ም ጉብኝታቸውን አጠናቀው ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ ደማቅ አቀባበል ጠበቃቸው፡፡ተመልሰውም በጉብኝታቸው ወቅት ያዩትን ስልጣኔ ኢትዮጵያ ላይ ተግባራዊ ለማድረግ ጥረታቸውን ቀጠሉ፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው አዳዲስ ስራዎች በስፋት መሰራት የጀመሩት፡፡

በለንደን ቆይታቸው በአፄ ቴዎድሮስ ጊዜ ከመቅደላ ተወስዶ ከነበረው ህልቁ መሣፍርት ከሌለው ቅርስ ውስጥ አንድ የወርቅ ዘውድ ከእንግሊዝ ንጉስ ከጆርጅ 5ኛ የ"ይመለሳል" ቃል ተገብቶላቸው ነበርና ሐምሌ 4 ቀን 1917 ዓ.ም ተመልሶ ንግስት ዘውዲቱ ተረክበዋል፡፡ ከውጭ አገር ነገስታትም በየጊዜው የአድናቆት መልዕክት ይደርሳቸው ጀመር፡፡

ይህን ወዳጅነት መሠረት በማድረግም ራስ ተፈሪ በርካታ ኢትዮጵያውያንን እየመለመሉ ለትምህርት ወደ አውሮፓ መላክ ጀመሩ፡፡ ትምህርት ቤቶችም በአዲስ አበባና በየጠቅላይ ግዛቱ እንዲከፈቱ አደረጉ፡፡ በጥቅሉ በአልጋ ወራሽነታቸው ዘመን ዛሬም ድረስ ግልጋሎት እየሰጡ ያሉ ተቋማትንና ልዩ ልዩ የመሠረተ ልማት አውታሮችን ለመገንባት መሠረት የጣሉበት ወቅት ሆነ፡፡ ጎን ለጎንም የስልጣናቸውን መንገድ ይገነቡ ነበር፡፡

በ1921 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ አውሮፕላን አስመጥተዋል፡፡ ይህንንም ለዚያው ለመከረኛው ስልጣን በንብ ሲያዘንቡበት ወደፊት እናያለን፡፡ በተጨማሪም ከአውሮፓውያኑ ጋር የተለያዩ የሞኖፖል ውሎችን ሙሉ ኃላፊነት ወስደው ይፈራረሙ የነበሩት ራሳቸው ራስ ተፈሪ ነበሩ፡፡

በንግስተ-ነገስት ዘውዲቱ ዘመነ-መንግስት እነዚህንና እነዚህን የመሣሠሉ ተግባራት ሲከናወኑ አገሪቱ ሠላም የሠፈነባትና የዘውዲቱ የስልጣን ዘመንም የተረጋጋ የነበረ ሊመስለን ይችላል፡፡ነገር ግን ከመቸውም ጊዜ የበለጠ አደገኛ የስልጣን ትግልና ሽኩቻ የነበረበት፤በየጊዜው በአልጋ ወራሹ ላይ የሚነሱ አድማዎች የበረከቱበት፣ ሹማምንቱ ጎራ ለይተው የተናቆሩበት፤በወሬ፤በሐሜትና በአሉባልታ ብዙዎች የተቀጡበት፤ዘውድ የጫኑት ንግሥት የተካለቡና የተዋከቡበት፣ በሁለት ቤተ-መንግስት ግብር የተበላበት፤የንግስትና ያልጋወራሽ ስልጣን ማን አዛዥ ማን ታዛዥ እንደሆነ ያልተለየበት፤ብዙ አወዛጋቢ ክስተት



የተስተናገደበት ዘመን ነበር፡፡ ስለዚህም የተባሉትን ሁነቶች በአጭሩ አብራርቶ ለማስቀመጥ ከስረ መሠረቱ መጀመርና ልጅ እያሡ ስልጣኑን ካጣበት ጊዜ ጀምሮ መዳሰሱ ተመራጭ ነው፡፡

ልጅ እያሡ ከስልጣን መሻሩ በቤተ-መንግስቱ አደባባይ በአዋጅ ሲነገር በአዲስ አበባ መጠነኛ የተኩስ ልውውጥ ተደርጎ ከ5 ሰዎች በላይ ሞተዋል፡፡ ደጃዝማች አብርሃም አርአያም በልጅ እያሡ መሻር ተበሳጭተው ጊቢ ገብተው ለማስቸገር ሞክረው የነበረ ሲሆን፤ እንደማያዋጣቸው አውቀው እጅ ሰጥተዋል፡፡ ከዚያ በኋላም የእያሡ ደጋፊዎች ያደረጓቸው ጦርነቶች ሁሉ ሳይሳኩ ቀርተዋል፡፡ እነዚያ ሁሉ የፊት ለፊት ፍልሚያዎች አልፈው አዲሱ ሹም ሽር ከተከናወነበት ጊዜ ጀምሮ ደግሞ ትግሉ በሁለቱ ተሿሚዎች በንግስት ዘውዲቱና በራስ ተፈሪ መካከል ሆነ፡፡ ይህም ሲባል ሁለቱ ባለሥልጣናት በግልፅ ባይፋጠጡም የሁለቱ ጎራ ደጋፊዎች ትግል እየበረታ ሄደ፡፡

ባንድ ወገን በራስ ተፈሪና በደጋፊዎቹ ምሁራንና መኳንንት፣ በሌላ በኩል ደግሞ የቀድሞው ወግና ስርዓት የመቀጠል አለኝታ ምልክት አድርገው ዘውዲቱን በሚያዩ ወግ አጥባቂ መኳንንት መካከል የተደረገ ፍጥጫ ነው፡፡ ከወግ አጥባቂው በኩል የአቡኑና የእጨጌው መንፈሣዊ ድጋፍ የማይለያቸው ፊታውራሪ ሐብተጊዮርጊስ ግንባር ቀደምትነቱን ይይዛሉ፡፡

በሁለቱ ወገኖች መካከል የነበረውን ፍጥጫ ባህሩ ዘውዴ ሲገልፁት "በወግ አጥባቂዎቹና በተፈሪ መካከል የነበረው ልዩነት በጥቅሉ ሲታይ፤ኢትዮጵያ በነፃነት ባለችበት ቆማ ትቅር ወይስ የውጭ ኃያላንን ተጠግታ ወደፊት ትራመድ በሚለው አማራጭ ላይ የሚሽከረከር ነበር" ይሉታል፡፡የምሁራኑ ራስ ተፈሪን መደገፍም ከዚሁ ጋር በተያያዘ የሚታይ ነው፡፡

በምኒልክ ዘመን የተሾሙት 12 ሚኒስትሮች (በእያሱ ጊዜም እንደቀጠሉ ነበሩ) ስልጣናቸው ስር የሰደደ መሆኑ ይታወቃል፡፡ብዙዎችም ከተፈሪ ይልቅ ለዘውዲቱ አክብሮት ነበራቸው፡፡ለዚህም ይመስላል የመጀመሪያው አድማ "ሚኒስትሮች ይሻሩ" በሚል መነሻ የተጀመረው፡፡በዚህ በመጀመሪያው አድማ ላይ የራስ ተፈሪ ተሳትፎ እምን ድረስ እንደነበር በውል አይታወቅም፡፡ነገር ግን በቀጥታም ባይሳተፉበት በተዛዋሪ በደጋፊዎቻቸው አማካኝነት የተቀሰቀሰ አድማ እንደሆነ የብዙ ፀሐፍት ግምት ነው፡፡አድማው ህዝባዊ ገፅታ ያለው ይምሰል እንጂ አንቀሳቃሾች መሀል ሰፋሪዎች ነበሩ፡፡

መሐል ሰፋሪ ተብሎ የሚጠራው ጦር ንጉሥ ነገስቱ በሚቀመጥበት ከተማ ከየምድቡ እየተውጣጣ በወር ተራ እየገባ በቅርብ ሆኖ ከተማዋንና የመንግስትን ንብረት የሚጠብቅ የታጠቀ ሠራዊት ነው፡፡ በዚህ አድማ

የራስ ተፈሪ ሚና እንደነበረው የሚያስጠረጥረው የአድማው ቃል ላይ ገና እልጋወራሽ በሆኑ በ1ኛ ዓመታቸው ከሳሾቹ የተፈሪን ስም እያሞገሱ፣አስተዳደራቸውን እያጋነኑ ከአቤቱታቸው ጋር ማቅረባቸው ነው፡፡

መጋቢት 4 ቀን 1910 ዓ.ም በመሀል ሰፋሪው አነሳሽነት ተጀምሮ ወዲያው ህዝባዊ ድጋፍ የተላበሰው የ"ሚኒስትሮች ይሻሩ" ጥያቄ ለራስ ተፈሪ እጅግ ጠቃሚ መሆኑ ግልፅ ሲሆን፤ነገር ግን ሁለት ስጋቶች ነበሩ፡፡አንደኛው ሚኒስትሮች የከፍተኛ ስልጣን ባለቤትና በሹም ሽር ጉዳይ የሚመከሩ፣ የየራሳቸው ብዙ ወታሮች የነበሯቸው ናቸውና አሜን ብለው መሻር ባይፈልጉ አመፁ ሲፈራ፤በሌላ በኩል ደግሞ ህዝቡ የመሀል ሰፋሪው አነሳስ ተገቢ ነው ብሎ በአደባባይ መሰብሰቡና በዚህ አይነት ጉዳይ ቀጥታ የህዝብ ተሳትፎ መኖሩ የራስ ተፈሪ ስጋት ነበር፡፡ በሚገርም ሁኔታ ግን አንዱ ስጋታቸው በሌላኛው ስጋት መቀረፍ መቻሉ ነው፡፡በሌላ አገላለፅ ራስ ተፈሪ ያልጠበቁት የህዝብ አመፅ ቢያስጋቸውና ባይወዱትም ሚኒስትሮችን ግን አንለቅም ብለው እንዳያውኩ አግዶላቸዋል፡፡
በየጊዜው እያደገ የሄደውን ይህን አድማ አስመልክቶ የህዝቡን የክስ ቃል፣የመሀል ሰፋሪውን የተቃውሞ ድምፅና ከአልጋ ወራሹ የተሰጠውን ምላሽ ለአንባብያን ማድረሱ ጠቃሚ ነውና በደጃዝማች ከበደ ተሰማ ተፅፎ በ1963 ዓ.ም "የታሪክ ማስታወሻ" በሚል ርዕስ የታተመውን መፅሐፍ ጠቅሼ በሚከተለው መልኩ አካትቸዋለሁ፡፡

በጉዳዩ ላይ ህዝቡ ተሰብስቦ በሚዶልትበት ጊዜ የተሰበሰበውን ህዝብ የሚያስፈርድ አጋፋሪ ተሹሞ ስለበር እያስነሳ ይጠይቃል፡፡ በዚህ ጊዜ አንዱ፤

"ጌታችን እግዚአነ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ዓለም ፈጥሮ 12 ሐዋርያትን አገር ከፍሎ እንዲያስተምሩ ያሰማራቸውን ለመምሰል ላገሩና ለመንግስቱ ልማት በውነት እንዲመክሩና. እንዲሰሩ 12ቱን ሚኒስትሮች ደጉ ጌታችን አፄ ምኒልክ መርጠው ቢሾሟቸው፤ ለአገር ልማት ለህዝብ አንድነት በመምከር ፈንታ አንዱ ላንዱ ለየራሳቸው ጥቅም በመመልከት አገሩን አበላሹት፡፡ እንጂ ለመንግስት የጠቀሙትና የሰሩት ጉዳይ የለም፡፡ 12ቱን ሐዋርያት በማየት የተሾሙት ሚኒስትሮች 12 አጋንንት ስለሆኑ እንዲሻሩ ያስፈልጋል፡፡

ለምሳሌ የስራ ሚኒስቴር ተብሎ የተሾመው የራሱን ቤት ለመስራት በቤት ላይ ቤት እየቀጠለ ወደሰማይ ለመውጣት ይገሰግሳል፡፡ እንደዚሁም የግቢ ሚኒስቴር የተባለው የራሱን ሐብት ብቻ በማደራጀቱ ከምኒልክ ቤት ለግብር የሚሆን መሰናዶ ታጥቶ ባለፈው ሰሞን ከእርሱ ቤት ዱቄት ተግዞ ተሰናዳ፡፡ ይህ ምን ያሳያል? ሁሉም የየራሱን ጥቅም ለማደራጀት መዘጋጀቱን ነው፡፡"



በዚህ አይነት የአድማው ክስ እየተጧጧፈ ስለቀጠለ በቤተ-መንግስት ተመክረና ሊቀጻጻሱና እጨጌው ከሊጋባው (የመሃል ሰፋሪው አዛዥ) ጋር በመሆን በህዝቡና በመንግስቱ መካከል መላላክ ጀመሩ፡፡ ወዲያውም ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስ፣ እጨጌ ወልደጊዮርጊስ፣ ሊጋባ መኮንን ተወንድ በላይ በአንድነት ሆነው አድማው ላይ ለተሰበሰበው ህዝብ ከቤተ-መንግስት የተላከውን ተከታዩን ፅሁፍ አነበቡላቸው፡፡

"ከቤተ-መንግስት የተላከው ቃል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ፡፡

"በአንድነት ሆናችሁ በአባታችን እጅ የላካችሁት ቃል ደርሶናል፡፡ የንጉስ ወልደጊዮርጊስን መሞት የሰማነው ከትናንት ወዲያ ነው፤ (ዘውዲቱ በነገሱ በሳምንቱ የበጌምድርና የሰሜን ንጉስ አድርገው የሾሟቸው በወቅቱ ሞተው ስለነበር) ይህም ለእናንተ የሚያሳዝናችሁ አይደለምን? ሁለተኛስ እቴጌ ጣይቱን ያህል እናታችሁን ተዝካራቸው በሚወጣበት ቀን በእንደዚህ ያለ ምክንያት ተጓድሎ ቢውልና ድግሱ ቢበላሽ ሐዘኑና ጉዳቱ መልሶ ለእናንተ አይደለምን? የላካችሁልኝን ቃል ለንግስት አሳውቃለሁ፡፡ ከጥንትም ቢሆን የሚኒስትሮችን ሹመት ደጉ ንጉሠ ነገስት አፄ ምኒልክ ለህዝባቸው ጥቅምና እድገት የሚሆነውን ለማስጠበቅና ለማሰራት ሲሉ አቅደውት ነበር እንጂ ህዝብን ለመጉዳት በማሰብ እንዳልነበር ታውቁታላችሁና፤ አሁን አሳቡን ከራሳችሁ አውርዳችሁ እኛ እንድናሰብበት ካደረጋችሁ ለመላው ህዝብ ደስ የሚለውንና ለመንግስቱ ብልፅግናና ጥቅም የሚሆነውን ለሰኞ ጠዋት እስክናስታውቃችሁ ድረስ በንግግርም ሆነ ወይም በሌላ ረገድም ቢሆን ሽብር እንዳይነሳ አደራ ተጥሎባችኋል፡፡

ከሁላችሁም ወገን ሁከትና ሽብር እንዲነሳ ያደረገ ሰው ቢገኝ በመጀመሪያ ጠላትነቱ የኢትዮጵያ ስለሆነ፤ እኛም በበኩላችን ከእነሱ ወገን ሁከት እንዳይነሳ እናደርጋለን፡፡" የሚል ቃል ለተሰበሰበው ህዝብ ከተነበበለት በኋላ አድመኞቹም በበኩላቸው ተከታዩን ቃል በፅሁፍ ለመንግስቱ ላኩ፤

"የኢትዮጵያ መንግስት አልጋ ወራሽ ልዑል ራስ ተፈራ ሆይ፤

"እኛ ባሮችዎ የኢትዮጵያ ህዝብ በንግስታችን በንግስተ ነገስታት ዘውዲቱና በርስዎ በልዑል አልጋ ወራሻችን በኩል ተበድለናል፣ ተጎድተናል የምንለው ነገር የለም፡፡ ነገር ግን ታላቁ ንጉስ ዳግማዊ ምኒልክ ህዝቤን ይጠብቁልኛል፣ የጀመርሁትንም የስራ ውጥን ይፈፅሙልኛል ብለውና አስበው የሾሟቸው ሚኒስትሮች እንደገና ተሿሚዎቹ ብሰው ህዝብን መበተን፣አገራችንን ማጥፋት፣ አገሪቱን ከነገንዘቧ ለየራሳቸው መከፋፈልና፤እውቀትን ማጥፋት፣ ትምህርትንም

መድፈን፣ የጨዋን ልጅ ሁሉ ከጥንት ከአባቱ ማዕረግ ማውረድ ሆነ እንጂ ለመንግስት የረዱትና የጠቀሙት ነገር የለም፡፡

ስለዚህ ከመበደልና ከመከፋት፣ ከውርደትና ከመበሳጨት፣ ድሃው ከመዘረፉና መንግስቱም ጥቅሙን አጥቶ ጉዳት ከመድረሱ በፊት ለንግስታችንና ለአልጋወራሹ እናመለክታለን፡፡ እርስዎም ይህን ለንግስታችንና ለርስዎ የፃፍነውን ቃል አይተው የቸርነትዎን መልስ እንድናገኝ የታመነ ተስፋ አለን፡፡ 12 ሚኒስትሮች እስካሁን ያጠፉትን ስለኢትዮጵያ ስለአገርዎ አስበው እንዲያሻሽሉትና የተደላደለ እንዲያደርጉት ትክክለኛ እውቀትና ግምት እንዳለዎ እናውቃለን፡፡ እስካሁን ድረስ እነዚሁ ሚኒስትሮች መሰናክል ቢሆኑብዎ ነው እንጂ ንግስት በአባታችን ዙፋን ከተቀመጡበትና እርስዎ የኢትዮጵያ መንግስት አልጋ ወራሽ ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ብዙ ጠቃሚ ስራ ይሰሩልን ነበር፡፡ አሁንም እርስዎና ንግስታችን የጦር ሚኒስትሩን ፊታውራሪ ሐብተጊዮርጊስን ጨምረው ያስተዳድሩን እንጂ ከእንግዲህ ወዲህ ለነዚህ ሚኒስትሮች በእኛ ላይ ስልጣን እንዳይሰጡብን እንለምንዎታለን፡፡

በንግስታችንና በእርስዎ በአልጋወራሻችን በኢትዮጵያ በሀገራችን ክፉ የሚመክሩ ሰዎችና የሚያስቡም ቢኖሩ ከፊትዎ የምንሞትና ደማችንን በመጀመሪያ የምናፈስ እኛ ባሪያዎችዎ ነን፡፡ ይህም ጥርጥር እንደሌለው የኢትዮጵያ አምላክ ይመሰክርብናል፡፡ እግዚአብሔር ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪን ለኢትዮጵያ ቤዛ የሰጠን ክብር ምስጋና ይግባው፡፡" አልጋ ወራሹ ይህ ጽሁፍ ከደረሳቸው በኋላ በቀጠሮው መሰረት ተከታዩን የውሣኔ ደብዳቤ ጽፈው ላኩ፡፡

"ለህዝቡ የመንግስቱ ሁለተኛ መልስ፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ፡፡

"እናንተ በአንድነት ሆናችሁ ለላካችሁልኝ መልዕክት መልሱን ለሰኞ አስታውቃችኋለሁ ብያችሁ ነበር፡፡አሁንም አባቶችና ወንድሞች ከዚህ ቀደም ሁላችን በአንድነት ሆነን በልጅ እያሡ ላይ የተነሳው የእስላም ሴት በማግባታቸውና በመስለማቸው ይህን ህዝብና እኛም እርግጠኝነቱን ስላየነው በእውነት የኢትዮጵያን ሃይማኖት ለማቆምና ህዝቡን ከጥፋት ለማዳን ነው እንጂ ለራሳችን ጥቅም ብለን አይደለም፡፡ለዚህም ምስክርና አስረጅ ይሆነን ዘንድ ያን ጊዜውኑ አባታችን እጨጌውና ፊታውራሪ ሐብተጊዮርጊስ አንድነት ሆነው የምኒልክ ልጅ ትንገስ፣ አንተ አልጋ ወራሽ ሆነህ ስራው ሁሉ በአንተ ይሰራ ቢሉኝ፤ ሲሆን የአባቴን እርስት እያረስኩ በኢትዮጵያ ከሚመጣባት መከራ ሁሉ ሳልለይ ልቀመጥ፤ያለዚያ አይሆንም ካላችሁኝ ሐረርጌን ይገዩ ይህ ነገር እስኪፈፀም ድረስ እረዳለሁ ብዬ ገባሁ፡፡ መላው ህዝብ ተባብሮና አንድነት



ሆናችሁ የኢትዮጵያ መንግስት አልጋ ወራሽ አደረጋችሁኝ እንጂ እኔ ከሁሉ ይልቅ አውቃለሁ፤አደላድለዋለሁ ብዬ አልገባሁም፡፡

ይህም በተደረገ ጊዜ ንጉስ ሚካኤል ሊወጉን ቢመጡ፤ አሽከሮቾ ይምጡና ይከተሉኝ፣ ያባቴም ጦር ያብርልኝ ሳልል፤ ይህን አስባችሁ ካደረጋችሁልኝ ጋራ አብሬ ዘምቼ ገባሁ፡፡ አሁን ከእናቴ ከእመቤቴ ጋራ አብሬ ሆኜ የምረዳችሁና የማግዛችሁ ከሆነና አገሬስ በእኔ ምክንያት የምትድን ከሆነ ከሁሉ ይልቅ ደስ የሚለኝ ለእኔ አይደለምን? ነገር ግን በአንድነት የህዝቡ መሰብሰብ ምን ያህል የሚያጎድል ይመስላችኋል፡፡ ይህን በመሰለ ምክንያት መስኮብን /ሩሲያን/ ያህል ታላቅ መንግስት መቶ አርባ ሚሊዮን ህዝብ ያለውና በሰው ብዛትም ሆነ በአገር ስፋትም ቢሆን ከአውሮፓ መንግስታት ሁሉ የሚበልጠው በአስር ዓመት የማይደፈር ከተማውን በአንድ ቀን ውስጥ ጠላቶቹ ገቡበት፡፡ ሰዋቸው እርስ በርሱ ተላለቀ፡፡ አሁንም እናንተ ሚኒስትሮችን ይሻሩልን ማለታችሁ የተሾሙት ሰዎች ይሻሩልን ብላችሁ ነው እንጂ የተነሳችሁት የበደላችሁ ስራው አይደለም፡፡

አፄ ምኒልክ ስራቸው እየበዛ፣ የውጭ አገር ሰው እየበረከተ፣ መንግስቱ እየሰፋ ሲሄድ፤ የአውሮፓ ነገስታት ሁሉ የኢትዮጵያ ንጉስ መካርም የለው፣ ስራም አይሰራ እያሉ አገራቸውን ለመከፋፈል የሚፈልጉት ቢሆን፤ አገሬም በዓለም ካሉት ነገስታት ትክክል ሆና ትጠራ ብለው ሚኒስትሮች ሾመው ለየነገስታቱ ሁሉ ወኪሎች መሾማቸውን አስታወቁ፡፡ ስራቸው ይጉደል እንጂ ሚኒስትሮች በመሾማቸው በዓለም ነገስታት ዘንድ እጅግ ተመሰገኑ፡፡ በዓለም ያሉ ነገስታት ሁሉ ይልቁንም ከሚኒስትሮች ሌላ መካር የሚያስፈልግ መሆኑን መርምረው ከየሃገሩ ሽማግሌ 300 እና 500 የሚሆን የአገር ጨዋ መርጠው ይሾማሉ፡፡ ሰራተኛና አማካሪ ከሌለው መንግስት ተብሎ እንደምን ይቆጠራል፡፡ ይህንንም የመሰለው ሁኔታ ከጥንት ከአባቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው፡፡ የመንግስትና የህዝብ ኃይል ትክክል ነው፡፡ አሁንም ለሹምሽሩና ለሌላውም ስራ ቢሆን እኛም ብንጨርሰው፣ ከእኛም በኩል መካር አግኝተን ብንጨምር አስፈላጊነቱን እየተመለከትንና እያየን ለማድረግ እንችላለን፡፡ አሁን ያሉትን ሚኒስትሮች ግን ሽረንላችኋል፡፡

ይህንን ቀደም ብላችሁ በዝግታ ብታስታውቁን ኖሮ እንደሚሆን አድርገን፤ ህዝቡም በእንደዚህ ያለ አድማ ስራ ረገድ ተሰበሰበ ሳይባልና በሌላ ተመልካች ዘንድ ሳይታወቅና ሳይገለፅ እኛው አስበን እንጨርስላችሁ እንደነበር የታመነ ነው፡፡

መጋቢት 16 ቀን 1910 ዓ.ም ተፃፈ አዲስ አበባ ከተማ፡፡"

ይህ የአልጋወራሹ የውሳኔ ቃል በጃን ሜዳ ለተሰበሰበው ህዝብ ተነበበ፡፡ አልጋወራሽ ራስ ተፈሪ በሁለቱም ጽሁፋቸው ልዩ አፅንኦት

ሰጥተው የገለፁት የህዝብ አመፅና ተሰብስቦ ማደም በፍፁም እንደማያስፈልግ ነው፡፡ ይህም ለወደፊት እንዳይደገም የሚሹት ትልቅ ስጋታቸው መሆኑ በግልፅ ሰፍሯል፡፡ ለዚህም ይመስላል እጨጌ ወልደጊዮርጊስ የውሣኔ ቃሉ ከተነበበ በኋላ ለተሰበሰቡት ሁሉ ሚኒስትሮች እንዲሻሩና እንዲወጡ መወሰኑን እየጠቀሱ አስረድተው፤ ለወደፊቱ ግን ይህን የመሰለው የአድማ ስራ እንዳይደገምና ጉዳት የሚያመጣ መሆኑን በምክርም ጭምር ካስረዱ በኋላ የገዘቱት፡፡

በዚህ ጊዜ የወለጋ ሌቃ ባላባት የደጃዝማች ጆቴ ልጅ ፊታውራሪ መርዳሣ ጆቴ ከአድመኞቹ አንዱ የነበሩ ቢሆንም፤ ጎራዴያቸውን መዘው "ሁልጊዜ እየገዘትክ ማሳሰር ለምደሃል፤ ፍታ!" ሲሉ ከፍ ባለ ጩኸት ተናገሩ፡፡ እጨጌው ግን ጎራዴውን ከመጤፍ ሳይቆጥሩ በቁጣ "አልፈታም!" በማለት ግዝታቸውን አፀኑ፡፡

ጳጳሱ አቡነማቴዎስ ግን ፈራ ተባ እያሉ "... እግዚአብሔር ይፍታ..." በማለት ሲንተባተቡ እጨጌው "አልፈታም!" በማለታቸው ግዝቱ ስለፀና፤ ግልጥ ባለው በጃንሜዳ የጠመንጃ ማውረድና የጎራዴ መመዘዝ ተስተውሎ ሁኔታው ወደ ሽብር ለለውጥ ሲል፤ የምኒልክ ታማኝ አሽከር የነበሩትና በጦር ሜዳም በጀግንነታቸው የሚታወቁት ሊጋባ መኮንን ተወንድበላይ ፈንጠር ብለው ወጥተው ቆሙና "እግዚአብሔር ይፍታህ ብለዋል ባለህበት እርጋ!" ብለው ስለተናገሩ ሊነሳ የነበረው ሁከት ሰክኖ ሁሉም ፀጥ አለ፡፡

አልጋወራሹ በፅሁፋቸው ከጠቀሱት ውስጥ አንዱ ሚኒስትሮች ቢሻሩም ተተኪ ማስፈለጉ አይቀሬ መሆኑን ነው፡፡ ይህንንም ያለህዝብ አድማ በውስጥ እኛ እንጨርሳለን ማለታቸውን አይተናል፡፡ ስለዚህም እነዚህን ቱባ ቱባ ባለሥልጣናት በህዝብ ድምፅ መሻር መቻላቸው ትልቅ እፎይታ ሲሆን፤ የበለጠው ጥቅም ግን ሻሪው ህዝብ ተተኪዎቹን መምረጥ አለመቻሉና ለወደፊቱም አልጋወራሹ ይስማማኛል የሚሉትን መሾም መቻላቸው ነው፡፡ ከዚህ በኋላ የጦር ሚኒስትር የነበሩት ፊታውራራ ሐብተጊዮርጊስ ብቻ ሲቀሩ 11ዱ ሚኒስትሮች ተሽረው ወደየርስት አገራቸው እንዲሄዱ ተወሰነና እየታዘዙ ሄዱ፡፡

በእነሱ ምትክም በስራው ላይ ሚኒስቴር መባልንና በማናቸውም ጉዳይ ላይ እየገቡ ይመክሩ የነበረውን ስልጣን በመቀነስ፤ተወስኖ የተሰጠውን ስራ ብቻ የሚሰራ "የእገሌ መስሪያ ቤት ሹም" የሚል አዲስ የአሿሿም ዘዴ ተግባራዊ ሆነ፡፡ ይህም በአዲስ ተሿሚዎች ስራው ሲከናወን ቆይቶ ከአንድ ዓመት ተኩል በኋላ ደግሞ ሚኒስቴር የሚባለው ሹመት እንደገና ተከተለ፡፡ ሚኒስትርነት ግን እንደቀድሞው ልቅ ያልሆነና ተወስኖ የሚሰጥ ሥራ እንዲሰራበት ሆነ፡፡



ቀጣዩ አድማ ደግሞ በ1912 ዓ.ም በአልጋወራሹ በራስ ተፈሪ ላይ የተነሳ ነበር፡፡የገንዘብ ሚኒስትር የነበሩት በጅሮንድ ውብሸት ኃይሌ፤ፊታውራሪ መንገሻ ውቤ፡ቀኝአዝማች ደስታ ወሰኔ፤ነጋድራስ ፋላስ፤አቶ መልሴ ሣህሌ፤አቶ ተፈራ ንጉሤና የከተማ ዘበኞች ሹም የነበሩት አለቃ ገብሩና ሌሎችም ለየመኳንንቱ እየዞሩ "አልጋወራሹ አገራችንን ሸጦታልና እንክሰስ" እያሉ በመንገር እንዲተባበሩዋቸው ሲጠይቁና ለማስረጃነትም "በራህሌ የሚባለውን በጨው ቀረጥ ብዙ ገቢ ለመንግስት የሚያስገኘውን አገር መሸጣቸውን ..." ሲገልፁ ተደረሰባቸውና ተያዙ፡፡አለቃ ገብሩ እንግሊዝ ኤምባሲ /ለጋሲዮን/ ገብተው ስለተጠጉ ሳይያዙ ቀርተዋል፡፡"አገር በመሸጥ" የሚሉት አልጋወራሹ ከአውሮፓውያኑ ጋር የሚፈራረሟቸውን ውሎች መሠረት አድርገው ነው፡፡

አድማው ላይ ብዙዎች ተባባሪ ሆነው ስለነበር ከፍተኛ ስጋት ቢያሳድርም፣ እንቀሳቃሾች ብቻ በጥቅምት ወር ተይዘው ወደ ፍርድ ሸንጎ እንዲቀርቡ ተወሰነና ተባባሪዎቹ ግን እንዲተው ተደረገ፡፡ የእነዚህ የዋና ዋና አነሳሾች ፍርድም "እጃቸውን እስላም ቤት፣ ከብታቸውን እማድ ቤት" የሚባለው ሲሆን፤ ሐብታቸው ተወርሶ ግለሰቦች ይታሰራሉ የሚል ትርጉም አለውና ይሄንኑ ፈፀሙባቸው፡፡ በዚህ አድማ ደጃዝማች ባልቻም ተሳታፊ ናቸው ቢባልም አስተባብለው ራሳቸውን ነፃ አድርገዋል፡፡ ሌላው በ1917 ዓ.ም በአልጋ ወራሹ ላይ ሊደረግ ታስቦ የነበረው የግድያ ሙከራ ነው፡፡ ወ/ሮ ፀሐይወርቅ ዳርጌ ለዘውዲቱም፣ ለተፈሪም፣ ለእያሡም ዝምድናቸው እኩል ይሁን እንጂ፤ ለልጅ እያሡ የነበራቸው ፍቅር የበለጠ ነበር፡፡

ወይዘሮዋ የልጅ እያሡ አሽከር ከነበረው ከመሐመድ አባ ሻንቆ ጋር ተነጋግረውና ብዙ ተባባሪዎችን መልምለው፣ አስፈላጊውን ሁሉ አሟልተው አልጋ ወራሹን በቤተ-መንግስት ቅጥር ጊቢ ወደሚገኘው ወደ ቅዱስ ማርቆስ ቤተ-ክርስትያን ሲሄዱ ለማስገደል ተዘጋጅተው እንዳሉ ወሬው አፈትልኮ በተጠቀሰው ዓመት ነሐሴ 17 ቀን ተያዙና መስከረም 9 ቀን 1918 ዓ.ም ወደፍርድ ሸንጎ እንዲቀርቡ ተደረገ፡፡

በአደባባይ የነበረው ፈራጅ ሁሉ ቅጣቱ ሞት መሆኑ አያጠያይቅምና ከዚህ ይልቅ የአሟሟታቸውን አይነት በጩኸት ገለፀ፡፡ ገሚሱ በሥቅላት ሲል ሌላው ባውራ ጎዳና ላይ እስከአንገታቸው ተቀብረው አንገታቸው ብቻ ወጥቶ ከነነፍሳቸው ከብት ይነዳባቸው ማለት ጀመረ፡፡ ከፈራጆቹ አንዱ ግራዝማች ይገዙ ድባቤ በንዴት "እንዲያው በከንቱ እኛን ያስፈርዱናል እንጂ አይቀጧቸውም፡፡ የተፈረደበት ሁሉ ቢቀጣ ኖሮ እንዲህ ያለ ጥፋት አይበዛም ነበር፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሰዎች ሊማሩ አይገባምና ሁሉም በሞት ይቀጡ፤ የማሯቸው እንደሆነ ነፍስዎን አይማራት" ቢሉም ከፍርዱ በኋላ ሞቱ ቀርቶ በሐብት መወረስና በእስር ተለወጠላቸው፡፡

የአልጋወራሹ አካሄድም ሆነ ስራና ተግባር በሁሉም ዘርፍ ዘውዲቱን የበታች አልጋወራሹ የበላይ የሆኑበት አይነት ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ደጃዝማች በየነ (ሊጋባው) "ራስ ተፈሪ አልጋወራሽ ብቻ ናቸው እንጂ እንደራሴ አይደሉም፡፡ አልጋወራሹም ፈንታውን ይጠብቃል እንጂ በመንግስቱ ስልጣን ውስጥ ገብቶ የአስተዳደር ስራ መስራት አይችልምና፤በአስተዳደሩ ስራ የገቡት ያለሕግ ስለሆነ በአልጋወራሽነታቸው መብት ብቻ እንዲቆዩ ሆኖ ከሌላው ስራ እንዲታገዱ" የሚል ጥያቄ በማንሳት በአልጋወራሽ ላይ ማደምና ማሳደም ጀመሩ፡፡ ይህም ጥቂት እውነት አለውና ብዙዎች በዚህ አድማ ሊስማሙ አቆበቆቡ፡፡

ይህ ወሬ ለአልጋወራሹ በየምድቡ ባስቀመጧቸው ሰላዮቻቸው አማካኝነት እንደደረሳቸው፣ ሊጋባው እንዲያዙ አደረጉና ፊታውራሪ ሐብተጊዮርጊስ በተገኙበት የአልጋወራሽ ችሎት ላይ እንዲቀርቡ ሆነ፡፡ ሊጋባ በየነ ልጅ እያሡ ተሽሮ ዘውዲቱ ሲተኩና ራስ ተፈሪ አልጋወራሽ ሲባሉ በቦታው የነበሩ ናቸው፡፡ ነገር ግን ችሎቱ ላይ "በዚያ ወቅት ራስ ተፈሪ አልጋወራሽና ባለሙሉ ስልጣን እንደራሴ መባላቸውን አልሰሙም ወይ? ይህንንስ በጊዜው የነበሩት መካሮች ሁሉ እርስዎን ጨምሮ የሰሙትና የሚያውቁት አይደለም ወይ?" በሚል ፀጥታ በማደፍረስ ተብለው ቅጣት ተወሰነባቸው፡፡ ቅጣቱም በአደባባይ እንዲገረፉና ወደሐረርጌ ሄደው እንዲታሰሩ የሚል ሲሆን፤ ያለምህረት በአደባባይ ተገርፈው ታሰሩ፡፡ አልጋወራሹ በዚህ ጉዳይ ላይ ምህረት ማድረጉ ምን እንደሚያስከትል ያውቃሉ፡፡ ይህ የ1917ቱ አድማ እጅግ ተገቢ ከመሆኑም በላይ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በአልጋወራሹ ላይ የተነሱት ተከታታይ አመጾች ሁሉ ምንጭ ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡

ራስ ተፈሪ ከነገሡ በኋላ በፃፉት መፅሐፍ ላይም ሆነ በደጋፊዎቻቸው የተፃፉት መፃህፍት ላይ "አልጋወራሽ ተባልኩ፣ ቀጥዬ፣ እንደራሴ ሆንኩ፣ ከዚያ ንጉስ ተብዬ በመጨረሻ ንጉሠነገስት" እየተባለ ይፃፍ እንጂ እውነታው አይደለም፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ንጉሠነገስት ወይም ንግስተ ነገስት ተብሎ ዘውድ ሲጫን እዚያው በዚያው አልጋወራሽ አይሰየምም፡፡ቢሰየምም ቀደም ሲል እንዳየነው በተሿሚው ንጉሠነገስት ወይም ንግስተ ነገስት ተመርጦ መሰየም ይገባዋል፡፡ያ ሳይሆን ቀርቶ ሁለቱ እኩል ተሾሙ፡፡ይህ ያልተለመደ አካሄድ ይሁን ተብሎ ታልፎ ተግባራዊ ሆነና ዓመታት ካለፉ በኋላ "በወቅቱ አልጋወራሽና ባለሙሉ ስልጣን እንደራሴ ተባልኩ" ቢባል ሌላ ስህተት ይሆናል፡፡ስህተቱም "ባለሙሉ ስልጣን እንደራሴ" የሚባለው ስልጣን ተተኪ ነገስታት እድሜያቸው ሳይደርስ ሲቀር እስኪያድጉ እንደራሴ ተሾሞላቸው በእንደራሴው አማካኝነት የመንግስት ስራ



ይከናወናል፡፡በዘውዲቱ ዘመን የተፈጠረው አወዛጋቢ ነገር ግን አልጋወራሹ እንደራሴ መባሉ ነው፡፡ዘውዲቱ ራስ ተፈሪን በ20 ዓመት እድሜ ይበልጧቸዋል፡፡ ሞግዚት አያስፈልጋቸውም፡፡ዘውዲቱም ተፈሪም ለዙፋኑ ቅርብ ናቸው፡፡ በእድሜ ደረጃ ሁለቱም ያለእንደራሴ ለማስተዳደር የደረሱ ናቸው፡፡ዘውዲቱ የማስተዳደር ብቃት ከሌላቸው ደግሞ አልጋወራሽ ለመሆን ብቁ ሆኖ የተገኘውና ለዘውዱ የሚቀርበው ወንድ ልጅ ብቻውን ንጉሠነገስት መሆን ይችል ነበር፡፡የግድ ቀጥተኛ ልጅ ይሁን አይባልም፡፡ወንድ ሆኖ ለዙፋን ከቀረበ በቂ ነው፡፡የምኒልክ ቀጥተኛ ልጅ ዘውዲቱ እያለች ነበር የልጅ ልጁ እያሡ ያውም በልጅነቱ ለሥልጣን የበቃው፡፡ሌላው አማራጭ ሴት የነገስታት ዘሮች ልምድ ካላቸው የእቴጌነቱን ስልጣን ይዞ መቀጠል ነበር፡፡ወይም የንግስቲቱ ባል በባለቤትነቱ አስተዳደራዊ ስራዎችን ሊከውን ይችላል፡፡

ከተጠቀሱት ውስጥ አንዳቸውም ተግባራዊ ባለመሆናቸው ምክንያት ተጀምሮ እስኪጨረስ የዘውዲቱ ንግስና በዘመነ መሣፍንት "ግንብ ጠባቂ" ይባሉ የነበሩትን ነገስታት ያስታውሰናል፡፡ ሁኔታው ሌላ የሚያስታውሰን ነገር በወቅቱ ልጅ እያሱን የሚደግፍ በርካታ ህዝብ እንደነበረና ይህንንም በመፍራት የተከናወነ መሆኑን ነው፡፡

ይህ ውሉ ያልለየና ገደብ ያልተበጀለት ስልጣንን ጠቅልሎ የመያዝ ጉዳይ የዘውዲቱን ተቆርቋሪዎች ክፉኛ እያበሳጨና እያወዛገበ ሲቀጥል፤ አልጋወራሹም የዘውዲቱን ተቆርቋሪዎች የእኔ ጠላት እያሉ ጣት የመቀሰራቸውን ጉዳይ ገፉበት፡፡ በዚህም ክፍፍል ተፈጥሮ አንዱ ለአንዱ ጠላት የሆነበት እንዲሁም ተከታታይ አመጾች የተከታተሉበት ዘመን ሆነ፡፡ ይህን ጉዳይ በሚመለከት አርቀው ያሰቡ ጥቂት ሹማምንት "ሁለቱን በአንድ መሾሙ ወደፊት ችግር ሊፈጥር ይችላልና ይታሰብበት" ብለው የነበረ ቢሆንም ሰሚ አላገኙም፡፡ ሌላው ቀርቶ ፊታውራሪ ሐብተጊዮርጊስ የተፈሪ አካሄድ ወደመጨረሻው አላምር እያላቸው ሲሄድ "ምን አስቸኮለዎ? መንገዱን እየጠረግንና እያስተካከልን አይደለም ወይ? እኔስ አርጅቻለሁ ኢትዮጵያን አላያትም! እባክዎ እንዳያፈራርሷት አደራ!" ብለው በአክብሮት ነግረዋቸዋል፡፡

ፊታውራሪ ሐብተጊዮርጊስ በምኒልክ ጊዜ የተከበሩ ባለሥልጣን የነበሩና በልጅ እያሡ ጊዜ አክብሮት ከተነፈጋቸው ባለሥልጣናት ውስጥ አንዱ ናቸው፡፡ እያሡን ለመሻርም ትልቁን ሚና ተጫውተዋል፡፡ በዘውዲቱ መሾምም የሚስማሙና የወግ አጥባቂው ወገን መሪ ናቸው፡፡ ድጋፋቸው ለዘውዲቱ ይሁን እንጂ የራስ ተፈሪ ስልጣኑን የመጠቅለል ጉዳይ ስኬታማ እየሆነ መሄዱን ሲያዩና የዘውዲቱ ወገን እየተጠለፈ መውደቁን ሲያጤኑ ወደ ተፈሪ ማዘንበል ጀምረው ነበር፡፡ ምንም ቢባል ግን በዋናነት የዘውዲቱ ደጋፊ መሆናቸው ግልፅ ነው፡፡ ከሽረት የተረፉ

ሚኒስትር መሆናቸውም ምንጬ በአንድ በኩል የአድማው ተካፋይ ስለነበሩና፤ በሌላ በኩልም ከፍተኛ የፖለቲካ ተደማጭነት ስለነበራቸው ሲሆን፤ ራስ ተፈሪ እኒህን ሰው በማለዳ መሻር ትልቅ ጉዳት እንደሚያስከትል በማሰብ ባይወዷቸውም እንኳ ተከታዩን በመስጋት እንዳስተረፏቸው ይገመታል፡፡ፊታውራሪ ሐብተጊዮርጊስ በ1919 ዓ.ም በሞት ሲለዩ ለአልጋወራሹ እፎይታ ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ ለዘውዲቱ የሚቀረቆር ጠንካራ ክንድ አይኖርምና፡፡

በዚህ ጊዜ አልጋወራሹ የፊታውራሪ ሐብተጊዮርጊስን 15 ሺ ጦር ወረሱና የራሳቸው አደረጉት፡፡አልጋወራሹ በየጊዜው የሚነሳባቸውን አድማ በዘዴ እያከሸፉ፤ አድመኞቹን እያንበረከኩ ቀጥለዋል፡፡አሁን ሦስት ታላላቅ የዘውዲቱ ተቆርቋሪዎች የሆኑ ባለሥልጣናት ቀሯቸው፡፡ደጃዝማች ባልቻ፣አባ ውቃውና የዘውዲቱ ባለቤት ራስ ጉግሳ፡፡

ደጃዝማች ባልቻ አባነፍሶ የአፄ ምኒልክ ታማኝ፣የጦር ሜዳ ጀግና፤ በአድዋው ጦርነት በፈፀሙት ጀብድ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ከተሰኙት የዘመኑ ጀግኖች ውስጥ አንዱ ናቸው፡፡የእያሡ መሻር ካልተዋጠላቸው ውስጥም አንዱ ነበሩ፡፡ከራስ ተፈሪ ተቃዋሚዎች ውስጥም ሆነ፤ በአልጋወራሹ ከተበደሉት ውስጥም አንዱ ናቸው፡፡ገና በማለዳ በአልጋወራሹ ላይ የክስ አድማ ካደረጉት ውስጥም እንደዚሁ አንዱ ነበሩ፡፡

አልጋወራሹ የዘውዲቱን ስልጣን እየገዘገዙ መሄድ ያስቆጣቸው ባልቻ የተገዘገዘው ስልጣን ተገንድሶ ከመውደቁ በፊትም ሆነ በኋላ ለዘውዲቱ እንጂ እንደሌላው ባለሥልጣን አንድም ቀን ለተፈሪ ታዛዥ ሆነው አያውቁም፡፡ የኃይል ሚዛኑ ወደ አልጋወራሹ ማዘንበሉን እያዩ እንኳ የተለሳለሱበት ጊዜ የለም፡፡

በወቅቱ የሲዳሞ ገዥ ነበሩና፤ አልጋወራሹ ወደአዲስ አበባ እንዲመጡ (መጥተውም ታማኝነታቸውን እንዲገልፁ) መልዕክት ላኩባቸው፡፡ደጃች ባልቻ ግን የራሸ ተፈሪን ጥሪ በእንቢታ መለሱት፡፡አልጋወራሹ ንዴታቸውን በውስጣቸው ይዘው ንግስት ዘውዲቱን "እንዲመጡ የሚያሳስብ መልዕክት ላኩላቸው" አሏቸው፡፡ ንግስት ዘውዲቱ የተባሉትን ፈፀሙ፡፡

የዘውዲቱን መልዕክት ሲሰሙ ባልቻ በ1920 ዓ.ም በየካቲት ወር ጦራቸውን አስከትለው ከሲዳሞ ወደ አዲስ አበባ መጡና ሠራዊታቸውን በከተማው በስተደቡብ በሚገኘው በፉሪ ተራራ ላይ አስፍረው፤ ጥቂት አጃቢዎቻቸውን ብቻ አስከትለው ወደቤተ-መንግስት በማምራት በጥቂት ሠራዊታቸው ሰልፍ አሳይተው ንግስትና አልጋወራሹ ወደተቀመጡበት ሠገነት ሂደው እጅ ከነሱ በኋላ የዘውዲቱን ጫማ ሲስሙ፤አልጋወራሹ በተራቸው ለሰላምታ ሲነሱ ባልቻ ግን "ጉንፋን ይዞኛል" አሉና ሰላም



ሳይሏቸው ተቀመጡ፡፡በዚህም በተፈሪ ላይ ያላቸውን ጥላቻ ባደባባይ ገለፁ፡፡

በግብር ሰዓትም ቦታቸው ከአልጋወራሹ ጋር ስለነበር "አሞኛል" ብለው እልፍኝ ሳይገቡ ወደማረፊያቸው ባቀኑ ጊዜ ብልጡ ተፈሪ ወዲያው ታማኛቸውን ደጃዝማች ብሩ ወልደገብርኤልን የሲዳሞ ገዥ አድርገው ሾመው፤ሹመቱንም ፉሪ በሰፈረው የባልቻ ጦር ላይ አዋጅ አስነግረው ጉድ አደረጓቸው፡፡የባልቻ ጦር "ቁጥር ጦር" የሚባለው የንጉሠነገስቱ ጦር በመሆኑ አዋጁን እንደሰማ አዲሱን ገዥ ተከትሎ ወደ ሲዳሞ ሄደ፡፡በዚህ ጦር ላይ ማዘዝ የሚችሉት ንግስተነገስቷ የነበሩ ቢሆንም የሆነው ግን ያ አልነበረም፡፡ ስለዚህ ባልቻ አባነፍሶ ነፍሳቸውን ብቻ ይዘው ቀሩ፡፡

የደጃዝማች ብሩ ሹመትም ብዙ አልቆየም፡፡እሳቸው ተሽረው የአልጋወራሹ ልጅ የልዕልት ተናኘወርቅ ባል ለሆኑት ለራስ ደስታ ዳምጠው ተሰጠች በቡና ሐብቷ የምትታወቀው ሲዳሞ፡፡

ደጃዝማች ባልቻ ጥቂት አጃቢዎቻቸውን ይዘው መጋፈጣቸውን ቢቀጥሉም ያመጡት ለውጥ የለም፡፡ በመጨረሻም በግዞት እንዲቀመጡ ተፈረደባቸው፡፡ በግዞት እንዳሉ ኢጣሊያ ኢትዮጰያን ዳግም ስትወርር እንኳ በተፈሪ ላይ እንጂ በኢትዮጵያ ላይ ቂም ስለሌለባቸው በሽምግልና ዘመን በአርበኝነት ጠላትን ሲያጠቁ ቆይተው ከብዙ ፍልሚያ በኋላ በወራሪው ኃይል ተገድለዋል፡፡

ሌላው በአልጋወራሹ ላይ ጠንከር ያለ ተቃውሞ ያነሱና የንግስት ዘውዲቱ ስልጣን አልባነት በእጅጉ ያስቆጣቸው ደጃዝማች አባውቃው ብሩ ያነሱት አመፅ ነው፡፡ አባ ውቃው በአፄ ምኒልክ ቤተ-መንግስት በእልፍኝ አሽከርነት ያደጉ ናቸው፡፡ አስፈሪውን ስም ያገኙት በልጅነታቸው በእድሜ የሚበልጧቸውን በትግል እያሸነፉ ስላደጉና በጉልበት የሚወዳደራቸው ስላልነበረ ነው፡፡ ብዙዎችን ስለወቁም ውቃው የሚለው ስማቸው ፀንቶ "የሻለቃ አባውቃው" ተብለው የደረጃ እድገት አገኙ፡፡ ቀጥሎ የቤተ-መንግስቱ የወታደር አለቃ ሆነው፣በዘውዲቱ ጊዜ በሊቀመኳስነት የቡኖ ደጃዝማች ተብለው የወላሞ አውራጃ ገዥ ሆኑ፡፡ከዚያም የእልፍኝ ዘበኞች አለቃ ሆነው ተሾሙ፡፡

ደጃዝማች አባውቃው ለአመፅ የተነሱበት ምክንያት ዘርፈ ብዙ ይሁን እንጂ ዞሮ ዞሮ ግን የዘውዲቱ በተፈሪ የመገፍተር ጉዳይ ነው፡፡ተጀምሮ እስኪጨረስም አባውቃው ሙሉ በሙሉ የዘውዲቱ ደጋፊ የነበሩ ናቸው፡፡አልጋወራሹ ከኢትዮጵያ ጠላት ከኢጣሊያ ጋር የተፈራረሙት የወዳጅነት ውል አባውቃውን አስቆጥቷል፡፡ በተለይ ፊታውራሪ ሐብተጊዮርጊስ ከሞቱ በኋላ የአልጋወራሹ የዙፋን መንገድ ጠረጋ በጣም እየፈጠነ በመሄዱ ዘውዲቱ ማንም እንደሌላቸው በመረዳታቸውና፣ ከንግስቲቱ በኩልም "ተፈሪ ሐብተጊዮርጊስ ከሞተ ብሎ

ዘውዱን ሊነጥቀኝ ነው" የሚል ወሬ ተሰማ በመባሉ የአባውቃው ቁጣ እየተባባሰ ሂዷል፡፡ከሁሉም በላይ ግን በ1920 መገባደጃ ላይ ከመሀል ሰፋሪ ቡድኑ የተውጣጡ የአልጋወራሹ ደጋፊ የሆኑ ግለሰቦች በሌሎች ግፊት ተነሳሱና "ተፈሪን ያንግሱልን" የሚል ጥያቄ ማስተጋባት ጀመሩ፡፡ይህን የሰሙት አባውቃው ልባቸው ተነክቶ ያለማንም አነሳሽነት በራሳቸው ጊዜ በአልጋወራሹ ላይ ይነሳሉ፡፡ከዚህ ወሬ ጎን ለጎን ደግሞ የአባውቃው "እኛ በህይወት እያለን ይህን የመሰለ ተግባር አይፈፀምም!" የሚለው ዛቻ አብሮ መስተጋባቱ ቀጠለ፡፡

ይህ ሁሉ ሲሆን ንግስተ ነገስታት ዘውዲቱ አንድም ጊዜ የሌሎችን እርዳታም ሆነ የደጋፊዎቻቸውን ድጋፍ ፈልገውም ጠይቀውም አያውቁም፡፡ ጥያቄውን ዘውዲቱ ለጊዜው የሰሙት ልክ እንደ አባውቃው በወሬ ደረጃ ነበር፡፡ የዚህን ወሬ በሚመለከት ዘውዲቱ ለተፈሪ ሲጠይቋቸውም ተፈሪ የሚያውቁት ነገር እንደሌለ በመግለጽ በጉዳዩ ላይ ለመነጋገር ቀጠሮ ይይዛሉ፡፡በቀጠሮው እለት አልጋወራሹ ከንግስት ዘውዲቱ ጋር ለመነጋገር በማለዳ ሲመጡ፤ደጃዝማች አባውቃው ከቀጠሮው በፊት ወደ ንግስት ይሄዱና "ዛሬ እኔ ልታሰርና የታሰበው ሊፈፀም በእኔም ስራ ላይ አጋፋሪ ወልደማርያም ሊሾም ተመክሮ መወሰኑን ሰምቻለሁ፡፡ እኔ ከመያዜ በፊት አልጋወራሽ ከቤታቸው ሲመጡ ከዋናው በር ላይ እከላከላለሁና ይፈቀድልኝ" ብለው ጠየቁ፡፡ ዘውዲቱ በበኩላቸው "አልጋወራሽ የሚመጣው ይህንኑ ያድማውን አነሳስ አጣርቶ ለመነጋገር በቀጠሮ ነውና መከልከል አይሆንም፡፡አንተም አሁን የነገርከኝን ሲመጣ ብጠይቀው ይነግረኛልና ነገሩን አጣርቸ እስካስታውቅህ ድረስ አርፌህ ተቀመጥ" ብለው ገሰፁ፡፡ ጳጉሜ 1 ቀን 1920 ዓ.ም በቀጠሮው መሰረት ማለዳ 3 ሰዓት ላይ አልጋወራሽ ከመኖሪያቸው ከገነተ ልዑል ወደ ቤተ-መንግስት ገብተው ከንግስት ዘውዲቱ ጋር ያለማቋረጥ ለ8 ሰዓታት የቆየ ረጅም ውይይት አደረጉ፡፡

የምክክሩ ውጤት ምን ይሆን በሚል በአደባባይ የተሰበሰበው ህዝብ ይጠባበቃል፡፡ በመጨረሻ ጉባኤው 11 ሰዓት ላይ ተጠናቆ አባውቃውና አድማውን አስወርተዋል የተባሉት ደጃዝማች ወዳጄ እንዲታሰሩ ተወሰነ፡፡ ደጃዝማች ወዳጄ በአፈንጉስ አረጋይ እጅ እንዲታሰሩ ሆኖ ተይዘው ሲሄዱ፤ ደጃዝማች አባውቃውን ሊይዙ የሄዱት አጋፋሪ ወልደማርያም ግን ሳይሳካላቸው ቀረ፡፡

አባውቃው የምኒልክ አፅም ካረፈበት ግቢ ውስጥ በሚገኘው መታሰቢያ ቤት ከወታደሮቻቸው ጋር መሽገው መድፋቸውን ጠምደው አላስቀርብ አሉ፡፡ የተለያዩ መልዕክተኞች እየተላኩ በግድም በውድም፤ በሽምግልና መልክም አባውቃውን እጃቸውን እንዲሰጡ ቢጠይቁም፤



አልጋወራሹን ሊወቁ የተዘጋጁት አባውቃው ምላሻቸው "ደርበህ በለው!" የሚል ሆነ፡፡

አልጋወራሹ በየበሩ ታማኞቻቸውን እያቆሙ ራሳቸው ደግሞ በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን ታንክ ወደመታሰቢያ ቤቱ ጠምደው፤ከንግስት ዘውዲቱ ጋር በመልዕክተኛ የመፍትሄ ኀሳብ መለዋወጥ ጀመሩ፡፡ነገር ግን አባውቃውን ለመማረክ የተደረጉ ሙከራዎች ሁሉ ያሰቡትን አይነት ውጤት ሊያስገኝላቸው አልቻለም፡፡አባውቃው ባሉበት የፉከራና የሽለላ ድምፅ እየተሰማ ሌሊቱ ተገባደደ፡፡ በሽብር ስጋት ተወጥራ የዋለችው አዲስ አበባ በዚያው ሁኔታ ወደማደር ስትቃረብ ከምሽቱ ዘጠኝ ሰዓት አልጋወራሹ ባሳሰቡት መሠረት ንግስት ዘውዲቱ ቃላቸውን ስለሚሰማ እንዲልኩበት አዘዙ፡፡

ግርማዊት ንግስትም "አሁን በአጠገቤ የሚገኙት ሊቀመኳስ መኮንን ዋልቴና ቀኛዝማች ኃይለስላሴ ብቻ ናቸውና ማንኛቸው ቢላኩ ይሻላል!" የሚል ጥያቄ ወደ አልጋወራሹ ላኩ፡፡

"ሊቀመኳስ መኮንን ይሂድ" ብለው መለሱ አልጋወራሹ፡፡ ሊቀመኳስ መኮንን ግን "ብቻዬን አልሄድምና ከአልጋወራሹ ዘንድ ከሚገኙ መኳንንቶች አንድ ሰው ይጨመርልኝ" ስላሉ ይሄም ቃል ተላከ፡፡ የአልጋወራሹ መልስ "ፊታውራሪ ታፈሰ ሐብተሚካኤል አብሮ ይሂድ" የሚል ሆነ፡፡ "የታፈሰ መሄድ ጠቃሚ አይሆንምና ሌላ ሰው ይመረጥ" መለሱ ንግስት፡፡ ለነገሩ የታጩት ሁሉ የወቅቱን ሁኔታ እያገናዘቡ ሰበብ እየፈጠሩ ፈቃደኛ አልሆን አሉ፡፡ በመሃል ደጃዝማች አምደሚካኤል "ልጅ ተሰማ ከበደ ቢላክ ይሻላል" ስላሉና ልጅ ተሰማም ፈቃደኛ ስለሆኑ ለንግስት ሲነገራቸው፣ "ተሰማን ልጅ ነው በማለት እንዳይመለከተው መምህር ደስታና አለቃ ደስታ አብረው ቢሄዱ የተሻለ ነው" የሚል ቃል ለአልጋወራሹ ላኩና በዚህ ተስማሙ፡፡ እነዚህን የመሰሉ አለመተማመንን የሚያንፀባርቁ የቃላት ምልልሶችን ስናይ፤ በተለይ የዚያ ዘመን ፀሐፍት በዚያ ወቅትና ከዚያም በኋላ በነበሩ ክንውኖች ላይ "አልጋወራሹና ንግስት ፍፁም ቤተሰባዊ በሆነ የእህትና የወንድም አይነት ምክክር እያደረጉ ሁሉንም ነገር በሰላምና በስምምነት ይፈፅሙት ነበር ..." የሚል ገለፃቸውን ጥያቄ ውስጥ የሚከትና እውነቱ ተቃራኒው እንደነበር ይጠቁመናል፡፡

የተባሉት ሰዎች አባውቃው ወደመሸጉበት ቦታ ሲያመሩ "በጌታችን በምኒልክ ልጅ የደረሰ ክፉ ነገር አለወይ?" የሚል ጥያቄ ነበር የቀረበላቸው፡፡ መልዕክተኞቹ ምንም ክፉ ነገር እንዳልደረሰና የመጡትም የንግስትን የሰላም ይውረድ ቃል ይዘው መሆኑን ገለፁ፡፡ አባውቃው የተነገራቸውን ቃል ከሰሙ በኋላ "ከንግስት ከራሳቸው ቃል ካልሰማሁ በቀር ይሄን መልዕክት መስማትም ማመንም አልችልም" አሉ፡፡

ከመልዕክተኞቹ አንዱ "የኛን ቃል ካልሰሙ በማሕተማቸው የተረጋገጠ ጽሁፍ እናምጣልዎ" የሚል ምርጫ አቀረቡ፡፡በዚህ ጊዜ አባውቃው ጽሁፍ "ማሕተሙን የሚይዘው ፀሐፊ ትዕዛዝ ወልደመስቀል ስለሆነ ጽሁፉ ቢመጣም አልስማማም፡፡ንግስት ግን ሁልጊዜ የሚመጡበት ቤተ-ክርስቲያን ስለሆነ፤ወደዚህ መጥተው ካንደበታቸው ካልሰማሁ በመልዕክት የምፈፅመው ነገር አይኖርም፡፡እስካሁንም የቆየሁት በመጨለሙ ህፃን፣ ሴት መለየት ስላልተቻለ ነው፡፡እላይ ባመለከትኩት አይነት የንግስትን ደህንነት ከቃላቸው ካልሰማሁ ወገግ ብሎ ብርሃን ሲታይ መታኮሴ የማይቀር ነው" የሚል መልስ ሰጥተው መለሷቸው፡፡መልዕክተኞቹ ይህን ቃል ለንግስት ተናገሩ፡፡

ምስኪኗ ዘውዲቱ በእኔ ምክንያት ደም መፋሰስ ከሚደርስ ሁሉም ነገር ቢቀርብኝ ይሻላል በማለት ይመስላል ክብራቸው ባይፈቅድም ለባብሰው በሌሊት ለመሄድ ተነሱ፡፡"መሄዴ ነው ብላችሁ ለአልጋወራሹ ንገሩ" ብለው ሲነሱ፤ በቅርባቸው የነበሩ መኳንንቶችም "ከንግስት ቃል ካልሰማሁ ካለ በዚህ ምክንያት ተኩስ ተነስቶ ደም ከሚፈስ መሄድዎና ነገሩን ማብረድዎ መልካም ነው" ሲሉ ተስማሙ፡፡

በዚህ ጊዜ አርቆ አሳቢው፣ ጠርጣራውና የዋህነት በአጠገባቸው የማያልፈው አልጋወራሽ ራስ ተፈሪ የዘውዲቱን ለመሄድ መነሳት ሲሰሙ "አንድ ሽፍታ በተነሳ ጊዜ ንጉሠ ነገስቱ ራሱ ሄዶ መማለድ አይገባምና ንግስት እንዲሄዱ አልስማማም፡፡" የሚል ምላሽ ስለላኩ ግርማዊት ንግስት እንዳይሄዱ ሆነ፡፡ ሁሉም ግራ ተጋብቶ ፀጥ ባለበት ሰዓት ቀኛዝማች ኃይለስላሴ የተባሉት "ከንግስት ቃል ካልሰማሁ ካለና ንግስትም መሄድ ካልቻሉ አሁን ስልክ ቢጠለፍ ይደርሳልና ንግስት በስልክ ማነጋገር ቢችሉ የተሻለ ነው" የሚል ኀሳብ አቀረቡ፡፡ በዚህ ሁሉም ተስማምቶበት ባለሙያዎች ተጠርተው ገመድ የመቀጣጠሉ ስራ ሁለት ሰዓት ከፈጀ በኋላ ተሳካ፡፡

ንግስት ዘውዲቱ አባውቃውን በስልክ አነጋገሩ፡፡አባውቃው "ኧረ ለመሆኑ ንግስት ደህና ነዎት ወይ" ሲሉ "ደህና ነኝ" አሏቸው፡፡ "በንግስት ላይ የደረሰ ነገር ከሌለማ እኔ ምን ገዶኝ? አልነግስ" ብለው እጃቸውን ሰጡ፡፡ተፈሪ እፎይ አሉ፡፡ ቀጣዩ ስራ ስለፍርድ ሂደት መወያየት ነበርና ንግስትና አልጋወራሽ በፍርዱ ጉዳይ ሲወያዩ ራስ ተፈሪ "አባውቃው የሰው ህይወት ለማሳለፍ የተነሳ አመፀኛ ስለሆነ በችሎት ቀርቦ ነገሩ ታይቶ ውሣኔ በሚሰጥበት ጊዜ የፍርዱ ውሳኔ በሞት እንዲቀጣ የሚል የሆነ እንደሆነ ያለምህረት እንደፍርዱ ቅጣቱ በሞት እንዲፈፀም ያስፈልጋል፡፡" አሉ፡፡

ዘውዲቱ በበኩላቸው "አስቦ ይነሳ እንጂ በተነሳበት ነገር ነፍስ የጠፋ ስላልሆነ ሞት ቢፈረድበትም በእስራት ቢቀጣ እንጂ በሞት



መቅጣቱ ቅር ያሰኛል" የሚል መልስ ስለሰጡ፣በአልጋወራሹና በንግስት መካከል ከፍተኛ የኀሳብ ልዩነት ተፈጠረና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የውስጥ ለውስጥ ፍልሚያው ገሃድ ወጥቶ በሽማግሌ ብቻ የሚነጋገሩ ሆኑ፡፡

ዘውዲቱ አድርገውት የማያውቁትን ጠንከር ያለ ምላሽ በመስጠታቸው ተፈሪ ቢበሳጩም ዋናው የአባውቃው እጅ መስጠት እንጂ ቀሪው ጉዳይ ቀላል ስለሆነ በደጃዝማች ሙሉጌታና በደጃዝማች ወልደፃድቅ ሽምጋይነት ስለፍርዱ ሁኔታ ንግስትና አልጋወራሹ ሲነጋገሩበት ቆይተው በመጨረሻ አባውቃው በአልጋወራሽ ችሎት የሞት ፍርድ ተፈረደባቸው፡፡ከዚያም የሞቱ ፍርድ በእስራት ተለውጦ ደጃዝማች አባውቃው ታስረው ወደ አንኮበር እንዲሄዱ ተወሰነ፡፡ይህ ፍርድ በተፈረደበት እለት በወቅቱ የወንጀለኛ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት የነበሩት ደጃዝማች መስፍን ገመቹ ባልተለመደ ሁኔታ በችሎቱ ላይ አልተገኙም፡፡ፍርዱ ከተከናወነ በኋላ ለምን ችሎቱ ላይ እንዳልተገኙ ሲጠየቁ የሰጡት መልስ ሁሉንም ያስገረመ ነበር፡፡ እንዲህ ይነበባል፤

"በፍትሐ ነገስቱ ባንዱ አንቀፅ ጌታውን የከዳና የወጋ ይሙት ሲል፤ በአንደኛው አንቀፅ ደግሞ በጌታው ላይ የደረሰውን አደጋ ለመከላከል ሲል ቢገድል ሞት የለበትም ይላል፡፡ስለዚህ የዚህ ሰው ጥፋት ማንኛው ነው?" የሚል ነበር መልሳቸው፡፡

የአባውቃው ፍርድ ከተከናወነ በኋላ በከተማይቱ ለቀናት ሰፍኖ የነበረው ውጥረት ቢረግብም፤ ወዲያው ደግሞ በአባውቃው መያዝ የተደፋፈሩት የአልጋወራሹ ደጋፊዎች ያችኑ ጥያቄ እንደገና በገሃድ አነሷት፡፡

እነዚህ የተፈሪ ደጋፊ የሆኑ ግለሰቦች በወቅቱ ዝቅ ያለ ስልጣን የነበራቸውና ለመልዕክትም የማይመጥኑ ቢሆኑም፤በነሲቡ ዘ-አማኑኤል እየተመሩ በሌሎች ግፊት ተደርጎ የማያውቀውን ተግባር (በንግስተነገስት ፍላጎትና በምክክር ብቻ መፈፀም የነበረበትን) በኃይል ለመፈፀም ወደ ቤተ-መንግስቱ ሄዱና በድፍረት "ተፈሪን ያንግሱልን" የሚል ጥያቄ አቀረቡ፡፡በዚህ ጊዜ በፈቃድ የሚደረገውን ባድማ ማድረጉ ሳያንስ የተላኩት ሰዎች በንግስት ዘንድ የማይታወቁና ለመግባትም ማዕረጋቸው የማይፈቅድ መሆኑን አይተው ዘውዲቱ በእጅጉ አዘኑ፡፡ሆኖም ምንም ምርጫ አልነበራቸውም፡፡ከግራ ከቀኝ ሲያዋክቧቸው "እሺ ብየዋለሁ፤ ንጉስ ብየዋለሁ" አሉ፡፡ የተለመደው የአንድ ግዛት ንጉስ ማድረግ ነበር፡፡ አዲስ አበባ ደግሞ ንጉስ ተሾሞባት አያውቅም፤ንጉሰ ነገስት እንጂ፡፡ስለዚህ ግርማዊት ንግስተ ነገስታት ዘውዲቱ ሁሉም ወደ ተፈሪ አዘንብለው፣የነበሩት ደጋፊዎቻቸው ተማርከው፣ ተግዘውና ታስረው ብቻቸውን ቀርተው ስለበር ምንም ምርጫ አልነበራቸውምና "ንጉስ" አሏቸው እንጂ "የምን ንጉስ?" ተብለው ቢጠየቁ ራሳቸውም

አይመልሱትም፡፡የአንድ ክፍለ ሀገር ንጉስ እንዳይባሉ መቀመጫቸው አዲስ አበባ ነው፡፡አልጋወራሽም ናቸው፡፡የአዲስ አበባ ንጉስ የሚባልም የለም ሊኖርም አይችልም፡፡በጥቅሉ በንጉሰነገስት መቀመጫ (መናገሻ) ከተማ ላይ ንጉስ አይሾምም፡፡ግራ የተጋባ ብቻ ያን ሊያደርግ ይችላል፡፡ዘውዲቱ ይሄን ይመስሉ ነበር፡፡

እናም ልዑል አልጋወራሽ ራስ ተፈሪ መኮንን መስከረም 27 ቀን 1921 ዓ.ም ንጉስ ሆኑ፡፡ አሁንም ይሄ ሳያንስ ንጉስ ተፈሪ "የንግስ በዓሉ የሚደረገው በቤተ-ክርስቲያን ይሁንልኝ" አሉ፡፡ንግስት ዘውዲቱም "በቤተ-ክርስቲያን የሚደረገው የዘውድ በዓል ለንጉሰ ነገስት እንጂ ንጉሰነገስቱ የሚሾመው ንጉስ ዘውድ የሚጫንለት በቤተ-መንግስት ነው" ብለው ሞገቱ፡፡በዚህ ጉዳይ ብዙ ክርክር ከተካሄደ በኋላ ሁለቱን ሊያስማማ የሚችል አማካይ ቦታ ተመረጠና ከቤተ-መንግስቱ በላይ ከመታሰቢያ ቤቱ በታች ባለው ጎተራ ሜዳ በሚባለው ቦታ ትልልቅ ድንኳኖች ተጥለው የንግስ በዓሉ በድምቀትና የውጭ አገር መንግስታት ልዑካን ጭምር የተገኙበት ሆኖ በተጠቀሰው ዕለት ተከናወነ፡፡ንጉስ ተፈሪ ዘውዳቸውን ከደፉ በኋላ እዚህ ደረጃ ላደረሳቸው አምላክ የምስጋና ፀሎት ለማድረግ በቀረበላቸው ያማረ ሰረገላ ላይ ተሳፍረውና በክብር ታጅበው ወደ ቅድስት ስላሴ ቤተ-ክርስቲያን በማምራት የምስጋና ፀሎታቸውን ካደረሱ በኋላ ወደቤታቸው ወደገነተ ልዑል (ወደላይኛው ጊቢ) ሄደው መሳፍንት፣መኳንንት እና ህዝቡን ሰበሰበው ግብር አበሉ፡፡

ከዚህ ጊዜ በኋላ ንጉስ ተፈሪና ንግስት ዘውዲቱ ግንኙነታቸው ተቋርጦ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ከሆነ ብቻ በቀጠሮና በመልዕክተኛ አልፎ አልፎ ከመገናኘት በቀር በአካል ተያይተው አያውቁም፡፡ ይህም ብቻ አይደለም ላይኛውና ታችኛው ቤተ-መንግስት እየተባለ ቀድሞ ባንድ ቤተ-መንግስት ይደረግ የነበረው የግብር ማብላት ስርዓት ቀርቶ በሁለት ቤተ-መንግስት ሁለት ግብር ሆኖ አረፈው፡፡

ሹማምንቱም የለየው ለይቶለት አንዱን ወግኖ ሲቀር፤ ጥቂት ሹማምንት ደግሞ ጉዳዩ "ለሁለት ጌቶች መገዛት..." ሆኖባቸው በግራ መጋባት ቀሪዋን ዓመት ተኩል እንደምንም ለማሳለፍ ተገደዋል፡፡

ቀደም ሲል የተጠቀሰውን "የታሪክ ማስታወሻ" የሚለውን መፅሐፍ የፃፉትና ተጀምሮ እስኪጨረስ የተፈሪ ደጋፊ የነበሩት ልጅ ከበደ ተሰማ (በኋላ ደጃዝማች) "ይህን ታሪክ ማስታወሻ የምፅፈው በቅርብ ሆኜ ሁኔታውን እንዳጠናሁት የንግስትን አስተያየትና ጎሳብ ከዚህ በታች በተመለከተው አረፍተነገር በአጭሩ እገልፃለሁ፡፡" በማለት የንግስት ዘውዲቱን ሁኔታ እንዲህ ይነግሩናል፡፡"እኔን ሳያውቀኝና ሳልጠቅመው የአባቴን ውለታና ወሮታ ለመመለስ ሲል የኢትዮጵያ መሣፍንት መኳንንትና ህዝቡም በፈቃደ እግዚአብሔር ታዝዞ ለአባቴ ዙፋን



ቢያበቃኝ፣ ከእኔ አስተዳደር አለማወቅ የተነሳ ህዝቡ እርስ በርሱ ተፋጅቶ ከሚያልቅና ራሳቸውን አልቻሉም ተብሎ በዘመነ መንግስቴ የባዕድ መንግስትና ገዥ በኢትዮጵያ ላይ ከሚገባ እኔ የተጠየቅሁትን ስልጣን እየለቀቅሁና እየሰጠሁ ነገሩን ማብረድ ይሻላል" በማለት የሚገጥማቸውን ችግር ሁሉ ከፍ ባለ ትዕግስት ያሳልፉት እንደነበረ በግልፅ ይታወቅ ነበር" ይሉናል፡፡ ሲቀጥሉም "ይህ የእኔ ጎሳብ ብቻ ሳይሆን በዚያን ዘመን አንዳንድ ሰዎች ከመኳንንቱም ሆነ ከመሐል ሰፋሪው ወደ ንግስት ዘንድ እየመጡ ጥቃትዎንና በደልዎን አንወድምና ቅር የተሰኙበት ነገር እንዳለ ይንገሩን እያሉ ሲጠይቋቸው ለነዚህ ሰዎች ንግስት የሚመልሱትን መልስ በመስማቴ ገለፅኩ እንጂ አስመስዬ በመናገር የተፃፈ አይደለም" ይላሉ ያይን እማኙ፡፡

ከዚህ አንፃር በየትኛውም ፀሐፊ እይታ አገላለፁ ይለያይ እንጂ የንግስት ዘውዲቱ ስልጣን አለአግባብ እየተገዘገዘ መኖሩን ማንም የማያስተባብለው ሐቅ ነው፡፡ ንጉስ ተፈሪ አሁን አንድ አስጊ ባለሥልጣን ቀርቷቸዋል፡፡የዘውዲቱ ባለቤት ራስ ጉግሣ ወሌ፡፡ህዝቡ እንዳሰበው አልሆነም እንጂ እያሡ ወርዶ ዘውዲቱ ሲተኩ የአስተዳደሩን ስራ በባልነታቸው ራስ ጉግሳ ይይዙታል ተብሎ ተገምቶ ነበር፡፡ በእርግጥም ግምቱ ያስኬድ ነበር፡፡ሆኖም ወቅቱ ለተገቢ አካሄዶች የማይመች ነበርና ራስ ጉግሳ ከባለቤታቸው እንዲርቁ አስበው የሸዋ መኳንንት በዘየዱት መሰረት ወደቀድሞው ግዛታቸው በጌምድር ሾመው ልከዋቸዋል፡፡

ራስ ጉግሳ በግዛታቸው ላይ ሆነው የባለቤታቸውን በደል ቢያውቁም፤ለጊዜው እንደማንኛውም ባለሥልጣን ተመልካች ከመሆን በቀር ሌላ ዘዴ አልታያቸውም፡፡ ስለዚህም በስተመጨረሻ ቂማቸው ገንፍሎ በገሃድ ለማመፅ ይዘጋጁ እንጂ፤ ከዚያ ጊዜ በፊትም ፀረ-ተፈሪ መሆናቸው ለማንም ግልፅ ነበር፡፡

ራስ ጉግሳ በተፈሪና በተከታዮቻቸው ላይ ሃይማኖትን ማዕከል ያደረገ "ተፈሪና የሸዋ መኳንንት የውሻ ሥጋ ይበላሉ" ከሚለው ክስ ጀምሮ የተለያዩ መጥፎ መጥፎ ወሬዎችን ያስወሩ ነበር፡፡በዚህም ላይ እንደባልቻ የተፈሪን ትዕዛዝ "አልቀበልም" ባይ ሆነው የቆዩ ናቸው፡፡እነዚህን ወሬዎች የሰሙት አልጋወራሽም በራስ ጉግሳ ስር የነበሩትን ትልልቅ ሹማምንት በችሮታ እያባበሉ ጉግሳን ከድተው ለራሳቸው እንዲገቡ ማድረግ ከጀመሩ ቆይተዋል፡፡ከእነዚህም ውስጥ የስሜኑ ገዥ ደጃዝማች አያሌው ብሩ አንዱ ናቸው፡፡

ከሐሜቱም ባለፈ አልጋወራሹ በራስ ጉግሳ ስር የነበረውን የመተማን ጉምሩክ በስራቸው ለማድረግ ብዙ ጥረት ሲያደርጉ በራስ ጉግሳ እንቢተኝነት ሳይሳካ ቀርቷል፡፡ በእነዚህና በሌሎች ምክንያቶች የሁለቱ ጠላትነት ስር ሰዶ የቆየ ሲሆን፤ የጎጃሙ ራስ ኃይሉና የትግራዩ ራስ ስዩምም ውስጥ ውስጡን ለራስ ጉግሳ ከጎንህ ነን ባዮች መሆናቸው በአልጋወራሹ ዘንድ የተሰማ ስለሆነ

ራስ ጉግሳን ቻል ማለት አደገኛ መሆኑን ተረድተዋል፡፡ስለዚህ ንጉስ ተፈሪ እሺ እንደማይሏቸው ቢያውቁም ለጦርነቱ ግልፅ ምክንያት ማግኘት ነበረባቸውና በመጀመሪያ ወደ ወረኢሉ መጥተው እንዲገናኙዋቸው ላኩባቸው፡፡ራስ ጉግሳ "አልመጣም" አሉ፡፡ከዚያም በወቅቱ በችግር ምክንያት የራያና የአፋርን ግዛት በመውረርና በመዝረፍ በመንግስት ላይ ያመፀውን የራያና አዘቦ ህዝብ እንዲያረጋጉና ፀጥ እንዲያሰኙ ትዕዛዝ ተሰጣቸው፡፡ ራስ ጉግሳ ግን ጭራሽ የራያና አዘቦን ህዝብ ከጎናቸው አሰልፈው አመፃቸውን ገፉበትና ለጦርነት ተዘጋጁ፡፡አልጋወራሹም የፈለጉትን በቂ ምክንያት አገኙና በጦር ሚኒስትሩ በራስ ሙሉጌታ ይገዙ የሚመራ ጦር ላኩባቸው፡፡ በዚህ ጊዜ የጎጃሙ ራስ ኃይሉና የትግራዩ ራስ ስዩም አይዞህ ማለታቸውን ትተው ገሸሽ አሉ፡፡የራስ ጉግሳ አዝማሪ ስለጉዳዩ ተከታዩን ገጠመ፡፡

"ከኛይቱ ወረቀት ያልፈረመ የለም፣
መላው ታጥቆ ገባ ግዴለም፣ ግዴለም፡፡
ትግሬም ገባ አሉ ሰምቶ በፍጥነት፣
ጎጃምም ገባ አሉ ሰምቶ በፍጥነት፣
የወሌውን ጉግሳ ሞኙን የኔ ጌታ መፈተኛ አርጎት፡፡"

ራስ ጉግሳ ከጦርነቱ በፊት እጅ እንዲሰጡ ቢለመኑ እሻፈረኝ አሉ፡፡ በዘውዲቱ በኩልም በደብዳቤ ተሞከረ፡፡ "እባክህ እሺ ብለህ ግባ ከክፉ እንዳትወድቅ" ብለው ለባለቤታቸው ቢፅፉም ጉግሳ በጅ አላሉም፡፡

መጋቢት 22 ቀን 1922 ዓ.ም የአንችም ጦርነት ተካሄደ፡፡ ቦታው በበጌምድር ግዛት ውስጥ ያለ ሲሆን፣ ቋና ወይም ዘቢጥ ተብሎ ይታወቃል፡፡ የተፈሪ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በአውሮፕላን የታጀበ ጦርነት ሆነ፡፡ የተፈሪ ጦር ከላይ ቦምብ እያዘነበ፣ ከስር በጉግሳ ሠራዊት እጅ በማይገኝ ጠመንጃ እየተታኮሰ ውሎ በሠራዊት ብዛትና በመሣሪያ ብልጫ የጉግሳ ጦር ወደመሸነፉ ሲቃረብ፣ የጨበጣ ውጊያው ላይ ራስ ጉግሳ በፅኑ ሲፋለሙ ሳለ በጎራዴ ጭንቅላታቸውን ተመትተው ወደቁ፡፡ ራስ ጉግሳ ከተገደሉ በኋላ ሠራዊታቸው ውጊያውን ቢቀጥልም መሸነፉ አልቀረም፡፡ እንደተባለው ራስ ጉግሳና ሠራዊታቸው ያውሮፕላን መፈተኛ ሆነው አለፉ፡፡

አልጋወራሹ አስፈሪ አስፈሪ ጠላቶቻቸውን መንጥረው ጨረሱ፡፡ ስለዚህ ይህ ጦርነት በተፈሪ ዘውዲቱና ዘውዳቸው ያለደጋፊ ብቻቸውን ቀሩ፡፡ ስለዚህ ይህ ጦርነት በተፈሪ ድል አድራጊነት ከተጠናቀቀ ከሁለት ቀን በኋላ መጋቢት 24 ቀን 1922 ዓ.ም ዘውዲቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ፡፡ የንግስት ግርማዊት ንግስተነገስት ዘውዲቱ ህልፈት መንስኤው ተብሎ የሚገለፀው በአንድ በኩል ከሳምንት በፊት አሟቸው ስለነበር በዚያ ምክንያት እንዳረፉ፣ በሌላ በኩል የባለቤታቸውን መገደል ሲሰሙ በድንጋጤ ህመማቸው አገርሽቶ እንደሞቱ ነው፡፡ ንግስተ ነገስታት ዘውዲቱ በአባታቸው ዙፋን ተቀምጠው ኢትዮጵያን ለ12 ዓመት ከስድስት ወር አስተዳድረው በ53 ዓመታቸው አርፈዋል፡፡ በደመቀ የቀብር ስነ-ስርዓትም በአባታቸው መቃብርና ራሳቸው ባሰሩት በባዕታ መታሰቢያ ቤተ-ክርስቲያን ቀብራቸው ተፈፅሟል፡፡



# ምዕራፍ 84

*የአፄ ኃይለሰላሴ ዘመነ-መንግስት*

*ከ1923 - 1966 ዓ.ም*

የአፄ ኃይለስላሴ ዘመነ-መንግስት ተብሎ የተቀመጠው ጊዜ ንጉሠ ነገስት ከሆኑበት እለት ጀምሮ የሚሰላ ሆኖ እንጂ፣ በስልጣን ላይ ያሳለፉት ጊዜ ከግማሽ ምዕተዓመት በላይ ነው፡፡

ሐምሌ 16 ቀን 1884 ዓ.ም ከራስ መኮንን ወልደሚካኤልና ከወ/ሮ የሺእመቤት ዓሊ ከሐረር ከተማ 30 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ኤጀርሳ ጎሮ በተባለች ቦታ ልጅ ተፈሪ ተወለዱ፡፡



ህጻኑ ተፈሪ

አባታቸው የአፄ ምኒልክ የአክስት ልጅ ናቸው፡፡ እናታቸው ወ/ሮ የሺእመቤት ዓሊ ከተፈሪ በፊት ስድስት ልጆች ወልደው የነበረ ቢሆንም፣ ሁሉም እንደተወለዱ ሞተውባቸዋል፡፡ አሁንም ሰባተኛውን ልጅ ተፈሪን ለመውለድ ሁለት ወራት ቀርቶኛል ብለው ሲያስቡ ድንገት በከባድ ምጥ ይያዙና ፈጣኑ ተፈሪ በተረገዙ በሰባተኛው ወር ይወለዳሉ፡፡

ልጅ ተፈሪ እንደተወለዱ ቤተዘመድ "እናቱ ካዩት እንደተለመደው ይሞታል" በማለት ህፃኑን እናቱ ሳያዩት ይዘውት ይሄዳሉ፡፡

ይህ ክስተት በባህላዊ አገላለፅ "ሾተላይ" የሚባል ሲሆን፣ ሰው ላይ ሊኖር የሚችለው ኃይለኛ የዓይን ጨረር ሌላ ሰው ላይ ሲያርፍ እስከሞት የሚያደርስ ጉዳት እንደሚያስከትል ይታመናል፡፡

በሳይንሳዊ ገለፃ ደግሞ የእናት ወይም የአባት የደም አይነት RH Negative ሆኖ የሌላኛው RH Positive ይሆንና የሁለቱ ወላጆች ደም ሳይጣጣም ሲቀር የሚከሰት ችግር ተደርጎ ይገለፃል፡፡

በዚህ ምክንያት ህፃኑ ተፈሪ ከእናቱ ወዲያው መለየት ነበረበትና ከወላጆቹ ቤት ወጥቶ ዘመድ ቤት ማደግ ይጀምራል፡፡ እናቱ የህፃኑን ሁኔታ በመልዕክት ሲከታተሉ ከቆዩ በኋላ፣ በድጋሚ አርግዘው ነበርና ከ20 ወራት በኋላ መጋቢት 6 ቀን 1886 ዓ.ም በዚሁ በወሊድ ምክንያት

ህይወታቸው አለፈ፡፡ ልጅ ተፈሪ የእናትን ጣዕም ሳያውቀው ቀረ፡፡ ከህፃንነቱ ጀምሮ የአጎቱ የደጃዝማች ብሩ ሐይለማርያም ባለቤት ወ/ሮ ትሰሜ አባይርጋ ከእምሩና ከልጃቸው ጋር አሳደጉት፡፡



ተፈሪ በልጅነቱ ከአብሮ አደጎቹ እምሩና ማሚት ጋር፡፡

በዚያም ሳሉ አባታቸው ራስ መኮንን የፈረንሣይኛ ትምህርት እንዲማሩ መምህር ቀጠሩላቸውና ልጅ ተፈሪ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ አደጉ፡፡ በ10 ዓመታቸው በ1894 ዓ.ም ከሐረር ወደ አዲስ አበባ መጥተው ለመጀመሪያ ጊዜ ከአፄ ምኒልክ ጋር ተገናኝተው /ተዋውቀው/ ተመልሰው ወደ ሐረር ሄዱ፡፡

አባታቸው ራስ መኮንን በ1898 ዓ.ም ህዳር 10 ቀን የደጃዝማችነት ማዕረግ ሰጥተው "ጋራ ሙለታ" የተባለውን አውራጃ ሾሟቸው፡፡ "ተከታይ ልጄ ደጃዝማች ተፈሪ ነው" ብለውም ለመኳንንቶቻቸው ይፋ አደረጉ፡፡ ልጅ ተፈሪ በ14 ዓመታቸው የደጃዝማችነት ማዕረግ እንዳገኙ ወዲያው በ1898 ዓ.ም መጋቢት 13 ቀን አባታቸው ራስ መኮንን ሞቱ፡፡ በዚህ ጊዜ አፄ ምኒልክ ተፈሪን ከሐረር ወደ አዲስ አበባ አስመጥተው ደጃዝማችነታቸው እንደፀና ቀረብ የሚለውን የሰላሌን ግዛት ሾሟቸው፡፡ ተፈሪ ግን ለተሰጣቸው ግዛት ሌላ እንደራሴ ወክለው በኢትዮጵያ ብቸኛ ትምህርት ቤት በነበረው በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ገብተው ሐረር እያሉ የጀመሩትን ትምህርታቸውን ቀጠሉበት፡፡





ህጻኑ ተፈሪ እና አባታቸው ራስ መኮንን

ከዚያም በ1899 ዓ.ም የባሶ /በጌምድር/ ግዛትን፣ ቀጥሎ በ1900 ዓ.ም ሲዳሞን ተሾሙ፡፡ ከሁለት ዓመት በኋላም ሲዳሞን ትተው የአባታቸውን ግዛት ሰፊውን ሐረርጌንና አውራጃዋን እንዲያስተዳድሩ ተደረገ፡፡ የሐረርጌ ህዝብም በደስታ ተቀበላቸው፡፡ በ1903 ዓ.ም በሐምሌ ወር የንጉስ ሚካኤልን የልጅ ልጅ ወ/ሮ መነንን አግብተው መኖር ጀመሩ፡፡



ደጃዝማች ተፈሪ በ19 ዓመታቸው ወ/ሮ መነንን አግብተው በ1905 ዓ.ም የመጀመሪያ ልጃቸውን ልዕልት ተናኘወርቅን ወለዱ፡፡ ከምኒልክ ሞት በኋላ ስልጣን የያዘው እያሡ በ1907 ዓ.ም ደጃዝማች ተፈሪን ከሐረርጌ ግዛት ሽሯቸው ወደአዲስ አበባ መጥተው እንዲቀመጡ ተደረገና ወዲያው የከፋን ግዛት ሾማቸው፡፡ ሆኖም ደጃዝማች ተፈሪ አልሄዱበትም፡፡ ተፈሪ የአውሮፓ ቋንቋ የሚያውቁ፣ ከአውሮፓውያኑ ጋር ያለአስተርጓሚ በቀጥታ የሚነጋገሩ ጨዋ፣ ዝምተኛ ... እየተባሉ ቆዩ፡፡

በ1909 እያሡ ከስልጣን ተወግዶ ዘውዲቱ ሲነግሱም በወቅቱ አዲስ አበባ የነበሩት ደጃዝማች ተፈሪ ራስ በሚል ማዕረግ አልጋወራሽ ሆነው የራስ ወርቅ አሰሩ፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ንጉሠ ነገስት እስከሆኑበት እስከ 1923 ዓ.ም ድረስ በተከታታይ ልዑል አስፋወሰንን፣ ልዕልት ዘነብወርቅን፣ ልዕልት ፀሐይን፣ ልዑል መኮንንን እና አቤቶ ሳህለስላሴን ወልደዋል፡፡



ከ1903-1954 ዓ/ም ድረስ ለ 51 ዓመታት ያህል በትዳር አብረው የቆዩት እቴጌ መነን እና ራስ ተፈሪ(እቴጌዋ በ1954ዓ/ም በህመም ምክንያት በሞት የተለዩ ናቸው)

ተፈሪ አልጋወራሽ ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ የፈፀሟቸውን ተግባራቶችም ሆነ፤ ኢትዮጵያን የማዘመን እንቅስቃሴያቸውን፣ እንዲሁም ባለሙሉ ስልጣን እንደራሴ፣ ቀጥሎ ንጉስ እየተባሉ መምጣታቸውን ከንግስተ ነገስት ዘውዲቱ ታሪክ ጋር በሰፊው ያየነው ነው፡፡ ተቃዋሚዎቻቸውን ሁሉ እያንበረከኩ፣ የስልጣን መንገዳቸውን እየጠረጉ እዚህ መድረሳቸውንም እንዲሁ፡፡

ተፈሪ ከተፈሪነት ወደ ኃይለስላሴነት ለመሸጋገር ረቂቅ መንገድ ተጉዘዋል፡፡ ክቡር አቶ ብርሃኑ ድንቄ ተፈሪን ሲገልጿቸው፤ “ሀ. ራስ ተፈሪ ሰውን አያምኑም፡፡ ለ. በቀላሉ የሰው ምክር አይከተሉም፡፡ ሐ. ወሬ ከማንም ሰው መስማት ይፈልጋሉ፡፡ መ. እንደሚቀናቸው ካላመኑ በቀር አንድ ነገር ለመጀመር ያመነታሉ፡፡ ሠ. በሴትና በመጠጥ አይታለሉም፡፡ ከዚህም የተነሳ ማንኛውም አይነት አድማ በተነሳባቸው ጊዜ በልዩ ልዩ ዘዴ ለመመከት እንዲችሉ፤

1ኛ. ብዙዎችን የንግስትን የውስጥ አሽከሮች በገንዘብ እየደለሉ ማናቸውንም ሚስጥራዊ ዱለታ የሚከታተል የስለላ ክፍል አደራጁ፡፡

2ኛ. ታማኞች በሆኑ በአባታቸው በልዑል ራስ መኮንን ሹማምንቶች መሪነትና ተመልካችነት ብርቱ የወታደራዊ ድርጅት አቋቋሙ፡፡

3ኛ. ለፕሮፓጋንዳ አያሌ ገንዘብ እያወጡ የተቃዋሚዎቻቸውን ኃይል መከፋፈልና የመሃል ሰፋሪውን፣ የህዝቡንና የካህናቱን ልብ መማረክ ጀመሩ፡፡ በውነትም እቅዳቸው በትክክል ሰራላቸው፡፡ ተቃዋሚዎቻቸው አንድ በአንድ ወደቁ” በማለት ነው፡፡

ንግስተ ነገስት ዘውዲቱ መጋቢት 22 ቀን 1922 ዓ.ም እንዳረፉ፤ ስልጣኑን የተረከቡት ተፈሪ ከሰባት ወር በኋላ ጥቅምት 23 ቀን 1923 ዓ.ም ነበር የስርዓተ-ንግስ በዓላቸው በደማቅ ሁኔታ የተከናወነው፡፡



እነዚያ ሰባት ወራት በኢትዮጵያ ምድር ታይቶ የማይታወቅ የበዓል ማሸብረቂያ ዝግጅት የተካሄደባቸው ናቸው፡፡ ንጉሰነገስቱና እቴጌዋ የሚጓዙበት ሠረገላ ከጀርመን አገር መጣ፡፡ ልብሱ ሁሉ በወርቅና በሐር የተሸቆጠቆጠ ነበር፡፡ የአዲስ አበባ ክርንክስ ቤቶች እንዲወገዱ ተደረገ፡፡ መንገዱ አስፋልት ሆነ፡፡ የከተማ ፖሊሶች ለመጀመሪያ ጊዜ ዘመናዊ ዩኒፎርም ለበሱ፡፡ ቤተ-መንግስቱና አካባቢው በኤሌክትሪክ ብርሃን አሸበረቀ፡፡ ዘውዲቱ ያሰሩት የምኒልክ ሐውልትም በበዓሉ ዋዜማ ነበርና የተተከለው ለአዲስ አበባ ውበት ተጨማሪ ግብዓት ሆኗል፡፡

በበዓሉ ላይም ኢጣሊያን ወክሎ የሶቮይ ልዑል፣ እንግሊዝን ወክሎ የግሎስተር መስፍን የተገኙ ሲሆን፣ ከዚህም ባለፈ ከመላው አውሮፓ ጥሪውን አክብረው የታደሙ ከአሜሪካ፣ ከፈረንሣይ፣ ከጃፓን፣ ከጀርመን፣ ከግሪክ፣ ከሲውዲን፣ ከሆላንድ፣ ከቤልጂየምና ከግብፅ ... በዓሉ 15 ቀን ሲቀረው አዲስ አበባ የገቡ ባለሥልጣናት አገራቸውን ወክለው ተገኝተዋል፡፡ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ጋዜጠኞችም አዲስ አበባን አጥለቅልቀዋት ነበርና የበዓሉን ድምቀት የመላው ዓለም ህዝብ እንዲያውቀው አድርገዋል፡፡ በአጭሩ በአገሪቱ ብቻም ሳይሆን በአህጉሪቱ ታይቶ የማይታወቅ ደማቅ የንግስ በዓል ነበርና ብዙዎችን አስደንቆ አልፏል፡፡

በእለቱ ተፈሪ “ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ስዩመእግዚአብሔር ንጉሠ ነገስት ዘኢትዮጵያ” ተብለው ቅብዓ-መንግስቱን ተቀብተው የወርቅ ዘውዳቸውን የጫኑት በመናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን ነበር፡፡በእለቱም ወ/ሮ መነን የእቴጌነቱን ዘውድ ጭነው፤ ልዑል አስፋወሰንም ለአልጋወራሽነት የሚገባው ወግ ተፈፅሞለት የወርቅ አክሊል ደፉ፡፡ ስርዓቱ ተፈፅሞ ወደታላቁ ቤተ-መንግስት ተመልሰው ዙፋናቸው ላይ ሲቀመጡ 101 ጊዜ መድፍ ተተኩሶ፣ ልዩ ግብዣ ተደርጎ፣ የአዲስ አበባ ከተማም በንጉሠነገስቱና በእቴጌዋ ፎቶግራፍ፣ እንዲሁም በሰንደቅ ዓላማ አጊጣ፣ ለአንድ ሳምንት ያህል የደመቀው የኤሌክትሪክ ብርሃን ሳይጠፋ እንዳሸበረቀች ቆየች፡፡

ተፈሪ በንግስና ስማቸው “ኃይለስላሴ” እየተባሉ መጠራት ጀመሩ፡፡ ቀደም ሲል የጀመሯቸውን ኢትዮጵያን የማዘመን ስራቸውንም ቀጠሉ፡፡

የአፄ ኃይለስላሴን አገዛዝ የሚነቅፉ ምሁራን በርካታ ናቸው፡፡ የሚያደንቋቸውም ቀላል ቁ፣ር የላቸውም፡፡ስለእርሳቸው ታሪክም በርካታ ፀሐፍት የየራሳቸውን እይታ ማዕከል በማድረግ ፅፈዋል፡፡ራሳቸው ጃንሆይም “ህይወቴና የኢትዮጵ,ያ እርምጃ” በሚል ርዕስ በሁለት ቅፅ የተከፈሉ ዳጎስ ዳጎስ ያሉ መፃህፍት ፅፈዋል፡፡

የጃንሆይን የአገዛዝ ዘመን ታሪክ ከተቺዎቻቸውና ከከፊል ተቺዎቻቸው ተነስቶ ቢፃፍ እንኳ፤በተጨባጭ በዘመናቸው የተደረጉ ለውጦችን

የሚያዳፍን ሆኖ አይገኝም፡፡የአድናቂዎቻቸውና የተቺዎቻቸው የገለፃ ልዩነት የሰሩትን ስራ በማግዘፍና በማጣጣል የሚገለፅ መሆኑ እንጂ፤ጃንሆይ ይህችን አገር የማዘመኑን ስራ በፅኑ መሠረት ገንብተው ለትውልድ ማስረከባቸው መስተባበል የማይችል ሐቅ ነው፡፡

በጃንሆይና በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ጉዳዮች በርከት ያሉ መፃህፍት የፃፉት አሜሪካዊ ሐሮልድ ማርከስ ጃንሆይን "የዘመናዊት ኢትዮጵያ አርክቴክት" ይሏቸውና፤ ኢትዮጵያን በስልጣኔ ለማራመድ ስለሚጠቀሙበት ዘዴም ጥንቁቅ ነበሩ ብለው ይገልጿቸዋል፡፡ ስልጣኔ በአጠገቡ አልፎ ለማያውቀው ህዝባቸው ፈጣንና ድንገተኛ ማኅበራዊ ለውጥ ቢፈጠር ለህዝቡ ክፉ ዕጣ እንዳይሆንበት በመስጋታቸውም አረማመዳቸውን ለዘብ እንዳደረጉ ይጠቁማሉ፡፡

በተቃራኒው ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማርያም "Atse Haileselassie and Modern Ethiopia" በተሰኘ ጽሁፋቸው "ጃንሆይ አገር የማዘመን ሂደትን እንደ ውስብስብ መስተጋብር እንዳልተረዱት ..." በመግለጽ፤ ለመንግስታቸው በነበራቸው አመለካከትና ዘመናዊነትን ለማስፋፋት በሚያደርጉት ጥረት መካከልም የማይታረቅ ተቃርኖ ነበረ ይሉናል፡፡ ከተቺዎቻቸው በኩል የሚሰነዘረው ተደጋጋሚ ትንተና "የአፄ ኃይለስላሴ አገር የማዘመን ፕሮጀክት ቁልፍ ፍላጎት ስልጣናቸውን በተደላደለ መሰረት ላይ ለማስቀመጥ ሲሉ የተጓዙበት መንገድ የወለደው ነው" የሚል ነው፡፡

የ"SurviVal and Modernization" ፀሐፊ ፕሮፌሰር መሳይ ከበደ "ዘመናዊነት የአፄ ኃይለስላሴ መንግስት እውነተኛና ትክክለኛ ግብ ነው የሚለውን አስተሳሰብ ወደ ጎን ካላልነው በስተቀር፤ ኢትዮጵያን የማዘመን ፕሮጀክትን ፅንሰ ኀሳባዊ ድቀት ከመሰረቱ ልንረዳው አንችልም" በማለት የዘመን ሂደቱ ድቀት የመጣው በመዋቅራዊ ችግሮች ወይም ተገቢ ያልሆኑ ፖሊሲዎችን በመተግበር እንዳልሆነና፤ ይልቁንም ምንጩ ዘመናዊ ዘዴዎችን በመጠቀም ልማዳዊ ግቦችን ለማሳካት በሚደረጉ ሂደቶች በመጣ ተቃርኖ መሆኑን ያሰምሩበታል፡፡ "በውስጣዊ ለውጥ ያላለፉ ባህላዊ ኃይሎች ማኅበራዊ ለውጥን ከማነሳሳት ይልቅ ዘመናዊ ዘዴዎችን በመጠቀም ስልጣናቸውን ወደማጠናከር ያዘነብላሉ" ሲሉም ያክሉበታል፡፡

ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ "Haylasellasie: From progressive to reactionary" በተሰኘ ጥናታዊ ጽሁፋቸው "ኢትዮጵያ በአውሮፓዊ ቅኝ ገዥዎች ታጥራ ነፃነቷ እንደአዋኪ ቅንጦት በሚታይበት ጊዜ የነበራት አማራጭ ማዕከላዊ መንግስት ማጠናከር ብቻ ነበር፡፡ የኃይለስላሴም ታሪካዊ ሚና የውስጥ ሐብትንና የውጭ እርዳታን አቀናጅቶ ይህን አላማ ማሳካት ሆነ" ይላሉ፡፡



እነዚህንና እነዚህን መሰል ትንታኔዎች ስናይ አፄ ኃይለስላሴ በዘመናቸው ያከናወኗቸው ትልልቅ ስራዎቻቸውን አፍቃሬ ስልጣንነታቸው እንደጋረደባቸው፤ ወይም ስራቸው በበጎ ገፅታው ብቻ እንዳይታይላቸው ማድረጉን በቀላሉ እንረዳለን፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዘውም ጎን ለጎን የሚነሱ የጃንሆይን ስብዕና የሚገልፁ ትንታኔዎች አሉ፡፡ ገሚሱ ደግ፣ ሩህሩህ፣ እያለ ሲገልፃቸው፣ የቀረው ጨካኝ፣ ምህረት የለሽ... እያለ ይፅፉቻዋል፡፡

ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ ሁሉንም የሚያስማማ ሆኖ ያየሁትን ገለፃ ላስከትልና ወደ ዋናው ታሪካቸው እንለፍ፡፡ አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ "ቄሳርና አብዮት" በሚል መጽሐፋቸው ያሰፈሩት ገለፃ ነው፡፡ "በግል ጥላቻ ሳንታወር፣ ያለአንዳች አድልዎ ያለፈውን ድርጊት ለማስታወስና ትርጓሜውን ለመመርመር ጥቂት ጊዜ ካገኘን፣ አፄ ኃይለስላሴ ብዙ ገጾች ያሏቸው አስደናቂ ሰው መሆናቸውን ለመገንዘብ አያስቸግረንም፡፡ "ኮንሰርቫቲቭ" ናቸው ስንላቸው "ሊበራል" የሆነ ስራ ሲሰሩ ይገኛሉ፡፡ ንቅዝ ናቸው ስንል ፍትህ ለመስጠት ሲሞክሩ ይታያሉ፡፡ ጨካኝ ሲሆኑ፤ ደግሞ የርህራሄ ስራ ከመፈፀም አያቋርጡም፡፡ በቀለኛ ናቸው ሲሏቸው ምህረት ያደርጋሉ፡፡ ይህ ቅያጤ (combination) በምሳሌና በማስረጃ የሚደገፍ "ፓራዶክስ" ወይም ሊታመን የማይችል እውነተኛ ነገር ነው፡፡" ይሉናል የዓይን እማኙ፡፡ አፄ ኃይለስላሴ ንጉሰነገስት እንደሆኑ የፈፀሙት የመጀመሪያ ተግባር በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን ሕገ-መንግስት ማፅደቅ ነበር፡፡ ከዚሁ ተግባራቸው ተነስተን እንቀጥላለን፡፡

## የጃንሆይ ሕገ-መንግስት፤ ፓርላማና ምርጫ

አይነትና አደረጃጀቱ፣ ዘመኑና ሁኔታዎች ይለያዩ እንጂ አፄ ኃይለስላሴ የመሰረቱት መንግስት አፄ ቴዎድሮስ ሞክረው ያቃታቸውን አይነት ነው፡፡ ዘመናዊነትን የተላበሰው አስተዳደጋቸውም የስልጡን አስተሳሰብ ባለቤት ያደረጋቸው ይመስላል፡፡

ኢትዮጵያን በአንድ የዘውድ ስርዓት ስር አድርጎ ለመግዛት የቴዎድሮስ መሻት ነበር፡፡ የኃይለስላሴም ተመሣሣይ ነው፡፡ ነገር ግን የተጠቀሙት ዘዴ ለየቅል ነው፡፡ ኃይልና ብልሃት፡፡

አፄ ኃይለስላሴ የንጉሠ ነገስትነት ስልጣኑን ስለያዙ ብቻ "እፎይ" ተብሎ እንደማይኖር ገብቷቸዋል፡፡ በግልፅ ስናየው እንደመጣነው ያለፉት ነገስታት ከነገሱበት ጊዜ ጀምሮ ዙፋን ላይ ተቀምጠው ሳይሆን "ኮርቻ"ላይ ተቀምጠው ነበር የሚገዙት ለማለት ይቻላል፡፡ ሁሌ ዘመቻ ነው! እገሌ የተባለው መሳፍንት በጎንደር ተነሳ ይባላል፤ ነገስታት ወደ ጎንደር ጋልበው በኃይል አሣምነው መንገድ እንደጀመሩ፤ የወሎው ባላባት ሸፈተ ይባላል፡፡ በዚያው ወደ ወሎ፣ ቀጥሎ ሲዳሞ ... ወዘተ፡፡ ኃይል ሲጠፋ ጋብቻ እንዳማራጭ ይወሰዳል፡፡

አፄ ኃይለስላሴ የተጠቀሱትን መፍትሔዎች እንደ ተጨማሪ እርምጃ እንጂ እንደ ዋናና ዘላቂ ስልት አድርገው አልቀጠሉም፡፡ በአሳማኝ ዘዴ እና መሳፍንቱ፣ መኳንንቱ፣ ባላባቱም ሆኑ ሚንስትሮች እንዲሁም ሌላው አካል በጣም የማይደነግጥበት፣ በጣም የማይደሰትበት፣ የተለሳለሰ ሕግ አቁመው ንግስናቸውን ሕጋዊ መሠረት እንዲኖረው ማድረግ ነበረባቸው፡፡ ያ ካልሆነ እንዴትም ሆኖ ተረጋግቶ መግዛት፣ ማስተዳደርም ሆነ አገር ማሳደግና ህዝብ ማሰልጠን አይቻልም፡፡ በአጠቃላይ የተዘበራረቀው ነገር ሁሉ መልክ መያዝ ነበረበት፡፡ በዚህ ደግሞ ተጠቃሚው ራሳቸው ብቻ ሳይሆኑ ኢትዮጵያም ጭምር ናት፡፡

እናም የንጉሠነገስትነት ስልጣኑን ከያዙ ከወራት በኋላ በዙሪያቸው ከነበሩ ምሁራን ጋር ተባብረው ሐምሌ 9 ቀን 1923 ዓ.ም በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን ዘመናዊ ሕገ-መንግስት አፀደቁ፡፡

በዚያን ጊዜ እንዲህ አሉ፤ "... ሕግ ለሰው ከሁሉ የበለጠ የሚጠቅም መሆኑን ማንም አይስተውም፡፡ መከበርም መጠቀምም የሚገኙት በሕግ መተካከል የተነሳ ነው፡፡ መዋረድም መጎዳትም የሚመጡት በሕግ መጓደል የተነሳ ነው፡፡ ግፍ እና በደልም የሚበዙት ሕግ ባለመቆሙ ነው..."

የ1923ቱ ሕገ-መንግስት ረቂቁ ከመፅደቁ በፊት አስፈላጊው ክርክር ተካሂዶበታል፡፡ በተለይ በመሳፍንቱና በመኳንንቱ መካከል ጠንከር ያለ የጎሳብ ግጭት የተነሳው በርስትና በጉልት ጉዳይ ነበር፡፡

የመሳፍንቱ ጎሳብ ኢትዮጵያ በትልልቅ አውራጃ ተከፍላ የመሳፍንቱ የበላይነት እንዳለ ሆኖ ግዛቱም የራሳቸውና ለልጅ ልጅም የሚያልፍ፤ በጥቅሉ እንደቀድሞው እንዲቀጥል፤ ነገር ግን መሳፍንቱ በንጉሠ ነገስቱና በመንግስቱ ላይ ወንጀል ሰርተው ከተመሰከረባቸው ክርስታቸው እንዲነቀሉ፤ በተረፈ እንደቀድሞው በየውስጣቸው ያለው የትናንሽ አውራጃ ባላባት ለእነርሱው እዩገበረ እንዲኖር የሚል ነበር፡፡ ወንጀል ሰርተው ቢገኙ እንኳ ሌላ መሳፍንት እንዲተካ መሆኑ ነው፡፡ መኳንንቱና ሚኒስትሮች ግን "ኢትዮጵያ በትልልቅ አውራጃ ተከፍላ፣ ለመሳፍንቱና ለባላባቶች ለልጅ ልጅ የሚያልፍ ርስት ሆና ከተሰጠች ወደፊት የሚነሳው ትውልድ እንደምን ሊሆን ነው? ሹመት በዘር ይሁን ከተባለ ቢማርስ ቢያገለግልስ፣ ሹመትና ግዛት ካላገኘ ኢትዮጵያ አገሬ ናት ለማለት እንደምን ይችላል?" በማለት ተከራከሩ፡፡ ሲቀጥሉም "... ስለዚህ አሁን ያሉት መሳፍንትና ባለባቶች ጥፋት ካልተገኘባቸው ባገረ ገዥነታቸው ይቆዩ፡፡ ጥፋት ተገኝቶባቸው ቢሻሩ፣ ወይም ቢሞቱ ግን በግዛታቸው ላይ እውቀትና ችሎታ ያለው ማንም ኢትዮጵያዊ እንዲሾሙበት ይሁን..." በማለት ተሟገቱ፡፡ ከመሳፍንት ወገን ራስ እምሩ ከሚንስትሮችና ከመኳንንቱ ጎን ሆነው ጎሳባቸውን ደገፉ፡፡ ብዙ



ተከራከሩና በመጨረሻ አፄ ኃይለስላሴ አስታራቂ ጎሳብ አቅርበው አስማሟቸው፡፡

"... ንጉሠነገስቱ ለመሳፍንቱም ቢሆን ለሌሎችም የመንግስት አገልጋዮች ቢሆን ርስትና ጉልት ለመትከል ይችላል የሚል አንድ ክፍል /አንቀፅ/ በሕገ-መንግስቱ ይፃፍና ወደፊት አገልግሎታቸው እየታየ እንደሚያስፈልግ ይደረጋል እንጂ የፊውዳል መንግስት በዓለም ላይ መቅረቱን እያወቅን አሁን እንደገና ያንኑ አፅንተን በሕገ-መንግስት መፃፍ፤ ወይም ያለ ሕገ-መንግስት መግዛት የማይገባ መሆኑን ለመሳፍንቱ አስረድተን ተጣርቶ ተፅፎ እንዲፈረም ይሁን በማለት ነገሩን ቆረጥን...፡፡"

የንጉሱ አስታራቂ አንቀፅ ተካቶ ፀደቀ፡፡ የመሳፍንቱ ስልጣን እንዳለ ሆኖ፤ ነገር ግን እንደአስፈላጊነቱ በንጉሠነገስቱ ይሁንታ ማንም ሊሾም፣ ማንም ሊሻር፣ ሁሉም ስራው እየታዩ እንዳስፈላጊነቱ ንጉሡ ያመኑበትን ሊያደርጉ .... አይነት ሕግ መሆኑ ነው፡፡ ከንጉሡ ጋር ሕገ-መንግስቱን በፊርማቸው ያፀደቁት ጳጳሳት፣ መሳፍንት፣ መኳንንትና ሚንስትሮች የነበሩ ሲሆን፤ ቁጥራቸው 24 ነው፡፡ ብዙ አንቀጾችን መዘርዘር አያስፈልግም፡፡ ነገር ግን ንጉሡን የሚያስተቸውን ጠቅሶ ለማለፍ ሦስቱን ብቻ እንይላቸው፡፡

አንቀፅ 2፤ "የኢትዮጵያ መሬትም፣ ህዝብም፣ ሕጉም" በጠቅላላው የንጉሠ ነገስት ነው፡፡

አንቀፅ 3፤ "የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገስት ከኢየሩሳሌም ንጉስ ከሰለሞንና ንግስተ ሣባ ከተባለችው ከኢትዮጵያ ንግስት ከተወለደው ከቀዳማዊ ምኒልክ ነገድ ተያይዞ ከመጣው ከንጉስ ሣህለስላሴ ዘር ከተወለደው ከቀዳማዊ ኃይለስላሴ ትውልድ እንዳይወጣ በሕግ ተወስኗል፡፡

አንቀፅ 5፤ "ንጉሠነገስቱ የነጋሲ ዘር በመሆኑና ቅብዓ-መንግስት በመቀባቱ ክብሩ የማይቀነስ፣ ማዕረጉ የማይገሰስ፣ ኃይሉ የማይደፈር ሆኖ በቆየውም ልማድ፣ ባዲሱም ሕግ በሚገባው ክብር ሁሉ ይከበራል፡፡ ክብሩንም ለመንካት በድፍረት የተነሳ ሰው በሕግ እንዲቀጣ ተወስኗል፡፡" ... እያለ ይቀጥላል፡፡

እረፍ ክተት! ማንም እንደልቡ እየተነሳ ባመፀ ቁጥር ስንቱ በጦርነት ይለቅ?

ኢትዮጵያስ ለምን ቆማ ትቅር?

የ1923ቱ ሕገ-መንግስት በውስጡ ሰፋና ዘርዘር ያሉ አንቀጾች ያሉት ነው፡፡ ንጉሡ የራሳቸውን ስልጣን ብቻ ሳይሆን ህዝቡም፣ሹማምንቱም ሁሉም የማይጎዱበት ሚዛናዊ ሕገ-መንግስት

እንዲሆን ጥረዋል:: የተጠቀሱት አንቀጾችም ቢሆኑ ለዘመናት የኖሩ ናቸው::ንጉሡ የነበረውን ባህል ፃፉት:: ፅፈውም ሕግ አደረጉት::

በርካታ ምሁራን የተጠቀሱትን አንቀጾች እየጠቀሱ ሕገ-መንግስቱን ይተቹታል::በእውነቱ ያን ሕገ-መንግስት ለመተቸት የሚያስችል አንዳችም ታሪካዊ መነሻ በኢትዮጵያ ምድር ኖሮ አያውቅም::እርግጥ ነው በሕገ-መንግስቱ ንጉሠነገስቱ ለመሾምና ለመሻር፣ፍርድ ለመስጠት፣ጦርነት ለማወጅና ለማቆም፣ መሬትና የክብር ማዕረግ ለመስጠት ስልጣን አላቸው::ማንኛውም መሳፍንት ግን በግሉ እንዳለፈው ዘመን ከውጭ አገር መንግስታት ጋር መዋዋል፣መሳሪያ፣ ሽልማትና ማናቸውንም አይነት ጥቅማ ጥቅም መቀበል አይችልም::በአጠቃላይ እያንዳንዱ ነገር ከንጉሠነገስቱ የምትመነጭ ሆና መሳፍንቱን በቁጥጥር ስር ማድረግ ተችሏል::

"የመሳፍንቱ ስልጣን እንዳለ ነው፤ ነገር ግን ለሕግ መገዛት መልመድ፣ መቻል አለባቸው" በሚለውን እቅድ ብቻ እንኳ በበጎ ጎኑ ማየት ይቻላል:: "ስልጣናቸውን ለማጥበቅ" ሲሉ እንጂ አንዳችም ብሔራዊ ፋይዳ አልነበረውም ይባላል:: አፄ ኃይለስላሴ ስልጣናቸው ላይ አልተኙም:: ሠርተውበታል:: ስልጣን በማፍቀር ኃይለስላሴ እንደማንኛውም አፍሪካዊ መሪ ተወዳዳሪ እንዳልነበራቸው ግልፅ ነው:: ለዚህ ርህራሄም የላቸውም:: ታሪካቸውን ከልብ ስንመረምር ግን "ለኢትዮጵያ የማስፈልጋት እኔ ነኝ" ያሉ ይመስለናል::

ከሁሉም በላይ ደግሞ የ1923ቱ ሕገ-መንግስት ምን አይነት ይዘት ቢኖረው ይሻል ነበር? ብለን መጠየቅ አለብን:: መቸም ... መሳፍንቱን፣ መኳንንቱን በአንድ ጊዜ ስልጣናቸውን ነጣጥቀው እጅግ ዘመናዊ የሆነውን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲዘረጉና ራሳቸውን አደጋ ላይ እንዲጥሉ አሁን ላይ ሆነን አንመክራቸውም:: ያን ሁሉ ወግና ባህል በአንዴ መናድ እብደት ይሆናል::

የሆነ ሆኖ የ1923ቱ ሕገ-መንግስት መሳፍንቱ፣ መኳንንቱና ሚኒስትሮች ጥቅማችን ተነካ ብለው እንዳያጉረመርሙ አድርጎ ፀጥ ለማሰኘት ሲባል ፊውዳላዊ አካሄዱ እንዲቀጥል ግድ ሲሆን፤ ተራው ማኅበረሰብም እውቀትና ችሎታ እስካለው ድረስ የሚሾምበትን ሁኔታ አመቻችቷል::

አፄ ኃይለስላሴ "በዓለም ላይ ፊውዳሊዝም መቅረቱን እያወቅን..." ስላሉ አገዛዛቸው ፊውዳል አልነበረም ለማለት አያስችልም:: ሹማምንቱ የርስትና ጉልት ተተካዮች ስለሆኑም አገዛዛቸው ፊውዳል ነበር ለማለት አያስችልም::

አሁንም በርካታ ምሁራን አፄ ኃይለስላሴንም ሆነ አገዛዛቸውን ሙሉ በሙሉ "ፊውዳል" የሚል መጠሪያ ሰጥተውታል:: (አብዮቱን



ለማግነን ሲባልም ብዙ ተብሏል::) የፊውዳል ትርጓሜ የቀጥቃጭ ልጅ ቀጥቃጭ፣ የሸማኔ ልጅ ሸማኔ፣ የገበሬ ልጅ ገበሬ፣ የገባር ልጅ ገባር፣ የባላባት ልጅ ባላባት ... ነው:: ይሄኛው የፊውዳል ትርጓሜ በአፄ ኃይለስላሴ አጠገብ አልፎ አያውቅም:: ሹማምንቱ በርስትነት የሚይዙት ሰፊ መሬት ቀጥሎ መቆየቱ "ፊውዳላዊ" ካልተባለ በቀር:: እሱም ቢሆን ተራ ሰው ከተሾመ ከሹመቱ ጋር አብሮ ይሰጠዋል:: የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ደግሞ ለጊዜው የነበረው ሐብት መሬት ነው:: ጥቅማ ጥቅሙም በመሬት ነው:: በአጭሩ የኃይለስላሴ ዘመን ፊውዳል አልነበረም:: ከፊል ፊውዳል፣ ከፊል ካፒታሊዝም ነው:: እንደዛሬው:: መሬቱም ህዝቡም የንጉሠ ነገስቱ ነው...::

አፄ ኃይለስላሴን በንግስት ዘውዲቱ ዘመን በወግ አጥባቂዎቹ ጥርስ ውስጥ ያስገባቸው አንዱ ምክንያት ፊውዳል አለመሆናቸው ነው:: አሁን ግን ሕገ-መንግስቱም ይፈቅዳልና እንደልባቸው ሁሉንም አይነት የኅብረተሰብ ክፍል "ምን ሞያ አለው?" እያሉ ማሳተፍ የሚችሉበትን ሁኔታ አረጋግጠዋል::

ከእርሳቸው በፊት በነበረው ዘመን ግን ጥያቄው "የሰው ልጅ ነው ወይ?" የሚል የዘር ሐረግን ማዕከል ያደረገ ነበር:: የ1923ቱ ሕገ-መንግስት ኢትዮጵያ በውስጧ ሁከት የሌለባትና በሕገ-መንግስት የምትተዳደር አገር ተብላ እንድትታይ፣ ህዝቡ አዲስ የአስተዳደር ስርዓት እንዲለምድ መሠረት በመጣል፣ የመሳፍንቱን ልቅ ስልጣን ለመገደብ፣ ፊውዳሊዝምን በከፊል ቆርሶ ለመጣል፣ ምሁራንን እንደልብ ለማሳተፍ በማስቻል ... ከፍተኛ ሚና ነበረው:: አንዳንድ ምሁራን ዛሬ ላይ ሆነው እንደሚያጣጥሉት አይደለም::

ኢትዮጵያ በሕገ-መንግስቱ መሠረት የሁለት ፓርላማ ባለቤት ሆነች:: አንደኛው /የላእላይ ፓርላማው/ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት የሚል ስያሜ ሲሰጠው ሁለተኛው ፓርላማ ደግሞ የሕግ መምሪያ ምክር ቤት ተሰኘ::

ሁለት ምክር ቤቶች ያሉት ፓርላማ የአባላቱ አመራረጥ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላት መሳፍንቱና መኳንንቱ ሲሆኑ፤ እነሱም በቀጥታ በንጉሠነገስቱ የሚመረጡ ናቸው:: ይህም ሲባል መንግስታቸውን ብዙ ካገለገሉና መሳፍንት ካልሆኑ ተራ ሰዎችም ጭምር የተውጣጡ ተመራጮች ይሳተፉበታል::

የሕግ መምሪያ ምክር ቤት ደግሞ "ህዝቡ ለቀጥተኛ ፖለቲካዊ ተሳትፎ /ምርጫ/ ገና አልበቃም" በሚል መነሻ መሳፍንቱና መኳንንቱ፣ እንዲሁም ሌሎች ሹማምንት ያመኑባቸውን የበታች ሹማምንት የህዝብ እንደራሴዎች እንዲሆኑ የመምረጥ ስልጣን ተሰጣቸው::

እንደራሴዎች ከሚመረጡበት መስፈርት አንዱም "ሀብትና ንብረት ያላቸው" የሚል ተጠያቂነትን ማዕከል ያደረገ ነበር፡፡ ምክር ቤቶቹ "ወደፊት አስፈላጊ ሲሆን የሚጨመሩ" ተብሎ 56 አባላት እንዲኖሯቸው ተደረገ፡፡ሂደቱ በግልፅ እንደሚያሳየው ሕግ አውጭው አካልና ሕግ አስፈፃሚው አካል የተያያዙ እንጂ ለየቅል ሆነው የሚጓዙበት ሁኔታ የለም፡፡ለዚህም ነው "ንጉሡ ፓርላማ እንዲኖር ፈቅደው መልሰው በራሳቸው ቁጥጥር ስር አደረጉት" ተብለው የሚወቀሱት፡፡አሁንም በተመሳሳይ ለመንቀፍ የሚያስችል "ትክክለኛ" ሞራል እጃችን እስኪገባ ድረስ፤ወይም ማነፃፀሪያውን በአገራችን እስክናገኝ ድረስ በዚህ ጽሁፍ ከመንቀፍ ተቆጥበን እንቀጥላለን፡፡እንደዚያ መሆን እንዳልነበረበት ከታወቀ አልፎ ሄዶ ሙታንን መውቀሱ አህያውን ፈርቶ ዳውላውን ስለሚሆን እንጂ ወቀሳው ግን ተገቢ ነው፡፡

የመጀመሪያውን ፓርላማና ሕገ-መንግስቱን በሚመለከት የሕገ-መንግስቱ "ዋና" አርቃቂ በጅሮንድ ተክለሐዋርያት ነበሩና ከብዙ ዓመታት በኋላ ትዝታቸውን በቃለመጠይቅ ሲያካፍሉ፤

"በዚያን ወቅት የእኛ ፍላጎት የፓርላማ አባላት በደንብ እንዲሰሩ ወይ ዘመናዊ ሕግ እንዲያወጡ አልነበረም፡፡ እኛ የፈለግነው ህዝቡ መንግስት የሚያወጣውን ሕግ እንዲቀበልልን ነው፡፡ ይህንንም ተቀባይነት ለማግኘት የሚያመቸው መሣፍንቱ መጀመሪያ ተነጋግረውበት ከተቀበሉት ነው፡፡ /በሌላ አነጋገር/ እኛ የፈለግነው የኢትዮጵያን ሕዝብ በመሳፍንቱ አማካይነት ለማነጋገር ነው፡፡ ስለዚህ መሳፍንቱን ለአቅዳችንና ለዓላማችን መሳሪያ አደረግናቸው ማለት ይቻላል" ብለዋል፡፡

መሳፍንቱና መኳንንቱ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤትና የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባል ሆነው እንዲሰሩ መደረጋቸው እንዳለ ሆኖ፤ ነገር ግን የሚሾሙት መሳፍንትና መኳንንት ብቻ እንዳልነበሩ በቀላሉ መረዳት እንችላለን፡፡ ንጉሡ ሕገ-መንግስቱ ባጎናፀፋቸው የመምረጥ መብት ተጠቅመው የምክርቤቶቹ ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንት እንዲሆኑ የመረጧቸው ከመሳፍንት ወገን ያልሆኑና ቀደም ካለው ጊዜ ጀምሮ ታማኝ ሆነው የመጡትን ነው፡፡ ለምሳሌ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝደንት ሆነው የተሾሙት ቢትወደድ ወልደፃድቅ ጎሹና ብላቴን ጌታ ሣህሌ ፀዳሉ ነበሩ፡፡ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ ይህን ጉዳይ፤ "እነዚህ ሹማምንት እንደነራስ ካሣ ኃይሉ፣ ራስ ኃይሉ ተክለሐይማኖትና፣ ራስ ስዩም መንገሻን የመሳሰሉ መሳፍንት እንዲዳኙ መደረጋቸው መሳፍንቱ ምን ያህል በንጉሡነገስቱ መዳፍ ስር እንደወደቁ ጉልህ ማስረጃ ነው" ይሉታል፡፡

በዚህ መልኩ ጥቅምት 23 ቀን 1924 ዓ.ም ምክር ቤቶች በይፋ ስራ ጀመሩ፡፡ፓርላማው ሰባት ቋሚ ኮሚቴዎችን አደራጅቶ መንቀሳቀስ



ጀመረ፡፡ ቋሚ ኮሚቴዎቹ በቅደም ተከተል የሕግ ስራ ኮሚቴ፣ የውጭ ጉደይ ቋሚ ኮሚቴ፣ የመከላከያ ኮሚቴ፤የገንዘብ ኮሚቴ፤የበጀት ኮሚቴ፣ የህዝብ እድገት ኮሚቴ፤እንዲሁም የኮሚቴዎችን አባላት የሚመርጥ አንድ መራጭ ኮሚቴ ተብለው ተዋቀሩ፡፡

ሰባት አባላት ያሉት የሕግ ስራ ኮሚቴ የሕግ ረቂቆች ለምክር ቤቱ ከመቅረባቸው አስቀድሞ የሕግ ቅርፅ ይዘው መቅረባቸውን የሚያረጋግጥ ተግባር ያከናውናል፡፡ የውጭ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ የሚላኩለት ስራዎች ኢትዮጵያ የምታደርጋቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና የተባበሩት መንግስታት የስምምነት ግዴታዎች ናቸው፡፡
መከላከያን የሚመለከቱ ጉዳዮች የሚላኩለት የመከላከያ ኮሚቴ ነው፡፡የአገርን ኢኮኖሚ በማስፋፋት ረገድ ትልቁን ድርሻ የሚወጣው የገንዘብ ኮሚቴ ነው፡፡ የህዝብ እድገት ኮሚቴም ትምህርትን፣ ጤና ጥበቃን፣ እርሻን የሚመለከቱ ጉዳዮች ይቀርቡለታል፡፡መራጭ ኮሚቴው ደግሞ የቋሚ ኮሚቴ ዕጩዎችን በመምረጥ ለፓርላማው ያቀርባል፡፡ይህ የፓርላማ አሰራር እስከተሻሻለው ሕገ-መንግስት ድረስ ሲሰራበት ቆይቷል፡፡ሕገ-መንግስቱ የተሻሻለው በ1948 ዓ.ም ቢሆንም፤ በዚህ ጽሁፍ ዘመኑን ተከትለን ሄደን ከምናገኘው ከወዲሁ አጠቃለነው ማለፉ ይመረጣል፡፡

የተሻሻለው ሕገ-መንግስት የተሻለ የመምረጥ መብትን ለኅብረተሰቡ ሰጥቷል፡፡ በተሻሻለው ሕገ-መንግስት መሠረት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ 18 ዓመት ከሞላው የመምረጥ መብት ሲኖረው ለመመረጥ ደግሞ ከ21 ዓመት በላይ ሊሆን ይገባል፡፡ ማንበብና መፃፍ መቻል ግድ ነበር፡፡ የሚመረጡት አባላት የሕግ መምሪያ ምክር ቤት ይገባሉ፡፡ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤቱ ግን አባላቱ እንደቀድሞው በንጉሡነገስቱ የሚመረጡ ናቸው፡፡

የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ከንጉሱ በታች እና ከሕግ መምሪያ በላይ ሲሆን፤ ከንጉሡ በታች ሕግ የማፅደቅ ወይም ያለማፅደቅ ስልጣን ነበረው፡፡ በ1948ቱ ሕገ-መንግስትም ሆነ በ1923ቱ ንጉሡ ምክርቤቶችን መበተንና ምክር ቤቱ የሚያወጣቸውን ሕጎች መሻር የሚያስችላቸው አንቀጾች የተካተቱበት ነበር፡፡ የምክር ቤቱ ስልጣን የሚመነጨው ከንጉሡነገስቱ መሆኑም ግልፅ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንዳየነውም ሕጎች የሚፀድቁት የሕግ መምሪያው ምክር ቤት መክሮበትና ሕግ መወሰኛው ምክር ቤት ወዶ ሲቀበለው ነው፡፡ ያም ሆኖ የመጨረሻው የመወሰን ስልጣን የንጉሡ ነገስቱ እንደሆነ ግልፅ ድንጋጌ አለ፡፡ የምክር ቤቶቹ አባላት ሚኒስትሮች የሚያቀርቡላቸውን ጉዳዮች እየተቀበሉ ይመክራሉ፡፡ ምክርቤቶቹ በሚኒስትሮች ምርጫ ውስጥ ግን ጣልቃ አይገቡም፡፡ በ1948ቱ ህዝቡ እንደራሴውን በቀጥታ መምረጥ መቻሉ ደግሞ አንድ

ትልቅ ጅማሮ ነው፡፡ እነዚህ እንደራሴዎች በፊት በመሳፍንቱ ይሁንታ የሚመረጡ የነበሩ ሲሆን፤ ከ1948 ዓ.ም በኋላ ግን በህዝብ መመረጥ ጀምረዋል፡፡

ህዝባዊ ምርጫ በ1950 ዓ.ም ከተጀመረ በኋላም ለ5ዙር በየ4 ዓመቱ ምርጫ ተካሂዷል፡፡ተመራጮች እንደዛሬው አይሁን እንጂ ቅስቀሳ ያደርጉ ነበር፤ የመወዳደሪያ ምልክትም ነበራቸው፡፡ከተሻሻለው ሕገ-መንግስት ጋር ተያይዞም ሰባት የነበሩት የስራ ክፍፍሎች ወደ 14 አድገዋል፡፡ ከየግዛቱ ተመርጠው የሚመጡ እንደራሴዎችም ቀደም ሲል አነስተኛ ቁጥር ይኑራቸው እንጂ ወደኋላ 250 ደርሰዋል፡፡ደሞዙ በ300 ብር ተጀምሮ በየጊዜው እያደገ 1ሺ ብር ደርሶ ነበር፡፡ በርከት ያሉ ሴት ተመራጮች የፓርላማው አባል ነበሩ፡፡ከሰኞ እስከ አርብ ፓርላማው ስራ ላይ ነው፡፡ ሰኔ 1 ለእረፍት ይዘጋል፤ ጥቅምት 23 ስራ ይጀምራል፡፡ ንጉሡ በዓመት ሁለት ጊዜ ብቻ ይገኛሉ፡፡ በመዝጊያና በመክፈቻ እለት ብቻ ንግግር ያደርጋሉ፡፡
የመወሰኛ ምክር ቤቱ አባላት ብዛትም 175 ደርሶ ነበር፡፡ በአጠቃላይ ይዘትና ቅርፁ ከአሁኑ ብዙ የተለዩ እንዳልነበር በህይወት ያሉ የቀድሞው አባላት ይገልፃሉ፡፡

አፄ ኃይለስላሴ ምክር ቤቶችን ካቋቋሙና ሕገ-መንግስቱን ካፀደቁ በኋላ ግን፤ ብዙሃኑ ተስማምቶ ለሕገ-መንግስቱ ተገዥነቱን ያረጋግጥ እንጂ፣ጥቂቶች እውቅና ነፍገው ነበር፡፡

እንግዲህ በዚህ ሕገ-መንግስት መሠረት በርካታ የአስተዳደር ለውጦች የተፈጠሩ ሲሆን፤ ከእነዚህም ውስጥ የርስት ውርስ መብት አንዱ ነው፡፡ በዚህም ንጉሠ ነገስቱ ይሾማል እንጂ ያባቱ ግዛት የሚባል ነገር የለም፡፡

ይህን ህግ በመቃወም የጎጃሙ የንጉስ ተክለሐይማኖት ልጅ ራስ ኃይሉ ተክለሐይማኖት የጎጃም ገዢ ሆኖ ለ30 ዓመታት ያህል የቆየ ነበርና አልገዛም አለ፡፡ ይባስ ብሎ ልጅ እያሡ ታስሮ ከነበረበት ከ"ፍቼ" እስር ቤት ሊያስመልጥ ሲል ተገኝቶ ለፍርድ ቀርቦ ሞት ቢፈረድበትም ንጉሡ ሀብቱ ተወርሶ እንዲታሰር አደረጉ፡፡ ጎጃም ላይ የቅርብ ዘመዳቸውን ራስ እምሩ ኃይለስላሴን በ1924 ዓ.ም ሾሙ፡፡ ከዚያም አፄ ኃይለስላሴ ፊታቸውን ወደጅማ በማዞር፤ በቀዳማዊ አባጅፋርና በዳግማዊ አባጅፋር ጊዜ ለአፄ ምኒልክ በሰላም ከገበረች ጊዜ ጀምሮ ነፃ የውስጥ አስተዳደር የነበራት ጅማ በማእከላዊው መንግስት ቁጥጥር ስር ሆነች፡፡ ሌሎችም በተመሳሳይ ተጠቀለሉ፡፡

በቀጥተኛው አስተደደራዊ ቁጥጥር ስር ማዋል ከባድ ሆኖ የታየው የትግራይ ግዛት ብቻ ነበርና፤ የአፄ ዮሐንስ የልጅ ልጅ የሆኑት ራስ ስዩም መንገሻና ራስ ጉግሳ አርአያ ምዕራብና ምስራቅ ትግራይን ያስተዳድሩ



ስለነበር እነሱን በቅርብ ዘመድ ጋብቻ ጠልፈው ጠቀለሉ፡፡ መንግስት በየግዛቱ ላይ የበላይነቱ እያየለ ሲሄድ ምንም እንኳ የቀድሞው ባህሪውን የለወጠ ባይመስልም ንጉሠ ነገስቱ ግን በግዛቱ ብቻ ሳይሆን በሠራዊቱ ላይም ማዘዝ የሚችሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

ባየነው መልኩ የአፄ ኃይለስላሴ ስልጣን በጽኑ መሠረት የተገነባ መሰለ፡፡ የኢትዮጵያ የዘመናዊነት ጉዞም ፍጥነቱን ጨመረ፡፡ ታማኝ ምሁራንም በተቋቋሙት ዘመናዊ የመንግስት ድርጅቶችና መስሪያ ቤቶች እየተመደቡ በሕግ በተሰጣቸው ስልጣን ዘመናዊ አሰራራቸውን ገፋበት፡፡ ቀደም ባለው ጊዜ ከውጭ አገር የመጡ አማካሪዎችና የልዩ ልዩ ሙያ ባለቤቶች የተባሉትም አንዳንድ አገር የማዘመን ስራ ለመስራት እንቅስቃሴ ጀመሩ፡፡ ለምሳሌ ዘመናዊ ጦር የማሰልጠንና ሌሎች ከዚህ ቀደም ያልነበሩ ስራዎች ተጀመሩ፡፡ የተጀመሩትም ተጠናክረው ቀጠሉ፡፡

በጥቅሉ ከአልጋወራሽነታቸው ዘመን ጀምሮ የታቀዱ ስራዎች ሁሉም መልክ እንዲኖራቸው ሆነ፡፡ ሕገ-መንግስቱን መሠረት በማድረግም የመንግስትን የገቢና የወጪ ስርዓት ቅርፅ እንዲይዝ አደረጉት፡፡ ለቤተ-መንግስት፣ ለቤተ-ክርስቲያን፣ ለጦርና ለጉልተኛ ሹማምንት የገባሪዎች የጉልበት አገልግሎት፤ የምግብ ግብር፣ የምርት ስፍር፣ የአስራት መዋጮ የመንግስት የግብርና እና የበጀት መሰረቶች ነበሩ፡፡ ከሕገ-መንግስቱ መፅደቅ በኋላ ግን የመንግስት ገቢ ለመጀመሪያ ጊዜ በገንዘብ ግብር ላይ እንዲመሠረት ደነገጉ፡፡ ምንም እንኳ ወደፊት እንደምናገኘው ዘመናዊ የሆነ የበጀት ስርዓት ነበር ባይባልም፤ መሠረቱ የተጣለው ከወዲሁ ነበር፡፡ እናም የ1923ቱ ሕገ-መንግስት ለዘመናዊት ኢትዮጵያ ጅምር እንቅስቃሴ ሰፊ ሚና ነበረው፡፡ አገር የማሰልጠን ሂደቱ በቀጠለበት ሁኔታ ግን ብዙ ሳይቆይ ከ4 ዓመት በኋላ ወረራው ተከተለ፡፡
ከጣሊያን ወረራ እስከ ነፃነት

የኢጣሊያ ዓድዋ ላይ መሸነፍ የሱዋ ብቻ ሳይሆን የመላው ቅኝ ገዥ ኃይል ሽንፈት ነበርና፤ በቂ ዝግጅት ተደርጎ ሽንፈቱ በድል መለወጥ ነበረበት፡፡ ይህ የሀያላኑ ግልፅ መሻት ነው፡፡ አውሮፓውያን በጥቁር ህዝቦች ድል ከተደረጉ የሌላውም አገር ጥቁር ለነፃነቱ መነሳቱ አይቀሬ ነውና ሽንፈት ብቻ ሳይሆን ስጋትም ጭምር ነበር፡፡

በመሆኑም ዳግም ወረራው እንደማይቀር አሳምረው ያውቁታል፡፡ ኢጣሊያ ያቦካችውን እራሷ መጋገር እንዳለባትም እንዲሁ፡፡ ስለዚህ ፈረንሣይና እንግሊዝ የኢጣሊያ መንግስት ኢትዮጵያን ዳግም ወርሮ ሽንፈቱን በድል እንዲለውጥ ይፈልጋሉና ከፍተኛ ግፊትና ማበረታታት ቢያሳዩ አይደንቅም፡፡

የዳግም ወረራው ጥንስስ ከዓድዋው ድል ማግስት የጀመረ ነው፡፡ ጣልያኖች ከአድዋው ሽንፈታቸው በኋላ ከአፄ ምኒልክ ጋር ወዳያው ነበር

የድንበር ስምምነት ያደረጉት፡፡ በዚያው ጊዜም ቺኮዲኮላን የተባለው ቆንሲል ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ስላለው ቀጥሏል፡፡ በጥቅምት ወር 1898 ዓ.ም ፈረንሣይ፣እንግሊዝና ኢጣሊያ የተፈራረሙት ውልም ከኢኮኖሚያዊ ጥቅም ጋር ብቻ የተያያዘ ይምሰል እንጂ ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ለሚኖራት ጥቅም ቅድሚያ የሚሰጥ፤ የወደፊት ወረራዋን የሚያመቻች ነበር፡፡

በ1ኛው የዓለም ጦርነት ጀርመን ኢጣሊያን የጦር ጓደኛዋ እንድትሆን ጥያቄ ስታቀርብላት ደግሞ ፈረንሣይና እንግሊዝ ኢጣሊያን መልቀቅ አልፈለጉምና ኢጣሊያ ከእነሱ ጋር ሆና ፀረ-ጀርመን አቋም መያዝ እንዳለባትና ከድል በኋላ ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛቷ እንድታደርግ አስፈላጊውን ትብብር ሁሉ እንደሚያደርጉላት ቃል ገቡ፡፡

ኢጣሊያም ከቅኝ ግዛት ድንበረተኞቿ ጎን ብትሰለፍ እንደሚሻል መረጠች፡፡ በዚህም ላይ ከድል በኋላ የጀርመንንና የቱርክን ግዛቶች መካፈል ይችሉ ነበርና ኢጣሊያ በተለይ የሰሜን አፍሪካን የቱርክ ግዛቶች ፈለገች፡፡ እንደነሊቢያ ያሉትን ጓደኞቿ እንደማይሻሟት ቃል ገቡላት፡፡ የኢጣሊያ እያንዳንዱ እንቅስቃሴም ኢትዮጵያን ዳግም በእጇ ከማስገባት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በ1916 ዓ.ም ኢትዮጵያ የመንግስታቱ ማኅበር አባል ስትሆንም የይስሙላ ተቃውሞ ከእንግሊዝ በኩል የተሰነዘረ ቢመስልም ኢጣሊያ ድጋፏን አሳይታለች፡፡

ራስ ተፈሪ አውሮፓን በጎበኙ ጊዜ የኢጣሊያ አቀባበል ከሁሉም የተለየ ሆኖ፤ "ቪቫ ኢትዮጵያ!" እያሉ በይስሙላ አድናቆት እንዲቀበሏቸው ተደርጓል፡፡ የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ፍቅር በደንብ መጠንከሩን ለማሳየት ደግሞ ሐምሌ 28 ቀን 1920 ዓ.ም ለ20 ዓመት የሚዘልቅ የወዳጅነትና የሠላም ውል ተፈራረሙ፡፡ ከዚሁ ጋርም አሰብንና ደሴን የሚያገናኝ የመኪና መንገድ ለመስራት ተስማምተው ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ስታዘናጋና ስታሰልል ከረመች፡፡ ጎን ለጎንም ከፍተኛ የጦር ዝግጅት እያደረገች ቆየች፡፡
ኢትዮጵያ የጦር መሣሪያም ሆነ ሌላ ነገር ገዝታም ሆነ በእርዳታ ለማስገባት ብትፈልግ እንኳ ወደቦቿ ሁሉ በሦስቱ አገሮች ቁጥጥር ስር ነበሩና በተለያዩ ምክንያቶች ሲዘጉባት፣ለማስመሰል ጥቂት ነገሮችን ሲለቁላት ቆዩ፡፡በመጨረሻ ረጅም ዓመት የወሰደው ዝግጅት ተጠናቆ ውላቸውን በወልወል ጥሰው ጀመሩ፡፡


ወልወል የሚገኘው በምስራቁ የአገራችን ክፍል በኦጋዴን አካባቢ ነው፡፡ ከጥቂት ምዕተ ዓመታት በፊት የኢትዮጵያ ንጉሠነገስት የነበሩት አፄ ዘርዓያዕቆብ ያስቆፈሩት በጣም አስፈላጊና በርከት ያሉ የውሃ ጉድጓዶች በዚሁ በወልወል ይገኙ ነበር፡፡የፋሽስት ኃይልም ጦርነቱን ለመጀመር ሰበብ ያደረገው ይህንኑ ቦታ በመውረር ነው፡፡ ከሶማሊያ



ተነስቶ በኢትዮጵያ ድንበር ከሚገኘው ወልወል ላይ በሰፈሩ የኢትዮጵያ ጠረፍ ጠባቂዎች ላይ ሳይታሰብ ተኩስ ከፍቶ ቀላል የማይባል ጉዳት አደረሰ፡፡ ይህን የመጀመሪያ ያልታሰበ ጥቃት የኢትዮጵያ 250 ወታደሮች መከቱና ጠላትን መለሱ፡፡ ሸሽቶ የሄደው ጥቂት የጠላት ጦር ህዳር 26 ቀን 1927 ዓ.ም በደንብ ታጥቆ ተሰለፈ፡፡

የወቅቱ የአካባቢው ጠባቂ ጦር አዛዥ የነበሩት የሲዳሞ ተወላጅ ዓሊኑር ከጥቂት ጦራቸው ጋር ሆነው "ይህን ድንበር ለመያዝ የሚነሳ ካለ እኛ የኢትዮጵያ ልጆች አይደለንግ! ያውም ጣሊያን? ያባቶቻችን ተሸናፊ? እኛ የአባቶቻችን አባቶቻችን የእኛ ናቸው!" በሚል ወኔ ቀስቃሽ ንግግር ወታደሩን አነቃቁት፡፡

በዚህ ቀን እለተ ረቡዕ ህዳር 26 ቀን 1927 ዓ.ም ከቀኑ 9 ሰዓት እስከ ምሽቱ 5 ሰዓት ድረስ ያለእረፍት ተዋጉ፡፡ ከኢትዮጵያ 94 ሰው ሞቶ 45 ሲቆሰል ከኢጣሊያ 77 ወታደሮች መገደላቸውን ጳውሎስ ኞኞ "የኢጣሊያና የኢትዮጵያ ጦርነት" በሚለው መፅሐፉ አካቶት ይገኛል፡፡ በዚህም የኢጣሊያ ጦር አፈገፈገ፡፡ እነዚህ ውጊያዎች ኃይል መፈተሻ አይነት ነበሩ፡፡ ኢትዮጵያ የወልወሉን ግጭት እንዳየች ፊቷን ወደ ዲፕሎማሲው ብታዞርም፤ ሰሚ የለም፡፡ የመንግስታቱ ማኅበር አባል አገር መሆኗን እያስታወሰች ብትከራከር፣ ኢትዮጵያና ኢጣሊያ በ1920 ዓ.ም የተስማሙበትን የድንበር ውል ኢጣሊያ መጣሷን እያነሳች አቤቱታዋን ብታቀርብ፤ ከማንኛውም ወገን አዎንታዊ ምላሽ አጣች፡፡ ራሷን የምትከላከልበት የመሣሪያ እርዳታ በእርዳታም ሆነ በግዥ እንዳታገኝ አደረጉ፡፡ ወራሪው ኃይል ደግሞ ወረራው ወረራ እንዳይመስል የተለያዩ ዘዴዎችን ለመጠቀም ሞከረ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በወልወሉ ትንኮሳው የተገደሉበትን ወታደሮች በመጥቀስ "ቀድመው ትንኮሳውን የፈጠሩት የኢትዮጵያ ድንበር ጠባቂዎች ናቸው" በማለት የካሣ ጥያቄ አቀረበ፡፡ "የተገደሉብኝ ዜጎቼ ደም አለ፤ ለዚህ ካሣ 200 ሺ ብር ይሰጠኝ፤ በኢጣሊያ ድንበር ጠባቂዎች ላይ ከባድ ጥፋት ያደረሰው ደጃዝማች ኡመር ሰመተር ተላልፎ ይሰጠኝ..." ቢልም የኢትዮጵያ መንግስት አልተቀበለውም፡፡ የካሣ ጥያቄው ምላሽ ቢያገኝ ኖሮ እንኳን ወረራው እንደማይቀር ግልፅ ነው፡፡ የወልወል ግጭት የኢጣሊያ የወረራ ጅምር እንጂ ይፋ የሆነና በዓለም ህዝብ ዘንድ በውል የታወቀ አልነበረም፡፡ ተራ ግጭት ተደርጎ ተወስዶ ነበር፡፡




ወደ ኢትዮጵያ ይጓዝ የነበረው የጠላት ጦር።

በ1928 ዓ.ም ግን ከኤርትራ በመነሳት ይፋዊ ወረራውን ጀመረ፡፡ ወረራው ከሁለት አቅጣጫ ሆነና የምስራቁ የፋሽስት ጦር በጄኔራል ግራዚያኒ እየተመራ፣ የሰሜኑ ግንባር በጄኔራል ባዶሊዮ እየተመራ፤ "የአድዋው ሽንፈት እንዳይደገም" በሚል 100 ሺ ጥቁሮች የተካተቱበት 500 ሺ ወታደሮች፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ አዋጊ ጄኔራሎች፣ በሰሜኑ ግንባር 300 የጦር አውሮፕላኖች፣ በምስራቁ ግንባር 100 የጦር አውሮፕላኖች በድምሩ 400 አውሮፕላኖች በርካታ ታንክና መትረየስ፤ መድፎች ... ወዘተ ታጥቀው ወረራውን ቀጠሉ፡፡ ኢትዮጵያም 8 አውሮፕላኖች ያውም ለጭነት እንጂ ለውጊያ የማያገለግሉ ነበሯትና እነሱን ይዛ፤ ቁጥሩ በብዙ ፀሐፍት ዘንድ ስምምነት ላይ ያልተደረሰበት ሠራዊትና /3 መቶ ሺ የሚደርስ/ 60 ሺ የድሮ ጠመንጃ ካለ በቂ ጥይት ...ፍፁም እንደማይመጣጠኑ መገንዘብ እንችላለን፣ ገጠመች፡፡ በመስከረም ወር አጋማሽ 1928 ዓ.ም የኢጣሊያ ጦር ከ40 ዓመት በፊት አፍሮ የተመለሰባትን አድዋን ያዘ፡፡ በዚሁ ጊዜም በምስራቅ በኩል ቆራሄ ተያዘች፡፡ ... እያለ ቀጠለ፡፡ በእንግሊዝና በፈረንሣይ ክህደት ያዘኑት ንጉሡ የትኛውም አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘምና ወደ ማይጨው ለመዝመት ወሰኑ፡፡

መስከረም 22 ቀን 1928 ዓ.ም ክተት አወጁ፡፡ ወደ ሰሜን ገስግሰውም ከፍተኛ ውጊያ በተካሄደበት በማይጨው ጦርነት ተካፈሉ፡፡ "አርሊኮን" የሚባለውን የአየር መጣያ ተኳሽ ሆነው አውሮፕላን ለመጣል በመሞከር አገራዊ ግዴታቸውን ሊወጡ ጥረት አደረጉ፡፡





ጃንሆይ አርሊኮን የተባለውን የአየር መጣያ ደግነው

ከታህሳስ እስከ ጥር ወር ድረስ እልህ አስጨራሽ ትግል ተደረገ፡፡ በተለይ በሰሜኑ ግንባር ኢትዮጵያውያኑ ከመከላከል ወደማጥቃት ተሻገሩ፡፡ በዚህ ጊዜ ያለፈው ሽንፈት የመደገም አዝማሚያ እንደመታየት ሲል ነው ፋሽስት የመርዝ ጋዝ መጠቀም የጀመረው፡፡"ሙስታርድ" እና "ኤፕሪት" የተባሉ በመንግስታት ማህበር የተከለከሉ የመርዝ ጋዞች በአውሮፕላን ሲያዘንቡ የኢትዮጵያ ጦር በአሰቃቂ ሁኔታ ማለቅ ጀመረ፡፡በዚህ መሰሉ አደገኛ ጥቃትም ተዋጊ ወታደሮችን ብቻ ሳይሆን ንፁሐን ዜጎችን፣የቤትና የዱር እንስሶችን፣የምግብ ሰብሎችንና መኖሪያ ቤቶችን አነደዷቸው፡፡

የኢጣሊያ መንግስት ራሱ ብቻ ሳይሆን መላው አውሮፓዊ ቅኝ ገዥዎች በኢትዮጵያውያን ቢሸነፍ ያውም በድጋሚ እጅግ ሐፍረትና ስጋት ነበርና አሰቃቂውን የመርዝ ጋዝ ሲያዘንብ በቃል እንኳ ያወገዘው አባል አገር አልነበረም፡፡

በዚያ ጊዜ የሰራዊታቸውን ማለቅ የተረዱት ንጉሱ ጦሩ እንዲሸሽ አዘዙ፡፡ ሸሽተውም ወደ አደስ አበባ በመገስገስ ሚያዚያ 22 ቀን 1928 ዓ.ም ማለዳ ላይ አዲስ አበባ ደረሱ፡፡ አፄ ኃይለስላሴ በማይጨው ጦርነት ድል ሆነው ወደ አዲስ አበባ እንደተመለሱ የመሳፍንትና የመኳንንት አስቸኳይ ስብሰባ በቤተ-መንግስት ተደረገ፡፡ በዚህ ስብሰባ ሁለት ዓይነት ኀሳቦች ቀርበው ተነጋገሩባቸው፡፡

የመጀመሪያው ኀሳብ ከብላታ ታከለ ወልደሐዋርያት የቀረበ ነው፡፡ እንደ ብላታ ታከለ አስተያየት የኢትዮጵያ መንግስት ዋና የጦር ሠፈርና የአስተዳደር ከተማ በፍጥነት ወደ ጎሬ መዛወር ያስፈልገዋል፡፡ ንጉሠነገስቱ የመሪነት ተግባራቸውን ለመቀጠል ወደ ጎሬ ያምሩና በየአውራጃው የአርበኝነት ውጊያ እንዲቀጥል ይደረግ፡፡ ጎሬ ከእንግሊዝ

ቅኝ ግዛት አገሮች ድንበርተኛ ስለሆነ ከውጭ አገር በእርዳታም ሆነ በግዥ መሣሪያ ማግኘት ይቻላል የሚል ሲሆን፣ ብላታ ታከለ ይህን ኀሳብ መሰረት አድርገው ንጉሡ ገና አዲስ አበባ ከመድረሳቸው በፊት በጃንሜዳ ታላቅ ንግግር አድርገው ነበር፡፡ ይህም "ወደዋና ከተማችን እየገፋ የመጣውን ጦር ከጣርማ በር ላይ አግደን የአርበኝነት ውጊያ ለመጀመር እንሰናዳ" የሚል ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከአንዳንድ የውጭ አገር እንደራሴዎች የቀረበላቸውን ምክር መሠረት በማድረግ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ብላቴን ጌታ ህሩይ ወልደስላሴና አቶ መኮንን ሐብተወልድ "ንጉሥ ነገስቱ ዋና የጦር ሠፈራቸውን ወደ ጎሬ አዛውረው ተስፋ የሌለው የመከላከል ሙከራ ከሚያደርጉ ወደ አውሮፓ ሄደው ለሊግ ኦፍ ኔሽንስ አቤቱታቸውን ያቅርቡ፣ እርዳታም ይጠይቁ፣ የኢትዮጵያ ከተማ ወደ ጎሬ ተዛውሮ በደጃዝማች ወልደፃድቅ እንደራሴነትና በራስ እምሩ የጦር ሚኒስትርነት የአርበኝነት ትግል ይጀመር" አሉ፡፡

በማግስቱ ሚያዚያ 23 ቀን 1928 ብላታ ታከለ ሃሳባቸው ውድቅ መሆኑን ሲያውቁ ያለልክ ተቆጥተው "ንጉሠ ነገስቱ ወደአውሮፓ ለመሄድ የሞከሩ እንደሆነ የእኔ እስረኛ ይሆናሉ" ብለው ዝተዋል የሚል ወሬ ስለተሰማ የንጉሡን ወደ አውሮፓ መሄድ ብላታ ታከለ /በኋላ ደጃዝማች/ ሳያውቁ በሚስጥር እንዲሆን ተቆርጦ ባቡር ላይ ከተሳፈሩ በኋላ ታከለን ጠርተው "የአዲስ አበባን ከተማ ያለአንዳች ውጊያ በስርዓት ለጠላት ጦር አዛዥ እንዲያስረክብ" አዘዙት፡፡ በአልሞት ባይ ተጋዳይነት የከተማዋ ህዝብ በመርዝ ጋዝ እንዳያልቅ በመስጋት፡፡ በብላታ ታከለና በጥቂት አረበኞች እይታ የንጉሡ ለአቤቱታ ወደ አውሮፓ መጓዝ "አገርን ከድቶ መሸሽ" እንደማለት ነበር፡፡ ስለዚህም ከዚህች ጊዜ ጀምሮ ብላታ ታከለ ወልደሐዋርያትና ንጉሱ የእድሜልክ ዐበኞች ሆኑ፡፡ እንዲያውም ከነፃነት በኋላ ንጉሡን ለመፈንቀል ሞክረው ነበር፡፡ ሳይሳካ ቀረ እንጂ፡፡

የረጅም ጊዜ የውጭ ጉዳይ አማካሪያቸው የነበረው አሜሪካዊው ጆን ስፔንሰር በሐምሌ ወር 1984 ዓ.ም በኢትዮጵያን ሪቪው መፅሔት ላይ ባሰፈረው ጽሁፍ የግርማዊነታቸው በአጣብቂኝ ወቅት ወደጄኔቭ መጓዝ ለኢትዮጵያ ትልቅ የዓለም አቀፍ ግንኙነት ታሪክ ተክሎ እንዳለፈ ይገልፃል፡፡"ኢትዮጵያ ለጋርዮሽ ደህንነት (Collective Security) ያላትን ታማኝነት በዓለም ህዝብ መካከል የተከለችበት ክስተት ነው" ይለዋል፡፡ከዚህም ባለፈ ዲፕሎማሲው ያስገኘውን ውጤት መሰረት አድርገው የሽሽቱን ትገቢነት የሚገልፁ በርካታ ናቸው፡፡ነገር ግን በኢትዮጵያ ታሪክ በጦርነት ጊዜ አገራቸውን ጥለው የሸሹ ብቸኛ ንጉሠ ነገስት አሰኝቷቸዋል፡፡ሆኖም እዚህ ዘመን ላይ ሆነን ለመፍረድ ከመዘጋጀታችን በፊት የዚያን ወቅት ሁኔታ ማገናዘብና ባይሸሹ ኖሮስ ምን ይፈጠር ነበር? የሚለውን ቀድሞ ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ንጉሱ



ላለመሸሽ እንዳንገራገሩና የጳጳሱ ጎትጓችነት ታክሎበት እንደሸሹም ተፅፏል፡፡

የሆነ ሆኖ በተጠቀሰው እለት ምሽት የእነ አቶ መኮንን ሐብተወልድ ኀሳብ ተቀባይነት አግኝቶ የእነብላታ ታከለ ወልደሐዋርያት ኀሳብ ውድቅ ሆነ፡፡ራስ እምሩና ደጃዝማች ወልደፃድቅም የተጠቀሰውን ሹመት ይዘው መቀመጫቸውን ጎሬ አድርገው ትግሉ ... ቀጠለ፡፡

አፄ ኃይለስላሴ ሙሉ ቤተሰባቸውን ይዘው፣ በተጨማሪም ታማኝ ሹማምንቶቻቸውን ራስ ካሳን፣ እጨጌ ገብረጊዮርጊስን፣ ብላቴን ጌታ ህሩይ ወልደስላሴን፣ አቶ መኮንን ሀብተወልድን፣ አቶ ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንስን፣ አዛዥ ከበደ ተሰማን፣ ልጅ አሰፋው ከበደንና ሌሎችንም አስከትለው በእንግሊዝና በፈረንሣይ ከተወከሉ ዲፕሎማቶች ጋር በባቡር ተሳፍረው ወደ ጅቡቲ አመሩ፡፡ ብላታ ታከለም ወደ አርበኝነቱ ገቡ፡፡

ንጉሱ ከሁለት ቀን ጉዞ በኋላ ሚያዚያ 25 ቀን 1928 ዓ.ም ጅቡቲ ደርሰው ትጠብቃቸው ከነበረችው "ኢንተርፕራይዝ" ከተባለችው የጦር መርከብ ላይ ተሳፍረው ሄዱ፡፡ እንግሊዝ ደርሰው መኖሪያቸውን በ"ባዝ" መሠረቱ፡፡

ወዲያው ሚያዚያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም በጄኔራል ባዶሊዮ የሚመራው የኢጣሊያ ጦር አዲስ አበባን ተቆጣጠረ፡፡ምንም እንኳ የምስራቁ ግንባር መሪ ግራዚያኒ ገና ሐረርን ያላለፈ የነበረ ቢሆንም፤ማንም ቢቀድም ለውጥ አልነበረውምና ባዶሊዮ ቀድሞ አዲስ አበባን ይዞ ለሞሶሎኒ "እንኳን ደስ ያለህ" አለው፡፡

በዚሁ እለትም ሞሶሎኒ ካለበት ሮም ሆኖ ለህዝቡ "ሌላኛዋ የሮማ ኢምፓየር ተመሰረተች!" በማለት ቅኝ ገዥነቱን በደስታ ይፋ አደረገ፡፡ የኢጣሊያ ጦር ወደ አዲስ አበባ የደረሰው በቀላሉ አልነበረም፡፡ በየመንገዱ በሚደርስበት የጎበሾች የደፈጣ ጥቃት ብዙ ከስሯል፡፡

ለምሳሌ ሚያዚያ 26 ቀን 1928 ዓ.ም በማይጨው ጦርነት የተካፈለው ልጅ ኃይለማርያም ማሞ የኢጣሊያ ጦር ወደ አዲስ አበባ መቃረቡ አንገብግቦት ደብረብርሃን መንገድ ላይ ሜጫ ሉኬ ሴራቤ በምትባለው ቦታ ላይ መሽጎ ቆይቶ በጠላት ላይ የደፈጣ ጥቃት አድርሶ 7 ካሚዮኖች አቃጥሎ መቶ አርባ የኢጣሊያ ወታደሮችን በመግደል እረፍት የለሽ ቆይታቸውን ከጅምሩ አረጋግጠላቸዋል፡፡

ሆኖም ከሰማይም ከምድርም የሚያደርሱትን አደጋ ኋላ ቀር መሣሪያ ታጥቀው የሚከላከሉት አልሆነም፡፡ ስለዚህም ቀስ በቀስ የየአገሩን ተከላካይ ወታደርና ሰላማዊ ዜጋውንም ጭምር በመርዝ ጋዝ እያነደዱ ልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ግዛቶችን ለመያዝ ያደረጉት ሙከራ ተሳካላቸው፡፡

ኢትዮጵያውያኑ ከ1927 - 1928 ፊት ለፊት በመጋፈጥ፤ ከ1928 - 1933 ዓ.ም ደግሞ በአርበኝነት ጣሊያኖችን በጠንካራ ክንዳቸው

ሲከላከሉና ሲያጠቁ ነበር ያሳለፉት፡፡ በ5 ዓመቱ የአርበኝነት ዘመን ተዘርዝረው የማያልቁ ውድ የኢትየጵያ ጀግኖች በየግዛቱ መሽገው አገራቸውን ከወራሪው ፋሽስት ለመታደግ በቁርጠኝነት ተፋለሙ፡፡ በዚያን ጊዜ ሴት ወንድ፣ ሽማግሌ አሮጊት፣ ህፃናት ሳይቀሩ በየዘርፉ ለአርበኞች ያበረከቱት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነበር፡፡

መረጃ በማቀበል፣ ስንቅ በመቋጠር፣ ዶሮና እንቁላል ለኢጣሊያ ወታደሮች እየሸጡ በሚያገኙት ገንዘብ መልሰው ከራሳቸው ጥይት ገዝተው ለወገኖቻቸው በመላክ በራሳቸው ጥይት ራሳቸው እንዲሞቱ አድርገዋል፡፡ በባንዳነት ለኢጣሊያ ወግነው ወገናቸውን የወጉ የመኖራቸውን ያህልም ባንዳ መስለው ለአገራቸው ነፃነት የታገሉ የውስጥ አርበኞች የተጫወቱት ሚና ቀላል አልነበረም፡፡ 5 ጥይት የተኮሰ ባንዳ "25 ተኮስኩ" ብሎ ተናግሮ ሃያውን ለወገኖቹ ይልክላቸዋል፡፡ እንዲህና እንዲያ እያደረጉ ድፍን 5 ዓመቱን እረፍት ነስተዋቸዋል፡፡

የኢጣሊያ ጀኔራሎች የኢትዮጵያውያኑን ጀግንነት መቋቋም ሲሳናቸው የትግል ስልታቸውን በመለወጥ እርስ በርስ ለማፋጀት በዘር፣ በጎሣ፣ በሃይማኖት ህዝቡን ከፋፍለው ኦሮሞውን "የአማራ ተገዥነት ይብቃህ... ነፃ ልናወጣህ ነው የመጣነው..." እያሉ ለሌላው ብሔርም ተመሣሣይ መልዕክታቸውን እያሰራጩ የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ ለማሳጨድ ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም፡፡ ሆኖም እምብዛም ሰሚ አላገኙም፡፡

ቀጥለው ደግሞ ሃይማኖተኛ የሆነውን ህዝብ በጳጳስ ለማስገዛት ፈለጉ፡፡ አቡነ ጴጥሮስን ህዝቡ ለኢጣሊያ እውቅና እንዲሰጥ መልዕክታቸውን እንዲያስተላልፉለት /እንዲገዝቱለት/ ፈለገ፡፡ አቡነ ጴጥሮስ ግን በተቃራኒው "የግፈኛውን ወራሪ የኢጣሊያን ገዥነት የተቀበለ ኢትዮጵያዊ የተረገመ ይሁን፤ እንኩዋን ሰው ምድሪቱ የተረገመች ትሁን" ብለው ገዘቱ፡፡

በዚህ ጊዜ የኢትየጵያ የበላይ ገዥ ተብሎ የተሾመው ጀኔራል ግራዚያኒ እልህ ይዞት በጳጳሱ ላይ ሞት ፈረደባቸውና በአደባባይ በ11 ጥይት ተበሳስተው እንዲገደሉ አደረገ፡፡ሐምሌ 22 ቀን 1928 ዓ.ም ይህን ግፍ ፈፀመ፡፡ህዝቡ በእልህ ትግሉን አቀጣጠለው፡፡እኚህን ጀግና ኢትዮጵያዊ ታሪክ በልዩ ሁኔታ ሲዘክራቸው ይኖራል፡፡ከነፃነት በኋላም ለእኚህ ጀግና ጳጳስ በተረሸኑበት ቦታ በመዘጋጃ ቤቱ ጀርባ የአቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ቆሞላቸው ዛሬም ድረስ ታሪካቸውን እየዘከረ ይገኛል፡፡

የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ደግሞ በገነተ ልዑል ቤተ-መንግስት ግራዚያኒ የኢጣሊያው ንጉስ ቪክቶር ኢማኑኤል ወንድ ልጅ የመውለዱን ደስታ ለአዲስ አበባ ህዝብ ሊያበስር ስብሰባ ባደረገ ጊዜ ሞገስ አስገዶምና አብርሃ ደቦጭ የተባሉ ወጣቶች በአዳራሹ ውስጥ ቆሞ ንግግር



የሚያደርገውን ግራዚያኒን ቦንብ ወርውረው እሱን አቁስለው ሌሎች ጀኔራሎችን ገድለው አመለጡ፡፡ግራዚያኒ ባይሞትም በቁሙ ገድለውት ነበር የሸሹት፡፡የእነዚህን ሁለት ጀግኖች ፍፃሜ ከወዲሁ አይተን ለማለፍ ያህል፤ከዓለም ጀግኖች ታሪክ መፅሐፍ ውስጥ የተካተተውን አሟሟታቸውን ላስፍር፡፡

አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም ጥቃቱን ካደረሱ በኋላ ስምኦን በሚባለው . በጓደኛቸው ታክሲ ከአዲስ አበባ ወደ ፍቼ ከተማ ነበር የሄዱት፡፡ ስምኦን እነሱን አድርሶ ተመለሰ፡፡ ሁለቱ ጀግኖች እስከ 1932 ዓ.ም ድረስ ከራስ አበበ አረጋይ ጎን ተሰልፈው በአርበኝነት ሲታገሉ ቆይተዋል፡፡ ፎቶግራፋቸው ተበትኖ ስለነበር አርበኞችን አስፈቅደው ወደ ሱዳን ለመሻገር ተነሱ፡፡ ተጉዘውም ቋራ ደረሱ፡፡ ምግብና ውሃ ለመፈለግ ወደ አንድ መንደር ሲጠጉ በጠላት እጅ ወደቁ፡፡ ወዲያው የስቅላት ፍርድ ተበየነባቸውና በመጀመሪያ ሞገስ ሊሰቀል ሲል አብርሃ "የወንድሜን ሞት አላይም፤ በመጀመሪያ እኔን ግደሉኝ" ብሎ ለስቅላት ቀረበ፡፡ ከዚያም "በግራዚያኒ ላይ አደጋ የጣልኩ እኔ ነኝ፡፡ ለሀገሬ በሰራሁት ሁሉ እኮራለሁ፡፡ አሁንም ለሀገሬ ስሞት ደስ ይለኛል" ብሎ ሲናገር አዛዡ ንዴቱን መቆጣጠር አቅቶት በስቅላት እንዲገደል የተወሰነውን ሽጉጡን አውጥቶ በፍጥነት ገደለው፡፡ ሞገስም በቁጣ "አንተ ፋሽስት አሁን የገደልኸው የዚህ አገር ውድ ልጅና ደም መላሽ ነበር፡፡ ብዙ አብርሐሞች በዚህ ጀምበር በቅለው ያድራሉ፤ አንተም አተላ ከሆነው ታሪክህ ጋር ወደ መሬት ትወርዳለህ" ብሎ ሲናገር እሱንም በሽጉጥ ገደለው፡፡ ሬሳቸው ቋራ ላይ እንደነገሩ ተቀብሮ ነበር፡፡ በኋላ ግን ነፃነት ሲመለስ በአፄ ኃይለስላሴ ትዕዛዝ አፅማቸው መጥቶ በክብር ከአርበኞች የመቃብር ቦታ በአዲስ አበባ በስላሴ ቤተ-ክርስቲያን አረፉ፡፡ (መቼም ኤርትራዊነታቸው ኢትዮጵያዊነታቸውን አይቀብረውም!)

ግራዚያኒ በዚህ ብስጭት 30 ሺ የሚሆኑ የአዲስ አበባ ነዋሪዎችን በመሣሪያ፣ በመጥረቢያ፣ በገጀራ አስጨፈጨፋቸው፡፡ እነ ሞገስ ወደሸሹበት ተብሎ ወደደብረሊባኖስ ገዳም የኢጣሊያ ወታደሮች ሄደው በገዳሙ ብቻ 358 ካህናትን ገደሉ፡፡ ይህንንም ግራዚያኒ ለኢጣሊያው ገዥ ለቢኖቶ ሞሶሎኒ እና ለንጉሡ ቪክቶር ኢማኑኤል በላከው የቴሌ ግራም መልዕክት ሲያረጋግጥ፤ በዚህ ቂም በቀል ሳቢያ ገና ብዙ ሺዎችን ሊያስፈጅ መዘጋጀቱንም አብሮ ገልጾ ነበር፡፡ በየካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም በመጥረቢያ ለተጨፈጨፉት ንፁሐን ዜጎች መታሰቢያ ይሆን ዘንድም ከነፃነት በኋላ ከየካቲት 12 ሆስፒታል ፊት ለፊት የሚገኘው የስድስት ኪሎው ሐውልት ተሰርቶላቸዋል፡፡

ግራዚያኒ መረር ያለ እርምጃውን በመቀጠል ተማርከው የተያዙትን ኢትዮጵያዊ ጀግኖች፤ የጥቁር አንበሳ አባላትን ጨምሮ

(የጥቁር አንበሳ አባላት ማለት በ1927 ዓ.ም በሆለታ ገነት ጦር ት/ቤት የመኮንንነት ስልጠና ይማሩ የነበሩትና ትምህርቱ እንደተጀመረ ወረራው ስለተነሳ ሰልጣኞች በወለጋ ክፍለሃገር ያቋቋሙት ማኅበር ነበር፡፡ ይህም የጥቁር አንበሳ ማኅበር የተባለው ሲሆን ከፍተኛ ጀብድ የፈፀሙ ጀግኖች የነበሩበት ማኅበር ነው፡፡ ወዲያው ቢፈርስም፡፡) ከአውሮፕላን ላይ ወደ ገደል ከነህይወታቸው በመወርወርና፣ በተመሳሳይ ጭካኔ ብዙዎችን አስፈጀ፡፡ ይህ ሁሉ ድርጊቱም የአርበኞቹን ትግል የበለጠ አፋፍሞ የሚያስቀጥል እንጂ አስፈራርቶ የሚያሸሸው አልሆነም፡፡

ግራዚያኒ ይዞ ያልያዛትን አገር ካርታ እያሰራ በጎንደር፣ በጅማ፣ በአዲስ አበባና በተለያዩ ከተሞች አዳዲስ ድልድዮችና ህንፃዎች እንዲገነቡ አደረገ፡፡ የኢጣሊያ ባለሃብቶች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ጥሪ ቢያደርግም፣ ጥቂቶች ሲመጡለት ብዙሃኑ በየጊዜው ከአርበኞች የሚሰነዘረውን ጥቃት ፈርተው ዘገዩ፡፡

የአዲስ አበባን ልዩ ልዩ መንደሮች እያስከለለ እንደ ካዛንቺስ ያሉትን የኢጣሊያ ባለስልጣናት መኖሪያ እንዲሆኑ አደረገ፡፡ የነጮች ገበያ በአራዳ አካባቢ ሆኖ የጥቁሮች ገበያ መርካቶ እንዲሆን እየወሰነና፣ የተለያዩ የአስተዳደር አዋጆችን እያወጣ ተግባራዊ አስደረገ፡፡ ከ1928 ዓ.ም ጀምሮም መቀመጫቸውን ጎሬ አድርገው የነበሩት እነራስ እምሩ አካባቢውን በኃይል ከመልቀቃቸውና ከመማረካቸው በፊት ከንጉሱ ጋር እየተፃፃፉ፣ በየግዛቱ ካሉ አርበኞች ጋርም እየተላላኩ ትግላቸውን ለመቀጠል ሞከሩ፡፡ ነገር ግን የኢጣሊያ ጦር በግፍና በጭካኔው በርትቶ የኢትዮጵያን ግዛቶችን ሙሉ በሙሉ ባልተረጋጋ ሁኔታ ተቆጣጥሯል፡፡

አንድ አገር በቅኝ ግዛት ሕግ መሠረት እንደተወረረች ታምኖ እውቅና የሚሰጠው 1ኛ. ዋና ከተማዋ ስትያዝ፣ 2ኛ. ተወራሪው ህዝብና መንግስት ወረራውንም ሆነ ሽንፈቱን አምኖ ሲቀበል፣ 3ኛ. ንጉሠ ነገስቱና የአገሪቱ ማሕተም በጠላት እጅ ሲገባ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያኑ ግን እጅ አልሰጡም /አላመኑም/ እንደገናም የአገሪቱ ማሕተም በጠላት እጅ አልገባም፡፡ ንጉሠ ነገስቱ ሸሽተውና ተቃውመው ተሰደዱ እንጂ እውቅና አልሰጡም፣ አልተማረኩም፡፡ መሀል ከተማዋን ግን ይዟል፡፡ ያም ሆኖ እነራስ እምሩ ጎሬ ሆነው ይልኩ በነበረው መልዕክት አማካኝነት የከተማ ለውጥ መደረጉ መከራከሪያ ሆኖ መቅረብ ይችል ነበር፡፡ እስኪማረኩ ድረስም ሰፊ የመረጃ ልውውጥ ያደርጉ ነበር፡፡ ለኢትዮጵያ ግን አንድም የደረሰላት አንቀፅ አልነበረም፡፡ አፄ ኃይለስላሴ በ1929 ግንቦት ወር ላይ ለመንግስታቱ ማኅበር አቤቱታቸውን ለማቅረብ ከለንደን ወደ ጀኔቭ ሲያቀኑም በቂ መረጃ ነበራቸው፡፡ ነገር ግን ሲጀመርም ሕገ-ወጥ ወረራው በኃያላኑ ይሁንታ ስለተደረገ፣ አሁንም ኃያላኑ ወረራውን እውቅና ሰጡት፡፡ የኢትዮጵያ ጩኸት ለብዙዎች የሚሰማ አልሆነም፡፡



ሰኔ 23 ቀን 1929 ዓ.ም የዓለምን ህዝብ ህሊና ሰርስሮ የሚገባ ንግግራቸውን በጉባኤው ፊት አደረጉ፡፡ "ኃይል ሕግን ያሸንፋል? ወይስ ሕግ ኃይልን ያሸንፋል? በአንድ ውል ግርጌ የተፈረመ ፊርማ የሚረጋው ፈራሚዎቹ መንግስታት የሚጠቅማቸው በሆነ ጊዜ ብቻ ነውን? እግዚአብሔርና ታሪክ ፍርዳችሁን ሲያስታውሱት ይኖራሉ" የሚሉ ዓረፍተነገሮች የተካተቱበት ሰፊው ንግግራቸው በወቅቱ አንዳች ፍሬ አለማስገኘቱም የሊግ ኦፍ ኔሽንስን የይስሙላ ማኅበርነት በግልፅ ከማሳየት አልፎ ንጉሱን ደግሞ ነብይ ሊያሰኛቸው በቃ፡፡

ፈረንሣይና እንግሊዝን እግዚአብሔርና ታሪክ ሳይዘገዩ ሊፈርዱባቸው መጡ (ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ይሄው እየታወሱ ነው፡፡) ይኸውም በ2ኛው የዓለም ጦርነት የአሰላለፍ ለውጥ መከሰቱ ነው፡፡ ሒትለርና ሞሶሎኒ የጦር ጓደኛ ሆኑ፡፡ ፈረንሣይና እንግሊዝ ኢጣሊያ ከጀርመን ጎን እንዳትሰለፍ ለማባበል ብዙ ቢደክሙም ሞሶሎኒ ጀርመን ትሻለኛለች አለ፡፡

በእኛ አቆጣጠር በመስከረም ወር 1931 ዓ.ም ጀርመን ከኢጣሊያ ጋር ተመሳጥራ ቼኮዝላቫኪያን ወረረች፡፡ ብዙዎች በቸልታ ነበር ያዩት፡፡ በነሐሴ ወር 1931 ዓ.ም ፖላንድን ወረረች፡፡ ነገሩ ግልፅ ሆነ፡፡ በዚህ ጊዜ እንግሊዝና ፈረንሣይ ፈጥነው በጀርመን ላይ ጦርነት አወጁ፡፡ ጀርመን በፈጣን የወረራ እርምጃዋ ዴንማርክ፣ ኖርዌይ፣ ሆላንድ ... እያለች ቀጥላ ፈረንሣይን መታቻት፡፡ ጀርመን በፈረንሣይ ላይ በ1932 ዓ.ም የተቀዳጀችውን ድል እስኪያይ ድረስ ሞሶሎኒ የኃይል ሚዛኑ ወደማን እንደሚያዘነብል ከርቀት ሆኖ ይከታተል ነበርና፣ የፈረንሣይን በከፊል መሸነፍ ካየ በኋላ ሰኔ 3 ቀን 1932 በይፋ ከጀርመን ጎን ተሰልፎ ውጊያውን ቀጠለ፡፡ የፈረንሣይ ህዝብ በቻርለስ ደጎል መሪነት የአርበኝነት ትግሉን ጀመረ፡፡

ቀጣዩዋ ተወራሪ እንግሊዝ መሆኗም ግልፅ ሆነ፡፡ ወዳጇዋ ኢጣሊያ ከድታ ጦርነት አወጀችባት፡፡ ይህ ደግሞ በዚያው በአውሮፓ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ጦርነት ሳይሆን የአፍሪካ ግዛቶቻቸውን የመቀማማት ጉዳይም ያስከትላል፡፡ እናም እንግሊዝ በምስራቅ አፍሪካ ያለውን የኢጣሊያ ጦር መምታት ነበረባት፡፡ በዚህም የኢጣሊያን ኃይል በማዳከም የአፍሪካ ቅኝ ግዛቶቿን አስጠብቃ፣ ተገዥዎቿ የነፃነት አመፅ እንዳያስነሱ አረጋግታ፣ የኢጣሊያን ግዛቶች ሊቢያን ጨምሮ ተረክባ፣ ከተቻለም ኢትዮጵያን ከኢጣሊያ ነጥቃ የራሷ ለማድረግ የግድ መነሳት ነበረባት፡፡ ስለዚህም አገሯ ላይ በስደት ተቀምጠው የነበሩትን ንጉስ ከእንግሊዝ ጋር ተባብረው አገራቸውን ነፃ እንዲያወጡ አስለፈች፡፡

እንግሊዝ ኢትዮጵያን ከድታ "ትወረር" ባለችበት አንደበት አሁን በቸርችል ቸሮታ "ነፃ ትውጣ" ተባለ፡፡ የኢጣሊያን ጦር ለመምታትና

ከኢትዮጵያ ለማስወጣት ደግሞ ጥቁሮቹ የአፍሪካ ቅኝ ግዛት አገር ወታደሮቿ ብቻ አይሞቱም፡፡ ጀግና የኢትዮጵያ አርበኞች እንዳሉ ታውቃለች፡፡ ሁኔታው ብዙ የድል ፍሬን መልቀም የሚያስችል ነው፡፡

አፄ ኃይለስላሴ የአገራቸውን አርበኛ አስተባብረው አገራቸውን ነፃ ያወጡ ዘንድ ወደ ሱዳን ላኳቸው፡፡ ንጉሡ ሱዳን ደርሰው ተከታይ ትዕዛዞች ከእንግሊዝ እስኪደርሳቸው ድረስ 6 ወራት ያህል ቆዩ፡፡ በቆይታቸውም ተሰደው በሱዳን የሚገኙ አርበኞችን ሲያንቀሳቅሱና ወታደራዊ ስልጠና እንዲያገኙ ሲያስደርጉ ቆዩ፡፡ "መጣሁ በርቱ" እያሉም ወደ ህዝባቸው መልዕክት ይልኩ ነበር፡፡ በመጨረሻ እንግሊዝ ጦሯን ከሱዳንና ከኬንያ በማስነሳት ሂደቱ ተጀመረ፡፡ በደቡብ በጀኔራል ካኒንግሐም፣ በሰሜን በእነ ጄኔራል ዊንጌትና /ያኔ ኮሎኔል/ በእነሳንፎርድ የሚመራው ጦር በኢጣሊያ ላይ ጥቃት እያደረሰ፣ በአውሮፕላን በታገዘ ውጊያ ድል እያደረገ፣ ንጉሡም የአገራቸውን ጀግኖች እያስተባበሩ በጋራ ለሙሉ ድል በቁ፡፡ የጦሩ ሁሉ ጠቅላይ አዛዥ እራሳቸው ንጉሡ እንዲሆኑ ተደርገው ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ይህን ያዩ ሐበሾች፤

*"አባ ጠቅል ሐይሌ የጦሩ ገበሬ*


*እያዋጋው መጣ ነጩን ከነጭ በሬ"* ብለው አወድሰዋቸዋል፡፡ ውስጠነገሩን መረዳት ያኔ አስፈላጊ አልነበረም፡፡

እናም ሚያዚያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም አዲስ አበባ ገብተው በቤተመንግስታቸው የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በነፃነት አውለበለቡ፡፡ ሚያዚያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም የተያዘችው አዲስ አበባ በድፍን 5 ዓመቷ ሙሉ ለሙሉ ነፃነቷን አገኘች፡፡ ነገር ግን ቀደም ሲል በአጭሩ እንዳየነው 5 ዓመቱ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ አርበኞች በጀግንነት ሲፋለሙ እንጂ እጅ ሰጥተው ያሳለፉት አልነበረም፡፡ በንጉሡ ያኮረፉ የነበሩ ሳይቀሩ ጠላትን መፈናፈኛ አሳጥተው የኖሩበት ዘመን ነው፡፡ ከእነዚህ ውስጥም አንድ የማንዘነጋቸውን ጀግና ለአብነት ለማንሳት ያህል በንጉሡ ግዞት ወርደው ብስጭት ላይ የነበሩት ባልቻ አባነፍሶ ይጠቀሳሉ፡፡ ባልቻ የኢጣሊያን ወረራ እንደሰሙ ኩርፊያውን ትተው፤ ያውም ነፃነት ያገኙት በወረራው ምክንያት ሆኖ "የጌታዬ የምኒልክ ድል አይደፈርስም!" ብለው በአዲስ አበባው ማጥቃት ላይ ልዩ ጀብድ ፈፅመው ህይወታቸውንም ያጡበት ሆኖ አልፏል፡፡ እነ ሸዋረገድ ገድሌን የመሰሉ ጀግና ሴቶችም ሳይጠቀሱ አይታለፉም፡፡ እነዚህንና ሌሎችን ጀግኖች በሚመለከት ለእያንዳንዳቸው ታሪካዊ ገድል አንድ አንድ መፅሐፍ እንደማይበቃቸው ግልፅ ነው፡፡ ስለዚህ እገሌስ ለምን አልተጠቀሰም ማለት አይገባንም፡፡

እንግዲህ ድሉ የተገኘው በኢትዮጵያውያኑ ጀግና አርበኞች ነው ማለት ይቻላል፡፡የእንግሊዝ ውለታስ?ተብሎ ከሚጠየቅ የጀርመን ውለታስ? ቢባል ይሻላል፡፡ የእንግሊዝ ውለታ ተገቢ ክብር ቢሰጠውም የራሡዋን




ጥቅም ማእከል አድርጋ ማገዙዋ መዘንጋት የለበትም፡፡የሆነው ሆኖ ይህች ተዓምረኛ አገር በአምላክ እርዳታ ነፃ ሆናለች፡፡



በሱዳን የተዘጋጀው ጦር በአልጋ ወራሽ አስፋወሰን እየተመራ በጃንሆይ አጠገብ ሲያልፍ

ሴረኞቹ በስምምነት አስያዟት፣ ሲጣሉ አስለቀቋት፡፡ መቼም የኢትዮጵያ አምላክ ሒትለርን አስነሳላት አንልም፡፡ ግን ይገርማል፡፡ዲምትሪ የፍሞቭ የተባለ ሩሲያዊ "2ኛው የዓለም ጦርነትና የእስያና የአፍሪካ ህዝቦች ዕጣ" በሚለው መፅሐፉ በዚያ የዳግም ወረራ ጊዜ ያለቁትን ኢትዮጵያውያን 800 ሺ መሆናቸውን ፅፏል፡፡ ሌሎችም ተመሳሳይ አሀዝ ያስቀምጣሉ፡፡የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኀበር ምክትል ፕሬዝዳንት አቶ ወርቅነህ ተገኘ በገለፁልኝ መሠረት ደግሞ 1 ሚሊዮን ዜጎች አልቀዋል፡፡በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ቤቶች ተቃጥለዋል፡፡ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ዶሮ፣ፍየል፣በግ፣ከብት፣ አህያ ... ወዘተ አልቀዋል፡፡ያውም በአሰቃቂ ሁኔታ፡፡ስለዚህ የኢትዮጵያ ነፃነት በደም የተገዛ ነፃነት ነው፡፡ሚያዚያ 27 ቀን ብሔራዊ እለት ሆኖ የታወጀውም ለነዚሁ ጀግኖች ነው፡፡እኛም በዚሁ አጋጣሚ አመስግነናቸው እናልፋለን፡፡



በድል አድራጊነት አዲስ አበባ ሲገቡ

2ኛው የዓለም ጦርነትን የጀርመን ናዚዝም፣ የኢጣሊያ ፋሺዝም፣ የጃፓን ሚሊታሪዝም ተባብረው እስከመጨረሻው ሊገፉበት ቢሞክሩም የቃልኪዳኑ የአሜሪካ፣ የሶቭየት ኅብረት፣ የፈረንሣይና የእንግሊዝ ጦር በስተመጨረሻ ድል አርጓቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም በተለይ የኢጣሊያ የአፍሪካ ግዛቶች ከፊል ሶማሊያ፣ ኤርትራና ሊቢያ ከኢጣሊያ ተገዥነት ነፃ ወጥተዋል፡፡ ሆኖም ድል አድራጊዎቹ የቃልኪዳኑ አገራት እንደ የጋራ ውሣኔ እስኪያሳልፉ ድረስ ነፃ የወጡ አገሮች በእንግሊዝ ሞግዚትነት መቆየት ነበረባቸው፡፡ እንግሊዝም "ከጠላት የነጠቅናቸው አገራት ናቸው" አለች እንጂ ... "ነፃ አወጣናችሁ" አላለችም ነበር፡፡



ከነጻነት በኋላ ጃንሆይ በቤተመንግስታቸው የኢትዮጲያን ሰንደቅአላማ ሲሰቅሉ

## የእንግሊዝ የበላይነት

የእንግሊዝ ወታደሮችና የኢትዮጵያ አርበኞች በኅብረት ፋሽስቶችን በአጭር ጊዜ ድል አድርገዋል፡፡ የቀድሞው የኢጣሊያ ሶማሌላንድን ወደራሳቸው የሶማሊያ ግዛት መቀላቀል የቻሉትም ሆነ ኤርትራንም ደርበው የያዙት "በጦር ኃይል የተያዙ የጠላት ግዛቶች ናቸው" በሚል ነው፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ግዛት የሆነውን ኦጋዴንን



ቀደም ሲል ኢጣሊያ ከቀድሞው ግዛቷ ከኢጣሊያ ሶማሌላንድ ጋር ቀላቅላው ስለነበር አሁንም እንግሊዞች አብረው ሊወርሱት ፈለጉ፡፡ የእንግሊዝ ጦር ባለስልጣኖች የኢትዮጵያን ነፃነት እውቅና ቢሰጡትም፣ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ባደረጉት ለ2 ዓመት የሚቆይ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ውል አማካኝነት የእጅአዙር ቅኝ ግዛታቸውን ለመቀጠል ሞከሩ፡፡ይህ ውል ጥቂት ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጉ አንቀጾችን በማካተት የቀሩት የእንግሊዝን የበላይነት የሚያረጋግጡ ነበሩ፡፡ሆኖም ለከፋ የሚሰጥ ውል አለነበረም፡፡ንጉሱ ውለታ ስላለባቸው ብቻም ሳይሆን አንዳንድ ጠቃሚ ነገሮች ስለነበሩበትና ለ2 ዓመት ብቻ ስለሆነ ፈረሙበት፡፡የታሪክ አጥኚው ፕ/ር ላጲሶ ዲሌቦ ካካተቷቸው ጥቂቶችን ስናይ፣

"1. በኢትዮጵያ የእንግሊዝ አምባሳደር ከሌሎች የውጭ መንግስታት ተወካዮች የቅድሚያ ክብር ይሰጠዋል፡፡

2. የእንግሊዝ ዜጎች የጦር መኮንኖችና ባለስልጣኖች ለኢትዮጵያ መንግስት የፖለቲካ እና የሕግ አማካሪዎች ሆነው ይሰራሉ፡፡

3. ለእንግሊዝ መንግስት በቅድሚያ ሳያሳውቅ የኢትዮጵያ መንግስት ሌላ የውጭ አገር አማካሪዎችንና ሰራተኞችን ለመቅጠር አይችልም፡፡

4. በአራት ተከታታይ አመታት ውስጥ የእንግሊዝ መንግስት ለኢትዮጵያ መንግስት የ3 ሚሊዮን 250 ሺ ፓውንድ ስተርሊንግ በእርዳታ ሊሰጥ ተስማምቷል፡፡

5. የኢትዮጵያ መንግስት በበኩሉ ለእንግሊዝ የጦር ኃይሎች አገልግሎት የሚያስፈልጉ የማይንቀሳቀስ ሐብትና ንብረት ማለትም የመሬት አገልግሎት ያለክፍያ ለመስጠት ተስማምቷል፡፡

6. የኢትዮጵያ የውጭ ንግድና የገንዘብ ፖሊሲ የሚካሄደው በእንግሊዝ መንግስት የስራ መመሪያና ፈቃድ ይሆናል፡፡

7. የፋሽስት ጦር እስረኞችና የእንግሊዝ ዜጎች በኢትዮጵያ ሕግና ዳኞች አይከሰሱም፡፡

8. ከእንግሊዝ አየር መንገድ በስተቀር ሌላ የውጭ አገር አየር ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ ተወስኗል፡፡

9. በምስራቅ አፍሪካ የእንግሊዝ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ሳይፈቅድ የኢትዮጵያ መንግስት በወታደራዊ ጉዳይ ከሌላ የውጭ አገር መንግስት ጋር ምንም አይነት ስምምነት ለማድረግ አይችልም፡፡

10. አንድ የእንግሊዝ ወታደራዊ ቡድን ከምስራቅ አፍሪካ የእንግሊዝ ጦር ጠቅላይ አዛዥ በሚሰጠው የስራ መመሪያ የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት ይቋቋማል፡፡ ... በሚሉና የባቡር መስመር ሐዲዱን ሳይቀር የበላይ የሚሆኑበትን ውል በጥር ወር 1934 ዓ.ም አስፈረሟቸው፡፡ በዚህም ኢትዮጵያን ለ2 ዓመት ያህል በወታደራዊ ሕግ በጥገኝነት ይዘው ቆዩ፡፡"

የእንግሊዝ ጦር ባለስልጣኖች በሁለት ዓመት የጥገኝነት አገዛዛቸው ወቅት "በኢትዮጵያ የእንግሊዝ ወታደራዊ ተልዕኮ" የሚባል ቡድን በማቋቋም የአገሪቱን የመከላከያ አቋም በዘመናዊ መልክ ለማደራጀት ተስማምተው እንቅስቃሴያቸውን ጀመሩ፡፡ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የበላይ ተቆጣጣሪ ሆኑ፡፡ የኢጣሊያ ጦር ይጠቀምባቸው የነበሩትን ልዩ ልዩ ማቴሪያሎች ከአገር አወጡ፡፡ በአንድ በኩል የንጉሡ የፖለቲካና የጦር አማካሪ ሆነው እየሰሩ፣ በሌላ በኩል በድብቅ ህዝቡን ማጋጨት፣ አርበኛውን ከስደተኛ፣ ስደተኛውን ከአርበኛ በዘዴ እያፋጩ ከውል ውጭ በሆነ መንገድ ኦጋዴንን በቁጥጥራቸው ስር አደረጉ፡፡

ኤርትራ ከ1881 ዓ.ም ጀምሮ በኢጣሊያ ስር ስለነበረችና አሁን እንግሊዞች ስላስለቀቋት ከሌሎች የአፍሪካ ቅኝ ግዛት አገሮች ጋር እጣዋ እስኪወሰን በሞግዚትነት መያዛቸው አግባብነት ቢኖረው እንኳ፣ ኦጋዴን ግን እስከ 1928 ዓ.ም ድረስ ተነጥሎ ስለማያውቅ እንግሊዞች በአዲሱ የኢጣሊያ ክለላ መሰረት አድርገው ወደ ቅኝ ግዛታቸው መቀላቀላቸው ሕገ-ወጥ ነበር፡፡

የእንግሊዝ ጦር ባለስልጣኖች በዚህ ሳይወሰኑ የኤርትራን ህዝብም በዘር፣ በሃይማኖት፣ በጎሳ እየከፋፈሉ ወደፊት ከእናት አገሩ ከኢትዮጵያ ጋር እንዳይቀላቀልና ለነፃነት እንዳይነሳ ያመቻቹት ነበር፡፡

ንጉሱ ኤርትራ ለኢትዮጵያ መሰጠት አለባት ብለው እየተከራከሩ፣ ጭራሽ ኦጋዴንን ሊነጥቋቸው በመሞከራቸው ሊታገሱት አልቻሉም፡፡ የእንግሊዝ አካሄድ መጥፎ አቅጣጫ እየያዘ ሲሄድ ሌላ ረዳት ፍለጋ ማማተር ነበረባቸው፡፡ የሁለት ዓመቱ ውል አልቆ በታህሳስ ወር 1936 ዓ.ም ሌላ ውል ሲፈራረሙ የኦጋዴንን ጉዳይ ቢያነሱትም እንግሊዞች መልቀቅ አልፈለጉም፡፡ ለ2 ዓመት የዘለቁት ውሎች በሁለተኛው ውል አማካኝነት ቢሻሩም የኦጋዴን ጉዳይ አልተመለሰም ነበር፡፡ በተረፈ የ1936ቱ ውል የባቡር መስመር ሐዲዱን ለኢትዮጵያ ያስመለሰ፣ የአምባሳደሩን የበላይነት ያስቀረ፣ ኢትዮጵያ ከየትኛውም አገር ጋር በነፃነት በአማካሪነትም ሆነ በቅጥረኝነት እንዲሁም በማናቸውም አይነት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ቀጥታ ማድረግ የምትችል በአጠቃላይ ሙሉ ለሙሉ ለማለት በሚያስችል ሁኔታ ነፃነቷን የመለሰ ውል ነበር፡፡

ከዚህኛው ውል በኋላም ነው ንጉሡ ከሌሎች ኃያላን አገራት ጋር ጥብቅ ትስስር ለመፍጠር እንቅስቃሴ የጀመሩት፡፡ የኦጋዴን ጉዳይ ግን እስከ 1941 ዓ.ም ድረስ በጅጅጋ ማዕከልነት በእንግሊዞች እጅ ቆይቶ በ1941 ከፊሉን የኦጋዴን ድንበር ማለትም ከእንግሊዝ ሶማሌላንድ ጋር የሚዋሰነውን ሀውድን ቆርሳ ወደራሷ ከቀላቀለች በኋላ "የተከለለ ድንበር" ብላ ወስና ከፊሉን ለኢትዮጵያ መለሰች፡፡ በመጨረሻ በ1947 ዓ.ም ደግሞ እሱንም መልሳ ለቃ ወጣች፡፡



ይህም የኢትዮጵያ መንግስት ሙግትና ክርክር ብቻውን ያስገኘው ውጤት ሳይሆን ዓለም አቀፍ ይዘት ያለውን የኢምፔሪያሊዝም መፍረክረክን ተከትሎ የመጣ ነው፡፡ የኦጋዴን ወደ ኢትዮጵያ መመለስ ደግሞ ከሶማሊያዎች ነፃ መውጣት በኋላ የይገባናል ክርክር አስነስቶ ነበር፡፡ በመጨረሻ ግን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ከተቋቋመ በኋላ በቅኝ ገዥዎች የተከለሉ ድንበሮች ሁሉ በዚያው መፅናት አለባቸው የሚል የውሳኔ ስምምነት ላይ ተደርሶ ኦጋዴን በትክክለኛ ታሪኩ የኢትዮጵያ ሆኖ እንዲቀጥል ሆኗል፡፡

የእንግሊዝ የበላይነት ቆይታ ምንም እንኳ የንጉሠ ነገስቱን መንግስት አስተዳደር ባይጋፋም ሴራ የተቀላቀለበት ችሮታ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት በእነዚያ ጊዜያቶች የድንበር ይገባኛል ጥያቄውንም፣ የአዲስ የአስተዳደር ስራውንም፣ ሕጎችን በማውጣት፣ አዋጆችንና ድንጋጌዎችን በማፅደቅ ... ወዘተ ተጠምዶ ነው የቆየው፡፡

ምንም እንኳ የኦጋዴን ጉዳይ የኃያላን አገራቱን ትኩረት መሳብ ቢሳነውና እንግሊዝ በራሷ የውስጥ ፖለቲካ ችግር ለመልቀቅ ብትገደድም የኤርትራ ጉዳይ ግን በደንብ መገላበጥ ነበረበት፡፡ ንጉሡም ለኤርትራና ለኦጋዴን መመለስ የጣሩት ጥረት እጅግ ከፍተኛና የሚያስደንቃቸው ነው፡፡ ነገር ግን ይህች ዓለም "የኔ" ተብላ የምትወሰንና እንደልብ የሚያደርጓት የየግል ግዛት ያላቸው መንግስታት የተካፈሏት ፈለክ ትሁን እንጂ የአንድ ወይም የጥቂት ልእለ ኃያላን ብቻ ንብረት ናት፡፡ ጥንትም ዛሬም ያው ነው፡፡ የዘመንና የአገዛዙ አይነት ብቻ ይለያያል፡፡

እንግሊዝ በኦጋዴን ተክላው የሄደችው እሾሃማ ችግኝ በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ የሱማሊያንና የኢትዮጵያን ልጆች እያዋጋ አፋጅቷቸዋል፡፡ አውሮፓውያን ኢምፔሪያሊስቶች ምንም እንኳ ሳይወዱ በግድ አፍሪካን ለቀው ቢሄዱም፣ ለዘመናት ስንናጭ እንድንኖር የሚያደርገውን የቤት ስራቸውን አጠናቀው ነው የሄዱት፡፡ ፈፅሞ የአፍሪካን ሰላም አይፈልጉም ነበር፡፡ አሁንም ወደፊትም አይፈልጉም፡፡

የተባበሩት መንግስታት ድርጅትም ቢሆን የጥቂት ኃያላን ፍላጎት ማሳኪያ እንጂ ሐቀኛ ድርጅት አለመሆኑ ጥንትም ዛሬም ግልፅ ነው፡፡ ኃያላኑ እርስ በርስ የተጣሉ ቢመስለንም፣ አፍሪካን በማተራመስ ረገድ አቋማቸው አንድ ነው፡፡ ልዩነቱ አንድ ኃያል አገር ስትከሰት ሰፊውን የአፍሪካ ክፍል የመቆጣጠር እድሏ መስፋቱ ብቻ ነው፡፡ አንድ ግልፅ ነገር አለ፡፡ ይረዱናል፡፡ መልሰውም ያርዱናል፡፡ እንግሊዝ ለቃ የወጣችው በተባበሩት መንግስታት ውሣኔ ይሁን እንጂ ለአሜሪካ መልቀቅ ስለነበረባት ነው፡፡ አሜሪካ በአልበርት አንስታይን ምክር የአቶሚክ ቦምብ ባለቤት ሆና በጃፓን ሁለት አውራጃዎች የፈፀመችው ከፍተኛ ግፍ የበላይነቷን አረጋግጧል፡፡ እግረመንገዷንም በአለም ላይ የምትከተለውን

ፖሊሲ ማመላከቷ ነው፡፡ ጉዳዩ "እኔ ነኝ የማዋጣችሁ" አይነት ነው፡፡ እንዳለችውም ከ2ኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ብቸኛዋ የሶቪየት ኅብረት ተፎካካሪ ሆናለች፡፡

## የኤርትራ ጉዳይ

2ኛው የዓለም ጦርነት በኃያላኑ ትብብር በአሜሪካ፣ በሶቭየት፣ በፈረንሣይና በእንግሊዝ የበላይነት ከተጠናቀቀ በኋላ የኤርትራ ጉዳይ ውይይት እየተካሄደበት ነበርና የእንግሊዝ ሞግዚትነት ቀጥሏል፡፡

ኤርትራን ከ1881 ዓ.ም ጀምሮ ኢጣሊያ በጉልበት ወስዳ እስከ 1933 ዓ.ም ድረስ ስትገዛት ኖራለች፡፡ የኢጣሊያ ጦር ከምስራቅ አፍሪካ እንዲለቅ ከተገደደ በኋላም የእንግሊዝ ጦር ባለስልጣኖች ይዘው ቀደም ሲል እንዳየነው የኤርትራን ህዝብ የመከፋፈል አላማቸውን ገፍተውበታል፡፡

ከኢጣሊያ መልቀቅ ጀምሮ በኤርትራ የተለያዩ ቡድኖች ተፈጠሩ፡፡ በመጀመሪያ "ማኅበረ አገር ፍቅሪ" በሚል የአንድነት ቡድን ተመሠረተ፡፡ ከዚህ ቡድን ተቃራኒ የሆኑ ሌሎች ቡድኖችም ተመሰረቱና የ‹‹ነፃነት››እና የ‹‹አንድነት›› ቡድኖች ሆኑ፡፡ የአንድነት ቡድኑ ሰፊ ህዝባዊ መሠረት የነበረውና ከኢትዮጵያ መንግስትም ድጋፍ ይደረግለት የነበረ ሲሆን፣ ዓላማው ኤርትራን ከእናት አገሯ ከኢትዮጵያ ጋር ማዋሐድ የሚል ነው፡፡

የነፃነት ቡድኑ ድግሞ በእንግሊዞቹ አማካኝነት ተወልዶ ከሁለት ተከፈለና አንዱ የሙስሊም ሊግ /ራቢጣ አል ዓረቢያ/ በሚል ስያሜው መሠረቱን በቆላማው የኤርትራ ክፍል አድርጎ ሲንቀሳቀስ፤ ሌላው ሊበራል ፕሮግሬሲቭ ፓርቲ በሚል ስያሜው መሠረቱን በደጋማው የኤርትራ ክፍል አድርጎ መንቀሳቀስ ጀመረ፡፡

የሙስሊም ሊጉ /ራቢጣ አል ዓረቢያ/ ዓላማው በምዕራባዊ ቆላ የሚኖረው ህዝብ በቋንቋ በሐይማኖትና ጠባይ ከሱዳን ጋር ስለሚመሳሰል ከኤርትራ ተገንጥሎ ከሱዳን ጋር ይዋሐድ የሚል ነው፡፡

ሊበራል ፕሮግሬሲቭ ፓርቲ ደግሞ ዓላማው ከሙስሊም ሊጉ ሳይቃረን ደጋማውና ትግርኛ ተናጋሪውን ክፍል ከመረብ ማዶ ከሚገኘው ወገኑ ጋር አዋህዶ ነፃ መንግስት ለማቋቋም ነበር፡፡ የኤርትራ ትግርኛ ተናጋሪዎችን ከትግራይ ጋር ቀላቅሎ ነፃ አገር ለመመስረት መሆኑ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ የኢጣሊያ ክልሶችና የቀድሞው ወታደሮች እንዲሁም የኢጣሊያ ወዳጆች ተደራጅተው የመሠረቱት "አፍቃሬ ኢጣሊያ ፓርቲ" ሲሆን፤ ዓላማው በነፃነት ሽፋን የኢጣሊያ የበላይነት (በሞግዚትነት) እንዲቀጥል የሚፈልግ ነው፡፡ ከፍተኛ የገንዘብ ድጋፍም ከኢጣሊያ በኩል ይደረግለት ነበር፡፡ ሙስሊም ሊጉም በዓረቦች ይደገፍ ነበር፡፡ እንግሊዝ የወለደችው ፕሮግሬሲቭ ፓርቲ ደግሞ በእንግሊዝ ይደገፍ ነበር፡፡



እንደሚታወቀው እንግሊዝ በወቅቱ ሱዳን ግዛትዋ ስለነበረች የኤርትራን ግዛት ከሱዳን አጣምራ መያዝ ትፈልግ ነበርና ፕሮግሬሲቩን ፈጥራ ማሳደግ ነበረባት፡፡ ሙስሊም ሊጉንም ቢሆን ዓላማው ከተሳካ በተዛዋሪ የእንግሊዝ አላማ መሳካቱ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ሙስሊም ሊጉና ፕሮግሬሲቩ የተለያዩ ይምሰሉ እንጂ በዓላማም በውልደትም አንድ ነበሩ፡፡ ነገር ግን ሁሉም ቅድመ ዝግጅቷ ሳይሳካ ቀረና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ከተለያዩ ገለልተኛ አገሮች የተውጣጡ አባላት ያሉበት ኮሚሽን አቋቁሞ ወደ ኤርትራ ሄደው የህዝቡን ትክክለኛ ፍላጎት እንዲያጤኑ አዘዘ፡፡ ኮሚሽኑ የታዘበው ከፍተኛ የአንድነት ስሜት ነበረና ይሄንኑ ሪፖርት አደረገ፡፡ ሪፖርቱን መሰረት በማድረግም ትዋሐድ፣ ነፃ ትውጣ፣ በፌዴሬሽን ትተሳሰር የሚሉ ተወካይ አገሮች ነበሩ፡፡

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በፌዴሬሽን ትተሳሰር የሚለውን ውሣኔ ተቀበለው፡፡ ይህም ሙሉ በሙሉ የአሜሪካ ይሁንታ የነበረ ሲሆን፤ ኃያሏ አሜሪካ በኤርትራ የሚገኘው "ሬዲዮ ማሪና" የተባለው የመገናኛ ጣቢያዋ ደህንነትን መሠረት ያደረገ ነውና ለጊዜው ኢትዮጵያ እንደምትሻላት መርጣ የፌዴሬሽን ፎርሙላውን ደገፈች፡፡

በዚህ መሠረት የእንግሊዝ የሞግዚትነት አስተዳደር አክትሞ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትተዳደር በመስከረም ወር 1945 ውሣኔው ፀደቀ፡፡ የአንድነት ቡድኑ ፓርቲ መሪ የነበሩት ተድላ ባይሩ በፌዴራሉ መንግስት ስር የኤርትራ ፕሬዝዳንት፣ የሙስሊም ሊጉ ፓርቲ መሪ ሼህ ዓሊ መሐመድ ሙሴ ራዳይን ደግሞ የኤርትራ ምክትል ፕሬዝዳንት ሆነው ተሾሙ፡፡

ሁለቱ አገሮች ለተወሰኑ አመታት በፌዴሬሽን ሲተዳደሩ ቆይተው ከ5 ዓመት በኋላ በ1950 ዓ.ም በፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ውሣኔ ውህደት ተፈጥሮ ኤርትራ የኢትዮጵያ አንደኛዋ ክፍለሀገር /13ኛዋ/ ሆነች፡፡ የኤርትራ ፕሬዝዳንት እና ምክትል ፕሬዝዳንት የነበሩትና ግብራበሮቻቸው ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ስትዋሃድና ፌዴሬሽኑ ሲፈርስ የኤርትራ ክፍለሃገር አስተዳዳሪነት ይሰጠናል ብለው ተስፋ አድርገው ነበር፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ራስ አንዳርጋቸውን ስለሾመባቸው አኩርፈው አገር ጥለው ወደ ግብፅ ተሰደዱ፡፡

በዚህ ጊዜ በመካከለኛው ምስራቅ በስደት የሚኖሩ ሙስሊም ኤርትራውያን ኤርትራ በትጥቅ ትግል ነፃ መውጣት አለባት ብለው በመነሳት የመጀመሪያውን ድርጅት የኤርትራ ነፃነት ግንባር በሚል ስያሜ አቋቋሙ፡፡ ግንባሩ የሙስሊም ኤርትራውያን እንደሆነና ትግሉም የዓረብ ህዝቦች እንደሆነ አድርገው በመነሳታቸው የዓረብ አገራት ለግንባሩ ልዩ ድጋፍ እንዲያደርጉ አነሳሱዋቸው፡፡ የዓረብ አገራት መሪዎችም ድጋፋቸውን ሰጡ፡፡ ሶሪያና ኢራቅ የግንባሩ የረጅም ጊዜ ዋና ደጋፊዎች

ነበሩ፡፡ ግንባሩ የዓረቡን ዓለም ድጋፍ ካገኘ በኋላ ግን አዲስ የተቋቋመ እንደመሆኑ መጠን የሰው ኃይሉ መጎልበት እንዳለበትና ክርስቲያኑንም በትግሉ ማሳተፍ እንደሚገባ ካስረዱ በኋላ የሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግ ሁሉንም ኤርትራዊ ያቀፈ የኤርትራ ነፃ አውጭ ግንባር /ጀብሐ/ን በ1952 ዓ.ም መሠረቱ፡፡ የጀብሐ /በአርበኛ አጠራሩ/ ታጋዮች ለማሰልጠን ሱዳን ካርቱም ውስጥ የማሰልጠኛ ትምህርት ቤት አቋቋሙ፡፡

ጀብሃ ኤርትራዊ የሆነ እድሜውና ጤንነቱ የሚፈቅድለት ሁሉ ወደ ካርቱም እንዲገባና ወታደራዊ ስልጠና እንዲወስድ፣ ለትጥቅ ትግል እንዲዘጋጅ፣ እድሜውና ጤናው የማይፈቅድለት የእርዳታ እጁን እንዲዘረጋ ጥሪ አቀረበ፡፡ በርካታ ወጣቶችም ቀስ በቀስ ተቀላቀሉት፡፡ የኢትዮጵያና የኤርትራ አብሮነትና አንድነት ያልተዋጠላቸው ቡድኖች ሁሉ ከኤርትራ ወጥቶ ካርቱም የገባውን ወጣት እጃቸውን ዘርግተው ተቀበሉት፡፡ በውትድርና ሙያ አሰልጥነው አስታጠቁት፡፡ የዓረቡ ዓለም መሪዎች ለጀብሐ የኢኮኖሚ የፖለቲካና የወታደራዊ ድጋፍ በመስጠት የጀብሐን እድገት በማፋጠን ለትጥቅ ትግል አዘጋጁት፡፡ ጀብሐ ባገኘው ወታደራዊ ስልጠና በመጠቀም መኖሩን ለማሳወቅ ታጣቂዎቹን ወደ ኤርትራ ምዕራባዊ ቆላ አስርጎ አስገባ፡፡ ጅብሐ በሽምቅ ውጊያ ስልት ሲጠቀም ዓመታት ተቆጠሩ፡፡ ድርጅቱ ኃይሉ እያደገ፣ ጥራት ያለው መሣሪያ ከደጋፊዎቹ እያገኘና ልምድ እያዳበረ ሄደ፡፡ ስልቱንም እያሻሻለ በፈንጂ ድልድዮችን ማፍረስ፣ የፋብሪካዎችን፣ የመብራትና የውሃ ጀኔሬተሮችን ማቃጠል ጀመረ፡፡

ቀደም ሲል የኢትዮጵያ መንግስት ጦር መጣ ሲባል ይሸሹ የነበሩት የጀብሐ ተዋጊዎች፣ እያደር ፊት ለፊት እየተጋፈጡ ሽንጣቸውን ገትረው መዋጋት ጀመሩ፡፡ በዚህ አይነት ፅኑ ፍልሚያ ለዓመታት ሲታገሉ ቆይተው ጀብሐ ውስጥ ባሉት ታጋዮች መካከል አለመግባባት ተፈጠረ፡፡

ይህን የአለመግባባት በርካቶች መነሻው የሃይማኖት ጉዳይ እንደነበርና በሙስሊምና በክርስቲያን ታጋዮች መካከል የተፈጠረ ቅራኔ ነበር በማለት ይገልፁታል፡፡ ሙሰሊሙ የበላይ፣ ክርስቲያኑ የበታች ሲሆን ክርስቲያኑ ተነጥሎ ወጣ የሚሉ የተሳሳቱ ገለፃዎች አሉ፡፡ ነገር ግን የክፍፍሉ ዋና ምንጭ ኢሳያስ አፈወርቂም ቆይቶ እንዳመነው የአሜሪካ ስውር ሴራ ነበር፡፡

እስላማዊነትን ተላብሶ የተነሳው ጀብሐ ኃይሉ እየጠነከረ ሲሄድና የዓረቡ ዓለም እገዛ እያጎለበተው የኢትዮጰያ መንግስት ስጋት መሆን ሲጀምር፤ ምናልባትም ድል ቢቀናው ወደፊት ፀረ-አሜሪካ እንደሚሆንና ከወዳጆቹ ከዓረቡ ዓለም ጋር እጅና ጓንት ሆኖ እንደሚቀጥል አሜሪካ ታውቃለች፡፡ ስለዚህ ምንም እንኳ ወዳጅነቷ በወቅቱ ከኢትዮጵያ ጋር እጅግ ጠንክሮ የቀጠለበት ዘመን ቢሆንም፤ በጎን በስለላ ድርጅቷ በኩል



በሃይማኖት ሽፋንም ይሁን በሌላ ምክንያት በጀብሐ ውስጥ ክፍፍል እንዲነሳና እርስ በርስ እንዲፋጁ ማድረግ ነበረባትና እሱን አድርጋለች፡፡

በዚህ መሠረት በጀብሐ ውስጥ "የሙስሊም ታጋዮች የበላይነት ጎልቷል፤ ክርስቲያን ታጋዮች የበታች ሆነዋል፣ ጀብሐ አላማውን እየሳተ ነው ... ወዘተ የሚል አሳማኝ ፕሮፓጋንዳ ተሰራጨና ከተለያዩ የኤርትራ ግዛቶች እየመጡ በመጀመሪያው ግንባር በጀብሐ ስር ሆነው ለመታገል የፈቀዱት ንዑሳን ቡድኖችና ግለሰብ ታጋዮች እንዲያኮርፉ ተደረገ፡፡በዚህም በተለያዩ የውጊያ ቀጠናዎች ተመድበው በሚታገሉ ሠራዊቶች መካከል ክፍፍሉን እንዲያስነሱ የተመለመሉት ተልዕኳቸው ተሳክቶ፤ ግጭቱ ተባብሶ ቀጠለና ከግንባሩ ያፈነገጡ ሦስት ቡድኖች ተቋቋሙ፡፡

እነርሱም በባርካ አካባቢ "የኤርትራ ነፃነት ኃይሎች" (ኦቤላይት)፣ በቀይ ባህር አካባቢ በኦስማን ሳልህ ሳቢ የሚመራው "ህዝባዊ ሀርነት ኃይሎች" እንዲሁም በአካለጉዛይ በኢሳያስ አፈወርቂ የሚመራው "ሰልፊ ናፅናት ኤርትራ" ናቸው፡፡ እነዚህም ሦስቱ በ1964 ዓ.ም ግንባር ፈጥረው "የኤርትራ ነፃነት ህዝባዊ ኃይሎች" የሚል ድርጅት አቋቋሙ፡፡ ወዲያውም በ1965 ዓ.ም "የኤርትራ ህዝባዊ አርነት ግንባር (ህዝባዊ ግንባር ሐርነት ኤርትራ)" ተብለው እንደገና ተደራጁ፡፡ ያለማንም ጣልቃገብነት በራሳቸው ጊዜ ከጀብሐ የተገነጠሉ ሆነው እንዲሳሉና፤ ጉዳዩ የስልጣን ሆኖ እንጂ የቀድሞውን ዓረባዊ የጀብሐ አነሳስ እንዳልጣሉ ለዓረቡ ዓለም በሚጠቁም ሁኔታ የግንባራቸውን ስያሜ በዓረበኛ ቋንቋ "ሻዕቢያ" አሉት፡፡ በዚህ መሠረት በጃንሆይ የስልጣን ዘመን መገባደጃ ዓመታት ላይ ለኤርትራ ነፃነት እንታገላለን ብለው የተሰለፉ ሁለት አበይት ተቃራኒ ድርጅቶች ተፈጥረው ነበር ማለት ነው፡፡

የመጀመሪያው "የኤርትራ ሀርነት ግንባር" በዓረብኛ አጠራሩ "ጀብሐ" እና "የኤርትራ ህዝባዊ ሐርነት ግንባር" በዓርበኛ አጠራሩ "ሻዕቢያ"፡፡ እነዚህ አንድ የነበሩና ባለመግባባት ከሁለት የተከፈሉ ቡድኖች በስልጣን ክፍፍል፣ በሃይማኖት ልዩነት፣ ወይም በዓላማና በርዕዮት መራራቅ አልነበረም የተከፈሉት፡፡ ጀብሐ ውስጥ ክርስቲያኖች ነበሩ፡፡ በሻዕቢያም ውስጥ ሙስሊሞች ነበሩ፡፡ ጀብሐ ውስጥ ክርስቲያን አመራሮች ነበሩ፤ በሻዕቢያ ውስጥም ሙስሊም አመራሮች ነበሩ፡፡ ጉዳዩ የባዕዳኑ ረቂቅ በሁለት ቢላዋ የመብላት ዘዴ የከሰተው ነው፡፡

ሻዕቢያ በተቋቋመ በአጭር ጊዜ ውስጥ የራሱ እዝ ያለው ተዋጊ ኃይል አደራጀና ቆላውን ክፍል ለጀብሐ በመልቀቅ በደጋው አካባቢ መንቀሳቀስ ጀመረ፡፡ በቀጣዩ እቅድ መሠረት ሻዕቢያ የደረሰው ትዕዛዝ ከጀብሐ ጋር ተፋልሞ ድል እንዲያደርገውና፤ ለዚህም ጀብሐ በቆላው አካባቢ ሆኖ በዓረቦች ከሚደረግለት የመሳሪያ እርዳታ የበለጠና የተሻለ

ዘመናዊ መሣሪያ ለሻዕቢያ አሜሪካ እንደምትለግስ ቃል ስለገባች እሱው ተግባራዊ ተደረገ፡፡ ይህ የኢትዮጵያ መንግስት ሳያውቅ በሚስጥር ሲከናወንም፤ ከኢትዮጵያ ጋር ወዳጅ የሆኑት አሜሪካውያን በይፋ ጀንሆይን "ከሻዕቢያ ጋር ጉዳዩን በድርድር መፍታት መሞከሩ የተሻለ እንደሚሆን በመምከርና፤ ከዚያ በፊት ግን ዓረባዊ ስሜት ያለውን ጀብሐን እራሱ ሻዕቢያ እንዲያጠፋው እርዳታዎን ለሻዕቢያ ቢያደርጉ የተሻለ ነው" እያሉ በወዳጅነት ያግባቡ ነበር፡፡

እናም ሻዕቢያ በጀብሐ ላይ ጦርነት ከፍቶ ሁለቱ ሲፋለሙ ከ1964 - 1966 ዓ.ም ድረስ የኢትዮጵያ መንግስት ትንፋሽ ማግኘት ችሎ ቆይቶ ነበር፡፡ የሻዕቢያና የጀብሐ ጦርነት ለዓመታት እንደቀጠለ ቆይቶ ስለነበር በደርግ ጊዜም አልተጠናቀቀም፡፡ በመጨረሻ በሻዕቢያ የበላይነት ተጠናቆ በ1970ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት ጀብሐ ከትጥቅ ትግሉ ጎራ እስከመጨረሻው ተሰናበተ፡፡ አሜሪካም እፎይ አለች፡፡ ከደርግ ዘመን በፊትና በኋላ ሻዕቢያ ቀላልና ከባድ መሣሪያዎች ከምርኮና ከደጋፊዎቹ ከአሜሪካውያን በብዛት አሰባሰበ፡፡

ኤርትራዊ የሆነ ወጣት በውዴታ ግዴታ ለትጥቅ ትግሉ ከጎኑ እንዲሰለፍ በማድረግ የሰው ኃይሉን አሳደገ፡፡ሠራዊቱም ለአመራርና ለቁጥጥር እንዲመች በክፍለ ጦር አደራጅቶ ስለቱንም ለውጦ ወደ መደበኛ /Conventional/ ስልት ተሸጋገረ፡፡

በዚህ መሰሉ አካሄድ የተጀመረው ትግል ከሌሎች የኢትዮጵያ የሽምቅ ተዋጊዎች ጋር የተቀናጀ እንቅስቃሴ ጋር ተዳምረው የደርግን ስርዓት እስከመጣል የደረሱ ሲሆን፤ ትግሉ ከንጉሡ የግዛት ዘመን መገባደጃ ጊዜ አንስቶ የተጀመረ ነበር፡፡ ከዚያም ከደርግ ውድቀት በኋላ ኤርትራ በ1984 ዓ.ም ተገነጠለች፡፡ ይህ ሁሉ ፍልስልሱ የወጣ ነገር የተከፈተው በእነዚያው በኃያላኑ ሸር ጉድ ነው፡፡ ኢሳያስ አፈወርቂ ዛሬ ላይ ሆኖ "እኔን የወለደኝ ሲ.አይ.ኤ ነው" እያለ ከተጣሉ በኋላ አሜሪካ ላይ ይፎትታል፡፡

ያ ሴራቸውም ዛሬም ድረስ ወንድማማች ህዝቦችን እያፋጀ ይገኛል፡፡ ምንትሴ ፓርቲ ቅብጥርሴ ፓርቲ ... ቢባል ያው ዞሮ ዞሮ ወላጆቹ ባዕዳን ናቸው፡፡ መውለድ ብቻ ሳይሆን የረቀቀ ጡጦ እያጠቡ ያሳድጋሉ፡፡ አሳድገው "ጧሪ" ያደርጓቸዋል፡፡መሣሪያ እየገዙ የራሳቸውን ወገን በመፍጀትና በማስፈጀት ያሳደጓቸውን ወላጆች ውለታ ይመልሳሉ፡፡

ጃንሆይ "ጀብሃን አጥፋልኝ" ብለው ለኢሳያስ እርዳታ ሰጥተዋል የሚለውን በይፋ ሲገልፁ የኖሩት ባዕዳኑ፤ ለረጅም ዓመት ራሳቸው ሻዕቢያን እንደረዱና እንደወለዱት ግን ትንፍሽ ብለው አያውቁም፡፡ አዎ ጃንሆይ ሰጥተዋል፡፡ ነገር ግን ጀብሐ ሙሉ ለሙሉ ሙስሊም ባይሆንም የዓረብነት ስሜቱን ፈርተው አሜሪካኖች አካሄዱን ስላልወደዱት እንዲጠፋ



ይፈልጋሉና ሻዕቢያን ለመርዳት በስውር መሳተፋቸውን የሸሸጉት አንሶ፣ ጃንሆይን መገፋፋታቸውንም ረስተው በስተመጨረሻ "ጃንሆይ ሻዕቢያን አምነው ባይረዱ ኖሮ የተሻለ ይሆን ነበር" እያሉ የዛሬውን መገንጠል እያነሱ የተሰማቸውን ሲገልፁ "ሁለቱንም ደርበው መምታት ነበረባቸው" ብለው ይሳለቃሉ፡፡ እነሱ እንዲህ ናቸው፡፡

ያኔ መሳፍንቱን መሣሪያ እየሰጡ በእነአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ያፋጁ እንደነበር ሁሉ አሁንም፣ ምናልባትም ወደፊት ያፋጁናል፡፡

የኤርትራ ጉዳይ ተጀምሮ እስኪጨረስ የነበረው ሂደት በአጭሩ ያየነውን ሲመስል፤ በቁጥር አንዱ መፅሐፍ እንዳየነው በአፄ ዮሐንስ 4ኛ ጊዜ እንግሊዝና ጣሊያን አፄ ዮሐንስን አታለው በ1881 ዓ.ም የነጠቋት ባህረ ነጋሽ /ኤርትራ/ ከ64 ዓመታት በኋላ ከኢጣሊያ አገዛዝ ነፃ ወጥታ፣ በጃንሆይ ልዩ የዲፕሎማሲ ጥረት ወደ እናት አገሯ ተቀላቅላ 40 ዓመታት እንዳሳለፈች በደርግ ውድቀት ማግስት ራሷን የቻለች አገር ሆነች፡፡

መስከረም 1 ቀን 1952 ዓ.ም ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር የተዋሃደችበት 7ኛ ዓመት ክብረ በዓል በታላቁ ቤተ-መንግስት በተከበረ ጊዜ ልዩ ልዩ ሰዎች በጃንሆይ ፊት ንግግር አድርገው ነበር፡፡ ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ተናጋሪ ክቡር አባ ጉግሣ ግደይ ነበሩ፡፡ አባ ጉግሣ ግደይ የኤርትራን ጉዳይ በሚመለከት ያደረጉት ንግግር እንዲህ ይነበባል፡፡

"... ኤርትራ በግርማዊነትዎ ብርቱ ድካምና ትግል ከባዕድ አገዛዝ ነፃ ከወጣች 7 ዓመት ጨርሰን 8ኛውን ዓመት መጀመራችን ነው፡፡ ግርማዊነትዎ ዘወትር የማይደክም ህሊና በፈጣሪው ተማምኖ የጀመረውን እፍፃሜው ሳያደርስ በማይተው ሰፊ በሆነ ልቦናዎ ታግሰው ኤርትራን ከእናት አገሯ ከኢትዮጵያ ጋር አቀላቀሏት፡፡ ኤርትራ በር ናት፡፡ የኢትዮጵያ ጉሮሮ ናት፡፡ ህይወት የሚሰጥ ምግብ የሚያልፍባት ሊባል ይችላል፡፡ ሰው ጉሮሮው ከታነቀ ህይወት የለውም፡፡

ጃንሆይ፤አንድ ሰው በር የሌለው ትልቅ አዳራሽ ቢሰራ እብድ በተባለ ነበር፡፡ ባለፉት ዘመናት ኢትዮጵያም በር የሌላት ውብ ህንፃ መስላ ትታይ ነበር፡፡ ዳሩ ግን ግርማዊነትዎ ሌት ከቀን ያለ እረፍት ጥረው ተጣጥረው በሯን ከፍተው ባህሯን ተረክበው ይኸውና ሰው ሁሉ በነፃነት ወደ ውጭ አገር እንደፈቀደው ይመላለሳል፡፡ ቶሎ ብለውም የመርከብና የአየር ትምህርት ቤት አቋቁመው በሚገባ ሠርተዋል፡፡

ከብዙ ስራ በኋላ እረፍት ለህይወት አስፈላጊ ነው፡፡ ነገር ግን ግርማዊ ጃንሆይ ከዚህ ሁሉ ስራቸው በኋላ እረፍት ያደርጋሉ የሚል ሰው አይገኝም፡፡ ቢገኝም ህሊና የሌለው ሰው ነው ተብሎ በተፈረደበት ነበር፡፡ ...." እያለ ይቀጥላል *(ፍሬ ከናፍር 1952)*

የኤርትራ ተወላጅ የሆኑት ሌላው የእለቱ ተናጋሪ የነበሩት ብላታ መሐመድ ኡስማን የነበሩ ሲሆን፣ ካደረጉት ረጅም ንግግር ውስጥ ጥቂት አንቀጾችን ጨምረን እንለፍ፡፡

"…. ግርማዊ ሆይ ኤርትራ ግዛትዎ በፋሽስቶች ተወርራ ከእናትዋ ኢትዮጵያ ተነጥላ፣ጥንታዊ ክብሯን አጥታ በጠላት አገዛዝ ስር ወድቃ የግርማዊነትዎ አርቆ ተመልካችነት የወጠኑት ተስፋ ባለማቋረጥ እነሆ ጽኑ በሆነ መሠረት ላይ የጣሉት ተስፋ ተፈፅሞ ኤርትራን ከጠላት መንጋጋ ፈልቅቀው ነፃነቷን አልብሰው መታየቷ ግርማዊነትዎ ከፈፀሟቸው እጅግ ሰፊና ታላላቅ ከሆኑት ታሪካዊ የድካም ፍሬዎች አንዱን ምዕራፍ ይዞ የሚገኘው የኤርትራ ከእናትዋ ከኢትዮጵያ ጋር መዋሃድ ነው፡፡

ግርማዊ ሆይ፡- እኛ ኤርትራውያን ህዝቦችዎን ከጠላት አገዛዝ ነፃ ለማውጣት ልዑል እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ በዘመናችን ግርማዊነትዎን ስለሰጠን ከሙሉ ጤንነት ጋር እድሜን እንዲሰጥልን ፈጣሪን ከመለመን በቀር ግርማዊነትዎ ለእኛ ለህዝቦችዎ የፈፀሟቸውን ታሪካዊ ስራዎች ይህን ያህላል ወይም ይህን ይመስላል ብሎ ለመተንተን ችሎታዬ ስለማይፈቅድልኝ ንግግሬን ባጭሩ አቆማለሁ፡፡" *(ዝኔ ከማሁ)*

## ጃንሆይና አዲሱ የመንግስት አወቃቀር

አፄ ኃይለስላሴ ከስደት ከተመለሱበት ከሚያዚያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1966 ዓ.ም ያለ እረፍት ይችን አገር ለመገንባት በተቻላቸው ሁሉ ጥረዋል፡፡ ከስደት እንደተመለሱና ኢትዮጵያም በእንግሊዞች የበላይነት ከነበረችበት ጊዜ ጀምሮ በውስጥ አስተዳደራቸው ጣልቃ ስላልገባች ሕጎችን ሲያወጡ፣ አዋጆችን ሲያውጁ፣ ድንጋጌዎችን ሲደነግጉ … ነው ያሳለፉት፡፡



ነፃነት በተመለሰ ማግስት የአገሪቱ ታላላቅ ሰዎች በሦስት ተከፈሉ፡፡ ስደተኛ፣ አርበኛ፣ ባንዳ በሚል፡፡ ባንዶችን በተመለከተ ወንጀላቸውን የሚያጣራ ልዩ ፍርድ ቤት እንዲቋቋም ተደረገ፡፡ በስደተኞችና በአርበኞች መካከል ግን ከረር ያለ ውዝግብ ተፈጠረ፡፡ በዚህ ላይ አንዱ የአንዱን ስም በከንቱ እያነሳ መወንጀል፣ የግል ቂም በቀልን



ለመወጣት በሐሰት ስም ማጥፋት፣ ሹመት ለማግኘት ያልነበሩትን "ነበርን" ማለትና የመሳሰሉት ጉዳዮች ለፍርድ የማይመች ሁኔታን ፈጠሩ፡፡ ንጉሡ ስደተኞችን ማስከፋት አልፈለጉም፡ ራሳቸውም ስደተኛ ናቸውና፡፡ አርበኞችን ማግለል አይችሉም፤ ከሃዲ መባልን ይፈራሉና፡፡ ባንዶችንም በሙሉ ማጥፋት አይችሉም፣ አገር ምድሩ ባንዳ ነበርና፡፡

በዚህ ውዝግብ አረበኞች ተሸነፉ፡፡ ስደተኞች ትልልቁን ስልጣን ያዙ፡፡ እዚህ ላይ ፍትሐዊ የስልጣን ክፍፍል አለመደረጉ ብዙዎችን አሳዝኗል፡፡ ለተሿሚዎችም ሰፋፊ መሬት ተሰጣቸው፡፡ ንጉሡ ከስደት መልስ የመጀመሪያ ስራቸው ያደረጉት የሚኒስትሮች ምክር ቤት አዲስ ሹመትን ማፅደቅ ነበር፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ማለትም ከ1933 ዓ.ም በኋላ ባሉት ተከታታይ ዓመታት አዳዲስ ሕግና ደንቦች እየቆሙ፣ የነበሩት እየተሻሻሉ አዲስ አስተዳደራዊ መዋቅር ለመዘርጋት ተቻለ፡፡

ለምሳሌ በ1934ቱ የአገር ግዛት ደንብ መሠረት ኢትዮጵያን በ12 የሸዋ፣ የአርሲ፣ የሐረርጌ፣ የሲዳሞ፣ የጋሞጎፋ፣ የከፋ፣ የኢሊባቡር፣ የወለጋ፣ የጎጃም፣ የበጌምድር፣ የወሎ፣ የትግራይ ተብለው ተከፈሉ፡፡ "የአውራጃ ግዛት" ተብለው ተከፍለው የነበረ ቢሆንም በኋላ በ1938 ጠቅላይ ግዛት ተሰኙና ለግብር አሰባሰብ ምቹ እንዲሆኑ ተደረገ፡፡ ከዚያ በኋላ ነው ኤርትራ ስትጨመር 13፣ በሐረርጌ ግዛት ስር የነበረው ባሌ ራሱን ሲችል 14 የሆነው፡፡ አዲስ አበባም "እምብርት" ተብላ በ1940 የጠቅላይ ግዛት ማዕረግ ተሰጣት፡፡

በመጀመሪያው ሹመት የአገር ግዛት፣ የፅህፈት፣ የውጭ ጉዳይ፣ የትምህርት፣ የፍርድ፣ የንግድና ኢንዱስትሪ፣ የፖስታ የቴሌግራፍና የቴሌፎን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እንደ አዲስ ተዋቀሩ፡፡ በየጊዜውም እየበዙ፣ እየሰፉ ሄደዋል፡፡ በዚህ መሰሉ የማዕከልና የክፍለ አገር ክፍፍል መሠረት አዲሱ የአገር ግዛት ደንብ ተግባራዊ ሆነና ዋናውን ስልጣንና ሰፊውን ስራ የአገር ግዛት ሚኒስቴር የሚሰራው ሆነ፡፡



አዲስ የተቋቋመው የሚንስትሮች ካቢኔ

ከንጉሡ የሚመነጨውና በማዕከል ከሚኒስትሩ ቢሮ ወደታች የሚተላለፈውን የስራ አመራር በክፍለ አገር ደረጃ በተግባር ላይ የሚያውሉ የአገር ግዛት ሚኒስትር ባለሥልጣናትና ሠራተኞች፤ 1. ጠቅላይ አገር ገዢዎች፣ 2. ዳይሬክተሮች፣ 3. ፀሐፊዎች፣ 4. የአውራጃ፣ የወረዳና የምክትል ወረዳ ገዢዎች፣ 5. ዳኞች፣ 6. የኃይል አዛዦች፣ 7. ወታደሮች፣ የፖሊስና የፀጥታ ተወካዮች፣ 8. ሌላ አግባብ ያላቸው፣ ለምሳሌ የገንዘብና የጤና ሚኒስቴር መስሪያቤቶች ተወካዮች ናቸው፡፡

የአገር ግዛት ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ሁለት ዋና ተግባራት አሉት፡፡ በአንድ በኩል በፀጥታ፣ በፖሊስ፣ በወህኒ ቤት፣ በጠረፍ ጥበቃና በኢሚግሬሽን ክፍሎች አማካኝነት የመንግስትን ደህንነትና ፀጥታ መጠበቅ፤ በሌላ በኩል በልዩ ልዩ የግብር፣ የቀረጥና የብድር ምንጮች የመንግስትን የገንዘብ ገቢ መጠን ማሳደግ ናቸው፡፡

በአዲሱ መንግስታዊ አወቃቀር ላይ ታማኝ ባለሥልጣናትን እየሾሙ፤ የሁሉም የበላይ ንጉሡ ነገስቱ ሆነው ሚኒስትሮች እስከ ቀበሌ ድረስ ስራው በተዋረድ እንዲቀጥል እያደረጉ በደሞዝ መስራት ጀመሩ፡፡እንደተባለውም የመንግስት ገቢ በግብር፣በቀረጥ፣በአገልግሎት ክፍያዎች ላይ ተመሰረተ፡፡የገቢ አሰባሰብን በተመለከተም በተለያዩ ጊዜያት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች እየወጡ ተግባራዊ ተደረጉ፡፡

ከ1928 - 33 የነበረው የፋሽስቶች ቆይታ የንጉሡን ስልጣን ለማጠናከር ረድቷል፡፡ ለአብነት ያህል አንዳንድ ተቃዋሚዎቻቸው ተደምስሰዋል፣ የየመኳንንቱና መሳፍንቱ የግል ጦር ፈርሷል፡፡ ምንም እንኳን ጣሊያን ዝሙትን አስፋፍቶ፣ ባህልን በርዞ፣ አንድ ህዝቦችን ለራሱ



በሚያመች መንገድ በብሔር፣ በጎሳ፣ በሃይማኖት ለመከፋፈል የሸረበው ሴራ ባይዘነጋም፤ አንዳንድ የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎቹን ለራሱ መጠቀሚያ ሲል ለማከናወን እንቅስቃሴ ጀምሯል፣ በሕግ ሽረው ያልሻሩትን የባሪያ ስርዓት ሙሉ ለሙሉ እንዲደመሰስ አስችሏል፡፡በዚህም በገንዘብ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰዎች በመበርከታቸው ጅምሩን ካፒታሊዝም አጠናክረው እንዲቀጥሉበት ረድቷል፡፡

ከጦርነቱ በኋላ በእንግሊዝ ተፅዕኖ ስር ቢሆንም፤ በትምህርት፣ በአስተዳደር፣ በጦር፣ በፖሊስ፣ በፀጥታ፣ በቢሮክራሲ፣ በመንገድ፣ በመገናኛ በንግድና በገንዘብ ስራዎች፣ ድርጅቶችን መልሶ ለመገንባት በተወሰዱ እርምጃዎችና ኤርትራ ወደ እናት አገሯ የመቀላቀሏ ጉዳይ ተደማምረው የጃንሆይን ስልጣን የበለጠ ሲያጠነክሩ፤ በሌላ በኩልም የካፒታሊዝሙ ስርዓት የበለጠ እያደገ እንዲሄድ በር ከፍቷል፡፡

ንጉሡ ከእንግሊዝ በኋላ በአሜሪካ፣ በስዊድን፣ በስዊዝ፣ በፈረንሣይ፣ በህንድ፣ በዩጎዝላቪያና በጃፓን አሰልጣኞችና አማካሪዎች፤ እንዲሁም እርዳታና እገዛ እየተደገፉ ሁሉንም ነገር በቁጥጥራቸው ስር ለማድረግ ችለዋል፡፡

የጃንሆይ መንግስት ቢሮክራሲ ላዕላይ መዋቅሩ በተለያዩ በአዋጅ በሚቋቋሙ መስሪያ ቤቶች እየደረጀና ሕግ እየወጣለት ሲቀጥል፣ ታህታይ መዋቅሩ በልዩ ልዩ የገቢ አሰባሰብ መሰረቱን ጥሎ በየእለቱ እየዘመነና እየጠነከረ እንዲቀጥል ሆነ፡፡

በወቅቱ የእንግሊዝ የበላይነት ጠንከር ያለ ነበርና የገንዘብና የወጪ ንግድ ቁጥጥሩ በእንግሊዞች የበላይነት ስር ነበር፡፡ ኢትዮጵያም የራሷ የሆነ የመገበያያ የወረቀት ገንዘብ አላሳተመችም፡፡ የእንግሊዝ የሁለት ዓመት ውል ካበቃ በኋላ ግን ነገሮች መልካቸውን ቀየሩ፡፡

ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያ የመገበያያ ገንዘቦች የማሪያ ትሬዛ፣ የኢጣሊያ ሊሬ፣ የእንግሊዝ ፓውንድ ስተርሊንግና የምስራቅ አፍሪካ ሽልንጎች ነበሩ፡፡ የገንዘብ ቦርዱም በእንግሊዝ ለንደን የነበረ ሲሆን፣ ከሦስቱ የቦርድ አባላት ሁለቱ እንግሊዛውያን አንዱ ኢትዮጵያዊ ናቸው፡፡

በ1937 ዓ.ም ኢትዮጵያ የራሷን "የኢትዮጵያ ብር" አሳተመች፡፡ ስርዓት ያልነበረው የኢኮኖሚ መዋቅር ዘመናዊ እየሆነ ሄደ፡፡ እጅግ ዘመናዊ የተባለው የግብር አሰባሰብና አጠቃላይ የበጀት ስርዓቱ ተግባራዊ መሆን የጀመረው በ1953 ይሁን እንጂ ከነፃነት በኋላ ዘመናዊ የበጀት ስርዓትን ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡

ከነፃነት በኋላ ንጉሡ ኢትዮጵያዊ ምሁራንን ያሰማሩት በአምባሳደርነት እየሾሙ ነበር፡፡ አገር ውስጥም በትልልቅ የመንግስት ተቋማት ታማኛቸው የሆኑ ምሁራንን መድበዋል፡፡ የእንግሊዞች የበላይነት በነበረ ጊዜ የውጭ ግንኙነቱን በአምባሳደሮቻቸው አማካይነት እንዲከናወን

አድርገዋል፡፡ በዚህም ጥረት ለምሳሌ በሰኔ ወር 1936 ዓ.ም ቁጥራቸው ከ250 በላይ የሆኑ አሜሪካውያን የልዩ ልዩ ሙያ ባለቤቶች በፍራንክሊን ሩዝቬልት መልካም ፈቃድ ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል፡፡ እነዚህም በሲቪሉ ዘርፍ እንጂ በፖለቲካው ጣልቃ ገብነት አልነበራቸውም፡፡ ኢንጅነሮች፣ የቴክኒክ አማካሪዎች፣ ነርሶች፣ ዶክተሮች፣ መምህራን፣ አናፂዎችና የልዩ ልዩ ዕደጥበብ ባለሙያዎች ነበሩ፡፡

ከ1937 በኋላ ግን ንጉሡ በነፃነት ከተለያዩ ስልጡን አገራት መንግስታት ጋር ግንኙነት በመመስረት አገር ግንባታውን በኢኮኖሚ፣ በጦር፣ በፖለቲካ፣ ወዘተ በስፋት ተያያዙት፡፡ ወደፊት እንደምናገኘው ሰፋ ያለው እገዛ ከአሜሪካ ነበር የተገኘው፡፡ የሚገርመው ግን ጃንሆይ አገር አይመርጡም፡፡ በአሜሪካ ድጋፍ ስራቸውን እየሰሩ በጎን ደግሞ የሶሻሊስቷን የዩጎዝላቪያን ድጋፍ ፈለጉ፡፡ አገኙም፡፡ ማርሻል ብሮዝ ቲቶ ምርጥ ወዳጅ ሆነው ተገኙ፡፡

የዩጎዝላቪያ እገዛ በኢኮኖሚው ዘርፍ ነበር፡፡ በተለይ በ1949 ዓ.ም የመጀመሪያውን ዘመናዊ የ5 ዓመት የበጀት እቅድ ነድፈው አበረከቱ፡፡ በዚህም ጥሩ የሚባል ኢኮኖሚያዊ እመርታ ታዩ፡፡ ከዚህ በኋላ በተከታታይ በወጡ የበጀት እቅዶች ዘርፈ ብዙ ስራዎች ተሰሩ፡፡ ይህም ከከፍተኛው የነዳጅ ማጣሪያ ፋብሪካ ጀምሮ እስከ አነስተኛ ተመሣሣይ የኢንዱስትሪ ዘርፍ፣ ከትልልቅ የትራክተር እርሻዎች እስከ አነስተኛው ተመሣሣይ የግብርና ዘርፍ፣ ከተራ አውራ ጎዳናዎች እስከ ዘመናዊ አየር መንገድ፣ በጦሩም ረገድ ከእግረኛ እስከ ታንከኛ፣ ከአየር ኃይል እስከ ባህር ኃይል በስልጡን አገሮች ድጋፍ ያቀላጥፉት ጀመር፡፡ እነዚህንም በአጭሩ በተከታታይ ለማየት እንሞክራለን፡፡

የጃንሆይ መሬትና እርሻ

‹‹በ1930ዎቹ አጠቃላዩ የኢትዮጵያ የህዝብ ቁጥር የኤርትራን ህዝብ ሳይጨምር 20 ሚሊዮን ያህል ነበር፡፡ አጠቃላይ የኢትዮጵያ የመሬት ቆዳ ስፋት ደግሞ 120 ሚሊዮን ሔክታር ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ 80 ሚሊዮን ሔክታሩ ለግብርና ስራ ተስማሚ እንደነበር ተገምቷል››(ፕ/ር ላጵሶ 1983)

በ ፕ/ሩ ጥናት እንደተመለከተው በዚያ ወቅት 57 ሚሊዮን ሔክታር በመንግስት ይዞታ ስር የነበረ ሲሆን፤ ከዚህም ውስጥ 40 ሚሊዮን ሔክታሩ የሚገኘው በደቡብ፣ 15 ሚሊዮን ሔክታሩ በመሐልና በምዕራብ፣ 2 ሚሊዮን ሔክታሩ በሰሜን ነበር፡፡ ከ1933 - 1966 ዓ.ም የኢትዮጵያ ዋና ዋና የመሬት ይዞታ አይነቶች ደግሞ 1ኛ. የመንግስት ይዞታ፣ 2ኛ. የታላላቅ ጉልተኛ መሳፍንቶች፣ መኳንንቶች፣ ባላባቶች፣ ነጋዴዎች፣ የቤተ-ክርስቲያን፣ የጦርና የፖሊስ ሹማምንቶች ይዞታ፣ 3ኛ. የእርሶ አደሮች



የማሳ ይዞታ ተብለው ይታወቃሉ፡፡ ንጉሡ በተለይ ከስደት መልስ ለታላላቅ ሹማምንት በልዩ ሁኔታ የመሬት ችሮታ አድርገዋል፡፡

ከ1933 ጀምሮ 5 ሚሊዮን ሔክታር መሬት ለሹማምንቶቻቸው በስጦታ በርስትነት ለግሰዋል፡፡ እነዚህም የመንግስት ባለሥልጣን እንደመሆናቸው መጠን በከተማ እየኖሩ በተቀጣሪ ያሳርሳሉ፡፡ በዚህም ላይ ግብር አይከፍሉም ነበር፡፡ በተጨማሪም የመሬት ስጦታው ወደ ደቡብ ነበር፡፡ 20 ከመቶ ያህሉ የቤተ-ክርስቲያን ርስት ነው፡፡ ቤተ-ክርስቲያንም ለመንግስት ግብር መክፈል አታውቅም፡፡ አልለመደችም፡፡

ቀደም ባለው ጊዜ በኢትዮጵያ ለቤተ-መንግስት፣ ለቤተ-ክርስቲያን፣ ለጦርና ለጉልተኛ ባለሥልጣኖች የገባሩ አገልግሎት የምግብ ግብር፣ የምርት ስፍር፣ የአስራት መዋጮ እየተባለ በአይነት ነበር የሚገበረው፡፡ በኃይለስላሴ ጊዜ ግን በገንዘብ እንዲለወጥ ሆኗል፡፡ ሙሉ ለሙሉ የነበረ ባይሆንም፡፡

ጃንሆይ “የ1923ቱን ሕገ-መንግስት መሠረት በማድረግ የመንግስት ገቢ በገንዘብ ግብር እንዲሆን አውጀዋል፡፡ በአዋጁም መሠረት ከ1926 ፣ 1927 ዓ.ም ድረስ ከአገሪቱ መኳንንት፣ ሻለቃና ባለማደሪያ ሹማምንቶች፣ ከከተማ ነዋሪዎችና ከገጠር ገባሮች በአንድነት ለመንግስት የገንዘብ ግብር 2.5 ሚሊዮን ብር ገቢ ተሰብስቦ እንደነበር” የፕሮፌሰሩ ጥናት ያመለክታል፡፡

ንጉሡ በ1934 በታወጀው የመሬት ግብር አዋጅ መሠረት ከወረራው በፊት በመሬት ላይ ተጥሎ የነበረው ግብር ህዝቡ በጦርነቱ ስለተጎዳ በሚል በግማሽ ቀነሱት፡፡ በ1927 በአንድ ጋሻ መሬት 30 ብር ይከፈል የነበረውን 15 ብር እንዲሆን ተደርጎ ነበር፡፡ በአዲሱ አዋጅ መሠረትም አንድ ወጥ ብሔራዊ የመሬት ግብር ሕግ ሲደነገግ ከአፈሩ ልማት አኳያ “ለም”፣ “ለምጠፍ” እና “ጠፍ” ተብሎ በሦስት ተመደበ፡፡ በአገር አቀፍ ደረጃ ለአንድ ጋሻ ለም መሬት በአመት 15ብር፣ በለምጠፍ 10 ብር በጠፍ 5 ብር እንዲሆን ተወስኖ የነበረ ቢሆንም፤ በተሻሻለው በ1937ቱ የመሬት ግብር አዋጅ ግን ለለም በዓመት 50 ብር ለለምጠፍ 40 ብር፣ ለጠፍ 15 ብር እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ይህ የሆነውም በአይነት ይከፈል የነበረውን ተጨማሪ የአስራት ግብር በጥሬ ገንዘብ ለመተካት ሲባል ነው፡፡ የዋጋ ተመኑ በስራ ላይ የዋለው በሸዋ፣ በሐረር፣ በወሎ፣ በወለጋ፣ በአርሲ፣ በሲዳሞ፣ በኢሊባቡር፣ በጋሞ ጎፋና በከፋ በሚገኙ የተለኩ መሬቶች ላይ ነበር፡፡

በሸዋ የርስት መሬት ላይ ዝቅ ያለ ተመን ሲጣልበት፣ የጎጃምና የበጌምድር መሬት ግን ግብሩ በቀድሞው ተመን ሆኖለት በአስራት በተገመተው እንዲከፍል ተደረገ፡፡ ከዚሁ አዲስ እርምጃ ጋር በተያያዘም

ቀደም ሲል በገበሬው ላይ ተጭነው የነበሩት ልዩ ልዩ ክፍያዎችና የጉልበት ስራዎች ተሽረዋል፡፡

ነገር ግን አዋጁ በበታች ሹማምንት እየተጣሰ ገበሬው ሕጉ-ወጥ ጭቆናው አልቀረለትም፡፡ የንጉሡ ስርዓት ያለው የግብር አሰባሰብ ዓላማም ግቡን ሊመታ አልቻለም፡፡ በስተመጨረሻ ከፍተኛው ዓመታዊ ግብር 80 ብር የደረሰበት ሁኔታ ሲኖር፣ በ1958 ዓ.ም በታወጀው 3ኛው የመሬት ግብር አዋጅ መሠረት ባለመሬቶች ግብሩን እንደቀድሞው ለጉልተኛ ሳይሆን በቀጥታ ለመንግስት እንዲያስገቡ ተደነገገ፡፡

ፕ/ር ባህሩ ዘውዴ "ይህ እርምጃ ተፈፃሚነት ቢያገኝ ኖሮ ርስተጉልትንና ሲሶ ጉልትን የመሻር ያህል ነበር፡፡ ነገር ግን እንዲህ አይነቶቹ ባለመብቶች በተለይም ርስተ ጉልተኞች ከፖለቲካ ስልጣን ጋር ባላቸው የተሳሰረ ግንኙነት ተጠቅመው የአዋጁን ተግባራዊነት ለማሰናከል ችለዋል፡፡ የቤተ-ክህነትን የጉልት መብት የመንካቱ ጉዳይ እንደሆነ ከቶም አልታሰበም" በማለት ያብራሩታል፡፡

የአፄ ኃይለስላሴ መንግስት ሲነሳ የመሬት ግብርና የገበሬ አመፅ የሚሉ ቃላቶች አብረው ይጠቀሳሉ፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ዋናው ሀብት ምናልባትም ብቸኛው ያኔ መሬት ነው፡፡ ሹመትና ሽልማት መሬት፣ የገቢ ምንጭ መሬት፣ ሁሉም ነገር መሬት ነውና የንጉሡ ዘመናዊ አስተዳደር ዝርጋታም ሆነ የመንግስት ገቢ በመሬት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ የመንግስትን ገቢ ለማሳደግ የመሬት ግብር ግድ ነው፡፡ ንጉሡን ወደ መሬት ያወረዳቸውም መሬት ነው፡፡ ጥፋታቸው የመሬት ግብር መጣላቸው ሳይሆን ሰፋፊውን መሬት ለሹማምንቱ መስጠታቸው፣ ሰጥተውም ግብሩን አለመጣላቸው፣ በክልሎች ደረጃ ከዘመኑ ፖለቲካ ጋር በተያያዘ ችግር ፍትሐዊ የግብር አጣጣል ማድረግ አለመቻላቸው ነው፡፡ ሆኖም በተደጋጋሚ የተለያዩ እርምጃዎችን ወስደዋል፡፡በ1960 የመጨረሻውን የእርሻ ገቢ ታክስ አወጁ፡፡ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ከግብርናው የሚገኘው ገቢ እጅግ ዝቅተኛ ነበር፡፡

የመጨረሻው አዋጅ እጅግ ፍትሐዊ የተባለና ሁሉንም ያማከለ፣ በመሬቱ አይነት ሳይሆን በምርት መጠን የሚለካ፣ ከፍተኛ ገቢ ያላቸውን በርከት ያለ ግብር የሚጠይቅ ሆኖ ቢታወጅም ማን ይፈፅመው? ገማች ኮሚቴዎች ማዳላት ጀመሩና አበላሹት፡፡ ምንም እንኳ ሰፊው መሬት ለግብርና ምቹ ሆኖ ቢገኝም፣ በተለያዩ ችግሮች ምክንያት በግብርናው ዘርፍ ተጨባጭ ለውጥ ሊመጣ አልቻለም፡፡ ለዚህ ደግሞ ዋናው ችግር ዘመናዊ የማምረቻ ግብአት አለመኖር ነው፡፡ ስለዚህ በውጭ ንግድ ላይ ያተኮረ ከፍተኛ የትራክተር እርሻ ተመራጭ ነበርና እሱኑ ተግባራዊ አስደረጉ፡፡



የዚህ ተሳታፊዎች መንግስት፣ የውጭ ባለሃብቶችና የአገር ውስጥ ባለሃብቶች ናቸው፡፡ ባለመሬቶች የራሳቸውን መሬት ሲያርሱና ሲያሳርሱ፣ ሌሎች መሬት ተከራይተው ማረስ ጀመሩ፡፡ እነዚህ በስፊ የእርሻ ልማት የተሰማሩ ባለሃብቶች በዋናነት በደቡብ ሸዋና በሁመራ አካባቢ ነበር፡፡ ለአብነትም በእንግሊዛዊው ሚቼል ኮትስ ኩባንያ የተቋቋመው የተንዳሆ የጥጥ እርሻ ልማት በአዋሽ ሸለቆ፣ በኤርትራ የጣሊያን ከበርቴዎች ያቋቋሙት የኤላበረድ እርሻ፣ በመንግስት በኩል በ1954 በአዋሽ ሸለቆ ባለስልጣን አማካኝነት የእርሻ፣ የአግሮ ኢንደስትሪና የሐይድሮ ኤሌክትሪክ እንቅስቃሴዎች ይካሄዱ ነበር፡፡

ለተራው ገበሬም "ሁለገብ የእርሻ ልማት" በተሰኘ ፕሮግራም ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ በማደል ግብርናውን ለማሳደግ ተሞክሯል፡፡ ይህም የእርሻ ዘዴና ጥቅም ማስፋፊያ በሚባለው የመንግስት ተቋም አማካይነት ይከናወን ነበር፡፡ ከዓለም ባንክ በተገኘ እርዳታ የተቋቋመው የወላይታ እርሻ ድርጅት "ዋዱ" በሰፈራ ፕሮግራሙ አማካይነት የመሬት መጣበብን ለማቃለል በመቻሉ ደሃውን ገበሬ በማገዝ ውጤታማ ነበር፡፡

የስዊድን ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት /ሲዳ/ ገበሬውን በልማት ሊያግዝ ቢቋቋምም ሐብታም ባለመሬቶች እነሱን የሚያግደውን ሕግ ጥሰው ዋና ተጠቃሚዎች ሆኑበት፡፡ ይህም የጭላሎ እርሻ ልማት "ካዱ" በመባል የሚታወቀው ነው፡፡ ድሆችን ሊረዳ ተቋቁሞ ማናለብኞች ተሻሙት ማለት ነው፡፡ ይሄው ነው፡፡ ፍትህ ከሌለ እርሻ ብቻ ሳይሆን "መና"ም ቢወርድ አይሳካልንም፡፡

የትራክተር እርሻ በተስፋፋበት ጊዜ ለበርካታ ጭሰኞች መፈናቀል ምክንያት ሆነ፡፡ ምክንያቱም ባለመሬቶች በጭሰኛ ከማሳረስ ይልቅ መሬት ማከራየቱን አዋጭ ሆኖ አገኙት፡፡ እለት እለት የጭሰኛው ችግር እየተባባሰ ስለሄደም መንግስት የተለያዩ የመፍትሄ እርምጃዎችን ለመውሰድ ቢሞክርም አጥጋቢ አልሆነም፡፡

በዚህ ረገድ መንግስት የጭሰኛውን ሁኔታ በሚመለከት በ1954 አንድ ኮሚቴ እንዲቋቋም አድርጎ ነበር፡፡ ይህ ኮሚቴ በ1957 ወደ "የመሬት ይዞታ ማሻሻልና ልማት ባለስልጣን" አድጎ ከዓመት በኋላ የመሬት ይዞታና አስተዳደር ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ለመሆን በቃ፡፡ በሂደቱም የጭሰኛውን ችግር ለመፍታት ተንቀሳቀሰ፡፡ "ነገር ግን የሚወጡት ረቂቅ ሕጎች /የጭሰኛውን ጥቅም በሚመለከት/ የባለመሬቱን መደብ ጥቅም ስለሚፃረሩ ምክር ቤቱና አባላቱ እያደናቀፉና እያጓተቱ አዘገዩት፡፡ የጭሰኛውን ችግር ይፈታል ተብሎ የታመነበት የ1957ቱ ረቂቅ ሳይፀድቅ በመቅረቱም ነው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች "መሬት ላራሹ" ብለው ሰልፍ የወጡት" እንደ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ

አገላለፅ፡፡ ከዚያ በኋላ ባሉት ዓመታትም ተመሣሣዩ የመጨረሻ እቅድ /ረቂቅ/ ሳይሰምር ቀርቷል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለም ድርቅ፣የአንበጣ መንጋና ሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎች ባደረሱት ቀውስ በ1950 በትግራይ፣ በ1958 በወሎ፣ ጥቂት ቆይቶ በ1965ም በዚያው በወሎ ተደጋጋሚ ድርቅና ረሃብ ተከስቶ የብዙ ዜጎችን ህይወት ቀጠፈ፡፡

ተሸፋፍኖ የቆየው ረሃብ በዩኒቨርስቲው ማኅበረሰብና በውጭ ጋዜጠኞች ተጋለጠ፡፡ የተፈጥሮ አደጋው እንዳለ ሆኖ፤ ዋናው ተጠያቂ ሙስና ነው፡፡ ሙስና ጉቦ መቀበል ብቻ አይደለም፡፡ ይህን ጉዳይ በስተመጨረሻ በሰፊው እንቃኘዋለን፡፡ የጃንሆይ አስተዳደርና መሬት በጣም በአጭሩ ያየነውን ሲመስል፤ በአጠቃላይ የግብርናው ዘርፍ በየጊዜው እየተስፋፋ ሄዶ በ1966 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት የመጀመሪያውን ደረጃ ይዞ 49.3 በመቶ ቢደርስም በውጤቱ ህዝብን መመገብ የሚችል አልሆነም፡፡

ጃንሆይና ንግድ

ንግድ በጃንሆይ ዘመን ነው የዘመነው፡፡ አብዛኛው ወደ ውጭ የሚላኩ ሸቀጦች የእርሻ ውጤቶች ነበሩ፡፡ከጠቅላላው የውጭ ንግድ 60 በመቶውን የሚይዘው በዘመናችው ግጥም ተገጥሞ በጅማ ወጣቶች ዜማ የተሰራለትና ዛሬም ድረስ የሚዘመርለት ቡና ነው፡፡ ቀጥሎ ቆዳና ሌጦ ነው፤ ከዚያም ጥራጥሬና የቅባት እህሎች ይከተላሉ፡፡

የወጪና ገቢ ንግዱ ከወደመጀመሪያ ተመጣጣኝ ስላልነበረ የውጪ ንግዱ ውጤት እዚህ ግባ የሚሉት አልነበረም፡፡ ከውጭ የሚገቡ ሸቀጦችን አገር ውስጥ ማምረት ሲጀመርና ኢንዱስትሪዎች ሲስፋፉ ግን መጠነኛ ለውጥ ታይቷል፡፡ የንግድ ሂደቱ የአገሪቱን የዓለም አቀፍ ግንኙነት አቅጣጫ የተከተለ በመሆኑ 40 በመቶው ከአሜሪካ ጋር ሲሆን በተለይ የቡና ንግድ 70 በመቶው በአሜሪካ ገበያ የሚጣራ ነበር፡፡

በገቢ ንግድ ረገድ ደግሞ በቅደም ተከተላቸው ጣሊያን፣ ጃፓንና አሜሪካ በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ ንግዱ ኪሣራ መሆኑ ሲታይም ነው የኢንደስትሪ ፖሊሲው ላይ ማተኮር ያስፈለገው፡፡ የውጪ ሸቀጦች ዋጋ እየወረደ፣ የገቢ ሸቀጦች ዋጋ እየናረ ብዙ ኪሳራዎች ታይተው ነበር፡፡ የአገር ውስጥ ንግድን በሚመለከትም ቀደም ሲል በወደቦች አቅራቢያ በሚገኙ የኢትዮጵያ ከተሞች ተጧጡፎ በመሐል ከተማው የቀዘቀዘ የነበረው የአገር ውስጥ ንግድ ወደ አዲስ አበባ አተኩሯል፡፡

የቀድሞው የምኒልክ የአራዳ ገበያ ከወረራው ጊዜ ጀምሮ "ፒያሣ" በሚል አዲስ ስም ተሰይሞ የነጮች መገበያያ ሆኖ ነበር፡፡መርካቶን ለሐበሻ መከለላቸውም ይታወቃል፡፡ ስለዚህ የችርቻሮው ንግድ ከፒያሣ ወጥቶ ወደ መርካቶ ተዛወረ፡፡ ፒያሣ ላይ ሰፍረው ይነግዱ የነበሩ የውጭ



ዜጎች የበላይነታቸው በታታሪው የጉራጌ ብሔረሰብ እየተሸረሸረ ከስሟል፡፡ የመርካቶ ጉራጌዎች በየመን ዓረቦች ቁጥጥር ስር ሆኖ የነበረውን የችርቻሮ ንግድ ለመቆጣጠር የቻሉትም ከነፃነት በኋላ ነው፡፡

አንዳንድ የላይኛው መደብ አባላትም አስመጪና ላኪ በመሆን አንዳንዴ በግላቸው፣አንዳንዴ በመንግስት ሽፋን ተሰማርተውበታል፡፡በመንግስት ደረጃም ብሔራዊ ኮርፖሬሽን የተባለው ድርጅት ተቋቁሞ የእህል ምርትን ለአገር ውስጥ ዜጎችም፣ ለውጭ አገር መንግስታትም ይሸጥ ነበር፡፡ ይህ ድርጅት በ2ኛው የዓለም ጦርነት የኢኮኖሚ ቀውስ ለደረሰባቸው ለአውሮፓውያን ጦርነቱ እየተካሄደ በነበረባቸው ተከታታይ 4 ዓመታት የእህል ምርቶችን በመላክ በሚሊዮን የሚቆጠር ትርፍ አግኝቷል፡፡ ከዚያም የኮርፖሬሽኑን ተሞክሮ መሠረት በማድረግ የውጭ ንግዱን ለመቆጣጠር ወይም ለማመጣጠን ሌሎች ተመሣሣይ የንግድ ተቋማት በመንግስት ደረጃ ተመስርተዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ "የንግድና የትራንስፖርት ማኅበር" ተብሎ የተሰየመው ድርጅት በቀድሞው አጠራር "ማኅበር ቤት" የሚባለው የተለያዩ የውጭ ሸቀጦችን ወደአገር ውስጥ የማስገባት ሞኖፖል የነበረው ይጠቀሳል፡፡ ሌሎችም ቡና ቦርድ፣ እህል ቦርድ ... ወዘተ ቦርድ የሚባሉ ነበሩ፡፡ የጃንሆይ ዋና የገቢ ምንጭ ጉምሩክ ነው፡፡ የወጪና የገቢ ንግድ ቀረጥ ድንጋጌዎች በተለያዩ ጊዜያቶች ተደንግገዋል፡፡

የአዋጆቹ ትኩረት ከሚወጡት ይልቅ በሚገቡት ላይ ነበር፡፡ በውጪ ንግድ በኩል ታሪፋቸው የተደነገገው ቆዳና ሌጦ፣ ቡና፣ ሰም እና ዝባድ ነበር፡፡ ይህም ዘመናዊ የሆነ አሰራር እስኪዘረጋ ድረስ የቆየ ነበር፡፡ ከገቢ ንግድ የሚገኘውን ቀረጥ ከፍ በማድረግም የመንግስትን ገቢ ማሳደግ ተችሏል፡፡ሆኖም ከወጪ ንግዱ የሚገኘው ገቢ አናሳ ስለሆነ በንግዱ ዘርፍ ተጨባጭ ለውጥ ሳይታይ ቀርቷል፡፡

በጥቅሉ አዲሱ የብሔራዊ ባንክ በገንዘብ ሚ/ር አጠቃላይ መመሪያ ስር የአገሪቱን የውጭ ምንዛሬ፣ የገንዘብ ሕትመት፣ የባንክ ብድርና የወለድ ፖሊሲ በሚመለከት ሃላፊነት ነበረበት፡፡ በ1935 የትራንስፖርት ሕግ ደግሞ በአገሪቱ ታሪክ ለዘመናት በንግድና በመገናኛ ስራዎች እድገት ላይ ተፅዕኖ ሲያደርግ የኖረውን የኬላ ስርዓትና ቀረጥ አስቀርቶ፣ በማዕከላዊ የመገናኛ መስሪያ ቤት ስር ዘመናዊ የሞተር ተሽከርካሪ ስርዓትና አሰራር በመፍጠር በአገራችን የንግድና የመገናኛ ታሪክ አዲስ የእድገት ምእራፍ ከፈተ፡፡ የ1935ቱ የጉምሩክ ሕግ የኢትዮጵያ መንግስት የገንዘብ ገቢ ዋናው ምንጭ የውጭ ንግድ እቃ ቀረጥ እንደሆነ አሳየ፡፡

ነገር ግን ምንም እንኳ እነዚህ መሠረታዊ የባንክ፣ የመገናኛ፣ የጉምሩክና፤ የገንዘብ ድርጅቶችና ስራዎች በአገሪቱ ለዘመናዊ የንግድና የመገናኛ እድገት አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች ቢሆኑም፤ የኢትዮጵያ

ቁልፍ የእርሻና የእደ ጥበብ ክፍለ ኢኮኖሚዎች ኋላቀር በመሆናቸው ለንግዱ ክፍለ ኢኮኖሚ እድገትና መስፋፋት ሊያደርጉ የሚችሉት አስተዋፅኦ በአይነትም በመጠንም የተወሰነ ሆነ፡፡
ቢሆንም የንግድና የመገናኛ ክፍለ ኢኮኖሚው ዘርፍ ከኪሣራ ተነስቶ በየእለቱ እያደገ ሄዶ በአብዮቱ ዋዜማ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ጠቅላላ የአገር ውስጥ አመታዊ ምርት /ገቢ/ 15.6 በመቶ ሆኖ ነበር፡፡ ይህም ከእርሻ፣ ከአገልግሎት፣ ከኢንደስትሪ ዘርፎች ቀጥሎ የመጨረሻ ደረጃ ላይ የሚቀመጥ ዘርፍ ሆኗል ማለት ነው፡፡

ጃንሆይ እና ኢንደስትሪ

የኢንደስትሪው ዘርፍ ከወረራው በፊት ከነበረው ጋር ሲነፃፀር ከነፃነት በኋላ የታየው ለውጥ ከፍተኛ የሚባል እንደነበር ብዙዎች ያምናሉ፡፡ የዚያ ዘመን ንግድና ኢንደስትሪ እንደ አቅሙ መስፋፋት የቻለው ንጉሡ አገሪቱን ለኢንቨስተሮች ምቹ በማድረጋቸው ነው፡፡ ለምሳሌ በ1941 ዓ.ም የተደነገገው የገቢ ቀረጥ አዋጅ ከ2 መቶሺህ ብር በላይ ካፒታል ያለውና በማዕድን፣ በኢንደስትሪና በትራንስፖርት ዘርፍ የተሰማራ ማንኛውም ኢንቨስተር በመጀመሪያው 5 ዓመት የሚያገኘው ትርፍ ከቀረጥ ነፃ ነበር፡፡ በንግድ ኩባንያዎች ትርፍ ላይ የሚሰበሰበው ቀረጥም ከ15 በመቶ እንዳይበልጥ ተደርጎ ነበር፡፡ በሦስተኛው የበጀት ዓመትም ትራክተሮችና ልዩ ልዩ ኬሚካሎች ከቀረጥ ነፃ ሆነው ነበር የሚገቡት፡፡

የንጉሡ አስተዳደር የኢንደስትሪ ፖሊሲ ወጪና ገቢው ይመጣጠን ዘንድ "ከውጭ የሚገቡ ሸቀጦችን በአገር ውስጥ ምርት መተካት" የሚል ነው፡፡ በዚህም መሠረት መጀመሪያ ጨርቃጨርቅ ትኩረትን አገኘ፡፡ አቃቂ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካና ባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

በኢንደስትሪ መስፋፋት ትልቅ ድርሻ የሚሰጠው በሆላንዱ ኩባንያ ፀኤች.ቪ.ኤ ይካሄድ የነበረው የስኳር ኢንደስትሪ ሲሆን፤ ከነፃነት በኋላ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮለት በ1946 ዓ.ም ሁለት የስኳር ማምረቻ ፋብሪካዎች ማለትም ወንጂ እና መተሐራን አቋቋመ፡፡ የወንጂ ስኳር ፋብሪካ መሠረቱ የጣሊያን ነበር፡፡ ጣሊያን በአዋሽ ሸለቆ የሸንኮራ ተክል ማሳ መስርቶ ነበር፡፡ በ1953 ዓ.ም ኤች ቪ ኤ ተብሎ የሆላንድና የኢትዮጵያ ተብሎ ተሰየመ፡፡ በርካታ ኢትዮጵያውያንም በሥራ ተሳታፊ ነበሩ፡፡ በኩባንያው አክሲዮንም ኢትዮጵያ አንድ ሦስተኛ ድርሻ ነበራት፡፡ በ1959 ከፍተኛ የተባለውን 10 ሚሊዮን ብር ትርፍ ያስገኘ ኩባንያ ነበር፡፡ ለሸማቹም ትልቅ ለውጥ ነበረው፤ ቀድሞ ስኳር ከውጭ ይገባ ስለነበር፡፡

ሌላው መጠጥ ሲሆን፣ የመንግስት የገቢ ምንጭ በመሆን ሰፊ ድርሻ ነበረው፡፡ ከወረራው በፊት የተመሠረተው የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ



ፋብሪካ የረጅም ዘመን ሞኖፖሉን ከሜታ አቦ ቢራ ፋብሪካ ጋር መጋራት ጀመረ፡፡ ኮካ ኮላና ፔፕሲም አገር ውስጥ መዘጋጀት የጀመሩት በንጉሡ ዘመን ነው፡፡

የማዕድን ኢንደስትሪን በተመለከተም ከነፃነት በኋላ በአዶላ የተጀመረው የወርቅ ማዕድን ቁፋሮ እጅግ የላቀውን ገቢ ያስገኘ ሆኗል፡፡ ለምሳሌ በ1937 ዓ.ም ከመንግስት ገቢ አንድ አምስተኛ የተገኘው ከአዶላ ወርቅ ነው፡፡ ይህ ዘርፍ መንግስትን ስላከበረ አዶላ የሚለው የአገር ስም በክብረ መንግስት ተቀየረ ይባላል፡፡

በጥቅሉ የኢጣሊያ መሠረት ያላቸውን ጨምሮ የጨርቃ ጨርቅና ሲሚንቶ ፋብሪካዎች፣የዘይት መጭመቂያዎች፣የእንጨት መሰንጠቂያዎችና የእህል ወፍጮዎች በእጅጉ ተስፋፍተዋል፡፡ የቆቃ ግድብም በ40 ሚሊዮን ብር ተሰርቷል፡፡ ይህ 40 ሚሊዮን ብር የኢትዮጵያ መንግስት ከኢጣሊያ ማግኘት የነበረበትን ካሳ ሳያገኝ ቀርቶ፣ነገር ግን 40 ሚሊዮን ብር ብቻ በሰጠው ካሣ የተሰራ ነው፡፡ የኢጣሊያ መንግስት ለሊቢያ ተገቢውን የጦር ካሣ በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር ቢከፍልም፤ኢትዮጵያ የጠየቀችውን ገንዘብ ግን አልከፈለም፡፡ከ40 ሚሊዮን ብር ውጪ፡፡

ሌላው የኢጣሊያ ጅምር ኢንደስትሪ የአዲስ አበባው የቃጫ ፋብሪካ የሚጠቀስ ሲሆን፤ አባ ሳሙኤል ተብሎ ከሚጠራው ግድብ የተጠለፈው የመብራት ኃይል ምንጭም የእነሱው አሻራ ነው፡፡ በንጉሡ ጊዜ ባየነው መልኩ ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ከፍተኛ ቀረጥ በመጣል ያገር ውስጡን ኢንደስትሪ ለማስፋፋት ተሞክሯል፡፡
የኢንደስትሪዎች ማዕከል በአብዛኛው በአስመራ፣ በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተሞች ሲሆን፤ በተለይ በአገሪቱ ካሉ ፋብሪካዎች ውስጥ ግማሽ ያህሉ በአዲስ አበባ ይገኙ ነበር፡፡ ለአብነት ያህል የተነሱት ዘርፎችና መሰል የኢንደስትሪ ተቋማት እየተስፋፉ በመሄዳቸውም የሰራተኛው ገቢ የጨመረበት ሁኔታ ከመፈጠሩም በላይ፤ በአብዮቱ መዳረሻ የሰራተኛው ቁጥር 54 ሺ ያህል ደርሶ ነበር፡፡

የዜጎች አማካይ የዓመት የነብስ ወከፍ ገቢም 72 ዶላር ከሃምሳ ሣንቲም ደርሶ ነበር፡፡የሰራተኛው መደብ ከየክልሉ መጥቶ ኢንደስትሪ በተቋቋሙባቸው ቦታዎች በጋራ ሲሰራም የመሰብሰብ እድሉን አግኝቶ በእድርም፣በእቁብም መልክ የተለያዩ ማኅበራትን መመስረት ጀመረ፡፡የክፍያ መሻሻልና የመሣሠሉት ጥያቄዎች በአቤቱታ መልክም በአድማ መልክም መካሄድ ሲጀምሩ፤ መንግስት በ1954 ዓ.ም የመጀመሪያውን የሠራተኛ ማኅበር አዋጅ ደነገገ፡፡ በዓመቱ የኢትዮጵያ ሰራተኞች ማኅበር ኮንፌዴሬሽን ተቋቋመ፡፡ የወንጂ አድማ በ1953 ነበር የተቀጣጠለው፡፡ የመጀመሪያው የስራ ማቆም አድማ በወንጅ ሠራተኞች

ተጀምሮ ወደሌሎችም በመዛመቱ ወደኋላ ላይ ለንጉሡ ውድቀት ዋናውና አንዱ ግብአት ሆኗል፡፡

ባጭሩ በኢንደስትሪው ዘርፍ የታየውን መሻሻል ስናይ በ1966 ዓ.ም 436 ፋብሪካዎች፣ 54 ሺ 816 የፋብሪካ ሠራተኞች ነበሩ፡፡ አጠቃላይ የክፍለ ኢኮኖሚው የብሔራዊ ምርት ድርሻ ከመቶ 16.1 ሆኖ የታየው በ1966 ዓ.ም ነው፡፡ ዘርፉ "ከባድ" በሚባሉት ሳይሆን አነስተኛና መካከለኛ የሚባል ሆኖ፤ የምግብ፣ የመጠጥ፣ የትምባሆ፣ የጨርቃጨርቅ፣ የቆዳና የጫማ፣ የእንጨት፣ የሲሚንቶ፣ የሸክላ፣ የመስታወት ስራዎች፣ የሚጠቀለሉ ብረት ነክ ያልሆኑ የማዕድኖች ስራ፣ የማተሚያ፣ የኬሚካል፣ የብረታ ብረትና የመሳሰሉትን የሚያካትት ነው፡፡

በአጠቃላይ በአብዮቱ ዋዜማ በኢኮኖሚው በኩል ግብርናው 49.3 በመቶ፣ የአገልግሎት ዘርፉ 19 በመቶ፣ ኢንደስትሪው 16.1 በመቶ፣ ንግድ 15.6 ከመቶውን ሸፍነው ነበር፡፡

**የጃንሆይ የጦር ግንባታና የመሠረተ ልማት ዝርጋታ**

ኢትዮጵያ ከጦርነቱ በፊት ዘመናዊ ጦር አልነበራትም፡፡ የሆለታ ገነት ጦር ትምህርት ቤትም የመጀመሪያ ሰልጣኞችን ሳያስመርቅ ነበር ጦርነቱ የተነሳው፡፡ "ነጭ ለባሽ" በሚል መጠሪያ የሚታወቁ ጥቂት የከተማ ፖሊሶች ነበሩ፡፡ ከነፃነት በኋላ ግን ዘመናዊ ፖሊስ ማግኘት ችላለች፤ በ1934 ዓ.ም በእንግሊዞች፡፡ እንግሊዞች ከመልቀቃቸው በፊትም 5 ሺህ የሰው ኃይል ያለው "የክቡር ዘበኛ ጦር" የተባሉት ወታደሮች በስዊዲናውያን መኮንኖች እንዲሰለጥኑ ተደረገ፡፡



የክብር ዘበኛ ጦር፣1928

በ1937 ዓ.ም ንጉሡ አሜሪካዊው አይዘንሐወር ግብፅ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ ወደ ግብፅ አምርተው ተገናኟቸውና በኢትዮጵያ ስላለው



ወቅታዊ ሁኔታ ተነጋገሩ፡፡ ስለ ኤርትራ፣ ስለኦጋዴን፣ ስለምድር ባቡር አጠቃላይ ሁኔታውን አስረዱ፡፡

የአሜሪካው የፔትሮሊየም ኩባንያ "ሲንክልየር ሊዉስ" በኦጋዴን የነዳጅ ዘይት ፍለጋ ጥናት ቢያካሂድ ኢትዮጵያ ፈቃደኛ እንደሆነች ንጉሡ ያስረዱትም፡የኦጋዴን ግዛት የይገባኛል ጥያቄ መፍትሄ እንዲያገኝና፣ በዚያውም ከአሜሪካ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ለመመስረት ነበ ፡፡

ከ1937 ዓ.ም በፊት የአሜሪካውያን ተሳትፎ በሲቪሉ ዘርፍ ነበርና አሜሪካ በወታደራዊው መስክ ልዩ ድጋፍ እንድታደርግ ንጉሡ ተማፀኑ፡፡ ሆኖም አሜሪካ ለዘብተኛ አቋም ይዛ ጥቂት ጊዜ ቆየች፡፡ ከ1938 ዓ.ም ጀምሮ የተወሰኑ ወታደራዊ እገዛዎችን ስታደርግ ቆይታ፣ በ1945 ዓ.ም ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ስትተሳሰር ግን አሜሪካም አስመራ ባላት የመገናኛ ጣቢያ ምክንያት የመካከለኛው ምስራቅ ስትራቴጂካዊ ጥቅሟ ከኢትዮጵያ ጋር ተያያዘ፡፡ ወዲያውም የእንግሊዝ ወታደራዊ ተራድኦ ቡድን ከኢትዮጵያ ሲወጣ ኢትዮጵያ የተሟላ ድጋፍ ከአሜሪካ ማግኘት ቻለች፡፡

በ1944 ዓ.ም በገማል አብደል ናስር አማካኝነት በግብፅ የተካሄደው አብዮትም አሜሪካ በመካከለኛው ምስራቅና በቀይ ባህር ዳርቻ ያላትን አቋም በደንብ እንድታጤን አስገደዳት፡፡በእነዚህ ሁኔታዎች መነሻነት አሜሪካና ኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ ስምምነት ተዋዋሉ፡፡

"የአሜሪካ ተፅዕኖ ከሁሉም ጎልቶ የታየው በስልጠናና በትጥቅ መስክ ነበር፡፡ ከ1938 እስከ 1964 ድረስ አሜሪካ ያደረገችው ወታደራዊ እርዳታ በ180 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚገመት ነበር፡፡ ከ1945 እስከ 1960 ባለው ጊዜ ከ5 ሺ 500 በላይ የሆኑ ኢትዮጵያውያን በአሜሪካን አገር የተለያዩ ወታደራዊ ስልጠና አግኝተዋል፡፡ ከዚህ በተረፈ ጀቱ፣ፀረ-አውሮፕላን መቃወሚያው፣ የባህር ኃይል መርከቡና ጀልባው፣ የእግረኛው መሣሪያና አንዳንዱ ዩኒፎርሙም ሳይቀር የሚመጣው ከአሜሪካ ነበር፡፡ በትጥቅም ሆነ በስልጠና የአሜሪካ ወታደራዊ እርዳታ ቁንጮ ውጤት ተብሎ የሚገመተውና በዘመናዊነቱና በቅልጥፍናውም ዝናን ያተረፈው የአየር ኃይሉ ነበር፡፡" (ፕ/ር ባህሩ ዘውዴ2002)

አሜሪካ በ1945ቱ ስምምነት መሠረት በአስመራ የሚገኘውን የመገናኛ ጣቢያዋን ማለትም በመካከለኛው ምስራቅ ኮሚኒስት አገሮችን ለመከታተል የሚያስችላትን የስለላ ጣቢያ "ቃኘው ጦር ሠፈር" በሚል ስያሜ በመሰየም ይዞታዋን ስታረጋግጥ፡በምላሹም "ማግ" በሚል ምህፃረ ቃል በሚታወቀው የወታደራዊ እርዳታ አማካሪ ቡድን አማካይነት ሦስት ክፍለ ጦር ሠራዊት ለኢትዮጵያ አሰለጠነች፡፡ አሰልጥናም አስታጠቀች፡፡የኢትዮጵያ የምድር ጦር ቀደም ብሎ ከሰለጠነው ጋር

ተዳምሮ በአራት ክፍለጦሮች ተደራጀና አንደኛው ክፍለ ጦር /ክቡር ዘበኛ/ በአዲስ አበባ፣ ሁለተኛው ክፍለ ጦር መጀመሪያ ደሴ፣ ቀጥሎ ኤርትራ፣ ሦስተኛው ሐረር፣ አራተኛው ክፊሉ አዲስ አበባ ክፊሉ ነገሌ ቦረና ተመደበ፡፡

በየክፍሉም አሜሪካውያን አማካሪዎች ተመደቡ፡፡ የምድር ጦሩን በዘመናዊ መንገድ ካደራጁ በኋላም በስዊዲኖች ተጀምሮ የነበረውን የአየር ኃይልና በኖርዌጅያኖች እየተደራጀ የነበረውን የባህር ኃይል ተሳትፈውበታል፡፡ በእንግሊዝ ስር በነበሩት ህንዶች ይተዳደር ለነበረው የሐረር ጦር አካዳሚም የማቴሪያል ድጋፍ ያደረጉ ሲሆን፤ የአሜሪካውያን አሻራ ያላረፈባቸው የጦር ክፍሎች ተብለው የሚጠቀሱት ክቡር ዘበኛና ፖሊስ ናቸው፡፡

በጃፓን አማካሪነትም ባፋጣኝ የማዕረግ እድገትና ሹመት ብዙ ከፍተኛ መኮንኖች ሊፈጠሩ ችለዋል፡፡ “ከ1939 እስከ 1948 ድረስ በዘጠኝ ዓመታት ውስጥ አራት ብርጋዴር ጀኔራሎች ብቻ የነበሩ ሲሆን፤ ከ1949 እስከ 1959 ድረስ በአስር ዓመታት ውስጥ 42 ብርጋዴር፣ ሜጀርና ሌተናል ጀኔራል መኮንኖች ተፈጥረዋል፡፡” (ፐ/ር ላጲሶ1983)

አጠቃላይ ጦር ኃይሉም በአንድ የጦር ሚኒስቴር ስር እንዲተዳደር ተደርጓል፡፡ ኢትዮጵያ ከ1940ዎቹ ጀምሮ በተከታታይ በአሜሪካውያን ሰፊ ድጋፍ በባህር ኃይል፣ በአየር ኃይል፣ በምድር ጦር በኩል በደንብ የተደራጀ የምርጥ ዘመናዊ ጦር ባለቤት ሆነች፡፡ ከባድ የጦር ካሚዮኖች፣ ታንኮች፣ ወዘተ አሜሪካውያን ለገሱ፡፡ ምንም እንኳ የ2ኛው የዓለም ጦርነት ቅሪት ቢሆንም፡፡

በጥቅሉ አሜሪካ ኢትዮጵያ ለኮሚኒዝም ጥቃት እንዳትጋለጥ በደንብ አዘጋጅታታለች ለማለት ይቻላል፡፡ (የሚገርመው ኮሪያ የዘመቱትና ከአሜሪካውያን ወታደሮች ጎን ተሰልፈው የተዋጉት ቃኘው ሻለቃ በአሜሪካውያን ካልሰለጠኑት ከክቡር ዘበኛ የተመለመሉ መሆናቸው ነው፡፡)

የአሜሪካ ድጋፍ በጦር ኃይሉ ብቻም ሳይሆን በአየር ትራንስፖርት በኩልም አለ፡፡ በ1938 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ወደ አሜሪካ ያቀናው ልዑክ በኢትዮጵያ የአየር መንገድ ለማቋቋም የአሜሪካን እርዳታ ጠየቀ፡፡ በሚቀጥለው አመትም በኢትዮጵያ መንግስትና በትራንስኮንትኔታል ኤንድ ዌስተርን ኤር ላይን /T.W.A/ መካከል ስምምነት ተደርጎ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በ1939 /1946 እ.ኤ.አ/ ተቋቋመ፡፡

ዋና ስራ አስኪያጆችና የቴክኒክ ተቆጣጣሪዎች አሜሪካውያን ሆነው ከቀጠሉ በኋላ፤ በ1964 ዓ.ም የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ስራ አስኪያጅ ተሾመ፡፡ ለየብስ መንገድም ቢሆን አሜሪካ ዋናውን ድርሻ



ትይዛለች፡፡ ቀደም ሲል በወረራው ጊዜ ተሰርተው የነበሩ መንገዶች በጦርነቱ ፈራርሰው ነበር፡፡አዳዲስ መንገዶችም በብዛት አልነበሩም፡፡ በ1943 ዓ.ም የአውራ ጎዳና ባለስልጣን ተቋቁሞ የኢትዮጵያን መንገዶች ለመጠገንና አዳዲስ መንገዶችን ለመገንባት እንቅስቃሴ ተጀመረ፡፡ የባለስልጣን መስሪያቤቱም የተቋቋመው በአሜሪካ ድጋፍና ትብብር ነው፡፡

የባለስልጣኑ መስሪያ ቤት በአሜሪካውያኑ የበላይነት ተቋቁሞ ስራውን ሲጀምርም ግንባታው እንደ አገራቸው አምሳያ /ኦፊስ ኦፍ ፐብሊክ ሮድስ/ ሆኖ ተነድፎ ነበር የቀጠለው፡፡በ1953 ዓ.ም የስራ አስኪያጅነቱን ስልጣን ኢትዮጵያውያኑ ቢረከቡም፤የመንገድ ስራ እንቅስቃሴዎች ይከናወኑ የነበሩት ግን በአሜሪካ ስር ከሚገኘው ከዓለም አቀፍ የመልሶ ግንባታና ልማት ባንክ /ኢንተርናሽናል ባንክ ኦፍ ሪኮንስትራክሽን ኤንድ ዴቨሎፕመንት/ በተገኘ ብድር ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ባንኩ በባለስልጣኑ ተግባራት ላይ ከፍተኛ የቁጥጥር ኃይል ነበረው፡፡

ቴሌን ለረጅም ጊዜ ይዘው የቆዩት ሲውዲኖች የነበሩ ቢሆንም፤ እንደገና በዘመናዊ መልክ ለማደራጀት የአሜሪካ እጅ ነበረበት፡፡ ከአፄ ምኒልክ ጀምሮም በየጊዜው እየተስፋፋ መሄዱ ይታወቃል፡፡

ከባንክ ጋር በተያያዘ እንግሊዞች ሰፊ ተሳትፎ ነበራቸው፡፡ በወረራው ጊዜ ቀደም ሲል ከነበረው ባንክ ውጪ ባንኮ ዲሮማና ባንኮ ዲናፖሊ የሚባሉ የኢጣሊያ ባንክ ቅርንጫፎች ተቋቁመው ነበር፡፡ ጣሊያኖች ከወጡ በኋላ በ1934 የተቋቋመው የኢትዮጵያ መንግስት ባንክ እንደ ንግድ ባንክም፣ እንደ ብሔራዊ ባንክም ሲያገለግል ከቆዬ በኋላ፤ በ1955 ዓ.ም ተግባራቸው በአዋጅ የተለየ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና ብሐራዊ ባንክ ተቋቋሙ፡፡ ከዚያ በኋላም እየተስፋፉ ሄደ፡፡

በትምህርቱም እንግሊዝና ፈረንሣይ የማይናቅ ተሳትፎ የነበራቸው መሆኑ እንዳለ ሆኖ፤ አሜሪካ የአንበሳውን ድርሻ ትይዛለች፡፡ በርካታ ኢትዮጵያውያን ለትምህርት የሚላኩት አሜሪካ ነበር፡፡ በጥቅሉ በአገር ግንባታው ዘርፍ ሰፊ አስተዋፅኦ ያበረከተችው አገር አሜሪካ ነበረች፡፡ ሂደቱ በዚህ ቀጥሎ በስተመጨረሻ ግን የንጉሡን አፍቃሬ ካፒታሊዝምነት እየተቃወሙ የመጡትና የኢትዮጵያን መንግስት ፊውዳል እያሉ የሚጠሩት ምሁራን /ተማሪዎች/ ይሄ የኢምፔሪያሊዝም ነፀብራቅ ነው እያሉ መንቀፍ ጀመሩ፡፡ የሚገርመው ልክ በዚያው ዘመን የሶሻሊስት ርዕዮት ይከተል የነበረውና ለአስዋን ግድብ ከሶቭየት እርዳታ ይጠይቅ የነበረው፣ ሲውዝ ካናልን ከእንግሊዝና ከፈረንሣይ ሊወርስ የተነሳው ጋማል አብደል ናስር ሞቶ አንዋር ሳዳት የግብፅ መሪ ሲሆን፤ ሶቭየትን ትቶ አሜሪካን ወዳጅ አደረገ፡፡ የቃኘው ጦር ሠፈር አስፈላጊነትም አከተመ፡፡ አሜሪካም የመካከለኛው ምስራቅ ስጋቷ ተወገደ፡፡ በዚያ ላይ ዘመን ተራቆ

በሳተላይት መረጃን መሰብሰብ ተችሎ ነበርና የስለላ እምብርቱ ዋጋ ቢስ ሆነ፡፡ ተማሪዎችም አሜሪካን፣ አሜሪካም ተማሪዎችን ተገላገሉ፡፡

አፄ ኃይለስላሴ ተደጋግሞ እንደተገለፀው ኢትዮጵያን ዘመናዊ አገር ለማድረግ የውጭ እርዳታ የግድ አስፈላጊ መሆኑን በማመን በዲፕሎማሲው መስክ ልዩ ጥረት አድርገዋል፡፡

ከአፍሪካ መሪዎችም ተወዳዳሪ ያልተገኘላቸው አገር ጎብኝ በመሆን /የዓለም አገራትን በመጎብኘት/ የአንደኝነቱን ስፍራ ይይዛሉ፡፡ ይህም ለመዝናናት ሳይሆን እርዳታ ፍለጋ ነው፡፡ ከግንቦት 1946 እስከ ታህሳስ 1947 ዓ.ም ድረስ ባሉት 8 ወራት ውስጥ ከፍተኛ ባለስልጣኖቻቸውን አስከትለው አሜሪካን፣ ካናዳን፣ ሜክሲኮን፣ ዩጎዝላቪያን፣ ግሪክን፣ ፈረንሣይን፣ ሆላንድን፣ ምዕራብ ጀርመንን፣ ሲውዲንን፣ ኖርዌይን፣ ዴንማርክን፣ ኦስትሪያን የጎበኙ ሲሆን፤ በህዳር 1949 ደግሞ ህንድንና ጃፓንን እንዲሁም ሌሎችን ጎብኝተዋል፡፡

ዋና አላማቸውም የኢኮኖሚና የቴክኒክ እርዳታ ለማግኘት ነበር፡፡ ለምሳሌ በህዳር 1949 ጃፓንን በጎበኙ ጊዜ በቶኪዮ ከተማ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ባደረጉት ንግግር "የአገራችንን የተፈጥሮ ሐብት በስራ ለማዋልና የህዝባችንን የኑሮ ደረጃ ከፍ ለማድረግ በያዝነው ተግባር አፈፃፀም የጃፓን ገንዘብና የቴክኒክ እውቀት ተካፋይ እንዲሆን በደስታ የምንቀበለው መሆኑን ለክቡርነትዎ ለማረጋገጥ እንፈልጋለን" ብለዋል፡፡በሌሎች አገራትም ተመሣሣይ ተማፅኖቸውን እንደቀጠሉ ግልፅ ነው፡፡ አገራቱም ኢትዮጵያን በማዘመን ረገድ የየድርሻቸውን ተወጥተዋል፡፡

እነዚህን የመሳሰሉ የስልጡን ባዕድ አገራት አስተዋፅኦ ስናይም እንዲሁ በችሮታና በርህራሄ ለኢትዮጵያ አዝነው እንዳደረጉት መወሰድ የለበትም፡፡ አገራቱ የየራሳቸውን ጥቅም፣ ክብርና ተወዳዳሪነትን በማሳየት ፖለቲካዊ ትርፍ ለመሸመትና በርዕዮትም በኩል ቀዳሚነትን ለማወጅ ሲሉ የሚራመዱበት መንገድ ነው፡፡

ሐሮልድ ማርክስ "The Politics of empire Ethiopia Great Britain and the United Sates 1941 - 1974" በሚል መፃህፋቸው፤ "ይህ አይነቱ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ የወሰዱት ዲፕሎማሲያዊ እርምጃ በቀዝቃዛው ጦርነት ኢትዮጵያ ወደ ምስራቁ ርዕዮት ልታዘነብል ትችላለች የሚል ፍርሃት አሜሪካን ክፉኛ አንቀጥቅጧት ነበር" በማለት ገልፀውታል፡፡ ስለዚህም "አሜሪካ የኢትዮጵያን ጉዳይ ከልቧ እንድታስብበትና ሙሉ ትኩረት ለኢትዮጵያ ፀጥታ እንድትሰራ የሚጋብዝ ነበር" ሲሉ ያክሉበታል፡፡



## ጃንሆይና ትምህርት

ጃንሆይና ትምህርት አብረው የተወለዱ እስኪመስል ድረስ አስገራሚ ፍቅር ነበራቸው፡፡ጃንሆይን ለመተቸት ብዕራቸውን የሚቀስሩ ምሁራን ጃንሆይ ያስተማሯቸው ናቸው፡፡በራሳቸው ገንዘብ ከፍለው ባያስተምሯቸውም፤ዜጐች በአገራቸው ላይ የመማር መብት ቢኖራቸውም፣ መንግስት ትምህርትን የማስፋፋት ግዴታ ቢኖርበትም፣ብዙ ብዙ ነገር ቢባልም፤የዛሬ አገር መሪዎችን በጊዜ እንዲሰለጥኑ አድርገዋልና ቢያንስ በትምህርቱ ዘርፍ በእጅጉ ሊመሰገኑበት የሚገባ ስራ ሰርተዋል፡፡

የትምህርት ፖሊሲው ልክ አልነበረም፣ የምዕራባውያን ምንትስ ነው፣ የመኳንንቱ ልጆች ናቸው የሚማሩበት፣ ትምህርቱ የመንግስት ሃብት ነው፣ የቅበላ አቅሙ አነስተኛ ነው… ወዘተ… እየተባለ ይወራል፡፡ ይሄን ሁሉ ወሬ ለማውራት የሚያስችል እውቀት፣ ስድብን ወደ ወረቀት ገልብጦ መፃፍ የሚያስችል ግንዛቤ፣ መፈክር ካርቶን ላይ በቀለም መፃፍን ሳይቀር ያለማመደ ዘመን ግን የጃንሆይ ዘመን ነው፡፡

ስለዚህ አንዱን መንግስት አግንኖ ሌላውን መንግስት ለማጣጣል ሲባል የሚካሄድ የትችት ዘመቻ፤ ምንም እንኳ "ጨቋኝ" የሚባል ስርዓት ነበረው ቢባልም፣ በመልካም መታወስ የሚችልበትን ታሪክ አብሮ ማንቋሸሽ ተገቢ አይሆንም፡፡ የውጭ አገር ጠላት ይመስል ይህንን ስራቸውን ሳይቀር ሊያዳፍኑ የሚሞክሩ ጥቂት አይደሉም፡፡ ይሄ አካሄድ የቀጣዩን መንግስት መነሳሳት ሊያዳክመው ይችላል፡፡ የምናወራው ስለ ኢትዮጵያ ነው፡፡ እናም ስለ ጃንሆይ የትምህርት አጀማመርና የሚደነቅ የማስፋፋት ስራቸው፡፡

አንድ የነበረችውን የምኒልክ ትምህርት ቤት እሱዋም በፈረንሳይኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተወሰነ ትምህርት የሚሰጥባትን ተቋም ከአልጋ ወራሽነት ዘመናቸው ጀምሮ በጥረታቸው በእርዳታም ይሁን በብድር በአገሪቱ ሃብትም ይሁን በምን መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ አስፋፍተው ብዙ ምሁራንን ለኢትዮጵያ አስረክበዋል፡፡የጃንሆይ በትምህርት ማመን ቀደም ብሎ የታወቀ ነው፡፡ የንግስና መንገዳቸውን ይጠርጉ በነበረበት ጊዜ የወደፊቷ ኢትዮጵያ በምሁራን አሰራር ትገነባ ዘንድ ዘር ሳይመርጡ ብዙዎችን ወደሰለጠነው ዓለም ለትምህርት ልከዋል፡፡ አፄ ምኒልክ በጣሉት መሠረት ላይ ተንጠላጥለው ጃንሆይ ከአልጋወራሽነት ዘመናቸው ጀምሮ ልዩ ትኩረት የሰጡት ጉዳይ ነው፤ ምሁራንን ማብዛት፡፡

ከኢጣሊያ ወረራ በፊት 250 ምሁራን ውጭ አገር ተምረው መጥተው የመንግስት ባለሥልጣን ሆነው ይሰሩ ነበር፡፡ በወረራው ዘመን የኢጣሊያ ባለስልጣኖች ምሁራኑን እያደኑ ገደሏቸው፡፡ በዚህም ከፊሉ አለቁ፡፡ የተረፉት ከነፃነት በኋላ አገራቸውን እንዲያገለግሉ ተደረገ፡፡